
ይስማዕከ ወርቁ



የአጋዴን ድመቶች

Scanned by CamScanner

የአጋዴን ድመቶች

ይስማዕከ ወርቁ

19/10/2009
At ደብረማ
- "I am planning to
Hawass before
Arriba mintch
page 47

አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ፡ ፱፻፺፱ ዓ.ም

Scanned by CamScanner

All Rights Reserved to Yismake worku.
ኃ ዘፈሐቆ ወዘሰረቆ በስልጣነ ኪን ውጥበብ
ውንዘ ለይኵን:: © ይስማዕከ ወርቁ-፪ሺ፱

OGADEN

A NOVEL BY YISMAKE WORKU

የመጀመሪያ ዕትም ሐምሌ ፪ሺ፱ ዓ.ም.

ዲዛይን:-ዬርቱጋዳ ማተሚያ ድርጅት
Email;- ramatohara@gmail.com
ሽፋን:- ስንታየሁ ብርሃኑ

Scanned by CamScanner

ሐተታ

ከደራሲ ይስማዕከ ወርቁ ሥራዎች ውስጥ ከዘጉር ድንጋይ ለእኔ ወደር የሌለው ድርሰት ነው። ምልአቱ፣ የኢማጅኔሽን ምጥቀቱና ሽሙጡ...ግሩም ያስብላል። ይህንን ቀደም ሲል በዛው ድርሰት ላይ ሀተታ የመፃፍ እድል ተሰጥቶኝ ለመግለፅ ሞክራለሁ። ይስማዕከ ወርቁ የግዕዝና የቅኔ ቤት አውቀቱን ጉና ዝቶ እንፍልፈረሰው በዚህ የአጋዴን ድመቶች በሚል ባበረከተልን ድርሰቱ እንደገና አረጋግጦልናል። በከዘጉር ድንጋይ የምናውቀው ዲዲሞስ ዶራ በአጋዴን ድመቶች ውስጥም የገጠመውን አስደናቂ ታሪክ ይተርክልናል። ሁለቱን ሥራዎች እንደተከታታይ ሥራዎች መቁጠርም አለመቁጠርም የሚቻል ይመስለኛል። ጥቂት ስበዞች ብቻ ናቸው የሚያያይዟቸው። ጥቂት ክሮች ብቻ ናቸው ከዘጉር ድንጋይ ተስበው አጋዴን ውስጥ የምናገኛቸው። ከዋናው ባለታሪክ ከዲዲሞስ ዶራ እና ኮፖቲት የህይወቱ ቁጢቶች በቀር አጋዴን የዘለቀ የለም። እርሱ ራሱም ከአስማት አለሙ ለመውጣት ነበር ወደ አጋዴን ራሱን በስራ ለመወጠር የዘለቀው። ይሁን እንጂ እዛ ደግሞ ሌላ ፈተና ያጋጥመውና ወደ አስማት ዓለሙ እዙሪት ሳያስበው ይገባል።

ይስማዕከ ወርቁ በዚህኛው የአጋዴን ድመቶች ሥራው በአስገራሚ ቴክኒኩ አጋዴንን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ባስደናቂ የመግለጽ ችሎታው በረሃው እንዲያቃጥለን፣ ሰቆቃው እንዲሰቀን፣ ባሩዱ እንዲሸተን ያደርገናል። በስነፅሁፋችን ውስጥ ሳይቀር ለዘመናት የተረሳውን የአጋዴንን ማህበረሰብ ስነ ልቡና፣ ከጎሳው እስከ አበሳው

Scanned by CamScanner

በጥልቀት ያስቃኘናል። ለዘመናት የተፈራረቀበት የጦርነት ግላት ለምን እንደሆነ ከነዳጅ ገደሉቹ እስከ ታላላቅ ሰዎቹ ቁልቁሉ አድርጎ ስሎልናል። በረሃው ውስጥ እያስገዘ አብረን የተራመድን ያህል እያንዳንዷን ጓዳ ጎድጓዳ ያሳየናል። ችግሩን ብቻ አያሳየንም፣ እንደ ጥናታዊ ዕሁፍ መፍትሄውንም ጭምር ያመላክተናል። በገጸ ባህርያቱ መካከል የሚደረገው ንግግር በቱሌፓቲ መሆኑም ሌላ አዲስ አይታ ነው።

ይስማዕከ ወርቁ ወደ አጋዴን እየተመላለሰ ለዚህ ሥራው ጥናት ሲያካሂድ እስራትን ጨምሮ ለህይወቱ አስጊ የነበሩ ፈተናዎችን አልፏል። እድለኛ በመሆኑ እንጂ ወደ አጋዴን ከዘለቁ አጥኚዎችና ጋዜጠኞች ውስጥ በሰላም የሚመለሱት ጥቂቶቹ ብቻ እንደሆኑ ይነገራል። ይህ የሚያሳዬን በዚህ ትውልድ ውስጥም ተስፋ ማድረግ እንደምንችል ነው። ይስማዕከ ወርቁ ይህን ብቻም ሳይሆን ሌሎች የሚወረወሩበትን ጦሮችና ፈተናዎች ሁሉ በጽናት እያለፈ ሥራዎቹ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉን ስመለከት! የታላላቆቹ አባቶቻችን ፅኑ መንፈስ እንዳልተለዬን አረጋግጫለሁ። ይህ የአጋዴን ድመቶች የተሰኘው ሥራውም የዚህ ዕናቱ ምልክት ነው። ያንን የተዘነጋ ምድር በጥልቀት ለማወቅና እንደገና ከይስማዕከ ወርቁ አፁብ ድንቅ አለም ውስጥ ገብቶ ለመሰንበት ለአንባቢዎች የአጋዴን ድመቶችን ጋብዣለሁ።

ዶ/ር አድማሱ መሸሻ

Scanned by CamScanner

በድጋሜ የወጣ ማስጠንቀቂያ

በመፅሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የአስማት ቃላት በመሞከር ለሚፈጠረው ችግር ደራሲው ኃላፊነት አይወስድም።

Scanned by CamScanner

"ከአገሬ አፈር የሚደባልቅ ቤልጅግና ጎራዴ ይዤ እንጂ ጫት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ!"

ኡመር ሰመተር

Scanned by CamScanner

፩

ለዓመታት ከተዘፈቅኩበት የአስማት ዓለም ውስጥ ለመውጣት ያላደረኩት ጥረት አልነበረም። የዛሬው ጉዞዬም የሙከራዬ አንዱ አካል ሆኖ ሊቆጠር ይችላል። ሞንቅላቴን እንደ አበያ በሬ በሌላ ሥራ ጠምጂ ላቀናው ኦጋዴን ገብቻለሁ። የሥራን ያህል ፈዋሽ መድኃኒት እስከ አሁን የትኛውም ኪሚስት አልቀመመም። የትኛውም ስር ማሽ የትኛውም ቅጠል በጣሽ ደብተራ፣ እንደ ሥራ ፈዋሽ የሆነ ፍቱን መድኃኒት እስከ አሁን አላገኘም። ሥራ ነው መድኃኒቱ። በሥራ ውስጥ ስላለው ህቡዕ ፈውስ ጡረተኞች ቢያብራሩት ይሻላል። ቤት መዋል ከጀመሩ ጊዜ አንስቶ ስንት ደዌ እንደተፈራረቀባቸው የሚያውቁት እነሱ ብቻ ናቸው።

ኦጋዴን ውስጥ የሚንቀሳቀስ አንድ የውጭ ድርጅት ለከፍተኛ የመስክ ጥናት ሲጋብዘኝ፣ ያለ አንዳች ማቅማማት የአውሮፕላን ትኬት ቆርጬ የመጣሁት ራሴን በሥራ ጠምጂ ከአስማት ዓለሜ ውስጥ ተመንጥቄ ለመውጣት ካለኝ ፅኑ ፋላጎት የተነሳ ነው።

Scanned by CamScanner

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የሆነው ቦይንግ አውሮፕላን ጎዴ አውሮፕላን ጣቢያ ለማረፍ ከፍታውን በመቀነስ ላይ ነው። ከታች ለጥ ያለው በረሃ የአሸዋ ሓይቁን ሠርቶ ብርሽር ብርሽር ይላል። ሚራገፍ ያጥበረብራል። አውሎ ንፋስ እዛም እዚህም ሰማይን ለመደገፍ የቆመ ምሰሶ ይመስል እንደ ዘንዶ ሽቅብ ይጥመለመላል።

አውሮፕላኑ በአውሎ ነፋስ ርችት ታጅቦ የጎዴ አውሮፕላን ጣቢያ ማኮብኮቢያ ላይ እንደ ጆፌ አሞራ ጉብ አለና ወደፊት ይንደረደር ጀመር። ሰላሳ አምስት ሜትር ስፋትና ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሜትር ርዝመት ባለው ማኮብኮቢያ ላይ እየቃሰተ ተንደረደረና ሲቆም፣ በሱማልኛ ቋንቋ ወሬያቸውን እያደሩት የመጡት ተሳፋሪዎች በአንድ ላይ ግር ብለው በመነሳት ለመውረድ ይጋፉ ጀመር።

ከአውሮፕላኑ የወረድኩት የመጨረሻው ተሳፋሪ እኔ ነበርኩ። ጎዴ በወበቅ እና በአሸዋ ጥፊ ተቀበለችኝ። በ1959 ዓ.ም በንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተመርቆ የተከፈተው ጎዴ አውሮፕላን ማረፊያ፣ አሁን የሲቪል አውሮፕላኖች ይስተናገዱበት እንጂ አሠራሩ ለወታደራዊ ቤዝ እንደነበር ያስታውቃል። በኦጋዴን ጦርነት ወቅት የሶማሊያ ወራሪዎች ጎዴን በያዙበት ቅፅበት አርሰውት የነበረው የኢትዮጵያ ጀቶች ለውጊያ እንዳያርፉበት ቢሆንም፣ ከድል በኋላ ታድሷል።

ተርሚናሉን እንዳለፍኩ ዓይኔን እያጨላሞስኩ ሰማዩን ቀና ብዬ ለማየት ሞከርኩ። እሳት የሚተፋ የገሃነም በር መስሏል። ፀሐይዋ፣ ቂም እንደቋጠረች ባልቴት የዓይኗን

ቂጥ ታንቦገቡገዋለች። የሚሰቀጥጥ ድምፅ የሚያሰማው የበረሃው ነፋስ ሊያንሳፍፈኝ ምንም አልቀረውም።

"ዶክተር ዲዲሞስ ዶሬ እንኳን ደህና መጣህ" የሚል ፅሁፍ ከፍ አድርጋ የያዘች ሴት እየጠበቀችኝ ተመለከትኩ። በአካል አትወቀኝ እንጂ በሥራዎቼ ታውቀኛለች። እኔም እስከ ዛሬ በዓይነሥጋ አልያት እንጂ በስልክ ብዙ ጊዜ አጋግሬአታለሁ- አያን ትባላለች። አያን እኔን የጋበዘኝ የውጪ ድርጅት ቢሮ ባልደረባ ናት።

"ዶክተር" የሚለውን ቅፅል ስመለከት የምሁርነት ስሜት ሊሰማኝ ሞከረ። በተለያዩ ሀገራት የቀሰምኳቸው የአርኪዎሎጂ፣የፊሎሎጂ እና የአንትሮፖሎጂ ትምህርቶቼ ለዚህ ቅፅል ቢያበቁኝም ውስጤ ግን ከጥንታዊው ዓለም ያልወጣሁ ጎላቀር (ፕሪሚቲቭ) ሰው እንደሆንኩ ይነግረኛል። ዛሬ ያስጋበዘኝና ዶክትሬት ድግሪ የያዝኩበት የሶሻል አንትሮፖሎጂ ጥናቴ ዓለም አቀፋዊ እውቅና ቢያስገኝልኝም ትክክለኛው እኔነቴ ግን በጥንቱ ዓለም ጥናት የተዘፈቀ ነው። በአስማቱ ዓለም ውቅያኖስ ውስጥ የሰጠምኩ የሰው መርከብ ነኝ። የሉቅያኖስ እጆች የሚታዩኝ አስማታዊ ሰው!

እስከ ዛሬዋ ጠዋት ድረስ ከአልጋዬ ሳልወርድ የለመደብኝን አስማት መዳፎቼን ዘርግቼ እደግማለሁ - የጥንት የምስራቅ ፓልሚስቶችን አስማት።

"ካራግራይ ዋሽታይ ላኸሸሚ
ካራማዳይ ሻራሸዋት
ካራመላይ ቱ ጆቢንዳይ
ራባታይ ካር ዳርሳናም!"

Scanned by CamScanner

በዘልማድ፣ ይህንን አስማት ሳልደግም ከአላጋጯ አልወርድም፣ ሰውም አላናግርም። ከንቱ የአፍ ልግድ ሊባል ይችላል። ይሁን እንጂ ትርጉሙ፣

ፕብልዕግና ኃይል በሣቶቿ ላይ ነህ፣ የጥል እውቀት ኃይል በመዳፈ ላይ ነህ፣ የፈጠራዎች ጋይል በመነመረ ላይ ነህ፣ ይሄ ቀን የእኔ ነው!... እንደ ግለት ነው። ይህን እደግምና በቀኝ መዳፌ ግንባሬን ነክቼ ቀኝ እግሬን አስተድሜ ቀኔን እጀምራለሁ።

አሁን እንኳ ይህ አመሌ አልለቀኝ ብሎ፣ ከአውርፕላኑ ስወርድና የኦጋዴን ወበቅ በአሸዋ ጥፌ ሲቀበለኝ፣

"....ሻራይ
ሹራይ
ራማይ ...." አልኩ። ወደ አዲስ ምድር ሲገባ የሚደረግ ድግምት ነው። ትርጉሙን ግን አላውቀውም። በሰጠምኩበት የአስማት አለም ውስጥ ብዙ ትርጉማቸውን የማላውቃቸው ይህን የመሳሰሉ ድግምቶች ያጋጥሙኛል። እደጋው እዚህ ላይ ነው። "አፍ ይዤውዕ ለሞት" ይሏል ይህን ነው- "አፍ ሞትን ይጠራል።"

ይህን ድግምት እያነበንኩኩ ስሜ እስክ ማዕረጌ የተሣፈፀትን የእንኳን ደህና መጣህ መልእክት ይዛ ወደምትጠብቀኝ ሴት ገሰገስኩ። እትፋ፡ አበባ ይባለች። አውሱ ንፋሱ የለበሰችውን ቢጫ መጎናፀፊያ ሊቀማት ይታገላል። የለበሰችውን ሐምራዊ ድሪያ ቀሚስ ወደ ጎን ወየሮ ሲያውለበልበው የጻሌዋን ትርዕ ለሁሉም አንልቶ ለማሳየት ያሰበ ይመስላል። እየቀረብኩ በመጣሁ ቁጥር ውበቷ ግሩም መሆኑን ተመለከትኩ። እንዳንድ ድምጻቸው የሚያምር ሴቶች በእነል ሲታዩ ፉንጋ ሲሆኑ ነበር እስክ ዛሬ የሚያጋጥመኝ። አያን ግን ድምጽዋ ብቻ አልነበረም ውብ

ሆና ያገኘሁት። ከቅርጽዋ እስከ ደም ግባቷ እንከን አይወጣላትም።

"ዶክተር ጂዲሞስ እንኳን ደህና መጣህ" አለች እትፋ፡ አበባውን እያበረከተችልኝ። "ስላዙሁህ መደሰቴን መደበት አልፈልግም።"

ከዚህ በፊት ፎቶዬን በዓለም አቀፍ ጆርናሎች ላይ አይታ ይሆናል እንጂ በድምዕ ቴሌፎን ከመነጋገራችን በቀር በአካል አታውቀኝም። ይሁን እንጂ የአካባቢው ሰዎች ቀልጣፎች መሆናቸውን ሰምቻለሁ፣ ወዘ-ልውጥን ሰው ከመ ቅዕበት የሚለዩበት አንዳች ተአምር አላቸው።

"እመሰግናለሁ! በዚህ እንድ ጠብታ ዝናብ ቤጠግው በረሃ ውስጥ ይህን የመሰለ አበባ ከወዴት አገኘሽ?" አልኩ እትፋ፡ አበባውን ተቀብዬ ሳበቃ። ለስላሳ ጉንጯን ስስማት ጠንከር ያለው ሽቶዋ ከአካባቢው የበረሃ ልዩ መዓዛ ጋር ተቀላቅሎ አወደኝ።

"አይዞህ በኩንትሮባንድ የገባ አይደለም" አለች እየተፍለቀለቀች። ሀጫ በረዶ የመሳሰሉት ጥርሶቿ በተመጠነ ፈግታዋ ውስጥ ሲፈልቁ ልዩ መስህብ አላቸው።

አያን ተጫዋች መሆኗን ለመረዳት ቀላል ነበር። ራቅ ብሎ ወደ ቆመው የመስክ መኪናዋ እየመራች ስትወስደኝ ያለማቋረጥ እያወራች ነበር። ኮልተፍ፡ ከሚል እንደበቷ የሚወጣው አማርኛ ልዩ ጣዕመ ዕዝን አለው። እኔም እንደ እርሷ መኮላተፍ ሳያምረኝ አልቀረም። መኪናውን የምትነዳው ራሷ ናት።

Scanned by CamScanner

"ድርቦቱ ሾፈር አልቀጠረልሽም እንዴ?" አልኩ እንዲያው ዝም ላለማለት ያህል ፡አነስተኛ ሻንጣዬን ከኋላ ሞኜ ሳበቃ ጓዚና ገበቼ እየተመቻቸሁ።

"ስላልፈለኩ ነው" አለች ሞተሩን እያስነሳች። "ብቻዬን ስሆን ደስ ይለኛል።"

"የእኔ አመል ነው ማለት ነው ያለሽ። ብቻቸውን መሆን የሚችሉ ሰዎች ላት ያለ ችሎታ ያላቸው ናቸው።" አልኩ። "የሰው ልጅ እንደ እንስሳ በመንጋ መጓዝ የለበትም። ከመንጋው መነጠል ላት ያሉ ሰዎች ችሎታ ነው።"

ራሷን በአወንታ ነቀነቀችና የበረሃውን አቧራ እያቦነነች መኪናውን ወደ ጎዴ እንደ አባ ጠቅል ፈረስ ታሰግረው ጀመር። አውሮፕላን ጣቢያው የሚገኘው ከጎዴ ከተማ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ ብሎ ነው።

የሀሰን አደን ሠሙተር "አሸቀ ሀባይን" የሚለው የሶማልኛ ሙዚቃ ከመኪናው የቴፕ ማጫወቻ ይንቆረቆር ጀመር።

"... ምግተሃይ ኡርያንከበ
ለጎሉ መጠይኔ
ለይጋነ ወሀሉይዴ
ኩም አረረዩ ለደን
ሊነይ ኩታምሉቃታን
ሀሸቀ ሀባይአን..."

ከቴፕ ማጫወቻ ጋር አብራ እያዜመች አያለ ግጥሙን እንድትተረጉምልኝ ወተወትኳት። ቃል በቃል የተረጎመችልኝን በስንኝ ደርድሬ ባማርኛ አነበንብኩላት።

"...እግሩን ያጣውን ሰው አይተሽዋል ውዴ?
ፈጣሪ እግር አጥቶት ያመሰልሻል እንዴ?
አርሱ ግን እንደዚህ እግር የተከነከነው፣
አጉል ሰሚርጡት ምሳሌ እንዲሆን ነው።
አንቺ ግን ለጫማ ትከራከሪያለሽ
ምን አለህ? ምን አለህ? ምን አለህ ትያለሽ
ፍትር ግን እንደዚህ ሸተጥ አንዳያመሰልሽ።"

ከት ብላ ሳቀችና፣

"ይነተር ግዴለሀም ጎበገ ገጣሚም ሳትሆን አትቀርም!" አለች። ሙዚቃውን ደጋግመን እያጣጣምን በዋቢ ሸበሌ ወንዝ ዳርቻ ወደምትገኘው የጎዴ ከተማ ገባንና የበረሃዋን ከተማ የጭቃ ምርግ ቤቶች እያለፍን ወደ አያን ቤት ገሰገስን።

Scanned by CamScanner

፪

አያን ወደ ቤቷ በቀጥታ ከወሰደችኝ በኋላ ግሩም የሆነ ምሳ ጋበዘችኝና ጥዑም የሆነ የሐረር ቡና አፈላችልኝ። አቦል ቡናዋን እያጣጣምኩ ሳሎኑን መቃኘት ጀመርኩ። ብቻዋን እንደምትኖር መገመት ቀላል ነው። ቤቷ በጥሩ ሁኔታ የተያዘና የጨካኙን በረሃ ክብድ ወበት ለመከላከል "ኤሲ" የተገጠመለት ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ አስካሁን በመቀቱ ቀልጬ ወደ ፈላሽነት ላለመለወጤ እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

ቡናዬን በዝግታ እየላፍኩ ግድግዳ ላይ የተሰቃቀሉትን ፎቶዎች እቃኝ ጀመር። ከፊት ከፊቴ ማዶ ባለው ጥግ ላይ ጥቁርና ነጭ በሆነ የአጅ ሥራ የተቀዳ ፎቶ ይታያል።

"አባትሽ ናቸው?" ስል ጠየኳት ፎቶውን እያየሁ መሆኔን መገንዘቧን እንዳወቅሁ።

"አዎ አባቴ ነው" አለች ቡና የጣደችበትን የከሰል ምድጃ ማርገብገቢን ገታ አድርጋ። "በሕይወት የለም።"

"ምነዋ?" አልኩ የፊትዋን በትዕቢት መሰዋወጥ እየተመለከትኩ።

"በስልሳ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት በተቀሰቀሰው የኦጋዴን ጦርነት ጊዜ ነው የሞተው። የሶማሊያ መራሪዎች ሰላይ ነው ብለው በግፍ ቀጥቅጠው ነው የገደሉት። ለኢትዮጵያ መንግሥት እኛን እየሰለልክ መረጃ አቀብለሃል በማለት ጨፍጭፈው ከገደሉት በኋላ በጎዴ ከተማ መንገድ ላይ ለመቀጣጫ ጣሉት።" አለችና ዓይናቿን ቡዝዝ አድርጋ ዝም አለች። ከመቀጽበት ፊቷ ላይ ክብድ ሀዘን እንደጨለማ ሲደፋ ተመለከትኩ። ስሜቷ ቅርብ እንደሆነ ለመገንዘብ ቀላል ነበር። እንዲህ አይነት ሰዎች ብዙ ጊዜ ያጋጥሙኛል።

"እናትሽስ በሕይወት አሉ?" ስል የቀሰቀስኩባትን ሀዘን በእናቷ ፎቶ አስረሳታለሁ ብዬ በማሰብ ከጎን ወደ ተንጠለጠለው ፎቶ ፊቴን አዙሬ ጠየቅኳት።

"የለችም" አለች እርሷም ወደ እናቷ ፎቶ ዓይናቿን ወርውራ። "... ረጅም ነው ታሪኩ ዶክተር። ... ሌላ ጊዜ እጫውትሃለሁ። በድካምህ ላይ ሰቆቃ ልጨምርብህ አልፈልግም።"

"ይቅርታ... አዝናለሁ ሀዘንሽን ስለቀሰቀስኩብሽ።"

"አረ ግዴለም! ከመንገድ መጥተህ እንዲህ አይነት ወሬ መስማት ተገቢ አይደለም" አለች ሁለተኛውን ቡና እየቀዳችልኝ - ቶናውን።

"ከአዲስ አበባ - ጎዴ በአውሮፕላን መምጣት ይህን ያህል አድካሚ አይደለም። መኪና እየነዳሁ ብመጣ ኖሮ ምናልባት ሶስት ቀናት መንገዝ ሊጠይቀኝ ይችል ይሆናል። በዛ ላይ በረሃውን አቋርጦ መምጣት ክብድ ነው። ያው መቼም ... ካልተለመደ ሁሉም ነገር ክብድ ነው።" ስል ንግግሬን ለማስረዘም ፈለኩ። ገና ቤቷ ከመግባቴ ወደ

Scanned by CamScanner

ማትፈልገው የህዘን ትውስታ ስለከተትኳት ሀፍረት ተሰምቶኛል። "ቅልብልቡ አንግዳ" ስል ራሴን ፀረፍኩት። "ምናለ ዝም ብል!"

"መቼም ስለ ስልሳ ዘጠኙ የአጋዬን ጦርነት የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም" አለች ቡናውን እያቀበለችኝ። "ያንን አስከፊ ጦርነት ጊዜ ቢረሳው የአጋዬን መሬት አይረሳውም።"

"ጊዜ የማይጠግነው ቁስል የለም" አልኩ ተመልሳ ወደ ህዘኗ እንዳትገባ በመስጋቴ።

"እኔ ውስጥ ያለው ቁስል ግን... ሞቼ ተቀብሬ እንደ ሱሲ ሚሊዮን ዓመታትን ባስቆጥር እንኳ፣ አጥንቴ ውስጥ እንደሚገኝ ጥርጥር የለኝም።"

ይህን ስትል ሞንቅላቴ ውስጥ ድግሚት የፈነዳብኝ ይመስል ፀጥ አልኩ። ወደ አጋዬን ከመምጣቴ በፊት ስለዚህ አካባቢ በውል ለማወቅ ያሳገላበጥኩት መገበገብና ያሳነብብኩት መፅሐፍ ያለ አልመሰለኝም። ... ግን ... በሰዎች ሕይወት ውስጥ የተቀበሩትን መዛግብት ማን ፈልፍሎ ያፈርሳቸዋል? በሰዎች ልብ ውስጥ የተደረደሩትን መጻሕፍት ማን አንብቦ ይፈትሻቸዋል? ...

አያን ስታወራ፣ በሌላኛው የአእምሮዬ ክፍል፣ ያገላበጥኳቸው መዛግብትና መጻሕፍት፣ ሰነዶችና ከርታሶች እየተዘበራረቁ ይተረማመሱብኝ ያመር። አእምሮዬ ወደ ኋላ የዘመን ፈረሱን ዝርፎ ሽመጠጠ። ልመልሰው ታገልኩ፣ አልቻልኩም። ሁልጊዜም አእምሮዬ የሚያስቸግረኝ በዚህ መልኩ ነው። አሁን እየሆነ ያለውን ከሰተት ወደኋላ ሄዶ ማተት አባዜው ሆኖ ያሰቃዬኛል።

አፍሪካን የተቀራመቷት ጡንቸኖ ሀገራት ብሪታኒያ፣ ኢጣሊያ፣ ፈረንሳይና ጀርመን በአጋዬን በረሃ ላይ ጥንብ አንዳዙ የሱስ ሲውዘገዘጉ በዓይነ ህሊናዬ ተሳሉብኝ። ሥጋዊ ዓይኖቼ ግን በአያን ውብ ሽፋሽፍቶች ሥር ከተቋጠሩት ዕንባዎች ውስጥ ፈዘው እየቀሩ ነበር።

ከወልወል ግጭት እስከ አጋዬን ጦርነት፣ የሰው ልጅ የእሞራ ቀሰብ የሆነበት፣ ሲያዩት የበረሃ ግሳት ላጡት የእግር እሳት የሆነው የአጋዬንን መሬት... በአያን ሕይወት ተጣድኩበት። በእንባዋ ፈሰስኩበት።

አጋዬን እንድ ሶስተኛውን የኢትዮጵያን ቆዳ የሚሸፍን አካባቢ ነው። በዚህ ውስት "የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል" እየተባለ ቢጠራም ቡብዙዎች ዘንድ ስያሜው ትቡል አይደለም። "የኢትዮጵያ አማራ"፣ "የኢትዮጵያ ኦሮሞ"፣ "የኢትዮጵያ ትግራይ"፣ "የኢትዮጵያ አፋር"... ተብሎ ሲጠራ እስካሁን ባንሰማም እንደ ሶማሌዎች ሁሉ እነዚህ ህዝቦችም በጎረቤት ሀገሮች ይገኛሉ- በኬንያ፣ በሱዳን፣ በጅቡቲ፣ በኤርትራ። ሌላው ይቅርና በዚህ ዘመነ ስደት ውስት፣ ኢትዮጵያዊ የማይገኝበትን የአለም ጥግ ፈልጎ ማግኘት ያዳግታል። በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድም አጋዬን የሚለው ስያሜ የተለመደ ነው። እኔም ብሆን ይህኛው ስም ይቀናኛል- አጋዬን።

አካባቢው 200,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ያህል ስፋት ያለው ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ከኬንያ፣ ከሶማሊያና ከጅቡቲ ትዋሰንበታለች። በአብዛኛው ለዓይን የሚያታክት በረሃ ሲሆን፣ ለዲካ ማረፊያ የሚሆኑ አምባ ተራራዎችም ይታዩበታል። ከደጋማው የኢትዮጵያ ክፍል ክባሌ ተራሮች የሚነሱት ዋቢ ሸበሌና ጮሌ ወንዞች በረሃውን ሕይወት ዘርተውበት ባያልፉ ኖሮ በዛ አካባቢ የሰው ልጅ ለመኖር

Scanned by CamScanner

መቻሉ ያጠራጥራል። የኢትዮጵያን ወሰን አቋርጠው ወደ ሶማሊያ የሚገቡት እነዚህ ወንዞች ሰሶማሊያ ህዝብ ሳይቀር ከድንበር ተሻግረው የሕያውቱ መሠረት ናቸው። ሰማኒያ በመቶ የሚሆነው የሶማሊያ ሀገር ህዝብ በእነዚህ ወንዞች ጸርቻ ነው ተከማችቶ የሚኖረው።

የወንዞቿን ምንጭ ለመያዝ እያሉ ጦርነቶችን በማድረግ ዘመንዋን የፈጀሰችው ኢትዮጵያ በሰሜን በአባይ ወንዝ ምክንያት ከግብፅና ከሱዳን፤ በደቡብ በጊቤ ሰበብ ከኬንያ፤ በወዲህ በምስራቅ በኩል ደግሞ በዋቢ ሸበሌና በገናሌ ሳቢያ ከሶማሊያ ተፋጣ መኖሯ ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ፤ ምንጮቿ የጦርነት ምንጭ ሆነውባት ቢኖሩም፤ አትሟ ቢዳብር፤ ወንዞቿ በሚፈሱባቸው ሀገራት ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር እንደሚጠቅሟትም የውኃ ፖለቲከኞች ይገልፃሉ።

ዋቢ ሸበሌና ገናሌ ሰንጥቀውት በሚያልፉት የኦጋዴን በረሃ ውስጥ በስስት የሚታዩት ረጃጅም ዘንባባዎች፤ ፈጣሪን ለማመስገኛ ደብተራ የሚዘምባቸው የማህሌት መቋሚያዎች ይመስላሉ - የቅዱስ ያሬድ በትሮች። ከዚህም በቀር እንደ ኪንኪ ወጉር ችምችም ብሉ በረሃውን የወረረ የእጣን ዛፍ በየአምባው ጥጋትና እናት ላይ ይታያል። ከቆንጥር ዛፍ ጋር ተቀላቅሉ የተቃጠለ ሞራሮ የሚመስለው የእጣን ዛፍ ላውቀበት ከፍተኛ የእጣን ምርት የሚያስገኝ ሀብት ነው። በዚህ ውስጥ አንበሳ፤ ነብር፤ አጋዘን፤ የፍየል ግልገል የምትመስል ኢንሹ የሚሳት ፍጡር፤ የሞተ የማይበላው ጅብ፤ ተኩሳና ከክብት ጋር አብሮ የሚግጥ ከርከሮ ይገኛል። ከዚህም በቀር በዘላን እረኛ ውኃ ፍልጋ የሚርመሰመስ ከፍተኛ የከብት መንጋ ሞልታል። ፍየሉ፤ ግመሉና ከብቱ በበረሃው ውስጥ

አልፈው አልፈው የተቆፈሩትን የውኃ ጉድጓዶች በረኽት ለመጎንፈት ሲካ,ትን ይውላል።

ይህን ሁሉ በዓይነ ህሊናዬ እያሰብኩ ከአያን ዓይኖች ሽፋሽፍት አምልጠው እንደ ሚርኩሪ የተንከባለሉትን እንባዎቿን ተከትዬ ነቃሁ። ኃያላኑን ሀገራት ለዘመናት በዚህ ምድር ላይ አፍጥጠው እንዲኖሩ ያደረጋቸው፤ ምን እንደሆነ የገለፁልኝ፤ የብረት አሎሎ ከመሰሉት የአያን ዓይኖች ላይ እንደ ሚርኩሪ ኩልል ያሉት እንባዎቿ ነበሩ። አሸዋ ባጠለቀው ረሞሟ በረሃ ውስጥ ሀገራትን ጦር ሲያመገዝዝ የኖረውና፤ እንደ አብድ ገላጋይ ድንጋይ ሲያቃብል ዘመናትን ያስቆጠረው አመጻሙ በረሃ ሳይሆን የከርሰ ምድሩ ሃብት ነበር። ሲያፋጅ የኖረው ነዳጅ ነው። ሲያስተራርድና ፈንጂ ሲያስቀብር የኖረው፤ በከርሰ ምድሩ ውስጥ ተቀብሮ ያለው ነዳጅ ነው።

የአያንን የእንባ ዘለላዎች ተነስቼ ልጠርግ አሰብኩና የእንግድነት ኩብሬ ከለከለኝ።

"እባክሽን ይቅርታ አድርጊልኝ" አልኩ ተቀምጬ እየተመለከትኳት። "እንዳልሽው ሁሉንም ነገር ሌላ ጊዜ ታጫውችኛለሽ፤ በቂ ጊዜ እንደሚኖረን ተስፋ አለኝ።"

"እኔ ነኝ ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ" አለች አያን እንባዋን ጠራርጋ የግጂን ፈገግ ለማለት እየሞከረች። "እንግዳ ተቀብሎ እንባ የሚጋብዝ ሰው ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።"

"እባክሽን ቀለል አድርገሽ እይኝ። ወግ አጥባቂ የምባል ሰው አይደለሁም።"

"ዶክተር ... በእኳል ባለውቅህም ብዙ ጉዚ በስልክም አውርቼሃለሁ።... አያሌ ጥናታዊ ፅሁፎችህንም

Scanned by CamScanner

አንብቤአለሁ። በውነቱ... ለረጅም ጊዜ የማውቅህ ያህል ይሰማኛል። ለዛ ነው ስሜቱን መደበቅ ያቃተኝ" አለች በረካውን ቀድታ እያቀበለችኝ።

"እኔም ብሆን ብዙም የእንግድነት ስሜት አልተሰማኝም"

"እንባዬ ሳይቀድም የቤተሰቦቼን ሰቆቃ ባጫውትህ በወደድኩ። ነገር ግን እነሱን በሳብኩ ቁጥር ስሜታዊ እሆናለሁ። ለነገሩ ለሌሎች ነገሮችም ስሜቱ ቅርብ ነው።"

"ሌላ ጊዜ ይደርሳል። ሌላ ጊዜ ሁሉንም ተረጋግተሽ ትነግሪኝ ይሆናል። ይልቁንስ ፀሐዩ በረድ ሳይል እይቀርም፣ ወጣ ብለን ብንናፈስ ይሻላል። እኔም ወደ ሆቴል መሄድ ይናርብኛል። ስለምሳውና ስለቡናው በእጅጉ አመሰግናለሁ።" ሀሳቧን ሳትቀይር ብድግ አልኩና የእነስተኛ ሻንጣዬን ጆሮ ያዝኩ። ወዲያው ግን የቤቷ ግቢ በር እስኪያስት ቢጎይል ሲንኳኳ ሰማሁ። በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ።

፫

አያን፣ ያለ እረፍት እስኪያስት ድረስ ይንኳኳ የነበረውን የግቢ በር ለመክፈት ሮጣ ከወጣች ቆይታለች። ከውጪ የሆነ ንግግር እየቀረበ ሲመጣ ይሰማኛል። የአያን ብቻ ድምፅ ነበር።

"ቀስ አትልም?!" ትለዋለች። እንኳኳው ወንድ እንደሆነ ተረዳሁ።

'ምናልባት ባለቤቷ ይሆን?' ራሴን ጠየኩ። 'ከሰው ቤት ዘው ብዬ ... ቢጠረጥራትስ?... ስለ እኔ ያውቅ ይሆን?... ደግሞ ጣቷ ላይ ቀለበት አላየሁም።' በቁሜ ዘሞ ብዬ ተቀመጥኩና ውርደቴን መጠባበቅ ጀመርኩ። ተጋብገፍ ሳይሆን ተገብገር የገባሁ ውሸማ የሆንኩ ያህል ተሰማኝ። ራሴን በውሸማ አምሳል በመቁጠሬ፣ ክብሬ ሁሉ ተንዶ ሲከዳኝ ታወቀኝ። ትንሽዬ አይጥ የሆንኩ መሰለኝ።

"ተነግረህ አትሰማም አይደል?! ወይ ጉድ! በሩን እኮ መገንጠል ነው የቀረህ"! የአያን ድምፅና የሌላ ሰው ጸና እየቀረበ መጣ። በዚህች አፍታ ያላሰብኩት አልነበረም። ራሴን ለፍልሚያ ማዘጋጀትም ቃጣኝ። እንደገና ተነስቼ ቆምኩና የቤቱ በር እስኪከፈት ተጠባበቅሁ።

Scanned by CamScanner

በሩ እንደተከፈተ ያየሁትን ማመን አቃተኝ። እያን አስከትላው የገባችው ግዙፍ ሰውዬ፣ የለበሰው ልብስ የአህያ ቆዳ የመሰለና ከመንተቡ የተነሳ ሽታው አፍንጫን የሚፎንን ነበር። ፀጉሩ እንደ ኦጋዴን የቆንጥር ዛፎች ቅርንጫፍ ተገምዶ የተንጨፈረረ ነው። ገና ከመግባቱ የደም እዥ የተቋጠረባቸው የመሰሉ ትላልት ዓይኖቹን እንደ እሳት ነበልባል አንቦገቦገብኝ። ይሁንና የተትር ጋኔን የመሰለው ይህ ሰውዬ ወደ እኔ አልተጠጋም። ምንም ሳይናገረኝ እዛው በሩ ስር ኩርትም ብሎ ተቀመጠ። ሲቀመጥ ያ የሰማይ ስባሪ የሚያህል ግዝፈቱ እንደ ዘንዶ ተጠቅልሎ ኩርትምትም ባለ አካሉ ውስጥ ገባ። እያን ከጓዳ ገብታ ጥቂት ኩፎች በኋላ በጎድጓዳ ሳሕን ሞልታ የሚበላ ነገር አመጣችና ሰጠችው።

"ዶክተር ተቀመጥ እንጂ ... ሰው አይተናኩልም" አለችኝና በዓይኗ ገዙ በል በማለት አይነት ጠቀሰችኝ። ትንፋሼን በረጅሙ ለትቂ ተቀመጥኩ።

ሰውዬው የጎድጓዳ ሳህኑን ምግብ በእንድ እፍታ በጥድፊያ አሻመደውና ተነሳ። እያን በፎሌ ውኃ ስትሰጠው በከንፈሮቹ ግራና ቀኝ እያዥረበረበ ገረገጨውና፣ ፎሌውን መልሶላት ምንም ሳይናገር ወጥቶ ሄደ።

ትንፋሼን ሰብስቤ እንደተቀመጥኩ ዓይኖቼን በቀስታ ወደ እያን መለስኩ።

"ሊባን ሁልጊዜም እንዲህ ነው" አለች ፎሌውን እያስቀመጠች።

"ምንድን ነው?" ዓይኖቼን የወጣበት በር ላይ ተክዬ ጠየቅኳት።

"ሊባን... ተለክፎ ነው። ግሉቴ ንክ ነው። አይናገርም፣ አይጋገርም። ተናግሮ አያውቅም፣ ዲዳ ሆኖ ግን አይደለም... አስከፊው የኦጋዴን ጦርነት ሰቆቃውን ጥሉባቸው ካለፉት እንደ እኔ ካሉ ሰዎች አንዱ ነው።" ወንበር ስባ ተቀመጠች። "ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት የአምስተኛ ብርጌድ ወታደር ሆኖ ጎዴ ተመድቦ ነበር- ሊባን። በሰላሙ ጊዜ እዚሁ ጎዴ ከተማ ውስጥ ሀቦን የምትባል ፍቅረኛ ነበረችው አሉ። ውበቷ ዓይን ያፈዝ ነበር ይባላል። ስለ ሀቦን ውበት መላ ጎዴ አንስቶ አይጠግብም። እንኳን ወንድን ሴትን ያፈዝ የነበረው ውበቷ ብቻም ሳይሆን የሀቦን እና የሊባን ፍቅር እንደ ዋቢ ሸበሌ ወንዝ ፈስሶ ያልቃል ተብሎ አይታሰብም ነበር። ይህን የፍቅር ዥረት ግን የኦጋዴን ጦርነት እስከ ወዲያኛው ገደበው። ሆኖም ገደበው እንጂ አላስቆመውም። እስከ አሁን በሊባን ልብ ውስጥ ሐይቅ ሆኖ እየኖረ ነው።"

"እንዴት እንዴት?..." አልኩ ይበልጥ ለማዳመጥ እየተመቻቸሁ።

"ጦርነቱ ሲጀመር፣ የዚያድ ባሬ ጦር የጎዴን ከተማ ክፉኛ አጠቃት። በዋቢ ሸበሌ ወንዝ ዳርቻ የኢትዮጵያ ልጆች ደም እንደጎርፍ ፈሰሰ። አስከሬን ከአስከሬን ተቃቀፈ። ይሁን እንጂ በሶቪዬት ህብረት እስከ አፍንጫው ታጥቆ ኢትዮጵያን የወረረው የሶማሊያ ጦር፣ የዋቢ ሸበሌን ወንዝ ተሻግሮ ጎዴን ሲይዝ የኢትዮጵያ ጦር የጦርነት ተፈናቃዮችን ይዞ አፈገፈገ። በዚህ ውትት ነበር ሊባንና ሀቦን የተጠፋፉት። ሊባን የኢትዮጵያ ጦር ወታደር እንደመሆኑ እሱም ከተማዋን ሰቶ መውጣት ነበረበት። ይሁን እንጂ እንደገና ሀቦንን ፍለጋ በሲቪል አለባበስ ጎዴ ገብቶ በፍለጋ እንደባዘነ ይነገራል። እድለ ቢሱ ሊባን ግን

Scanned by CamScanner

ሀቦንን ሊያገኛት አልቻለም። ተሰዳ ይሆናል ብሎ በመገመት ይመለስና ጎደቹን ይቀላቀላል።

"ሀቦን ግን በሶማሊያ ወራሪ ጦር ወታደሮች እጅ ወድቃ ነበር። ይህም የታወቀው በላስቃቂ ሁኔታ ተደፍራ በመጨረሻም ተገድላ በጎዴ ጎዳና ላይ የሚዘገንን በድኗ ተጥሎ ለመቀጣጫነት በመታየቱ ነው። ያቺ የዋቢ ወንዝ ዳር አበባ የመሰለችው ውቧ ሀቦን ፈራረሰች። እስከትፈራርስ ድረስ በድኗን አንስቶ ለመቅበር እንኳ የደፈረ አልነበረም። ይህም የሆነበት ምክንያት ለኢትዮጵያ መንግሥት ትሰልል ነበር ተብላ ስለነበር ነው።"

"ያሳዝናል" አልኩ የሀቦንን አሟሟት በአዓይነ ህሊናዬ እየሳልኩ።

"ምስኪኑ ሊባን... የሀቦንን ዘግናኝ አሟሟት የተረዳው በኢትዮጵያ አሸናፊነት ጦርነቱ ከተደመደመ በኋላ ነበር። የዚያድ ባሬ ጦር እግሬ አውጭኝ ብሎ ሸርጡን ለቆንጥር እያስረከበ ሞቃዲሾ እስኪገባ ከተባረረ በኋላ፣ ሊባን በድል አድራጊነት ጎዴ ይመጣል። ባዶ ቀርታ የነበረችውን ከተማ እንደገና የጦርነት ተፈናቃዮች ተመልሰው ነፍስ እየዘሩባት ነበር። ሀቦንን በየመንደሩ እየጠየቀ ሲያፈላልግ ሰነበተ። ይሁንና ሀቦንን ሊያገኛት አልቻለም። ይብሱን... የሀቦንን ዘግናኝ አሟሟት ያዩ ሰዎች ይነግሩታል። በድኗም እስኪፈራርስ ድረስ የወደቀበትን ቦታ ያሳዩታል። ከዛ በኋላ ነበር በሊባን ላይ ሰማይና ምድሩ የተገለባበጠበት። የሀቦን አስከሬን የበሰበሰበትን አፈር እየዘገነ፣ እንደተወጋ አውሬ እያጓራ ልብሱን ሲቀድ ፀጉሩን ሲነጭ ከሰነበተ በኋላ በዛው አእምሮው ተነካ፣ ለቀቀ። የጎዴ እብድ ሆኖ ቀረ።"

"ያንት ያለህ..." ራሴን በሁለት እጄቼ ይዤ አቀርቅሬ ተረሁ። አያን ቀጠለች።

"ወደ እኔ ቤት የሚመጣው የቤተሰቦቼን አሰቃቂ ታሪክ ሲያወሩ ሰምቶ ስለሚመስለኝ አጎርሰዋለሁ። ውዛም እሰጠዋለሁ።"

ወደ ራሷ ታሪክ እንዳትገባ በማሰብ፣

"እኔኮ ..." አልኩ ካቀረቀርኩበት ቀና ብዬ። "እኔኮ ላየው ...አስፈሪ ገፅታ ቢኖረውም፣ የተከበረ ሰው እንደነበር ሁኔታው ያሳብቅ ነበር።... እንዲያውም አግኝቶ ያጣ ደሀም ነው ስል አሳቤ ነበር። አሰ አይደል የከሰረ ሰው... የከሰረ ደሀ..."

"ደሀ ክስሮ አያውቅም" አለች አያን ራሷን እየተቆጣጠረች እንደሆነ በሚያሳይ ሁኔታ። "ክስር የማያውቅ ደሀ ብቻ ነው። ሊባን ግን የፍቅር ሃብታም ነበር። ያጣትን ሀቦንን የሚተካለት ምድራዊ ሀብት የትም ሊያገኝ አይችልም።"

"ልክ ብለሻል ... ሶማሊያ የተባለችውን ሀገር በክላ መልክ ቢሰጡት እንኳ ሊጠገን አይችልም።"

ለአያሌ ደቂቃዎች በየራሳችን አእምሮ ውስጥ ሰጥመን ከቆየን በኋላ ሻንጣዬን ይዤ ተነሳሁ። ወደ ሆቴሉ መሄድ አለብኝ። የተያዘልኝ መኝታ ቤት በጎዴ ከተማ መሀል በሚገኝ "ቀለዲድ" ከተባለ ሆቴል ጎን ነው። አያን ፒንሲዮኑ ድረስ ሸኝታኝ ስታበቃ መልካም እዳር ተመኝታልኝ ወደ ቤቷ ተመለሰች።

Scanned by CamScanner

፩

በዓይኔ እንቅልፍ ሳይዛል ማደሬን ያወቅሁት ጠዋት የመኝታ ቤቱ በር ሲንኳኳ ነበር። ስለ አያን፣ ስለ ሊባንና ስለ ሀቦን ሳሰላስል ነጋብኝ። የዚህን አካባቢ የጦርነት ቀጠና መሆን ባስብኩ ቁጥር እንግሊዞችን ስራገም አደርኩ።

እስክ አሁኗ ጠዋት ድረስ በአፍሪካ ውስጥ እንግሊዞች የረገጡት ምድር ሁሉ የጦርነት አውድማ ሆኖ እንደቋያ በመጋየት ላይ ነው። በትርምቱ ወቅት የወረሯቸው ቦታዎች ሁሉ በማዕድን የበለፀጉ እንደነበሩ ተገለፀልኝ።

ናይጀሪያ በነዳጅ የበለፀገች ሀገር ናት፣ ሆኖም የጦርነት አውድማ ናት። ደቡብ አፍሪካ በአልማዝ የተንቆጠቆጠች ምድር ናት፣ ነገር ግን ፕላኒታችን መሬት አስከትበላ ድረስ የተቆፈረችውና እየተቆፈረች ያለችው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ነው። ሱዳንን የረገጠው እግራቸው እስክ ዛሬ ድረስ የዳርፉር ሰቆቃ ሆኖ ቀጥሏል። እግራቸው በደቡብ ሲዳን በኩል የነካው የኢትዮጵያ መሬት ጋምቤላ በነዳጅ የበለፀገ

እንደሆነ ሲገለፅልኝ ምን አይነት መሣሪያ ፊልስፊው መሬትን ያስኑ እንደነበር በአስማት እንኳ ሰማው ዳዳኝ። ሌላው ይትርና አሁን የረገጥኩትን ምድር እጋዴንን፣ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ለኢትዮጵያ ያዝ መስለው ጣሊያንን በማስወጣት እንዴት ያዘው እንወጣም እንዳሉ ያታወቃል። ኢትዮጵያ ነጻኗን ከመቶፈር ይልቅ የእንግሊዞችን ሴራ ቆፍራ ለመንቀል ሀብቷንና ጉልበቷን ጨርሳለች። የኢጋዴን ጦርነት ስር መሠረቱስ ማን ሆነና?

የአውሮፓ ንበራ እየተባለ የሚዘበትበት ጣልያን ደቡባዊ ሶማሊያን ሲይዝ እንግሊዞች የያዙት ግን በማዕድን የበለፀገውን ሶማሌ ላንድን ነበር። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እንግሊዞች ይዘውት የነበረው ሶማሌ ላንድ እንደ ጎርጎርሳውያን አቆጣጠር በ1960 ዓ.ም ነፃ ወጣ። ወር ባልሞላ ጊዜ በዛው ዓመት ደቡብ ሶማሊያም ክብርነት ወደ አርነት ተሸጋገረ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ጣልያን በመሸነፏና ቅኝ ግዛቶቿን እንግሊዝ በመውረሷ ደቡብ ሶማሊያም በእንግሊዝ እጅ ወደቀች።

በ1941 ዓ.ም ንጉሡን አጅበው ኢትዮጵያ የገቡት እንግሊዞች ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ነጥቀው ከራሳቸው የእንግሊዝ ሶማሌ ላንድና ከጣሊያን የወረሱትን ደቡብ ሶማሊያ፣ ባንድ ላይ ጨፍልቀው "ታላቋ ሶማሊያ" የሚል ግዛት የመፍጠር ህልማቸውን አውን ለማድረግ ተንቀሳቀሱ። ይባስ ብለው ዓይናቸውን በጨው አጥበው ኦጋዴንን በዚያላ ወደብ ለመለወጥ ለኢትዮጵያ ጥያቄ አቀረቡ። ከዚህም በላይ በልዩ ልዩ ጋዜጦች "የታላቋ ሶማሊያ"ን አላማ በማስተዋወቅ ኢትዮጵያን የትኛ ገዥነት ምስል የሚያላብስ ፕሮፓጋንዳ ጀመሩ። ኢትዮጵያም "ዘኢትዮጵያን ሄራልድ" በሚባለው ጋዜጣዋ የእንግሊዝን "ታላቋ ሶማሊያ" የተባለ ሀሳብ ቅገሮት ነው ስትል

Scanned by CamScanner

አወገዘች። እነ ፀሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ዓለምን ብቻ ለብቻ ባይገዥሙት ኖሮ የእንግሊዞችን ፕሮፓጋንዳ መድቂም ነበር።

ይሁንና የቀዝቃዛው ጦርነት በመተካቱና የዓለም ፖለቲካ በመለወጡ ምክንያት ቅኝ ገዢዎቹ እንደ መኾርገር መነቀል ጀመሩ። ሶማሊያም ነፃ ወጣች። ኦጋዴንም ለኢትዮጵያ ተመለሰች። የእንግሊዞች ቦንብ ግን እንደተቀበረ ነበር። የውስብስቡ ሴራ ክር ቋጢት መመዘዝ የጀመረው ቆይቶ ነበር።

እንግሊዞች ኦጋዴንን ለቀው ሲወጡ በምስጢር ሠርተው የደበቁት መስፈርቱ 1:500,000 የሆነው ካርታና ሌሎች ኦጋዴንን የተመለከቱ ጥብቅ ምስጢራዊ ሰነዶች የውሃ ሽታ እንደሆኑ ቀሩ።

ሶማሊያ ነፃ ከወጣች በኋላ ለዘጠኝ ዓመታት የተዘጋጀችው ኢትዮጵያን ለመውረርና "ታላቋ ሶማሊያ" የተሰኘውን የእንግሊዝ ቦንብ ለማፈንዳት ነበር። ለዚህም ስትል የሶቭየት ህብረት የፖለቲካ የእንጀራ ልጅ በመሆን እስከአፍንጫዋ ታጠቀች። በመፈንቅለ መንግስት ሥልጣን ላይ ፈጥ ያለው ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ "የምዕራብ ሶማሊያ ህዝብ ነፃ አውጭ" የተባለውን ድርጅት በማስታጠቅ እያሰለጠነ ወደ ኢትዮጵያ ያሰገባ ጀመር።

በመቀጠልም ዝግጅቱን ያጠናቀቀው የሶማሊያ ጦር በ1969 ዓ.ም በይፋ ኦጋዴንን ወረረ። በጥቂት ቀናት ውስጥም በዶሎና በባሬ ተረማምዶ ኃይሉን ከአምስተኛ ብርጌድ እጅ ነጠቀ። ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬም ለሶማሊያ ወራሪዎች በአደባባይ መደስኮሩን ቀጠለ።

"... ወደ ኢትዮጵያ ስትገቡ በጉጉት የሚጠብቃችሁ ብሉት ያጎወዛው ሀረ መንግሥት ኃይል ነው። እፊታችሁ የሚቆም ወታደር የለም። ኢትዮጵያ ስትገቡም ስለምንም ችግር አይገጥማችሁ። ሥጋው፣ አህሉ፣ ከብቱ፣ ብርቱካኑ፣ ሙዙና ፓፓያው የተትረፈረፈበት ውብና የጥጋብ ሀገር ነው። ቦንብ እየወረወራችሁ ሳይሆን ሙዝና ብርቱካን እየተወራወራችሁ ነው ኢትዮጵያ የምትገቡት... ሂዱና ያቺን የጥጋብ ሀገር ያዟት!..." ሲል እንደ እንስሳ አገሳ። የወራሪው ጦር ታሳት ምት ጎዴ ላይ አረፈ።

የአየር ኃይልና ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት ስላሉበት፣ ጎዴን መያዝ ከፍተኛ የውጊያ ጠቀሜታ እንዳለው የተገነዘቡት የሶማሊያ ወራሪዎች በመድፍና በሞርታር ከተማዋን ያለ ምህረት ይደበድቡ ጀመር። የሚያስገመግም የከባድ መሳሪያ ተኩስ ሰማይዋን አረሰው። የባሩድ ሽታ የእጣንና የብርጉዷን መዓዛ ሸፈነው። የሙተረየስ ቶጪት የሕፃናቷን ሳቅ ዐጥ አደረገው። የልጃገረዶችንና የእዝዞቿን መፈንጠዣ ጎዳና ጥይት አረሰው። ምሽቷን የጥይት ርችት አነደደው። የወዳደቀ አስከሬን አጥሯ ሆነ። በሞት ሽታ ጠረኗ ተቀየረ። የመልዓከ ሞት ክንፍ ጥላ በጎዴ ላይ ወደቀ። አሞራዎቿ የሰው ሥጋ ሰመዱ።

የውቧ ሀቦን በድን በጎዴ ጎዳና ላይ ተጣለ። የአያንን አባት ቅዱስ አስክሬን አሞራዎች ተቧጨቁት። ይህንን ቀፋፊ የጦርነት ታሪክ በዓይነ ህሊናዬ ሳዳውር ነበር የመኝታ ቤቱ በር መንኳኳት ወደ አሁኑ ዓለም የመለሰኝ።

Scanned by CamScanner

፫

ፎጣዬን አገልድሜ በሩን ከፈትኩት። አያን እንደ ጠዋት ሙራ እየተፍለቀለቀች ቆማ ነበር።

"እንደምን አደርክ ዶክተር..."አለች ግንባሯን ቁጥር ፈታ እያደረገች። "ሙቀቱ እንዴት አደረገህ?"

"ኤሲው ባይናር ኖሮ እንደ ቲቤ እቀልጥ ነበር።" አልኳት ወደ ውስጥ እንድትገባ እየጋበዝኳት።

"እንትልፍ በደንብ እንዳልተኛህ ዓይኖችህ ያስታውቃሉ። ድልህ መስለዋል።"

"አም ጥሩ እንትልፍ አልተኛሁም ማለት ይቻላል። ስለ ሲባን፣ ስለ ሀቦንና ስለ አንቺ አባትም... የነገርሽኝን ሁሉ ሳመነዥክ ነው የነጋብኝ።"

"የእኔ ጥፋት ነው። መልካም አቀባበል እንዳላደረኩልህ ግልፅ ነው፣ ይትርታ ይደረግልኝ። ለዚህ ጥፋቴ ጥሩ ቁርስና ወፍራም ቡና አዘጋጅቻለሁ። እንሂድ" አለች ከደጅ እንደቆመች።

ወደ ውስጥ ተመለስኩና ተለቃልቄ ወጣሁ። ገና ጠዋት ቢሆንም ሙቀቱን በመፍራቴ ከጥጥ የተሠራውን ነጭ ልብሴን ለብሼ ወጣሁ።

"እውቀህበታል" አለች አያን አሰባበሌን አይታ። "የበዛ ልምድ አለህ ማለት ነው!"

"በትክክል። ከዚህ በፊት በኑብያና በግብፅ በረሃዎች ውስጥ ሰፊ የአርኪዎሎጂ ምርምር ከሚያደርግ የጥናት ቡድን ጋር ብዙ በመሥራቴ የበረሃን ጠባይ አውቀዋለሁ።"

"ፒራሚዶችን አይተሃቸዋላ!" አለች ወደ ቤቷ እየመራችኝ። "የመጀመሪያዎቹ ፈርኦናች ኢትዮጵያውያን ነበሩ የሚባለው እንዴት ነው? ፒራሚዶቹ የተሠሩትም በእነርሱ ትዕዛዝ መሠረት ነው የሚሉ ጥናቶች አሉ። አሁን ያለችውን ኢትዮጵያ ስናይ ይህ ተረት ተረት አይመስልም?"

"ቢመስል አይገርምም። ያቺ... የማያ፣ የአዜቲክ፣ የኢንካና የፎኒሺያ ስልጣኔ መነሻ የነበረችው የጥንቷ ኢትዮጵያ አሁን አንገቷን ደፍታለች። ፒጋሰስን የሠሩት እጆቿ ተጣጥፈዋል። ውቅያኖስን አቋርጠው ይቀዝፉ የነበሩ መርከቦቿ ሰጥመዋል።"

Scanned by CamScanner

"ምክንያቱ ምንድን ነው ትላለህ?" ርምጃዋን ገትታ አፈጠጠችብኝ። "ታላቋ ኢትዮጵያ ለምን ፈራረሰች?"

"ለዘመናት በተካሄደ አለም አተፍ ሴራ ምክንያት መሆኑ ግልፅ ነው። ...እስከዛሬ ኢትዮጵያ ያደረገቻቸውን ጦርነቶች ማን ቆጥሮ ይጨርሳል? በዘመኗ ያለ ጦርነት የመሸ ቀንና የነጋ ሴሊት የለም። ይህ ሁሉ ለምን ይመስልሻል?"

"ድንጋይ የሚወረወረው ፍሬ ወዳለው ዛፍ ነው።" አለችና ርምጃዋን ቀጠለች።

"ልክ ብለሻል። ዛሬ ላይ አንድ ፍሬ እንኳ የቀረ እስከማይመስል ድረስ ተጨፍጭፋለች። ለዘመናት በደረሰው ጭፍጨፋ የተነሳ ዛሬ ያሉት ህዝቦቿ ስላለፈው አኩሪ ታሪክ ማውራት ራሳቸውን እስኪያሳፍራቸው ድረስ እንቃታቸውን ደፍተዋል። ታሪካ በልባቸው ፍርስራሽ ውስጥ ተቀብሯል።" አንድ አነስተኛ አውሎ ነፋስ ጎዳናውን ቀውጢ አደረገውና ንግግራን አቋረጠኝ። የአያንን ጥቁር እስኳርፍ እንደ አሸባሪ ባንዲራ ያውለበልበው ጀመር። ዓይናቸችንን እያጨላሞሰን አንድ ግድግዳ ተከልለን አውሎ ነፋሱን ካሳለፍን በኋላ ስንተያይ፣ ሁለታችንም ወፍጮ ቤት የቆዩን ይመስል የአቧራ ዱቄት ውጠን ነበር። አያን ከት ከት ብላ ሳቀችብኝ።

"ቢያስገሳንኩ አቧራ ነበር የሚወጣን" አለች ሳቋን ሳታቋርጥ። "ቻለው እንግዲህ! አጋዴን እንዲህ ነው። ተመልከት! ሰማዩ ላይ የምታየው ደመና እንዳይመስልህ። የአጋዴን ሰማይ ሁልጊዜም በአውሎ ነፋስ ርችት እንደተንቆጠቆጠ ነው።"

"ወድቺ የገባሁበት ነው።"

የአያን ሳት እኔንም አሳቀኝ። ስትሰት የሳቋ ቅላጼ ይቀያየራል።

"...ባንዴ በትቢያ ጥፌ ከግብፅ ስልጣኔ ጎዴ አስገባኝ አውሎ ነፋሱ።"

"ገና በጠዋቱ እንዲህ አይነት አውሎ ነፋስ አይቼ አላውትም።"

"ገና ምን አይተህ! የአጋዴን ነፋስ የጎድን አጥንት ሳይቀር ለመንቀል ይታገላል።"

ከአያን ቤት እንደደረስን ያዘጋጀችውን ቁርስ ከበላን በኋላ፣ ቡና እየጠጣን ስለመጣሁበት የጥናት ጉዳይ መወያየት ጀመርን። በአንዳንድ ቅደም ተከተሎች ላይ ከተስማማን በኋላ ገና ጠዋት በመሆኑ፣ ወደ ዋቢ ሸበሌ ወንዝ ልትወስደኝ ትችል እንደሆን ጠየኳት።

"አይገርምም?... እኔም ወደ ወንዙ ልወስድህ አስቤ ነበር። አንዲት ደስ የምትለኝ ቦታ አለች። እዛች ሥፍራ ተቀምጨ የሚወርደውን ወንዝ ስመለከት መንፈሴ ይታደሳል። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ሰው በአካባቢው አለመኖሩን አይና አወላልቄ እዋኛለሁ። ተደብቀው ያዩኝ ጎረምሶች ወራውን ወደ ከተማ ስላመጡት የጎዴ ከተማ ሰዎች እንደ ጤነኛ ሰው አይቆጥሩኝም። እንዴት ሴት ልጅ እርቃኗን ወንዝ ውስጥ ትዋኛለች? አያሉ እንደሆንኩ ያወራሉ። ሻጣን ያለብኝ ይመስላቸዋል" አለች እየተዘገጃጀች። "የአካባቢው ማህበረሰብ ሰሌቶች ካለው አመለካከት የተነሳ እንደሆነ ስለምቆጥረው ምንም አይመስለኝም። የሴት ልጅ እርቃኗን መሆን ያለባት ባሏ ፊት ብቻ ነው የሚል አመለካከት አለ።"

Scanned by CamScanner

ከአያን ቤት ወጣንና ከተማዋን መሃል ለመሃል ሰንጥቆ የሚያልፈውን አውራ ጎዳና ያዝንና ወደ ዋቢ ሸንወርድ እግረ መንገዳችን ስለከተማዋም አጫወተችኝ።

የክልሉ ዋና ከተማ ወደ ጅጅጋ ከመሸጋገሩ በፊት ጎዴ የአጋያን ዋና ከተማ ነበረች። አያን እንደነገረችኝ ይህ የሆነው ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ነው። ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በወጣ ማግስት፣ በዋነኝነት የአጋዴን ጎሳ ጥርቅም የሆነው አብነግ በሽግግሩ ወቅት የተደረገውን ምርጫ በከፍተኛ ድምፅ አሸንፎ ክልሉን ተቆጣጥሮ ነበር።

ከአጋያን ውጪ የነበሩ በቁጥር አናሳ የሆኑ ጎሳዎች ፍርሃት ያደረባቸው፣ አብነግ "የራስን እድል በራስ መወሰን" የሚለውን ፈሊጥ ይዞ፣ የአጋዴንን ጎሳ በመያዝ ሌሎቹን የመጨፍለቅና የመገንጠል አላማም እንዳለው ውስጥ ውስጡን በመሰማቱ ነበር። አብነግ አኩርፎ ከሽግግሩ መንግሥት ፓርላማ ሲወጣ፣ ሌሎች ከአጋዴን ጎሳ ውጪ ያሉ ጎሳዎችን እንወክላለን የሚሉ ሰዎች፣ ኢሶዴሊ የተባለ ድርጅት መሥርተው አጋዴንን መምራት ጀመሩ። ይህኛው ፓርቲም ብቻውን ቀጠናውን መምራት ሲያዳግተው የቀድሞ የአብነግ ለዘብተኛ አባላትን በማሰባሰብ፣ ሶህዴፓ የተባለ ፓርቲ በማቋቋም ክልሉን መምራት ያዘ።

"ለምን የክልሉን መንግሥት ወደ ጅጅጋ ለማዛወር እንደተፈለገ አይገባኝም" አለች አያን ከተማዋን እያስቃኘችኝ። "ከተሞች መመሥረት ያለባቸው በወንዝና በኃይቅ ዳርቻዎች ነው። ያለ ጥቅም የሚፈሰው ዋቢ ሸበሌን ለማልማት ጎዴ አስፈላጊ ነበረች። በንጉሡም በደርግም ጊዜ የነበሩት ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች አሁን

ወድመዋል። አሸዋ ሰፍሮባቸዋል። ወንዙን ወደ ቢረሃው ይረፈጹ የነበሩ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች አሁን ዝገው ቆመዋል። ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ያሠሯቸው ተቋማት እንካ. አሁን በትጡ አልተያዙም። በዛ ባልሰለጠነ ዘመን ባንክ፣ ቴሌ፣ ፖስታ ቤትና መብራት አስገብተው ነበር። ለሙስሊሙ መስጊድ፣ ለክርስቲያኑ ቤተ ክርስቲያን፣ ትምህርት ቤት፣ ኤርፖርትና ሆስፒታልም አስገንብተው በከተማዋ ዙሪያ ዘላኖችን በማስፈር የተረጋጋ ኑሮ እንዲመሠርቱ ጥረው ነበር።"

ከተማዋን ግራና ቀኝ እየተመለከትን ቁልቁል ወደ ሚጥመለመለው ዋቢ ሸበሌ ወንዝ ወረድን። ሰማያዊ በርሜል የተሸከሙ አህዮች ብቻቸውን ሲጓዙ ተመለከትኩ።

"ተመልከት ዶክተር!" አለች አያን ወደ አህዮቹ በጣቷ እየጠቆመች። "ወደ ሰባ ሺህ የሚጠጋውን የጎዴ ህዝብ ውሃ የሚያጠጡት እነዚህ አህዮች ናቸው።"

"ወንዙን ያውቁታል ማለት ነው?" ተገርሜ ጠየቅኋት። አህዮቹን እንኳን የሚመራቸው የሚነዳቸው ሰው የለም። ዋቢ ወንዝ ጠብቀው ይሞኗቸዋል፣ ወደቤታቸው ቀጥ ብለው ይመለሳሉ።

"ሌላው ይቅርና አህያ አይታሰርም። ቤቱን ያውቃል። ውሃ ቀድተው የሚጭኑት አሽከሮች ወንዝ ይጠብቁትና ያሽከሙታል። በቀጥታ ወደ ቤቱ ይጓዝና ጭነቱን የሚፈታውን ሰው ይጠባበቃል።"

"ይገርማል!"...አልኩ አህዮቹን እየተመለከትኩ። "መሰልጠን እንደሚቻል ከዚህ በላይ ማሳያ የለም።

Scanned by CamScanner

ካሰለጠንከው እንኳን ሰው አህያም ይሰለጥናል። ይገርማል ሌሊትም አይታሰሩም?"

"አይታሰሩም" አለች አያን። "ጎዴ ውስጥ ጅብ አህያን በላ ሲባል ሰምቼ አላውቅም። እንዲያውም አህዮች ጅቡን ያባርሩታል።"

በዚህ እያሳቅን ወደ ዋቢ መንገዝ ደረስን። በመንዙ ላይ በተሠራው የብረት ድልድይ ላይ ቆመን ቁልቁል የሚጥመለመሉውን የዋቢ ሸበሌ መንገዝ መመልከት ጀመርን።

"ይህ መንገዝ ለሰፋፊ የመስኖ እርሻዎች ቢውል እንኳን ኦጋዴንን መላ ምሥራት አኖረሃን ይቀልባል። የኦጋዴን መሬት እንዲህ በረሃ መስሎ ስታዩው የማያበቅል ይመስልህ ይሆናል። ሆኖም ገርነቱን ለማዬት አንድ ዝናብ እስኪያገኝ መጠበቅ ይኖርብሃል። በአመት አንድ ዝናብ ብቻ የሚያገኘው ይህ በረሃ ሁለት ጊዜ ዝናብ ሲያገኝ የአመት ቀለብ ያስገኛል። አስገራሚው ነገር ዝናብ ከዘነበ ከሁለት ቀን በኋላ ይህ ገሃነም የሚመስለው በረሃ አረንጓዴ ሐመልማለሉን ተሳነፅር ገነት ይመስላል። በሁለት ቀን ዝናብ ብቻ ለግጦሽ ያደርሳል። በዋቢ መንገዝ ዳርቻ የሚገኘው ምዕራብ ጉዴ ሩዝ ሳይቀር ይመረትበታል። ቀላፎ ነጭ ሩዝ ይሰጣል። እዚህ ታች..." አለችና ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ በአንጫ አመለከተችኝ።

"እዚህ ታች ደርግ አምስት መንደሮች አቋቁሞ ነበር። ከኦጋዴን ጦርነት በኋላ። በሰላም ጊዜ አርሰህ ብላ፣ ሲውራህ ሲመጡ ተዋጋ ብሎ ደርግ ያሰፈረው ግብረ ኃይል ነበረ። የዋቢ ሸበሌን መንገዝ ጠልፈው አነባቢውን እሽት በእሽት አደርገውት ነበር። ኢህአዴግ ከገባ በኋላ የደርግ ጦር ነው ብሎ በታተነው። ከፊሉን መተማ ዮሐንስ ወስዶ

አስጎርታል ይባላል። ተረው ግን ወደየመጣበት ተበታትኖአል። ወደ ከተማ ገብቶ በልመና የተሠማራ እንዳለም ሰምቻለሁ። ይህ ሁሉ የምታዩው አሸዋ የተሞበት በረሃ በዋቢ መንገዝ መስኖ አረንጓዴ ነበር። መሬቱ ገር ነው። ሃምሳ ሳንቲ ሜትር ወደታች ብትቆፍር ለም አፈር ታገኛለህ።"

የወንዙን ዳርቻ ተከትለን ሽቅብ ከተጓዝን በኋላ ብቻዋን ከቆመች የዘንባባ ዛፍ ሥር ተቀመጥን።

"እናቴ ወደዚህ ቦታ አዘውትራ ትመጣ ነበር አሉ" አለች ደፍርሶ ቁልቁል የሚወርደውን የዋቢ ሸበሌን መንዝ ፈዝዛ ስትመለከት ቀይታ። ባለፈው ያቋረጠችው ታሪኳን ልታጫውተኝ እንደሆነ ገባኝ። "ከአባቴ ጋር ጣፋጭ ፍትር የተቃመሱባት ቦታ፣ ይህች ቦታ እንደሆነች በትርቡ የሞቴት ጉረቤቴ አጫውተውኛል።"

"በልጅነትሽ ነው ማለት ነው እናትሽንም ያጣሻቸው?"

"አም" አለች አሻግራ ከሩት ያለውን ድልድይ እየተመለከተች። "የሶማሊያ ጦር ጎዴን ሲወር ነበር እኔንና ህፃን ወንድሜን በፊትና በጀርባዋ አዝላ የተሰደደችው።"

"ወደ የት?"

"ወደ ሰሜን አቅጣጫ። ጎዴን የሶማሊያ ወራሪ ጦር ሲቆጣጠረው ከተባራሪ ጥይት የተረፈው ነዋሪ ከተማዋን ለቆ ወደ ደናን፣ ቱብሪ ደሃር፣ ቱብሪ በያህ፣ ደገ ሃቡርና ጅጅጋ ተሰደደ። እናቴ ግን በዚህ አልቆመችም። ሐረር ድረስ ገሰገሰች። እስከ ጦርነቱ ማብቂያ ሐረር ከቆዩች በኋላ የዚያድ ባሬ ጦር ተሸንፎ ሞቃዲሾ ድረስ መፈርጠጡን ስትሰማ ወደ ጎዴ ተመለሰች።

Scanned by CamScanner

"ጎዴ ፈራርሶ ነበር። ከተቃጠሉ ታንኮችና ከፈራረሱ ግድግዳዎች በቀር መጠለያ እንኳ አልነበረም። መንገዶችን የወዳደቁ አስከሬኖች ሞልተዋቸው ከተማዋ ጥንብ ጥንብ ትሸት ነበር። የጦርነት ተፈናቃዮች ወደ ከተማዋ አንዳንድ አያሉ ተመልሰው ነፍስ እስኪዞሩባት ድረስ ጎዴ ሲለል መስላ ነበር። ከሰደት የተመለሰው ነዋሪ አስከሬኖችን ቀብሮ ቤቶቹን እንዲነገሩ እየጠገነ መኖር ሲጀምር ግን ለላ ጦርነት ይጀመራል።"

"ደግሞ የምን ጦርነት?"
"የድመት ጦርነት!"

"እትቀልጂ! ደግሞ የድመት ጦርነት ተብሎ የተሰየመው የትኛው ጦርነት ነው?"

"ያልተባለ የጎዴ ጉድ ነው ቀልድ አይደለም። የጦርነት ተፈናቃዮች በተመለሱ በጥቂት ቀናት ውስጥ አያሌ ህፃናት መጥፋት ጀመሩ። እምጥ ይግቡ ስምጥ፣ ህፃናቱ የት እንደ ደረሱ ማምቅ ሳይቻል ብዙ ቀናት አለፉ። የእኔም ወንድም የጠፋው በዚህ ወቅት ነበር።"

"የት ጠፋ?"

"ልነግርህ ነው። ልጆቻቸው የጠፉባቸው ወላጆች ጓዳ ጎድጓዳውን ሲያስሱ ይሰነብቱና ቢጨንቃቸው በጋራ ልጆቻቸውን ለማፈላለግ ይስማማሉ። ከዚህ በኋላ ነው ጉዱ የተሰማው። አንድ ቀን አንድያ ልጁ የጠፋበት ወላጅ፣ ልጁን እየፈለገ ወደ ቤቱ ታዛ ይሄዳል። ከታዛው የድመት መንጋ ተከማችቶ የሆነ ነገር ሲቧጨቅ ይደርሳል። ጠጋ ሲል አንደኛው ድመት ተወንጭፎ አንገቱን ያንቀዋል። ሌሎችም ድመቶች እየዘለሉ ላዩ ላይ ይወጡና ማንቁርቱን አንተው ሊጥሉት ይታገሉታል። ሰውዬው ግን የነፍስ አድን ጩኸቱን እያሰማ የሰፈረበትን የድመት መንጋ

እንደተሸከመ ወደ መንገድ ይወጣል። መንደርተኛው ሁሉ ይወጣና ከድመቱ መንጋ ያስጥለዋል። ሰውዬው የሆነውን ሁሉ ያስረዳል። መንደርተኛው በሰውዬው መረጃ ወደ ቤቱ ታዛ ሄዶ ሲያይ የሆነውን ማመን ያቅተዋል። ድመቶቹ ሲቧጨቁት የነበሩት የሰውዬውን ልጅ ነበር።"

"ያንት ያለህ" አፌን በመዳፌ ያዝኩ።

ለረጅም ደቂቃዎች ስትተክዝ ቆይታ ቀጠለች።

"የእኔም እናት ህፃን ልጇ ጠፍቶባት ስትፈልግ ሰንብታ ይህን ወሬ ትሰማና የቤቷን ታዛ ስታስስ ትንንሽ የህፃን እጥንቶች ታገኛለች። ልጇን ድመቶች ተቀራምተውት ነበር።" ከዚህ በኋላ መናገር አቃታት። ላግ ሊተናነቃት ቆዩችና ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር። እኔም እንባዬን መቆጣጠር አልቻልኩም።

ከአያሌ ደቂቃዎች በኋላ እንባዋን እየጠራረገች ቀጠለች።

"ድመቶች የሰው ሥጋ ለምደው ነበር። ነዋሪዎች የጦርነት ቀጠና የሆነችውን ከተማ ለቀው ሲወጡ ድመቶች የወዳደቀውን አስከሬን ቀመሱ። ስደተኞች ሲመለሱ ከተማዋ በድመት መንጋ ተወራ ነበር። የቤታቸው ድመት ወደ አውሬነት ተቀይሮ ጠበቃቸው ልጆቻቸውን፣ ወተት አጠጥተው ያሳደጓቸው ድመቶቻቸው ነጠቋቸው። እናቴም ልጇን ድመት እንደበላባት ሲገባት በቁሟ ተገለፍልፋ ወደቀች። አልተነሳችም።"

"ያንት ያለህ! ከዚህ የበለጠ የጦርነትን ሰቆቃ ማሳያ የሚሆን ምሳሌ ምን አለ? ...የኦጋዴን ሰቆቃ!....የጎዴ ጉድ!... አንቺስ እንዴት ተረፍሽ?"

Scanned by CamScanner

ገአድል ብንለው ይሻላል። ይህን ሁሉ ሀዘን ተሸክመሽ ኑሪ ብሎ ፈጣሪ ፈርዶብኝም ይሆናል" አለች ዓይናቿን ደጋግማ እየጠራረገች።

"ከዛስ ማን አሳደገሽ?"

"እናቱን ለመቅበር የመጣችው አክስቱ ሐረር ወስዳ አሳደገችኝ። ስትወስደኝ ገና የሶስት አመት ህፃን ነበርኩ። ቤተሰቦቼን የማውቃቸው በፎቶ ብቻ ነው። አክስቴ ልጅ አልነበራትም፣ መሀን ናት። እንደ ልጇ ተንከባክባ ነው ያሳደገችኝ።"

"አማርኛሽ የሰላው ለዚህ ነው... ሐረር በማደግሽ።"

"ከሆነ ልክ ነው። ...እዛው ሐረር ተምሬ ጥሩ ውጤት ካመጣሁ በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመግባት የመጀመሪያ ድግሪዬን በሶሾሎጂ ያዝኩ። ሁለተኛ ዲግሪዬን ደግሞ ሆላንድ ሀገር በአንትሮፖሎጂ ሠርቼ ተመልሻለሁ። ይኸው ነው ታሪኬ። በቃ።"

ተነስታ በሚፈሰው የወንዝ ውሃ ፊቷን ታጠበችው። እንባዋን ለዋቢ ሰጠችው።

፭

ከምሳ በኋላ፣ ሞቃታማውን ቀን መኝታ ቤቴ ውስጥ ገብቼ አመለጥኩት። ከውጪ መዋል የማይታሰብ ነው። ቤት ገብቶ ኤሲን ከፍቶ መዋል ግድ ይላል። ሊያን ነፈስፈስ ሲል እንደምትመጣ ነግራኛለች። ሥራችንን በይፋ የምንጀምርበት ምሽት እንደሆነ ተነጋግረናል። ስለ እርሷ ብዙ አውቄአለሁ። ጎደሎ ተወልዳ ሐረር ማደጓን፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሶሾሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪዋን እንደያዘች፣ ማስተርስዋን ሆላንድ ሀገር እንደተቀበለችና አሁን እኔን በጋበዘኝ አለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ እየሰራች እንደሆነ ተርካልኛለች።

ከሁሉም ልቤን የነካው ግን በቤተሰቧ ላይ የወረደው መትሰፍሰት ነበር። በሰላይነት ተጠርጥሮ በሶማሊያ ጦረኞች በግፍ የተገደለው አባቷ፣ በድመት መንጋ የተበላው ህፃን ወንድሟና የልጇን ጥቃትን አፅሞች በማዩቷ በድንጋጤ ወድቃ የሞተች እናቷ ...

ዕንባዋ በዓይኔ እየተመላለሰ የመጣሁበትን ሁሉ አስረስቶኛል። ገና ስለ ሊያን ያላወቅሁት አንድ ነገር አለ። እጮኛ ይኖራት ይሆን?... እጇ ላይ ቀለበት ስለሌላት ባል እንደሌላት ግን ደምድሜአለሁ። ኧረ ለመሆኑ ይህን

Scanned by CamScanner

ለማምት ለምን ያስፈልጋል? ተነስቼ በተዘቃዛ ውሃ ተለቃለኩና ክፍሌን ዘግቼ ወጣሁ። ለእያን ስልክ መደወል ነበረብኝ። ተንቀሳቃሽ ስልኬ ላይ ስሚን ፈለግሁ።

"ሃሎ ዶክተር... ኔታህ?" አለች ስልኩን በፍጥነት አንስታ። እየጠበቀችኝ እንደነበር ግልፅ ነበር።

"ወጥቻለሁ።"

"መታወቂያ ወይም ፓስፖርት መያዝህን እንዳትረሳ።"

"መታወቂያ? ...ምን ይሠራልናል?"

ከትከት ብላ ሳቀችና፣

"ፍተሻ መኖሩን አልነገርኩህም ለካ።"

"የምን ፍተሻ ነው? ከሀገሬ ወጥቻለሁ እንዴ?"

"በል ተመለስና ፓስፖርትህን ይዘህ ውጣ። የቀረውን ስንገናኝ እናወራለን። ሁሁ!" እየሳቀች ስልኩን ዘጋችው።

ለክፉም ለደጉም ብዬ ወደ ክፍሌ ተመለስኩና ፓስፖርቴን ይዤ ወጣሁ። አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ደረሰች።

"ለምንድን ነው ፓስፖርት ያዝ ያልሽኝ?" በጥያቄ ተቀበልኳት።

"ከተማው ውስጥ ልንሽራሸር አይደለም?"

"እም። አካባቢዬን በደንብ በመቃኘትና በመልመድ ሥራዬን መጀመር የሁልጊዜም ተግባሬ ነው።"

"ሀሳብህ ጥሩ ነው። ሆኖም የመጣህበት ክልል ከተቀሩት የኢትዮጵያ ክልሎች የባሰ አደገኛ አካባቢ መሆኑን መርሳት የለብህም።"

"ፓስፖርትም ይጠየቃል ማለት ነው?"

"መታወቂያም ይሁን ፓስፖርት፣ ብቻ እንተን የሚገልፅ ነገር ይዘህ መንቀሳቀስ ግዴታ ነው። እንኳን አንተ ወዘልውጡ፣ የከተማዋ ታዋቂ ነዋሪዎችም መታወቂያ ይዘው የመንቀሳቀስ ግዴታ አለባቸው።"

"ለምን?"

"ፍተሻ አለ።"

"ለምንድን ነው ፍተሻው?"

"ዶክተር ዲዲሞስ..." አለች አያን ፍጥጥ ብላ እያየችኝ በለሆሳስ። "የመጣህበት ክልል ሞቀ ስትለው የሚቀዘቅዝ፣ ቀዘቀዘ ስትለው የሚሞቅ፣ ሁኔታውን መተንበይ የማይቻል ቀጠና ነው። ለበርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት ገዢ የሆነ፣ ክልሉን ለማጥናት የሚመጣ ተመራማሪ ቀልጠ የሚቀርበትና አለሁ የሚል ጋዜጠኛ የማይደፍረው አካባቢ መምጣትህን በድጋሜ ልነግርህ እወዳለሁ።"

እኔም ዓይናቿ ላይ ፈጥጬ ቀረሁ።

"ገባህ?"

"ገባኝ። ግን..."

Scanned by CamScanner

አልመለሰችልኝም። ሆራ በዝግታ መራመዷን ተጠበች። ምንድን ነበር ልጠይቃት የነበረው? በረጂሙ ተንፍሼ ተከተልኳት።

"ፍተሻው ከምን የመጣ ነው?" እሷን ለተም አደረኳት። "ቢደንብ አልመለስሽልኝም። ፍርሃቱ ከምን የመነጨ ነው?"

"...የመጣሃው ...አንዳንድ ተንታኞች የኢትዮጵያ ጻርፋር እያሉ ወደሚጠሩት አካባቢ ነው። በአንድ በኩል መንግሥት በቀጠናው የሚፈፀመው የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲጋለጥበት አይፈልግም። ታጣቂ ቡድኖችን ለመምታት ሲል የወሰዳቸው እርምጃዎች፣ ያቃጠላቸው መንደሮችና ያደረሳቸው ሰቆቃዎች እንዳይጋለጡ በማለት አለም አቀፍ ድርጅቶችና ጋዜጠኞች በአካባቢው በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ አይፈቀድም። በሌላ በኩል ይወጣል ተብሎ በጉጉት የሚጠበቀው ነዳጅ ሌላኛው የአካባቢው ስጋት ነው።"

"የነዳጁ መውጣት እንዴት ስጋት ሊሆን ይችላል?"

"የተፈጥሮ ሀብት አንዱና ዋነኛው የግጭት መንስኤ መሆኑን ለአንተ ማስረዳት አይጠበቅብኝም። እጮኛዬን ያጣሁት..." ርምጃዋን ገታችና ቆማ አጤነችኝ። "...እጮኛዬን ያጣሁት በነዳጅ አውጪ ሰራተኞች ላይ በተፈፀመ የሽብር ጥቃት ነው። ጂአለ-ጂስት ነበር።"

'በሞት የተከበበች ሞት ሞት የምትሸት ልጅ! የሞት መናኸሪያ!' አልኩ በውስጤ። ያልሞተችው እሷ ብቻ ናት።

"አያን...አዝናለሁ።" ሁለቱንም ትከሻዎቿን ይዤ ቆምኩ። "ብዙ በደል ደርሶብሻል።"

"ያልሞትኩት እኔ ብቻ ነኝ" አለች በጎደፈ እንባ እየተንቆረዘዘ። "እኔም ብሆን ግማሽ አካሌ እንደሞተ እንደሞተ ይቆጠራል።"

የአቤ ጉበኛን ስንኝ አስታወሰችኝ።

"...እናንት ወገኖቼ አልሞትኩም ሞቻለሁ።" አቤ በዛፈው ዕሁፍ ምክንያት፣ሞቻ በተባለ ተራራ ላይ በግዞት ታስሮ እያለ የቋጠራት ሰምና ወርቅ ስንኝ ናት።

አያን፣ እንባዋን ታግላ መለሰችና መጓዛችንን ቀጠልን። እንዳለችውም በየትያሱ ቆመው የሚፈትሹ ወታደሮች አላፊ አግዳሚውን ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍር እየፈተሹ ነበር። ለበርካታ ጊዜ ተፈተሸኩ። ፓስፖርቴን ባልይዝ አልቆልኝ ነበር።ይህም ሆኖ ፓስፖርቴን አይተው አያበቁም፣ በሶማልኛ ቋንቋ ከአያን ጋር ይነጋገራሉ።

በኋላ ስጠይቃት፣ ከየት እንደመጣሁና ለምን እንደመጣሁ ነበር የሚጠይቁት። እርሷ የምትሰራበት የውጪ ድርጅት አዲስ አባል እንደሆንኩ አድርጋ ያሰናዳችውን መልስ ነበር የምትነግራቸው።

ጎያ መሸት ሲል ትንሽ ተንፈስ ትላለች። ከምሳ በኋላ መሥሪያ ቤቶች ሳይቀር ዝግ ናቸው። አመሻሽ ላይ እንደገና ሥራ ይጀመራል።

የቀኑ ሀሩርና ገሃነም መሰሉ መቀት ጋብ ሲል ነዋሪዎች በየበራቸው ይወጡና ይቀመጣሉ። ጫት የጨረሰ የቢራ አንገት ያንቃል።

Scanned by CamScanner

አልመለስችልኝም። ሁራ በዝግታ መራመዷን ቀጠለች። ምንድን ነበር ልጠይቃት የነበረው? በረሿሙ ተንፍሼ ተከተልኳት።

"ፍተሻው ከምን የመጣ ነው?" እኔን ሰቀም አደረኳት። "በደንብ አልመለስሽልኝም። ፍርሃቱ ከምን የመነጨ ነው?"

"...የመጣሃው ...እንዳንድ ተንታኞች የኢትዮጵያ ጸርቃር እያሉ ወደሚጠሩት አካባቢ ነው። በአንድ በኩል መንግሥት በቀጠናው የሚፈፀመው የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲጋለጥበት አይፈልግም። ታጣቂ ቡድኖችን ለመምታት ሲል የወሰዳቸው እርምጃዎች፣ ያቃጠላቸው መንደሮችና ያደረሳቸው ሰቆቃዎች እንዳይጋለጡ በማለት አለም አቀፍ ድርጅቶችና ጋዜጠኞች በአካባቢው በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ አይፈቀድም። በሌላ በኩል ይወጣል ተብሎ በጉጉት የሚጠበቀው ነዳጅ ሌላኛው የአካባቢው ስጋት ነው።"

"የነዳጁ መውጣት እንዴት ስጋት ሊሆን ይችላል?"

"የተፈጥሮ ሀብት አንዱና ዋነኛው የግጭት መንስኤ መሆኑን ለአንተ ማስረዳት አይጠበቅብኝም። እጮኛዬን ያጣሁት..." ርምጃዋን ገታችና ቆማ አጤነችኝ። "...እጮኛዬን ያጣሁት በነዳጅ አውጪ ሰራተኞች ላይ በተፈፀመ የሽብር ጥቃት ነው። ጂአሰ-ጂስት ነበር።"

'በሞት የተከበበች ሞት ሞት የምትሸት ልጅ! የሞት መናኸሪያ!' አልኩ በውስጤ። ያልሞተችው እሷ ብቻ ናት።

"አያን...አዝናለሁ።" ሁለቱንም ትከሻዎቿን ይዤ ቆሞኩ። "ብዙ በደል ደርሶብሻል።"

"ያልሞትኩት እኔ ብቻ ነኝ አለች በዓይኗ እንባ እየተንቆረዘዘ። "እኔም ብሆን ግማሽ አካሌ እንደሞተ የሚቆጠር ነው። ማንም የለኝም። ብቻውን የቀረ ሰው እንደሞተ ይቆጠራል።"

የአቤ ጉበኛን ስንኝ አስታወሰችኝ።

"...እናንት ወገኖቼ አልሞትኩም ሞቻለሁ።" አቤ በዛፈው ዕሁና ምክንያት፣ሞቻ በተባለ ተራራ ላይ በግዙት ታስሮ እያለ የቋጠራት ሰምና ወርቅ ስንኝ ናት።

አያን፣ እንባዋን ታግላ መለሰችና መጓዛችንን ቀጠልን። እንዳለችውም በየትያሱ ቆመው የሚፈትሹ ወታደሮች አላፊ አግዳሚውን ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍር እየፈተሹ ነበር። ለበርካታ ጊዜ ተፈተሸኩ። ፓስፖርቴን ባልይዝ አልቆልኝ ነበር።ይህም ሆኖ ፓስፖርቴን አይተው አያበቁም፣ በሶማልኛ ቋንቋ ከአያን ጋር ይነጋገራሉ።

በኋላ ስጠይቃት፣ ከየት እንደመጣሁና ለምን እንደመጣሁ ነበር የሚጠይቁት። እርሷ የምትሰራበት የውጪ ድርጅት አዲስ አባል እንደሆንኩ አድርጋ ያሰናዳችውን መልስ ነበር የምትነግራቸው።

ጎያ መሸት ሲል ትንሽ ተንፈስ ትላለች። ከምሳ በኋላ መሥሪያ ቤቶች ሳይቀር ዝግ ናቸው። አመሻሽ ላይ እንደገና ሥራ ይጀመራል።

የቀኑ ሀሩርና ገሃነም መስሉ መቀት ጋብ ሲል ነዋሪዎች በየበራቸው ይወጡና ይቀመጣሉ። ጫት የጨረሰ የቢራ እንገት ያንቃል።

Scanned by CamScanner

፭

የውጪዉ ድርጅት ላቀደው ጥናት ለምን እኔን መምረጥ እንደፈለገ ሳስላስል አደርኩ። ሁልጊዜም ለአዲስ ፈተና ራሴን ማዘጋጀት ደስታ ቢሰጠኝም፣ ይህኛው ፈተና ግን ከጥናቱ ውጪ ያለ ከባድ ተግዳሮት አለበት። እስራት ወይም ሞት ሊሆን ይችላል። ይህ ከየትኛው ወገን ሊመጣ እንደሚችል አለመታወቁ ደግሞ ሌላው ችግር ነው። ማንን መጠንቀቅ እንዳለበት የማያውቅ ግዳይ፣ ወደ ገዳዩ እየገሰገሰ ላለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይችልም።

ተነስቼ ከተጣጠብኩ በኋላ፣ ማስታወሻዬን ይዤ ከክፍሌ ወጣሁ። ትናንት አያን ባስጠነቀቀችኝ መሠረት ፓሰፖርቴን ኪሴ ወሽቄአለሁ።

ከፒኒሲዮኑ ፊት ለፊት ካለች የክኒን ዛፍ ሥር፣ ቡና የምታፈላ ሴት አየሁና ሄጄ ባርጩማ ላይ ተሰየምኩ።

ቡናው የገለጠልኝ ይመስል የውጪው ድርጅት ሁኔኛ ላለው ጥናቱ የጋበዘኝ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆነ ተረዳሁ። አንደኛው በግብፅ በረሃ ውስጥ ያከናወንኩትና አዓለም አቀፍ እውቅና ያስገኘልኝ ጥናት ይሆናል ስል ገመትኩ። ብዙ ምሁራን ያጣቀሱት ጥናት ነው። ጥናቱ ብቻ ሳይሆን ፈታኝ በነበረው በረሃ ውስጥ የተከናወነ ምርምርም በመሆኑ፣ ድርጅቱ የበረሃ ልምዴን

ከግምት አስገብቶ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ግን የሰላል አንትሮፖሎጂ ሞያዬን አጢኖ ሊሆን ይችላል የሚል ግምትም አጫረብኝ።

እንደሚታወቀው ሶሾሎጂ የተባለው የእውቀት ዘርፍ ከአንትሮፖሎጂ ጋር ሲጣመር፣ ስለ አንድ ማህበረሰብ በጥልቅ ለማምቅ ምሉዕ የሆነ መሣሪያ ይሆናል። ሶሾሎጂ የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታ፣ ጥቅል በሆነ መልኩ ወይም ጥልቅ በሆነ መንገድ የሚያጠና ሳይንስ ሲሆን፣ ባህሉንና የማህበረሰቡን ስነ ልቡናም በጥልቀት ይመረምራል። በማህበረሰቡ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ፣ ጠፍንገው የያዙትን ችግሮች፣ ግጭቶችን የሚፈታባቸውን ባህላዊ መንገዶች፣ ሊለውጣቸው የሚችሉትን ልማዶች፣ ሊተዋቸው የማይችሉትን ሁኔታዎች፣ ትኩረት የሚሰጣቸውን ኩነቶች እና ሌችንም ሁኔታዎች ይተነትናል። ካርል ማርክስ እንደሚለው ማህበረሰብ የመደብ ግጭት ውጤት ነው፣ የግጭቱ መንስኤ ደግሞ እያለቀ የሚሄደው የተፈጥሮ ሀብት ነው። ይህንን ሁኔታ በሙል ለማጥናት ሶሾሎጂ የተባለው የእውቀት ዘርፍ ጥሩ መሣሪያ ሲሆን፣ ከሥሩና ከጥሩ ማህበረሰቡን ለማምት ደግሞ አንትሮፖሎጂ የተሰኘው የጥናት መስክ ሁነኛ ዘርፍ ነው።

ሶሾሎጂ በብዙ መንገድ ከሳይኮሎጂ፣ ከፖለቲካል ሳይንስ፣ ከኢኮኖሚክስ፣ ከታሪክና ከጂኦግራፊ ጋር ቢገናኝም ከአንትሮፖሎጂ ጋር ግን ከሁሉም የበለጠ ትስስር አለው። ሶሾሎጂ የዘመኑ ማህበረሰብ ችግር ላይ ሲያተኩር፣ አንትሮፓሎጂ ግን የሚያተኩረው በጥንቱ ማህበረሰብ ችግር ላይ ነው። አሁን ያለው ማህበረሰብ ችግር ሲንከባለል የመጣ ሊሆን ይችላል።

Scanned by CamScanner

ስለዚህ እኔ የተፈለስኩበት ዋናው ምክንያት ይኸው ነው ማለት ነው። ድርጅቱ ባቀደው ጥናት ላይ ሁለቱንም አውቀቶቼን እንድጠቀም ተፈልጓል። ጥቅሙ ግልፅ ነው። አንድ ሰርጂን ታካሚውን ከበሽታው ለመፈወስ ቆዳውን እንደሚቀደው አጥንቱን እንደሚሰብረው፣ የአንድን ማህበረሰብ ችግሩን ሰርስሮ ጠልቆ ማምቅ፣ ፖሊሲ ለመንደፍና ማህበረሰቡን ለማሻሻል ይረዳል። ሀገሬን ለማምቅ ከመረምጀ ይልቅ የውጪ መርማሪዎቿ ለምን እንደሚተጉ ግልፅ ነው። አሁንም ድረስ አይናቻቸውን ከዚህች ጉደኛ ሀገር ላይ አልነሱም።

በተቃራኒው ማህበረሰቡን ጠልቆ ማምቅ፣ ለፖለቲከኞች በደነማ ጎኑ ገብቶ ጠፍንጎ ለመግዛትም ያመቻል። ኧረ ለመሆኑ እኔን አሁን የጋበዘኝ የውጪ ድርጅት በጥናቱ መጨረሻ የሚያገኘው ጥቅም ምንድን ነው? ከሰጠምኩበት ሀሳብ ስነቃ የጨበትኩት የቡና ሲኒ ቀዝቅዞ ነበር።

"ምነው ጌታው? ቡናው እጅም ላይ ቀዘቀዘኮ!" ቡና ሻጯ በግርምት እያየችኝ ነበር። "ሌላ ልቅዳልም?"

"ይሻላል።" ፍንጃሉን ከመስጠቱ በፊት የቀዘቀዘውን ቡና በመንተፍረት ቀመስኩት። የገዘሆን ሃሞት የቀመስኩ መሰለኝ። ሁለተኛውን ቡና በትኩሱ ከመቅመሴ አያን እየተፍለቀለቀች መጣች። ትናንት ለትሶ ዛሬ ሳቅ...

'ዛሬ ደግሞ ምን ሰቆቃ ትነግረኝ ይሆን?'

"እንደምን አደርክ ዶክተር?" አለች እጇን ለሰላምታ እየዘረጋችልኝ። ጊዜ ለማሳለፍ ይመስላል እጇ ላይ ያልሳለችበት ነገር የለም። ጥፍሮቿ በተለያዩ የጥፍር

ቀለሞች ተንቆጥቁጠዋል። "ዛሬ ቤጠዋት ተነቃትተሃል። ለሥራውም ዝግጁ የሆንክ ትመስላለህ።"

"በትክክል!" አልኩ በውል ላላስብበት። "ቡና ጠጪና ወደ ምትፈልጊበት ውሰጂኝ።"

"ሰምቹ ስላልደረሱ አንድ ተጪማሪ ቀን መጠበት አለብን" አለች የተቀዳላትን ቡና እየተጎጨች።

"ሰምቹ?!..እኮማን ናቸው ሰምቹ?!...."

"ጥናቱን ለመሥራት የሚያግዙን ሰዎች ናቸው። ምነው ደነገጥክ?"

"አያይ!...አልደነገጥኩም።" ከቡና ሻጯ ፊት ለላ ጉዳይ ማውራት አልፈለኩም። በዛ ላይ ከመግቢያ መውጫዬ ፊት ለፊት ናት። ሒሳቡን ከፍዬ ተነሳሁ።

"እንግዲያውስ ... ቀትሩ ላይመጣ ወደ ትናንቱ ቦታ ብንሄድ ደስ ይለኛል" አልኳት የጠዋቷን ጮራ በስተምሥራቅ በኩል እየተመለከትኩ።

"ወደኸዋል ማለት ነው?"

"ውሃ ደስ ይለኛል። በተለይ የሚወርድ ወንዝ መንፈሴን ይማርከዋል። አዲስ አበባ ስለምናር ንፁህ ወንዝ ሲወርድ ለማዬት ባልታደልም ወደፊት ቀሪ ህይወቴን ወደ ገጠር ወጣ ብዬ ወንዝ ዳር ቤት ሠርቼ ብናር እያልኩ እመኛለሁ።"

"የእኔም ምኞት ነበር።" "እንዳቀረቀረች ጥቂት ርምጃዎችን ተራመደች። የተገደለው እጮኛዋ ትዝ ብሏት መሆን አለበት።

Scanned by CamScanner

"ለምንድን ነው ስለ እኔ ብቻ የምለፈልፈው? ስለ አንተ ታሪክ ለምን አትነግረኝም?" አለችኝ ቆም ብላ።

"ምን ታሪክ አለኝ ብለሽ ነው?" አልኩ ፈገግ ብዬ የምን ግዴን። ከየት ጀምሬ ልነግራት ነው? ከባዶነቴ ጋር አፋጠጠችኝ።

"ሚስት አለችህ?"

"አሁን የለችኝም" አልኩ ሳቁን አፍኜ ታሪኬን ከሚስቴ መጀመሯ አየገረመኝ። ለነገሩ ልክ ናት። እንዲያውም ትክክል ናት። ከሴት ስለመጣን ታሪካችን ሁሉ ከሴት ይጀምራል። አንዳንዴ ሳስበው ሴት ቀድማ የተፈጠረች ይመስለኛል።

"ምን ማለትህ ነው?" አለች ሳቅ ብላ። "አሁን የለችኝም ማለት ...እዚህ ይዣት አልመጣሁም ማለትህ ነው?"

"ፈታናለች ማለቴ።"

"ምነው መጥፎ ሰው ነህ እንዴ?" ቆም ብላ አስተዋለችኝ። ገፍቶም መጥፎ ሰው አትመስልም። ግን... መልካም በሚመስሉ ሰዎች ውስጥ የተሸፈነ አደገኛ አውሬ ሊኖር ይችላል።"

"ትክክል ልትሆኚ ትችያለሽ።"

"ውስጤ አውሬው አለ እያልከኝ ነው?"

"የእኔውን አውሬ እንኳ አስካሁን ወጥቶ አላዩትም። በሚስቴ ውስጥ የነበረው አውሬ ግን እስከ ሰባት ቀንዶቹ ወጥቶ በዓይኔ በብረቱ ተመልክቼዋለሁ።"

"አልገባኝም።"

"ረጅም ነው ታሪኩ።" የልጆቼ እናት...መልኳ የምትመስል ውብ ሴት ነበረች። ከገፏ የሳጥናኤል እንደነበር ያወቅሁት በኋላ ነው።...በምድር ላይ የምጠላውን ሰው መርጣ በማግባት ነው የተበቀለችኝ።"

"ምን ብትበድላት ነው?...ያን ያህል..."

"ቀድሞም አብራኝ አልነበረችም። ሥጋዋ እንጂ ነፍሷ ከእኔ ጋር እንዳልነበር የተረዳሁት በኋላ ነው።"

"እንዴት ታዲያ ልጆች ወለደችልህ? ...ወይስ ልጆችም የአርሱ ናቸው?"

"በፍፁም!" ሳይታወቀኝ ድምጼ እንደ ቢጋ መብረቅ ድንገት ባረቀ። ልጆቼ የአርሱ ቢሆኑ ናሮ ምን ይውጠኝ ነበር?

"በዲ.ኤን.ኤ አላረጋገጥኩም። ባ... ባለረጋገጥም የእኔ ለመሆናቸው አንዳች ጥርጥር የለኝም። ወንዱ ቁርጥ እኔን ነው የሚመስለው። ሴቷም በህፃንነቷ እናቷን ትመስል እንጂ ቅንድቧ ሳይቀር የእኔን ነው የሚመስለው። በምድር ላይ ያሉኝ ብቸኛዎቹ ደስታዎቼ እነርሱ ናቸው።"

"ይቅርታ..." አለች አያን እጄን ሳብ አድርጋ መንገድ እያስቀጠለችኝ። "እንዲህ ትሆናለህ ብዬ አላሰብኩም ነበር። ስሜት የሚነካ ጥያቄ በመጠየቄ ይቅርታ። ያሳደገው ልጁ የአርሱ እንዳልሆነ የተነገረውን አባት ያህል ስሜቱ ሊጎዳ የሚችል የለም። እውነቱ ግን የብዙ አባቶች ታሪክ እንዲህ መሆኑ ነው።"

"አያን!... የወራሾችንን ርዕስ መቀየር እንችላለን?"

"ይቅርታ..."

"...እኔ እዚህ በረሃ ውስጥ በዚህ ቅፅበት ድብን ድፍት ብል ግድ የለኝም። ተስፋ መቁረጥ የማልችለው

Scanned by CamScanner

ልጅቷ ስላሉ ነው። ልጅቷን ሳስብ ስለነሱ ስል ሞትን አጥብቄ አፈራዋለሁ።"

"ርዕስ ቀይራ... አላልከኝም?" ክት ብላ ሳቀች። "እኔስ ለምን እንደምኖር ታውቃለህ?...በግፍ የተገደለው አባቴና ከልታማዋ እናቴ ቢያንስ በእኔ ውስጥ መኖር አለባቸው ብዬ ስለማስብ ነው። እነርሱ ሞትን የገደሉት በእኔ ውስጥ ነው። ልጅ ማለት ሞትን የምትገድልበት መሣሪያ ነው። መኖር የምትችለው በልጅህ ውስጥ ብቻ ነው።"

"ታዲያ...ይህን ሁሉ እያወቅሽ ምን አይነት ቀልድ ነው የምትቀልጂው?"

"በጥያቄ ውስጥ የተረዳሁትን የማውቀው እኔ ነኝ። ልጅቷን የሚወድ አባት መልካም ሰው ነው ማለት ነው።" ፈገግ ብላ አጥብቃ ተመለከተችኝ።

እኔም በመልሱ ፈገግ ብዬ ተመለከትኳት። የቀድሞዋ ሚስቴ ከዘጻችኝ በኃላ፣ ሴትን ልጅ ከልቤ ፈገግ ብዬ ስመለከት የመጀመሪያዬ ነው። ሁሉንም ነገር ላጫውታት ወሰንኩ። የዋቢ ሸበሌን ወንዝ አወራረድ ማጀቢያ ሙዚቃ አድርጌ ታሪኬን በሙሉ ልዘክዝላት ቆረጥኩ - ሁለተኛ አንዳች የምትጠይቀኝ ነገር እስከማይቀር ድረስ!

፲

ከዋቢ ወንዝ ማዶ ከምትገኘው የአያን ቦታ ተቀምጠን ታሪኬን ባጭሩ አተርክላት ጀመር።

"...አዲስ አበባ ነው የተወለድኩት። ከቀበና ወንዝ ማዶ በምትገኝ መንደር ውስጥ። ቀበና ወንዝ እየዋኘሁ አደኩ። አሁን ሃምሳ ዘጠኝ ዓመት ሆኖኛል።"

"በቃ?!" ዝም ስላት ጊዜ አያን ሳቋን ለቀቀችው።

"አባቴ አለቃ ዶሬ የታወቁና የተከበሩ ሰው ነበሩ። ገና በልጅነቱ ባህላዊውን የኢትዮጵያን ትምህርት አስጠንተውኛል። በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመን የተቋቋመው የቅርስ ምርመራ ቡድን አባል ስለነበሩ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ጥበቦች በየጓዳውና በየጎድጓዳው እየገቡ አስሰዋል። ያልዞሩበት ጥበብ አለበት የተባለ ሀገር የለም። ከፋርስ እስከ ባቢሎን፣ ከሺናሻ እስከ ሱዳን ለጥበብ ዘምተዋል። ከጥንቷ ኑቢያ እስከ ግብፅ እየዞሩ ጥንታዊ ጥበቦችን ቃርመዋል።"

"ምን አይነት ጥበብ?"

"ሌሎች የናቁትን ጥበብ። ሌሎች እንደ ጎላቱርና እንደ ዘበት የሚያዩትን የአስማት ጥበብ ሳይቀር ሰብስበዋል።"

Scanned by CamScanner

"አስማት?"
"አዎ አስማት። በአስማት አታምኝም?"

"በፍፁም!"

"አታስቂኝ!...እኔም አላምንም ነበር። አንትሮፖሎጂ ያጠናሽ ምሁር ሳለሽ እንዴት እንደዚህ ያሉትን ጥበቦች ለመመርመር ዓይኖችሽን አልገለጥሽም?..."

"አሉዝቢሊላሂ....እንኳን ልመረምረው ይህን የሻጣን ሥራ ስሙ ሲጠራ እንኳ ያስደነግጠኛል።"

ረጂም ሳቂን ለቅቂ ቀጠልኩ።

"በእኔ የደረሰውን ብታይ ኖሮ እንዲህ ባላልሽ!... ለማንኛውም ታሪኬን ልቀጥልልሽ። ባህላዊዉን ትምህርት በአባቴ እግር ሥር ካጠናሁ በኋላ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ገባሁ። ከልጅነቴ ጀምሬ በጥንቴ እውቀት ላይ ስለተሳብኩ በዘመናዊ ትምህርቴም ወደ ጥንቴ አለም ያጋደሉ ትምህርቶችን ነው የቀሰምኩት። አርኪዎሎጂን በጀርመን ሀገር፣ አንትሮፖሎጂን በፈረንሳይ ሀገር፣ ፊሎሎጂን በእንግሊዝ ሀገር አጥንቻለሁ። በመጨረሻም በሶሻል አንትሮፖሎጂ የዶክትሬት ዲግሪዬን በመያዝ ብዙ የምርምር ሥራዎችን ሠርቻለሁ። ሁሉም ማለት ይቻላል፣ የጥንቱን አለም ምስጢር የሚመረምሩ ናቸው። ትዳርን በተመለከተ... ወደ ሀገር ቤት ከተመለስኩ በኋላ፣ አንዲት በውበቷ የማረከችኝን ሴት አብሻቼ ሁለት ልጆች ወልጃለሁ።"

"ፈትቻለሁ...ምናምን ያልከው ነገርስ?"

"...ከልጅነቴ ጀምሬ ስለማመደው የነበረው አስማት ነው ጉድ የሠራኝ። ከአራት አመታት በፊት ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ለአንድ ጥናት ሄጄ ነበር። ...ከደርጋሶም ከተማ አለሳ፡ እንዳልኩ በሐመልማል በተሸፈነው ጫካ መመራት ጀመርኩ። መኪናዬን አቁሜ ወረድኩና ተጉዤ ሳላስበው ጫካው ውስጥ ራሴን አገኘሁት። የሚጣራ ልዩ መስህብ ያለው ጫካ ውስጥ፣ በተፈጥሮው ውበት ተማርኬ በመደመም አንዳች አስማት ማነብነብ ጀመርኩ። አስማቴ ወደ ውሻነት የሚለውጥ ናሯል ሉካ"

አያን አፏን በድንጋጤ ከፈተች።

"ወደ ውሻነት ተለወጥኩ!"

"የፈጣሪ ያለህ!" ዓይኖቿ ፈጠጡ።

"አስቸጋሪው ነገር እንደገና ወደ ሰውነት መመለሻውን አስማት አላጠናሁም ነበር። 'ከድጡ ወደ ማጡ' እንዲሉ ወደ ሰውነት መመለሻው አስማት አዲስ አበባ ከሚገኘው ቤቴ ውስጥ ሳንዱቅ ከተቆለፈባቸው ጥቅሎች ውስጥ ነበር ይገኛል ብዬ የገመትኩት።"

"አዲስ አበባ ሄድክ? ...ማ...ማለቴ እንዴት ተመለስክ ...ያን ሁሉ መንገድ?..."

"...ከሰውነት ክብሬ ወርጄ ...እንደ ውሻ አጥንት እየጋጥኩ ...ፍፁም ውሻ ሆኜ ... በስንት አሣርና መከራ አዲስ አበባ ለመድረስ አመት ፈጅቶብኛል። አዲስ አበባ ከደረስኩ በኋላ ግን ሌላናችግር ገጠመኝ።"

"ምን አይነት ችግር..."

"...እጅግ አፈቅራት የነበረችው ባለቤቴ ኤፍራታ፣ እጅግ በምድር ላይ ጠላቴ የነበረውን የቀድሞ ጓደኛዬን አግብታ ጠበቀችኝ። ሞቷል ተብዬ ናሯል። ሁለተኛ

Scanned by CamScanner

ገደለችኝ። ልጆቼ አነብቱ በምጠላው ሜንጦ በሚባል አጋሰስ ሰው እጅ ወድቀው ጠበቁኝ። አንገታቸው እንደ መቃ መንምኖ፣ ራሳቸው እንደ ጅብ ጥላ ተንጠልጥሎ በውሻ ዓይናቸው ተመለከትካቸው። ሚስቱ ግን ከባላንጣዬ ጋር አዲስ አበባን ባንድ አግሯ አቁማት ነበር። ለአሸሸ ገዳሜው፣ እድሜ ልካቸውን የሚቀልባቸው ሀብቴን፣ ከባንኩ አውጥታ ቀርቅባለች። በራሴ መኪና በራሴ ቤት እየተንፈላሰሰ፣ በዛ ላይ በራሴ አልጋ ላይ ሚስቴን እያፈሰ የጠበቀኝ ባላንጣዬ፣ የድሮ ጓደኛዬ ነበር።"

"ታዲያ ምን በጀህ..."

"በውሻነቱ ውስጥ ራሴን አረጋግቼ፣ ወደ ሰውነት የሚመልሰውን አስማት ወደ ቤቴ ገብቼ ለመፈለግ ስልቶችን መንደፍ ጀመርኩ። አያሌ ቀናትን ፈጀሁ። በመጨረሻም ጥቅሱቹን አገኘኋቸው። በጥቅሱቹ ውስጥ ግን በቀጥታ ወደ ሰውነት የሚለውጥ አስማት አልነበረም።"

"ያንተ ያለህ!"

"...በመጀመሪያ ወደ ዘንዶነት ተለወጥኩ። በመቀጠል ወደ ሌላ የማላውቀው ቀጭን መንማና ሰው ተቀየርኩ። ተስፋ ባለመቁረጥ ስሞክር ወደ ሌላ ባለፀጋ የነበረ ወደሚመስል ሰውዬ ተለወጥኩ። እንባ እየተናነቀኝ የመጨረሻ እድሌን ሞከርኩ። በዚህ ጊዜ ነበር ወደ ገረጣው እኔነቴ የመጣሁት። መለመላዬን ነበርኩ። ...ረጂም ነው ታሪኩ። ላሳጥርልሽና...በጓሮ በር በኩል ገብቼ ልብስ ለብሼ ወደ ባንክ ቤት ሄድኩ። ከአንዱ ባንክ በቀር በሌሎች ባንኮች ሁሉ ያለኝን ሀብት በሙሉ ጠራርገው አውጥተውት ነበር።

"ዘመን ከሚባለው ባንክ ያስቀመጥኩት ጠቀም ያለ ሀብት ግን አልተነካም ነበር። እሱን አውጥቼ ለሰው ልጅ

የሚያስፈልጉትን ነገሮች አደረኩ። ቀንጂ ቤት ገዝቼ ካስተካከልኩ በኋላ ልጆቼን ይገር ብቻዬን መኖር ጀመርኩ።"

"...ሚስትህና ውሽማዋ እንደገና ሲያዩህ ምን አሉ?"

"...ከወጥመድ እንደገባች አይጥ ከመቁሰጭስ በቀር ያሉት ነገር አልነበረም። ሽጉጤን አቀባብዬ ዝቼ ልገድላቸው ከፊት ለፊታቸው ተቀምጬ ነበር። ግን...ባዶ እጅ ላይ እንደመተኮስ ቆጠርኩት። ጥያቼው ወጣሁ። ባለመግደል ተበቀልኳቸው። ዘበኛዬን፣ የቤት ሠራተኛዬንና ልጆቼን ይገር ወደ አዲሱ ቤቴ ተሰደድኩ።"

"የሚገርም ታሪክ ነው። ልቦለድ ይመስላል።"

"ለእኔም እንደዛ ነው የሚመስለኝ።"

"ከዛ በኋላስ? ...ሚስት ለማግባት አልሞክርክም?"

"በፍፁም!...ከሌት ጋር ይህን ያህል ሳወራ እንኳ ከአራት አመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።"

"ጥሩ! ...ወደፊትስ..."

"የሚሆን አይመስለኝም። በልጆቼ ዓይኖች ውስጥ የማገኘው ደስታ በቂ ነው።"

"ልጆችህን የምትወድ ሌት ብትመጣስ?"

"አይመስለኝም።... ይልቁንስ ሥራዬን ጨር ልጆቼን የማይበት ጊዜ ገና ካሁኑ እየናፈቀኝ ነው።"

Scanned by CamScanner

አያን፣ ብዝምታ ለረጂም ደቂቃዎች ራሷን እየነቀነቀች ከቆዩች በኋላ፣ ከተቀመጠችበት ተነስታ፣ ወደ ሚወርደው ወንዝ ጠጠር ትጥል ጀመር።

"ዛር ልትልልኝ ትችላለህ?" አለች ከረጂም ደቂቃዎች በኋላ። "ልዋኝ አፈልጋለሁ።"
ደንግጬ ተነሳሁ።

፱

ጀርባዬን ለወንዙ ሰጥቼ ገንቡን እየወጣሁ እያለ፣ "ቾፍ" የሚል ድምፅ ሰማሁ። አያን ልብሶቿን አወላልቃ ከላ ወንዙ ውስጥ ለመዋኘት ስትገባ የተፈጠረው ድምፅ መሆኑን ገመትኩ። አስቀናችኝ። ፀሐይዋ እየከረረች በመምጣቷ መቀቱን ለማስታገስ ዋቢ ወንዝ ውስጥ ዘሎ ገብቶ መዋኘትን ያህል የተሻለ ነገር የለም። ሆኖም የአያንን ትዕዛዝ ማክበር ነበረብኝ። ከአርስዋ ጋር አብሬ ስዋኝ ብታይ የሚፈጠረውን ችግር መገመት ቀላል ነው።

ከወንዙ ገንብ አፋፍ ላይ ባለችው ብቼኛ የከኒን ዛፍ ሥር ተቀምጬ አሻግሬ ቀዩውን ሁሉ መቃኘት ጀመርኩ። አያን እንደነገረችኝ፣ የጎዴ አካባቢ ነዋሪዎች ከኒን እየተባለ የሚጠራውን ዛፍ ለወባ መድኃኒትነት ይጠቀሙታል። ቅጠሉ የፓራሲታሞል ምሬት ቢኖረውም ጨትጭተው ወባ ለያዘው ሰው እንደሚግቱት ነግራኖለች።

ከከኒኗ ዛፍ ስር ተቀምጬ፣ ቁልቁል ወደ ወንዙ ስመለከት በረባዳው ሽጥ ውስጥ ያለ ቱማታ ፀጥ ብሎ ይፈስ የነበረው ወንዝ ሲንቦጫረቅ አየሁ። የአያን የደስታ ሲቃ ድምፅ በጥቂቱ ይሰማኛል። ዋቤን ያለ አንዳች ዋቢ ንብታ እየደነከረችበት ነው። ከጥብቁ ባህል ያለአንዳች ፍርሃት በማፈንጠጧ እኔን ሳይቀር አስቀናችኝ።

Scanned by CamScanner

ከነፃነት በላይ የሚያስቀና ነገር የለም ስል ደመደምኩ። ሌሎች የሚያስቀኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ነገሮችም በነፃነት ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ይሁን እንጂ ...ነፃነት በነፃ አይገኝም። እንደ አያን መወገዘንና እንደ ስማዕት መወገርን ይጠይቃል። መወገዙንም መወገሩንም የሙቷም አትም ይጠይቃል። አያን 'ወንዴ' የሚል ትዕል ወጥቶላታል። ግን ከቁብ አትጥፈውም። ...ይልቁን በቀሰመቻት ትንሽ እውቀት አካባቢዋን አጥንታ ለመለወጥ ትብከነለች።

ከተቀመጥኩበት ተነስቼ በወንዙ ዳርቻ እየተንሸራሸርኩ፣ ከሩት ያሉት ኮረብቶች ዓይናቼን እስኪጋርጿቸው ድረስ አካባቢውን መቃኘት ጀመርኩ። ከአድማሱ ጥግ ያሉት ኮረብቶች የዚህን በረሃ ታሪክ ይተርኩልኝ ይመስል በዓይናቼ ጨረሮች ዳሰስኳቸው። ወደዚህ ከመምጣቱ በፊት ስለዚህ አካባቢው ነዋሪዎችና ስለዚህ በረሃ የሰቆታ ታሪክ ያነበብኩት ሁሉ የጀሮ ታንቡር እንደሚበሳው ነፋስ ያፏጭብኝ ጀመር።

ሱማሌዎች በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1200 ዓመተ ፍዳ ጀምሮ የዚህን በረሃ ፍዳ እየቀመሱ መኖራቸው በታሪክ የተመዘገበ ነው።

ቀደምት ጥንታውያ ዕሁፎች እንደሚያስረዱት፣ ይህን በረሃ ይዘውት የነበሩት ነገዶች፣ ከነም ነገድ የወጡ አፋር የተባሉ ህዝቦች ነበሩ። አጋኤን ውስጥ ጥንታዊ ከተማም እንደነበራቸው ጥንታዊ ከታቦች ይገልፃሉ። ዘመኑ በውል ባይታወቅም እነዚህ ህዝቦች ስልጣኔ እንደነበራቸው ውስን የሆኑ ድርሳናት ይገልፃሉ። ምናልባት የራሳቸው የዕሁፍ ባህል ስላልነበራቸው ይሆናል ስልጣኔአቸውን የበረሃው

አሸዋ ውጦት ቀርቷል። እስከዛሬ ድረስ በብዙ ሊቃውንት ዘንድ አወዛጋቢ ሆኖ የቆየው ነፍንት ምድርም ይህ ቢረሳ እንደሆነ በመግለፅ የሚከራከሩ አልጠፉም።

ምሁራኑ ይህ አካባቢ የፑንት ምድር እንደሆነ እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡትም የአካባቢውን ኮረብቶች የወረረውን የአጣንና የከርቤ ዛፍ ነው። የጥንታዊቷ ንግሥት በነበረችው ሃትሸፕሱት ዘመን በፒራሚድ ላይ ተቀርፆ እንደተገኘው፣ የፑንት ምድር ከርቤና እጣን የሚታፈስበት ሰማዕድናት የበለፀገ የንግድ መናኸሪያ ነበር። የፑንት ምድር ቀጫጭኖች ጥቋቁር ተዋህቦችም፣ አልመው የማያስቡ ነበሩ። ምድራቸውንም፣ የግብፅ የፒራሚድ ላይ የሄሮግሊፊክስ ዕሁፎች የአማልክት ምድር ሲሉ ይጠሩታል። ጥንታዊ ግሪኮች፣ ይህ ምድር ኢትዮጵያ እያሉ የሚጠሩት ሀገር አህል የሆነና የተቃጠለ ፊት ያላቸው የፑንት ህዝቦች የሚኖሩበት እንደሆነ ዕፈዋል።

ከክርስቶስ ልደት ከ1473 እስከ 1488 ዓመተ ዓለም የነገሡትው የግብፅዋ ንግስት ሃትሸፕሱት ወደዚህ ምድር ከሳተኛ ልዑካንን፣ በንግድ ለመተሳሰር ፑንትን ያመራ የነበረው ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ፓሬሉ እንደነበር በደር አል-ባሪ ቤተመቅደስ ላይ በሄሮግልፊክስ ተቀርፆ ይኛል።

በኋላ ግን የኤደን ባህረ ሰላጤን እየተሻገሩ የመጡና በልዕላ የነበረ ንግዳቸውን ለመቆጣጠር የቋመጡ የአረቢያ ምድር ነገዶች ገብተው ተቀየጧቸው። ምድራችንን እንሰትም ያሉት የመጤዎችን ባህልና ሃይማኖት በመተበል በረሃውን ሙጥኝ ብለው ሲቀሩ፣ ጥንታዊ ባህላቸውንና ወጋቸውን የያዙት ግን ወደ ደጋማው የኢትዮጵያ ከፍል እንደ ሸሹ ከታቦች ያስረዳሉ። አሁንም ድረስ የሶማሌ ወገዶች ራሳቸውን 'እንደ ጎበዝ ጦረኛ መቁጠራቸው ከዚህ የተደመ

Scanned by CamScanner

ታሪክ በመነሳት ይሆን?... አሁንም ድረስ የሶማሌ ወንዶች፣ እረኝነትን ለሴቶች በመተው ኢላማ ሲለማመዱ መዋል ልማዳቸው ነው። የሶማሌ ልጃገረዶች የፍቅል መንጋ ሲከተሉ ማየትና ወንዶቹ መሣሪያ አንግተው ሲንጎማለሉ መመልከት አዲስ አይደለም።

ሶማሌዎች፣ ተመሣሣይ ቋንቋ ቢናገሩም፣ ዘጠና ዘጠኝ በመቶ ተመሣሣይ የሆነ የእስልምና ሃይማኖት ቢከተሉም፣ ሁልቆ መሣፍራት በሌለው ጎሳ የተከፋፈሉ ናቸው። ደም አፋሳሽ ለሆነ አልቂት የሚዳርግ የጎሳ ጦርነትም በረሃውን ለዘመናት ሲያምስ የኖረ ነው። ነገር ግን እርስ በእርስ ይጋጩ እንጂ ለሌላ ጠላት ግን አንድ ላይ ይነሳሉ።

የረጋ ሀይማት መሥርተው በግብርና እና በእደ ጥበብ የተሠማሩ ጎሳዎች ቢኖሩም፣ በዘላንነት የከብቶቻቸውንና የግመሎቻቸውን ጭራ ተከትለው በረሃውን የሚያካልሉ ጎሳዎችም አሉ። ዘላኖቹ፣ ከእንጨት ቅርንጫፎች ተውተርትረው በተሠሩና ስጋጃ በለበሱ ተንቀሣቃሽ ጎጆቻቸውን ከሌቶቻቸው ሲቸሩ፣ ምግቦቻቸውን ከሚከተሏቸው መንጋዎቻቸው ያገኛሉ። የፍዙልና የግመል ውተት፣ የግመል ሥጋ ሲመገቡ በረሃው ሲቸርም ፍራፍሬ ይለቅማሉ። ከጥንታዊ አረቦች ወይም ህንዶች የወረሱት እንደሆነ የሚነገርለት ሻይ በወተታቸውም ዝነኛ የባህላቸው መገለጫ ነው።

ሶማሌዎች... አጆራን፣ በርሱክ፣ ካለድሬ፣ ዳሮድ፣ ዲር፣ ጋዳቡርሲ፣ ጉርጉራ፣ ሃባር ገደር፣ ሃርቲ፣ ኢሳ፣ ሃራብ፣ ማጂርቲን፣ ሙሴ፣ ማር ሃን፣ ጂድ ዋቅ፣ ሺካል፣ ይብር... የተባሉ አያሌ ጎሳዎች ሲኖሩት፣ ኢጋዴን የተባለው ጎሳ ግን ላቅ ያለውን ቁጥር ይይዛል። እንዲሁም ራዌና ከዲር የተባሉ ጥቂቁር የሶማሌ ጎሣዎች ሲኖሩ፣

ዱቤ እና ኤረርበሬ የተባሉት ደግሞ ለየት ያለ ታሪክ እንዳላቸው የሚነገርላቸው የሞቢ ሽበሌን ወገዝ ተከትለው የሚኖሩ ጎሳዎች ናቸው። እነዚህን የሞቢ ሽበሌ ወገዝ ተከትለው የሚኖሩ ጎሳዎች እዚ ምኒልክ አምጥተው እንዳሰፈሯቸው አንዳንድ አዛውንቶች ይናገራሉ።

በጥልቅ ሀሳብ ውስጥ ገብቼ የወገዙን ጸርቻ በመከተል ረጂም ርቀት እንደተጓዝኩ የተገነዘብኩት ኩንክ ኮሚባለው የመስና እርሻ ስደርስ ነበር። እንደለመደብኝ በጥንቱ ዓለም ታሪክ ጠልቄበት ኖሯል። የዚህን እሸዋ ያስጠመው ቢረሃ ጥንታዊ ታሪክ አእምሮዬ ከአካሉ ወጥቶ ይቆፍር እንደነበር የተገነዘብኩት፣ ከሃሳቤ ስነቃ የፀሐይዋን መክሸር አይቼ ነበር። በጤናዬ ብሆን ናሮ ላቢን ለመጥረግ የሰበሰኩት ልብስ ሁሉ ባልበቃኝም ነበር። ነገር ግን ከራሴ ጋር አብሬ ባለመኖሬ የተነሣ ግንባሬ ችፍፍ ያለ ሳብ ቀርቶ ወዝ እንኳ አልነበረውም። በፍጥነት ወደመጣሁበት መመለስ ጀመርኩ።

ብቻዋን ወንዙ ውስጥ ንብታ እየዋኘች የነበረችው አያንን ይህን ያህል ጥያት መምጣት አልነበረብኝም። የሚያጋጥማትን ማን ያውቃል? ልብሷን ለማውሰት ቦር በልልኝ አለችኝ እንጂ ትተሽኝ ሂድ አላለችኝም። በአእምሮዬ ውስጥ ክፉ ክፉ ሃሳብ እየመጣ ተሰንሰንኝ። ወደኔ አቅጣጫ የዞረ የራሴን ዱካ ተከትዬ ወደመጣሁበት ገሰገስኩ።

Scanned by CamScanner

1

እያለከለኩ ወደ ወንዙ ወርጄ ውሃው ጸር ቆምኩ። ላቤ በጉንጨ እየተንቆረቆረ ነበር። የአጋጄን ወበት ልብሴን አስወልቆ ሊያሳብደኝ ደርሷል። ዋቢ ላይ ዓይናቸን እንከራተትኳቸው። መቀቱ ወንዙን እንደ ሽሮ ያንተከትከው ይመስላል። የኢያንን ልብሶች ነፋሱ ወስዶ በየቆንጥሩ ሰቅሏቸዋል። አያን ግን የትም አትታይም። ዓይናቸን ፀጥ ረጭ ብሎ በሚፈሰው የዋቢ ወንዝ ላይ አትበዘበዝኳቸው። አያንን ግን ማዬት አልቻልኩም። የት ገባች?

"አያን!" ተጣራሁ። የራሴ ድምፅ፣ በወንዙ የገደል ማሚቶ መላልሶ አስተጋባብኝ። ደጋግሜ ተጣራሁ።

"አያን!...አያን!...አያን!..."የገደል ማሚቶው ደጋግሞ አስተጋባ።

የት ገባች? ልብሶቿ ከወንዙ ማዶ ባሉት የቆንጥር ዛፎች ላይ እንደ ባንዲራ ተሰትሰው በፈጣኑ ነፋስ ይርገበገባሉ። በወንዙ ጸርቻ ከወዲያ ወዲህ በፍጥነት እየተመላለስኩ ተጣራሁ። መልስ የለም። በአእምሮዬ ያሰብኳቸው ሰቅጣጭ ቅዠቶች ምስል ሠርተው ተንቀሳቀሰብኝ። የወንዙ ጸር የበረሃ ዘንዶ ተወርውሮ የተጠመጠመባት መሰለኝ። ግዙፉ ዘንዶ መገቢን ጨምቶ ካደቀቃት በኋላ

በጉሮሮዋ አፉን መልማዶ ሲውጣት በዓይነ ህሊናዬ ተመለከትኩ።

ዓይናቸን አርገብግቤ አሁንም ተጣራሁ።...አራሴ የድመቷ ማሚቶ በቱር አሁንም መልስ አላገኘሁም። ፣ደራሽ ውሃ መሰናት ይሆን?፡ ስልም አሰብኩ። የዋቢ ሸለቆ ወንዝ ከታላላቆቹ የኢትዮጵያ ተራሮች ስለሚነሳ ምናልባት እላ ዘንበ ሊሆን ይችላል ስል ገመትኩ። እዚህ በረሃ ውስጥ እንዲት የዝናብ ጠብታ ሳትኖር የዋቢ ሸለቆ ወንዝ እስከ አናቢሙ ግጥም ብሎ እንደሚሞላ ሰምቻለሁ። ይሁን እንጂ ወንዙ ምንም ለውጥ አላሳዬም፣ ጠዋት ስመጣ እንዳዬሁት ነው። በወንዙ ጸርቻ ምንም አይነት አዲስ የመጣ ግፋር የለም።

አጥብቴ በመመልከቴ ብቻ በፀሐዩ ጨረሮች የሚያንፀባርቀው ወንዝ አያንን ይተፋት ይመስል፣ የራሴን ምስል እስክይ ድረስ አፍጥጬ ከቆዬሁ በኋላ አንድ ውሳኔ ላይ ደረስኩ። ጉበቼ ልፈልጋት ቆረጥኩ።

የዛሬን አያድርገውና በልጅነቴ ቀበና ወንዝ ውስጥ ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር እዋኝ ነበር። ዛሬ ግን ቀበና ወንዝ ውስጥ ገብቶ የሚዋኝ ልጅ ያለ አይመስለኝም። ቀበናን የአዲስ አበባ የቆሻሻ ጉድ ይዝቦጎደጎድበታል። በድልድዩ ላይ ሳልፍ እንደተመለከትኩት የየሸንት ቤቱን ቆሻሻ ይዞ የሚገዘው የቀበና ወንዝ፣ ያልወጣውን የአጋጄንን ነጻድ ድፍድፍ እንጂ ውሃ አይመስልም። እዚህ ቆሚ አዲስ አበባን ሳስብ ገብቶ ለመዋኘት ቀርቶ አይቶ ለማለፍ የሚያስጠይፉት ወንዞቿ በዓይናቸ ላይ ተሳለብኝ። የአዲስ አበባን ጥንካት እንጂ የህገዘቡን ብሶት ይዘው የማያወርዱት ወንዞቿ ሲፈሱ ታዩኝ። በልጅነቴ የለመድኩት ዋና፣ እንኳን ሌላን ሰው ለማዳን፣ ለራሴም የማያወላዳ ቢሆንም ልብሶቼን

Scanned by CamScanner

አወላልቄ ልገባ ተሰናዳሁ። አያንን ባላድናት እንኳ ሳልፈልጋት ትቻት መሄድ አይቻለኝም።

መለመላዙን ቆሜ እጀቼን ወደ ወንዙ ዘረጋሁና አመነታሁ። በመስጠምና በመንሳፈፍ መሃል ያለውን ልዩነት ለምን ማሰብ እንዳስፈለገኝ አልገባኝም። ሰዎችን የሚያስጥመን ፍርሃታችን እንደሆነ ሰምቻለሁ። ይሁን እንጂ ስለዚህም ማሰብ አያስፈልገኝም ነበር። የሰው ልጅ ትልቁ የሽንፈቱ ምስጢር ፍርሃቱ ነው። ፍርሃት በራሱ ያስፈራል። ሆኖም... ፍርሃት የሚመጣው ለመኖር ካለ ጉጉት ነው። መኖር እንዳለብኝ ግልፅ ነው። ሰው ከወለደ በኋላ ፍርሃቱ በእልፍ ይጨምራል። ሰው ከወለደ በኋላ መኖር ምርጫው አይደለም፤ ግዴታው ነው። የመኖርና ያለመኖር መብቱን በልጁ ይነጠቃል። አዲስ አበባ ጥያቼው የመጣኂቸው ልጀቼ ውልብ አሉብኝ። አባታቸውም እናታቸውም እኔ ነኝ። እናታቸው ወልዳ እንደ እቡት ጥላቸዋለች።

የልብ ምቴ ይሰማኛል። በመስጠምና በመንሳፈፍ መሃል ቆምኩ። በመላምት መዋኘት ቢቻል ኖሮ ይህን ያህል ባላንበቀበቀኝ ነበር። ዋና ስለማመድ የተኖው የአእምሮአችን ክፍል ለመንሳፈፍ እንደሚያስችለን አውቃለሁ። የፊተኛው የአእምሮአችን ክፍል ፍርሃታችን ተቆጣጥሮ እንደ አስከሬን ያንሳፍፈናል። አስከሬን የማይሰጥመው ስለማይፈራ ነው። ነፍስ ያላወቁ ህፃናትም አይሰጥሙም። ይኸውም ፍርሃት ስለሌላቸው ነው። ዋና የማይለማመዱት እንስሳት ብቻ ናቸው። ወደ ወንዙ ልገባ ስንደረደር አሳትና ውሃ ሲበዙ እንደሚያስፈሩ እያሰብኩ ነበር።

እንደምንም ጥርሴን ነክሼ ወንዙ ውስጥ ተደነበቅሁ። ለለኮንዶች ራሴን ስቼ ነበር። በደመ ነፍስ እየተንሳፈፍኩ

ነበረ። በልጅነቴ የለመድኩት ዋና አልጠፋብኝም። በሊቃ መሀከ።

"ሁሁ!" የልብ ልብ ተሰምቶኝ በወንዙ ላይ ከወዲያ ወዲህ እየተንቦራጨኩ አያንን መጣራቴን ቀጠልኩ። ነገር ግን አሁንም ደምሰዋ የውሃ ሽታ እንደሆነ ነው።

ጠልቄ ለማዩት ሞከርኩ። ውሃው የጠራ ባለመሆኑ ጉም ከመሰለ ነገር በቀር የሚታዩኝ ነገር የለም። ያለሱን እንድ ትልቅ ቋጥኝ ግንባሬን ሊያረቅሰኝ ለጥቂት ተረፍኩ።

ለአያሉ ደቂቃዎች በወንዙ ላይ እየጠለኩና እየተንሳፈፍኩ ፈልጌ ከአጣኂት በኋላ ተስፋ ቆርጨ ዋናዬን ለማቋረጥ መስንዙ። ወደ ከተማ ሄጀ ለፖሊስ ማመልከት ይኖርብኛል። በወንዙ ዳርቻ ላይ ነፋስ ወስዶ የሰቀላቸውን ልብሶቼን ባዬሁ ቁጥር የበለጠ እንጀቴ ይላወስ ጀመር። ጉርሮዬን እንዳች ነገር እያነቀኝ ያጫወተችኝን ታሪኢን ሁሉ አስታወስኩ። የአባት የእናቷ አለቃቂ እሚሚት የጫነባትን የሀዘን ካባ ሳታወልቀው ወደ መጣችበት መመለሷን ሳስብ እንባ ተናነቀኝ። ሆደ ቡቡ ያልነበርኩት ሰውዬ ባር ባር እያለኝ ወደ ወንዙ ዳርቻ ዋኘሁ። ነገር ግን ኮኂላዬ ባለው የወንዙ ዳርቻ የሆነ ነገር የወንዙን ፀጥታ ሲያደፈርሰው ሰማሁ። ሽዋ! ካለው የውሃ ድምፅ ጋር የተቀላቀለ ሳቅ ስሰማ ከመቅፅበት ድምፁን ተከትዬ ዞርኩ። አያን ከወዲያኛው አቅጣጫ እየዋኘች ወደ እኔ እየመጣች ነበር።

"የፈጣሪ ያለህ!" አልኩ በተዘበራረቀ ስሜት።

"ምን ነካሽ?!...ኦሞትሽ መስሉኝ ነበር።"

እየሳቀች ብቻ ኮጥጌ ደረሰችና በጠምታ ተመለከተችኝ።

"እዛ ማዶ ካለው ቋጥኝ ውስጥ ተወሽቄ የምታደርገውን ሁሉ እየተመለከትኩኝ ነበር። አለች ትንፋሽዋ እስኪገርፈኝ ተጠግታ።

Scanned by CamScanner

"ዝግም ነው ያስደነገጥሽኝ።"

"ባለፈው በነገርከኝ የአስማት ችሎታህ በውሃው ላይ እየተራመድክ ትፈልገኛለህ ብዬ ገምቼ ነበር።" ኮኮነ ስትዋኝ አግሮቿ አግሮቼን እየነኩኝ እንደሆነ ተሰማኝ።

"እንዴ! ምን ነካሽ? እኔ እዚ አስማተኛ አይደለሁም።"

"ስለ አስማት አጥብቀህ ከማጥናትህ የተነሳ ከአስማተኞች ሳትበልጥ አልቀረህም። ወደ ውሃው ከመግባትህ በፊት እጆችህን ዘርግተህ ሰረጅም ደቂቃዎች ስትቆይ አንዳች ነገር ሲታሰት እንደሆነ እየገመትኩ ነበር። አስማት እየሠራህ መስሎኝ ነበር።"

"ከፍሁም እንደዛ አልነበረም። ዋና ያቆምኩት በልጅነቴ ነበር። ተረስቶኛል ወይስ አልተረሳኝም? እስጥማለሁ ወይስ አልሰጥምም ብዬ በመጨነቅ ላይ ነበርኩ።"

"ህይወቴን ለማዳን ደፍረህ እዚህ የማታውቀው ወንዝ ውስጥ ስለገባህ አመሰግናለሁ!" አለችና ይበልጥ ተጠግታ ዓይኖቿን ዓይኖቼ ላይ አንከባለለችብኝ። አንዳች ልዩ ስሜት የሚፈጥሩ ጨረሮች የረጩችብኝ መሰለኝ። ከራሴ ጋር እየታገልኩ ዝም አልኳት። በነገረችኝ ግለ ታሪኳ መሠረት በ1969ዓ.ም ከተወለደች በዚህ ሰዓት እድሜዋ 39 አካባቢ ይሆናል። ይሁን እንጂ ገና የሃያዎቹ አካባቢ ልጃገረዶች ትመስላለች። ሰውነቷ ጥርት ያለና ልዩ መስህብ ያለው ነው። የዋና ልብስ ባለመልበሷ ምክንያት መላ አካሏን አለማዬት አልቻልኩም። ከሾሉት ጡቶቿ ላይ ዓይኖቼን ለማሸሽ ጥረት ባደርግም፣ እርሷ ግን እንዳያቸው ፍላጎት ያላት ይመስል ከፊት ለፊቴ እየተስተካከለች መዋኘቷን ቀጠለች። ህይወቷን ለማዳን

አደጋ ላይ ጥዬ መግባቴን እየደጋገመች ሦስት ጊዜ በማመስገን በዙሪያዬ እየተሽከረከረች ስትዋኝ፣ ልዩ ትርፎ ያለው ዳሌዋንና የዘንባባ ፍሬ የመሰሉ ሞኖቿን ማየቴን አላቆምኩም። እውነት ለመናገር ካለፋት አራት አመታት ወዲህ የሴት ልጅ ሙሉ እርቃን ገላ ላይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። በዘይል ሰርጨሜ የገረፈችኝ የቀድሞዋ ሚስቴ በልቤ ላይ ለሴቶች የጥላቻ አመዳይ እንዲወድቅ አድርጋለች።

"ሚስትህ ያሳደረችህብህ ጥላቻ ሁሉንም ሴቶች በጥቅል አስፈርጀሃል። አይደለምን?" አለች አያን እንደገና ከአጠገቤ እየዋኘች።

"ውስጤን ማንበብ እንዴት ቻልሽ?...እኔም ይህንኑ እያሰብኩ ነበር።" ስሜቴ እንዳይነበብብኝ እየታገልኩ መለስኩላት። "እም...ሴቶች ሁሉ የአንድ ዛፍ ቅጠሎች ይመስሉኛል።"

"ስህተት ነው" አለች ከት ብላ ስታስቃ። "...እኔ የማስበው ግን ተቃራኒውን ነው። ፌሚኒስት ሆኜ ግን አይደለም። እንዲያውም ለወንዶች ሳላዳላ አልቀርም። ሞራሽ ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው ብዬ አላምንም። ሰዎች እኩል መሆን ያለባቸው በህግ ፊት ብቻ ነው። ከዛ ውጪ ባለው ሁሉ ግን መነሻዐር እንኳ የለባቸውም። ጠባያቸውና አመለካከታቸው ሁሉ እንደተቀዱበት ማህበረሰብ፣ እንደቀሰሙት እውቀትና ልምድ ይለያያል። ኢፍራታን ባዩበት ዓይን አያንን ማዬት ፍዙም ስህተት ነው።"

መልስ ሳልሰጣት ለአያሌ ደቂቃዎች ተመለከትኳት። ሳቀችብኝ። ደጋግማ ሳቀችብኝ። እያላገጠችብኝ ነው ብዬ እስካሰብ ድረስ ሳቀችብኝ። ጠፍንጎ ያሰረኝ አመለካከ

Scanned by CamScanner

ሊያስጥመኝ እየታገለ፣ ዋኝተን ከወንዙ ዳርቻ ስንደርስ፣ የሚቀባበል የክላሽንኮቭ ቃታ ሰምቼ በደመ ነፍስ ቀና አልኩ። ስድስት ያህል፣ ሞንብል ያጠለቁና አውቶማቲክ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች፣ የተቀባበሉ መሣሪያዎቻቸውን ወድረው ከወንዙ እንድንወጣ አዘዙን።

16

መሳሪያ ያቀባበሉት ሰዎች ባንክ ሲዘርፍ፣ እንደተያዘ ወርበላ በንደል ተጫጫሁብን። ቋንቋቸው ሶማልኛ እንደሆነ ተረድቻለሁ። አዛዣቸው ይመስለኛል አንዳንድ የአረብኛ ቋንቋ ይቀላቅላል።

"ቢሱር አህ! ...ቢሱር አህ!" ይላል እየደጋገመ። "ቶሎ በል! ...ቶሎ በል!"

እንደኛው ተንደርድሮ መጣና ሞንቅላቴ ላይ የክላሽንኮቩን አፈሙዝ ደቀነብኝ።

"ወሪያ! ሶአ!" አለ ወደፊት እየገፈተረኝ። "አንተ! ቀጥል!" የጫማው ቁጥር መቀመጫዬ ላይ አስኪቀረፅ ድረስ ረገጠኝ። ሌላኛው አፋኝ፣ ልብሶቼን አይነ ምድር የነካቸው ይመስል ተጠይፎ በጠመንጃው አፈሙዝ አንስቶ ሲያበቃ፣ ሰለላኛው አቀበለው።

አለቃቸው እንደሆነ የገመትኩት አስፈሪ ሰውዬ፣ አረብኛና ሶማልኛ እየቀላቀለ ሲለፈልፍ ከቆዩ ቦኋላ ልብሶቼን የወሰዳቸው ሰውዬ ሽርጥ አምጥቶ ሰጠኝ። እየተንዘፈዘፍኩ በወገቤ ዙሪያ አሸረጥኩ። ከወገቤ በላይ እርቃኔን ነኝ።

"ሶአ!" አለኝ ሰብሼ እንደጨረሰኩ በጠመንጃው አፈሙዝ ሞንቅላቴ አስኪበሳ ጎስሞኝ። "ቀጥል!" እያጣደፈ ጫንቃን በአፍንጫ አስወጣኝ።

Scanned by CamScanner

ጻተቱን ጨርሼ ወደኋላ በትዕበት ስመለከት፣ እንደኛው ወንበዴ የሚያብለጨልጭ ጨቤውን ከአያን አንገት ሥር ወሽቆ ወጉሯን ጨምድዶ ወደ ጻተቱ እያንደረደራት ነበር። አርሷም እንደ እኔ አሸርግሰች። ሞንቅላቱ በአንገቱ ዙሪያ እስኪሽከረከር ክብድ ጥፊ መንጋጭላዩ ላይ ሲያሳርፍበኝ አያንን ማዬቱን አቁሚ ጉዞዬን ቀጠልኩ።

"ሚን ፋድላክ?!" ስትል ብቻ ይሰማኛል በአረብኛ. "እባክህ!?" ወጉሯን እየንጫት ወይም ሳንጻው አንገቷ ሥር ቀጿት ይሆናል።

"ዋሲኽ!" ይላታል ድምፁን ከፍ አድርጉ "ቆሻሻ!"። ሌሎቹ ሞንብል ያጠለቱ ወንበዴዎች በግራና በቀኝ በፍጥነት እየተራመዱ አካባቢውን በጥንቃቄ ይቃኛሉ። የቀትሩ ጊዜ ስለተቃ በአካባቢው ዝር የሚል የሰው ዘር የለም።

በግምት ለሃያ ደቂቃ ያህል እንደጋለ ብረት ምጣድ አግርን በሚጠብሰው የበረሃ አሸዋ ላይ ከተንገዘን በኋላ በረሃው ውስጥ ወደ ቆመ ከፍት የመስክ መኪና ደረስን። የእኔንና የአያንን አግርና እጆች ጠፍንገው ካሰሩ በኋላ ዓይኖቻችንንም በጥቁር ሻሽ ግጥም አድርገው ጠፍረው ሲያበቁ፣ አየተሸከሙ ወደ ከፍቱ መኪና እንደ አቃ ወረወሩን። ሁለታችንም በከፍቱ መኪና ወለል ላይ እያቃሰትን ወደቅን። ወንበዴዎቹ በፍጥነት ከወጡ በኋላ መኪናው ሞተሩን አስንርቶ ሲያስነሳ ተሰማኝ። ትንሽ ቆዩና በበረሃው ወጣ ገባ መንገድ ላይ ገጭ ኃ እያለ እንደ የሱስ ይከንፍ ጀመር።

፲፬

በግምት ለሶስት ስዓታት ያህል፣ በረሃው ውስጥ በከፍቱ መኪና ነፍሳችን እስክትወጣ እየተንጫንጭን ከተጓዝን በኋላ፣ መኪናው በድንገት ቆመ። ወንበዴዎቹ እንደ እቃ ተሸከመው ወደ ታች ሰቀቁን። ወደ ገደል ሊጥሉን መስሎኝ ነበር። ጀርባዬን የሚከናስኝን ቋጥኝ ስጠበቅ፣ በድብደቱ አሸዋ ላይ ሳርፍ ከዚህ በፊት አውጥቸው የማላውቀውን ድምፅ አወጣሁ። ድቡሽቱ አሸዋ ባፍ ባፍንጫዬ ገብቶ ትንፋሼን አሳጠሮት ትን ብሎኝ አላልኩ።

አያንም አንርታ ስትወድቅ ሰማሁ። እግሮቻችንን ተራ በተራ ከፈቱልን በኋላ፣ አየረገጡ አስነሱንና እንደገና በእግር ይነዱን ጀመር። የምንወርደው ቁልቁለት እንደሆነ ተረዳሁ። የመንገዱ ጎንና ጎን የሾሉ ድንጋዮች እንዳሉበት የገባኝ በተደጋጋሚ ሲንስሙኝና አጥንቱ እስኪሰበር ንን አጥንቴን ሲወጉኝ ነበር። አያን ከፊት ለፊቴ እንደሆነች የተረዳሁት የቋጥኙቹ ውግ ሲያስቃስታት ነበር።

ቁልቁለቱን ለሃያ ደቂቃ ያህል ወርደን ስናበቃ በሚዎጉ ጠጠሮች ላይ መንገዝ ቀጠልን። ከሾሉት ጠጠሮች ንፁ በኋላ ደግሞ እግሮቼ ከውሃ ውስጥ ሲገቡ ታወቀኝ። ውሃው ቀስ እያለ እስከ ወገቤ ድረስ እያስጠመኝ ሲመጣ ታወቀኝ። ውሃው ከወገቤ ሳያልፍ እየተንሰ መጣና አበቃ። ወንዝ

Scanned by CamScanner

እንደተሻገርን ተረዳሁ። ምናልባት ዋቢ ሸበሌን በሌላ አቅጣጫ መልሰን እየተሻገርነው ይሆናል።

እንደኖና በወገቡ ዳር ጠጠሮች ላይ ካለፍን በኋላ ጫጉ እየወጣን መሆኑን ተገነዘብኩ። ንግግር የለም። የእያንዳንዳችን ወገቡን ከተሻገርን በኋላ አልተሰማኝም። በንጹት ለአሥር ደቂቃ ያህል ጫጉን ከውጣን በኋላ አስቆመን።

በሰማልኛ ቋንቋ እየተጫጫሁ ሲያወሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ሆነ ሽለቆ ወደሚመስል ነገር ታጠፍን።

ከዮቂት ደቂቃዎች ጉዞ በኋላ የሆነ በር ተንጫጫው ሲከፈት ሰማሁ። ወዲያው አንድ ፈርጣማ ሰውዬ እንኳ አስኪሰበር ወደታች ጭንቅላቴን ደፋና አንደረደረኝ። እንደገባሁኩ ተንደርድሬ ባፍ ጢሜ ተደፋሁ። ድውሸ አፈር ሲውጠኝ ምንም አልተረዳም።

የወረወረኝ ሰውዬ ምንም ላይናገር በራን ከኋላዬ በኃይል ዘግቶት ሲሄድ ተሰማኝ። ከወዲያኛው ጥግ አያን ስታ ስትት ተሰማኝ።

"እያንሮ ተጣራሁ። ያለንበት ቦታ ያስተጋባል። ዋሻ እንደሆነ ተረዳሁ።

"ዲዲሞስ!"

"ተጎዳሽ?!
"እንተስ?!"
"ደህና ነኝ!"
"እንማን ናቸው?!....ምን ፈልገው ነው?!...."
"አላውቅም!...አላውቃቸውም።"
"የትነው ያለነው? ዓይናቸሽን አልፈቱልሽም?!"

"አላወቅሁም። አልፈቱልኝም። ያንተንስ?!"
"አልፈቱልኝም። ያለንበት ዋሻ ውስጥ ሌላ እንደኛ የታሰረ ይኖራል!?" ስል ጠየኳት።
"ዮሴም መሰለኝ። ... ስጠይቅ ጥያቄዬን የመለሰልኝ ድምፅ የለም።"

አፈራ ባጠለቀው ዋሻ ውስጥ እንደወደቅን፣ በፍርሃት የሚሆነውን መጠባበቅ ጀመርን። ሞታችንን ከመጠባበቅ በቀር ሌላ አማራጭ አልታዬኝ አለ። ግንድ ላይ አንተርሰው አንገቶቻችን ሲቀሱን በዓይነ ህሊናዬ ተሳለፉኝ።

"በምን አይነት ጥፋት ይጠይቁን ይሆን?" ስልም በቅዱሳት መፃህፍት ውስጥ ያነበብኳቸውንና ፈጣሪን የሚያስቆጡ መንገዶች ሰማስታወስ ሞከርኩ። ለደሃ መፅውቼ አውቅ ይሆናል። አሱንም ለመፅደት ብዬ ሳይሆን ህሊናዬ ስለሚያስገድደኝ ነው።

የእያንን ባላውቅም እኔ በብኩሌ ሃይማኖቴ ላይ ጥሩ የምባል ሰው አይደለሁም። የስልጣኔን መጎሻ እንጂ የፈጣሪን እጅ መንሻ ስፈልግ አልኖርኩም። እንዲያውም ሃይማኖቶችን በአደባባይ አይሁን እንጂ በውስጤ እንቅፋለሁ። የሰውን ልጅ መጨቆኛ የፖለቲካ መሣሪያዎች መስለው ይታዩኛል። በታሪክ እንደምንረዳውም ሃይማኖቶች የሰውን ልጅ ስልጣኔ አውድመዋል። ይህ ማለት ግን ሃይማኖቶች በራሳቸው ያመጡት ስልጣኔ የለም ማለት አይደለም። የተረገምኩ ሰው እንደሆንኩ የምቆጥረው ለዚህ ነው። የመሲን አስርቱ ትእዛዛት ሳንብ በግብፅ ፒራሚዶች ላይ ከተፃፉት ቀደምት ህጎች ጋር ይመሳሰልብኛል።

"እያን ...በፈጣሪ መኖር ታምኖለሽ?" ስል ፈራ ተባ እያልኩ ጠየቅኳት።

Scanned by CamScanner

"እንጄ! ...ይቅር ይበልህ! ...እንጄታ! ውሁ ከመሣኢ የተነሳ እንደተሰነጠቀ ዋሽንት ይንፋንፍ የነበረ ድምፅዋ ተሳለ። "ያንት ያለህ! አንተስ አታምንም ማለት ነው?"

"ከልጅነቴ አምን ነበር። ፈጣሪን ከመፍራቴ የተነሳ ...ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በስህተት በመፍሳቴ እንኳ! ፈጣሪ ይቅር እንዲለኝ ሶስት ቀን መጾሜን አስታውሳለሁ።"

የግሷን ኩት ብላ ሳቀች። "ይቅር ይበልህ!"

"እሜን!... ዛሬ እንደዛ ጊዜ ብሆን እንዴት ደስ ባለኝ! የልጅነቴ ልብ ለፈጣሪ ቅርብ ነበር።...ሰማዩን ቀና ብዬ ባዬሁ ቁጥር ፈጣሪን የማየው ይመስለኝ ነበር።"

"በእርግጥ በፈጣሪ መኖር አታምንም ማለት ነው?"

"እምኔ አልጨረስኩም።" አልኳት ጥቂት ሳስብ ቆይቼ።

"ያንት ያለህ? ሞትን እየተጠባበቅን ሳለን እንዴት እንዲህ ትሳለህ?...። እነዚህ ሰዎች በምን መንገድ መገደል እንዳለብን እየመከሩ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። አበትቶልናል። ፈጣሪን ልናዬው የቀረን ደቂቃ የለም።"

"ምን አጠፋን?...ምን አጥፍተን ነው የሚገድሉን?"

"ዶክተር ዲዲሞስ ...ያለነው እኮ አጋጄን ውስጥ ነው። ማን እንደሚያስርህ አታውቅም። የፌድራሉ መንግሥት ወታደሮች ይሁኑ፣ ወይም የክልሉ መንግሥት ልዩ ኃይሎች... ማንኛው በዓይን ቁራኛ ሲከታተለን እንደነበር መገመት አይቻልም። በሽምቅ ተዋጊዎች እጅም ወድቀን ሊሆን ይችላል።"

"በድንቋቸው ልትለያቸው አልቻልሽም? ማለቴ..."

"ሶማልኛና አረብኛ እየቀላቀሉ ነበር ሲናገሩ የነበሩት። ሶማልኛ ተናገሩ ማለት የየትኛው ቡድን ሰዎች እንደሆኑ ይለያሉ ማለት አይደለም።"

"እሺ እኔንስ ወዘልውጥ ነው ብለው በሰላይነት መርጥሪው ይያዙኝ። እንቺ የዚህ አካባቢ ተወላጅ ነሽ። ሠላ ላይ ቁንቋሽ ቁንቋቸው ነው። እንቺን ለምን ያዙሽ?"

"አጋጄን ውስጥ የሚታሰረው፣ የሚንላታውም ሆነ የሚገደለው፣ ለጥናትና ምርምር የመጣ ወዘ ልውጥ ብቻ አይደለም፣ ነዋሪዉም ጭምር ነው። እንዲያውም መረጃ በሚያቀብለው የቀዬው ሰው ላይ በትሩ ይበረታል። በባንዳነት ተፈርጆ ፍዳውን የሚበላው የዚሁ በረሃ አሳሪኛ ነዋሪ ጭምር ነው። ተገድሎ ለበረሃ አሞራ ሲሳይ የተሰጠውን የሚያውቀው የአሞራዎች ሆድ ብቻ ነው። ...እኔም እጣ ፈንታዬ ደርሷል። አንድ ቀን ይህ መከራ ሊመጣ እንደሚችል አገምት ነበር። ሆኖም ይህ በረሃ እንዲለወጥ በመጣሬ አልቆጭም!..."ሳግ እየተናነቃት እንደሆነ ገባኝ። ድምፅዋ መቆራረጥ ጀመረ። "እንተዝም ጨምሬ የገደልኩህ እኔ ነኝ። አበቆቶልናል።"

Scanned by CamScanner

፲፫

ሌሊት ይሁን ቀን አይታወቅም። አያሌ ሰዓታት ተቆጠሩ። ወደ ተጣልንበት ዋሻ መጥቶ ያንጋገረን አልነበረም። እህል አልቀመስንም። በዛ ላይ አስክንያዝ ድረስ፣ ውሃው ውሶ እየሞንን ስለነበር ረሃብ ሰቆቃናል። አያንን ብጠይቃት በረሃብ ጠኔ ከመያዟ የተነሳ ጥያቄዎቼን መመለስ እንኳ እንደማትችል ነገረችኝ። አልፈረድኩባትም።

"ይቅርታ..." አለችኝ በዛለ ድምፅ። "ይቅርታ ዶክተር ዲዲሞስ ...የዚህን የተረገመ በረሃ ኑሮና ህዝቡን ማጥናት እንደምትችል ለውጪው ድርጅት የጠቆምኩት እኔ ነኝ። ይህን በብዙ አሳርና ሰቆቃ የሚማትት ህዝብ አጥንቶ መላ የሚያበጅለት ካንተ የተሻለ ምሁር እንደሌለ በኩራት ነበር የተናገርኩት። ...ያነበብኳቸውና ከዚህ ቀደም የሠራሃቸው ጥናቶችህ እስክመልክህ ድረስ አጃኢብ አሰኝተውኝ ነበር።...አንተን በአካል ማዬት በራሱ ለኔ ተአምር ነው። ...እውነቱን ልንገርህ? ...ገና ሳላገኘህ በሥራዎችህ ፍቅር ወድቄ ነበር። በረባ ባልረባው እየደወልኩ አንጋግርህ የነበረው ለዛ ነበር።...ይቅር በለኝ! ...እንደተቀየምከኝ መሞት የለብኝም..."

"አይዞሽ አትሞቺም!" አልኩ ቢጨንቀኝ ራሴን እንደ ነቢይ ቆጥሬ። "አይዞሽ!"

ግደም ጥሙ የማይቀርጥሰት የተረገመ በረሃ! የሚያጭርል ዐሐያ እንጂ ቀን የማይወጣት ርጉም በረሃ!..." አያን በምራት ስትራገም ዋሻው ያስተጋባ ነበር።

ሞቴንና ሞቷን በስመመን እየተጠባበኩ ስለምትረገመው በረሃ አስብ ጀመር! የመከረኛው በረሃ የመከራ ታሪክ ወደ አእምሮዬ እንደ ደም ይንቆረቆር ጀመር።

የአሚሮችና የሱልጣኖች ምህረት የለሽ ሰያፍ የተትዘመዘመበት የደም በረሃ! አያሌ የሰው አንገቶች የተቀሰበት፣ ሚንቅላቶች እንደቅል በቆሙ ሰዎች ደረቶች ላይ የተንከባለሱበት የደም ምድር! ውሃ እንጂ፣ ደም የጠገበው አኬልዳማዊዉ ግራጋዴስ!

ይህ ምድር፣ ሰው ባልረከሰበት ዘመን ይኖሩበት የነበሩትን ጎሳዎች፣ በንግድ ምክንያት ባህር እየተሻገሩና በረሃውን እያቋረጡ የመጡ ነገዶች ባህላቸውንና ወጋቸውን ቦርቡው አላበቁም። ጥንታዊ እምነቶቻቸውን አስጥለው ሲያበቁ በገደም በውድም እንዲሰልሙ አድርገዋቸዋል።

ከስምንተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ የንግድ መስመሩን ተከትሎ የአስልምና ሃይማኖት የበረሃውን ምድር ያጥለቀለቀው ጀመር። አጋዴኖቹ፣ አጣን፣ ከርቤና ዝሆኔ ሲሸጡላቸው፣ የአረብ ነጋዴዎች ደግሞ አስልምናን በነሳ እደሏቸው። እስከ ምሥራቅ ሸዋ የቆላ ኮረብታዎች ዘልቆ አስልምና መስፋፋቱን ተያያዘው። ሃይማኖቱን እንደመሣሪያ በመጠቀም አረቦቹ የኢትዮጵያን ወደቦች በሙሉ መቆጣጠር ጀመሩ። ከዚህም በላይ በርካታ ሥርዎ መንግሥታትና ሱልጣኖች ተመሥርተው የበረሃውን ሰላን ማስገበርም ጀመሩ።

Scanned by CamScanner

ያልሰለመ ዘላን እንደ አውራሪስ ቀንድ ተቆጥሮ በባርነት ተሸጠ። የመጤ አረቦችን ሃይማኖት አልቀበልም ያለ ጽንፈው ተቀርጦ ለግመል አረኝነት ተጋዘ።

በሌላ በኩል፣ ከ1108ዓ.ም ጀምሮ የተመሠረተው የሸዋ ሱልጣን፣ የሸዋን ምሥራቃዊ ኮረብቶች ተቆጣጠሮ ነበር። እስከ ኢጋዴን የበረሃ መከረኞች እየወረደ ከብቶቻቸውን ነድቶ ይመለስ ነበር።

በኢማዎች ይመራ የነበረው የአጼራ ሱልጣን፣ በ13ኛው ክፍለ ዘመን ምሥራቅ አፍሪካን ተቆጣጥሮ፣ ወቅቱን በመከተል በቀላፎና በመርሳ በአስልምና ስም አስተዳደሩን እየተከለ ኢጋዴንን አንገፍግፎ ገዝቷል።

መናገሻውን ዘይላ ላይ ያደረገው የይፋት ሱልጣን፣ ከ1285 ዓ.ም ጀምሮ አፋርና ሐረርን ጨምሮ በኢጋዴን ላይ 18 ሱልጣኖቹን አፈራርቋል።

በይፋት ሱልጣን እግር የተተካው የአዳል ሱልጣን፣ ከ1415 ደክቶ የኢጋዴንን መንጋ ነድቷል። የይፋትንም የአዳልንም ግዛቶች ያስተዳደረው የወላስማ ሥርወ መንግሥትም፣ ምሥራቅ አፍሪካን ሲያምስ የኢጋዴን በረሃ ብረት ምጣዱ ነበር።

በኢጋዴን ላይ ያልተቅበጠጠመ ሰይፍ ያልተሰበቀ ጦር አልነበረም። አሚር ከአሚር፣ ሱልጣን ከሱልጣን፣ ዓሳ ከንሳ፣...ሌላው ይቅርና አውሮፓ ውስጥ ይፋለሙ የነበሩት የመስቀል ጦረኞች፣ ኢጋዴን ድረስ ወርደው ሰይፋቸው እስኪቀላ ደም አፋስሰዋል- አቶማን ቱርክና ፓርቱጋል። ቱርኮቹ ሶሙሰሊሙ ፖርቱጋሎቹ ለክርስቲያኑ ሰይፍ አቀበለዋል።

የአንደኛው የዓለም ጦርነት ተፋላሚዎችም አዚህ ምድር ላይ ተፋጠዋል። ይህ በረሃ የሁለተኛው የአለም ጦርነት ገፈትንም ቀምሷል። እንዲያውም የሁለተኛው የአለም ጦርነት ደርመን ሀንጋሪን ወርሯ ተቀስቀሰ ይባል እንጂ፣ ጣሊያን እዚሁ በረሃ ውስጥ ወልወል በተባለው ቦታ ኢትዮጵያን ስትወር ነው የተጀመረው ማለት ይቻላል።

በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜም፣ ዓለም በርእዮተ ዓለም ጎራ ለይቶ በቃላት ሲፋለም፣ ይህ ምድረ በዳ ግን ቃላት ሳይሆን ጥይት ነበር ይዘንብበት የነበረው። ኢትዮጵያ አያሌ ጀግኖቿን እዚህ ገሃነማዊ በረሃ ውስጥ የቀበረችው፣ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ነበር- በኢጋዴን ጦርነት።

የኢጋዴን ጦርነት ካበቃ በኋላ የወቡ ልጆች እንዳረጋገጡት፣ ኢትዮጵያ፣ ወደ አሥራ ሺህ የሚጠጉ ልጆቿን እዚህ በረሃ ውስጥ ቀብራለች። ከዛ ሺህ በላይ ቀስለኞቿን እንስታለች። ወደ ሙቶ ሃምሳ የሚጠጉ ልዩ ልዩ አይነት ታንኮቿ ወድመውባታል። ከሙቶ በላይ የሆኑ የተያዩ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎቿ ጋይተውባታል። የወደመባትን የጦር አውሮፕላኖች ቁጥር አላውቅም።

ይህ ሁሉ ውድመት በሀብት ወይም በገንዘብ ቢተመን፣ ኢጋዴንን ገንቶ ማድረግ የሚችል ሀብት እንደነበረ መገመት አያዳግትም። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የኢጋዴን ምድር መከረኞች በጦርነቱ ምክንያት ህይወታቸው ተመሰቃቅሏል። ህፃናቶች በጦርነቱ የወደቀን አስከሬን ሥጋ የሰጠዳ ድመቶች በልተዋቸዋል። እናቶችንና አዛውንቶችን ተባራሪ ጥይት ከጎላቸው ጥሏቸዋል።

Scanned by CamScanner

ዘሊህ ላይዘቅ አሁንም ድረስ በእጋዴን ሰማይ ላይ ጥይት ላያቋጭ አያድርም። ድርቅና ቸነፈር ረሃብና ጥይት የዚህ በረሃ ቀለቦች ናቸው። ይህን ሁሉ ላስብ መምጣቴ ትክክል እንደሆነ ተረዳሁ። አያንም ትክክል ናት። እንኳንም ጋበዘችኝ ወይም አሲጋበዘችኝ።

አም በአርንዮ ታስረን ወደ እንጦርጦስ ተጥለናል። ግን ለምን ላይገድሉን እንሞታለን? ሼክስፒር እንዳለው ላይሞቱ የሚሞቱት ፈሪዎች ናቸው። ላልገደል አልሞትም። ራሴን በውስጤ እጀግኔ ላልጨርስ የዋሻውን በር በጎይል በርግደው ሁለት ወንበዴዎች ገቡ።

፲፩

ሁለቱ ወንበዴዎች እኔን አልፈው አያንን ከወደቀችበት አነሷት።

"ምን ፈልጋችሁ ነው?" በጎይል ጮኽ። "አማርኛ ትችሉ አደለም እንዴ?! በአማርኛ አናገሩኝ!"

እኔ እንድሰማ ስለፈለገች መሰለኝ፣ በሶማልኛ ቋንቋ ጠቡ ቢለፈልፉም ልታናግራቸው አልፈለገችም።

"እኛ ንፁህ ሰዎች ነን! በዛ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው የውጪ ድርጅት ባልደረቦች ነን። ስለእኛ ከፈለጋችሁ ድርጅቱን መጠየቅ ትችላላችሁ። ምን አድርጉ ነው የምትሉን?" አማርኛዋ አኔም ይሻል ነበር። በዛ ላይ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋዋ ተፅእኖ ሊሆን ይችላል እያንዳንዱን ፊደል እየረገጠችና እያንዳንዱን ቃል እያስረገጠች ጮሃ ነው የምትናገረው።

አንደቴን አራሰችው። 'ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ' የሚባለው ብሂል ሃሰት የለውም። ግመልን ደጋ ላይ መጥመድ አይቻልም። አያን ዓይናጅ እንዳያዩ በዓይነ ርግብ ቢታሰሩም፣ ለግዙት የዳረጉንን ሰዎች በንግግራቸው ለመለዩት ስትል በራሳቸው ቋንቋ ታስለፈልፋቸው ጀመር።

Scanned by CamScanner

ዝም በል ቲካላ" አለ አንደኛው ጎይለኛ ጥፊ አሳርፎባት ሲያበቃ። ሦስተኛውን ሥቃይ ሰቆጥጠኝ መንጋጋዋን ከረቸምኩ።

"ሚን አባኪ ቲከላምጂያሌሽ! ኪትረኖ" አለ ሁለተኛው። "ፊረንጂ ሚንዲን ና?! ሀበሺ ሚንዲን ና?! ...ሼርሙታ" አሱም በጥፊ አጋላት።

"ኪንቲራም! አንቲን ቢሉ ተመራማር?! ቱ! ኢኖ ያንቱ መቻወቻ ና?!"

"ኪንባህ እኔም እንዳንተው ሶማሌ ነኝ! እንዲያውም ካንተ የተሻልኩ አጋዴን ..."

"ዝም በል! ባንዳ ና!"

"አይደለሁም! ባንዳው አንተ ነህ!... የማይማር የማይለውጥ ወገኖቹን የማይለውጥ ነው ባንዳ! ...አስኪ ምን አደረክ አንተ?! እኔን መምታት ነው ያንተ ጀግንነት?! ...አስኪ ንገረኝ! እ?! ... አጋዴን ውስጥ አንድ የውሃ ጉድጓድ ቆፍረሃል?! በውሃ ጥም የሚሞት አንድ ግመል አትርፈሃል? ...አፉ በረሃብ ደርቆ አንቋሮ የሚሞት አንድ ህፃን አድነሃል?! ....ጥላው ከሀሩር ከማያድን ቆንጥር ሥር ተቀምጠው፣ በረሃብ ምክንያት መነሳት ያቃታቸውን አዛውንት አንስተሃል?!"

"ዝም በል!" ሁለተኛው ዋሻውን ሳይቀር የሚያንጋ ጥፊ አሳረፈባት።

"ቱ!..." ስትተፋበት ተሰማኝ። "...ክስክስ ጫማ ሲለጡሆና ጠመንጃ ሲያስታጥቁህ ንጉሥ የሆንክ ይመስልሃል! ...አንተ ነህ ባንዳ! እንተ ነህ የእጋዴን ና!..."

"ዝም ባል አንቱ ቲርቲር ሽርሙታ"
ደረቷ ላይ የተመታች መሰለኝ።
"ህእ!..." የሚል ድምፅ አሰምታ ፀጥ አለች።

እየንተቱ ይዘዋት ሲወጡ ተሰማኝ። የዋሻው በር ተከረቸመ። ደረቷን ሲመቷት ሞተች ይሆን? ወይስ ሊደፍሯት ይሆን? የሚንቀት መርግ ተጫነብኝ። ጨለማ በዋጠው ዋሻ ውስጥ ጨለማ ተደፍቶብኝ ብቻዬን ቀረሁ። ጆሮዬ ይጮህብኝ ጀመር።

በሰቀቀን ተራዬን መጠባበቅ ጀመርኩ። እኔ ነኝ ተረኛው ቀጣዩን ፅዋ የምቀበለው እኔ ነኝ። የፀጋዬ ንብረ መድህንን ስንናቸ ቀጣዩን ፅዋዬን እየጠበኩ አስታወስኳቸው።

"...ይድረስ ወገን ከእኛው ለእኛ፣
አበትቱ ሁሉን አልሳተም፣ ፅዋህን ተቀበለኛ!...
ሕዝብ መርተን ያለ ዓላማ፣ ያለ ግተብ ያለ ሃይማኖት፣
በአምባ ገነንነት አብረት፣ ያለ ዴሞክራሲ ፍናት፣
ጠመንጃ ነክሰን በመግደል፣ ጠመንጃ ነክሰን በመሞት፣
ኅብር ፈርተን፣ ሰላም ፈርተን፣
አንድነታችንን ቀብረን፣ እምቡጥ ህልማቸውን በልተን፣
ሳይነጋ እየጨለመብን፣ ሳንጎለምስ እያረጀን፣
የሥጋችንን ጨርሰን፣ በመንፈስ እየሞትን ነን።..."

Scanned by CamScanner

፲፫

የሥቃይ ዕዋዬን እየተጠባበኩ፣ ጨለማ በዋጠው ዋሻ ውስጥ ወድቄአለሁ። ለነገሩ፣ ጨለማ ይሁን ብርሃናማ፣ ላውቀው አልችልም፣ ዓይናቹ እንዳያዩ ሆነው በጥቁር ዓይነ ርግብ ታስረዋል። ቢሆንም ያለሁት ዋሻ ውስጥ እንደሆነ መገመት አላዳገተኝም። በዛ ላይ በሩ ተከርችሟል። ብርሃን በዙትም በኩል ሊገባ አይችልም። ያለምንም ጥርጥር ያለሁበት ሥፍራ፣ እንደ ኦጋዴን ሀይወት ጨለማ ነው። ደኅንን። ድቅድቅ ጨለማ።

ዓይኔ ከአይታ ቢጋረድም እሳምሮዬ ማሰቡን አላቆመም። ስለ ሴላ ስለምንም ማሰብ አልቻልኩም። የማሰላስለው ሁሉ ስለ ኦጋዴን ብቻ ነው። ስለ እድለ ቢሱ በረሃና እድለ ቢስ ስለደረትት ኃይሉች ማሰላስሌን መግታት አልተቻለኝም። እያንዳንዱን ዝር ስመዝ የምደርሰው አሁን ላለው አሣሪኛ ምድር ሲረኞች ታሪክ ላይ ነው። ሱልጣኖች ሰስልጣን እንደተፋጁበት፣ እንግሊዞች ለክርስ ምድር ሀብት እስካሁን የማያባራ የጦርነት ሴራ ጎንጉነውበታል።

እንግሊዞች በረቀቀ ሴራቸው "የታላቋ ሶማሌን" ዕንስ ሀሳብ ለማራገብ እንዲያመቻቸው የሶማሊ ወጣቶችን ለማነሳሳት፣ "የሶማሌ ዩዝ ሊግ" የተባለ ድርጅት ሀርጌሣ ላይ መሥርተው፣ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት በ1937 ዓ.ም አካባቢ ነበር።

"የታላቋ ሶማሌን" ዕንስ ሀሳብ ኮሚኒ ሚኒ ሶማሊያ፣ እንግሊዞች ኦጋዴንን ለእናት ሀገሯ ኢትዮጵያ ከመመለስዋ በፊት፣ ይኸው "የሶማሌ ዩዝ ሊግ" የተባለው ቡድን ጅጅጋ ላይ ላይቶር ባንዲራውን ሰቅሉ ይቀሰቅስ ነበር። እንግሊዞች ኦጋዴንን ሰቀው ከጨው በኋላ ወደ ሽምቅ ተዋጊነት ተቀይሮ፣ የኮሚኒዝም ርዕዮተ ዓለምን በማቀንቀን፣ የሶብዬት ህብረት ጥሩ ሆኖ፣ ኮትን ግዛት አርንት በወጣችው ሶማሊያ ውስጥ ስብከቱን ቀጠለ።

በ1955 ዓ.ም፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተርን ለማፅደቅ በተጠራው ስብሰባ ላይ ነበር፣ አዲሷ ሀገር ሶማሊያ፣ ኦጋዴን ይገባኛል ስትል ኢትዮጵያን ወደያባይ መክሰስ የጀመረችው። በወቅቱ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩትና፣ ስለኢትዮጵያ ሀገራችው ወንስም አደባባይ በመከራከር እንቱ የተባሉት አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ለሶማሊያው መሪ የሰጡት መልስ የተሰበሰቡትን የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ሁሉ ያስደመመ ነበር።

"የተሰነዘረብን ክስ ፍሬ ቢስ ነው። ኢትዮጵያ ለብዙ ዓመታት ነፃ መንግሥት ሆና የኖረች ናት። ከሳት ሺህ አመታት በላይ በታሪክ የታወቀች ሀገር ሆና የኖረች ናት። የሶማሊያ መንግሥት የሚባል ወይም ሶማሊያ ሪፐብሊክ የሚባል ሀገር የትም ተመዝግቦ አይገኝም። አዲሱ የሶማሊያ ሪፐብሊክ መንግሥት የ1908 ዓመተ ምህረቱን ስምምነት የማይቀበል ከሆነ ከኦሮራሽ የሶማሊያ ሪፐብሊክ የሚባል ሀገር አይኖርም። በአሁኑ ወቅት ቅኝ ገዥዎች ቦክርታ ላይ ያስመሩትን ወሰን ጥሩም ሆነ መጥፎ አፍሪካውያን እንዲቀበሉ ሁኔታው ያስገድዳቸዋል። ለሶማሊያ የሚበጃትም ይኸው ነው።..." በማለት የሶማሊያውን መሪ ፀጥ አሰኙት።

Scanned by CamScanner

ይሁን እንጂ፣ ሦሶማሌ ዩዝ ሊግ የተለያዩ ፀረ ኢትዮጵያ ትስቀሳዎች ማድረጉን አላቆመም። ሰርጎ አየገባም የኢጋዴንን ምድር የጦርነት ቀጠና አደረገው። በ1955 ዓ.ም በሻምበል ደምሴ ቡልቶ የሚመራ አንድ ሻምበል የአየር ወለድ ጦር ደገሃቡር ላይ ከአውሮፕላን በጃንፕላ ወርዶ ሰርጎ ገቡን ቡድን አይቶው ቅጣት ቀጥቶ አባሮት ነበር።

በ1957 ዓ.ም "ሶማሌ-አሆ" የተባለ አማፂ ቡድን በሶማሊያ አጋፋሪነት ተመሠረተ። አነሳሱ፣ ዋቆ ጉቱ፣ ኦሮሞ ቢሆንም፣ ከባሌ ሹማምንት ጋር በፈጠረው አለመግባባት፣ አኩርፎ በመሸፈቱ ቢሆንም፣ ይህን ወርቃማ እድል ለመጠቀም የቋመጠችው ሶማሊያ፣ ራዕዩን ከኩርፊያ ከፍ አድርጋ ሶማሌዎችንና የባሌ ኦሮሞዎችን በእስልምና ጥላ ሥር በማሰባሰብ አዲስ ራስ ምታት ለኢትዮጵያ ፈጠረችላት። ከሌሎች ሰርጎ ገብ ቡድኖች ጋር በማጣመር ጉልበቱን አፈረጠመችው።

በ1958 ዓ.ም ኢትዮጵያ ቦአሆ ላይ አንድ የአየር ወለድ ጦር ብትልክም፣ ዋቆ ጉቱ እንደተራ ሽፍታ የዋዛ ሆኖ አላገኙትም። ጥቅጥቅ ባለው የባሌ ጫካ ውስጥ ገብቶ የሰለጠነውን የአየር ወለድ ጦር ገትሮ ተፋለመው። የአየር ወለዱ ጦር የአየር ድጋፍ ቢጠይቅም፣ የመጣው የጦር አውሮፕላን በስህተት በአየር ወለዱ ጦር ላይ የታጠቀውን ቦንብና ጥይት አራግፎበት ተመለሰ። የኢትዮጵያ መንግሥት ዋቆ ጉቱ በሰላም እጁን እንዲሰጥ አዋጅ ቢያስነግርም እርሱ ግን የተመናመነ ኃይሉን ይዞ እጁን ባለመስጠት ቀጠለ።

ጉዳዩ ያሳሰበው የኢትዮጵያ መንግሥት በሚደር ደነራል ጃጋማ ኬሎ የሚመራ ኃይል ዋቆ ጉቱን እንዲያዝ ላከ። በመጨረሻም ጃጋማ ኬሎ ተሳክለትና ዋቆ ጉቱን በማጥፋት እጁን እንዲሰጥ አደረገው። ዋቆ ጉቱ አዲስ አበባ መጥቶ ንጉሡ ፊት በመቅረብ ምህረት ከተደረገለት በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጠው። ለዋቆ ጉቱ ሽንገላው አልተዋጠለትም ነበር። ባልታሰበ ሰዓት ጠፍቶ ሶማሊያ ገባ። የሶማሊያ መንግስት ዋቆ ጉቱ ሞቃዲሾ ሲገባ የጀግና አቀባበል ነበር ያደረገለት። ራሱን ጀነራል ብሎ በመሰየምም ኃይሉን እያደራጀ አመቺ ጊዜ እስኪገኝ እዛው ሞቃዲሾ አቆየው።

"በሶማሌ ዩዝ ሊግ የተጀመረው የአማፂ ቡድናዊ ጥንሰስ በ"አሆ" አላበቃም። "የሸበሌ ነፃ አውጪ ድርጅት"፣ "የኢጋዴን ነፃነት ድርጅት" እና "ምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ድርጅት" የተባሉ የደፈጣ ተዋጊዎች በኢጋዴን ምድር ላይ መፈልፈል ጀመሩ።

"የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ድርጅት"፣ ከ1969 ዓመተ ምህረቱ "የኢጋዴን ጦርነት" በፊት ጀምሮ፣ "ሶማሌ ዩዝ ሊግን" አላማ በማንገብ፣ ኢጋዴን ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት ተቋማት ላይ ከፍተኛ ውድመት አድርሷል። የኢጋዴን ጦርነቱን ርችት የለኮሰውም በሶማሊያ መንግሥት ስንቅና ትጥቅ ጉልበቱን በኃይል አፈርጥሞ ሲያበቃ ነበር። በጦርነቱ ወቅት የኢጋዴንን ጓዳ ጎድጓዳ እንደ መዳፉ መስመር የሚያውቀው የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር፣ በየኩርባው ቆሬጣ እየገባ የኢትዮጵያ ጦር የአግር አሳት ሆኖ ነበር።

የኢጋዴን ጦርነት ሲያበቃና የሶማሊያ ወራሪ ጦር ሲመታ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባርም ደጀኑን አጥቶ

Scanned by CamScanner

ተቢታትና ነዘር። ይሁን እንጂ በ1984 ዓ.ም ‘የኢጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር’ በአንሩ ተተካ።

ምንም እንኳ የሶማሌ ብሔር፣ የአብሳም፣ የጌራ እና የመርሐን ነገዶችን ያቀፈ ቢሆንም፣ አብነግ ግን በዋናነት ከፍፍድ ነገድ የሚመዘዘው የኢጋዴን ጎሳ ስብስብ ነዘር። ሲመሠረት የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር አመራር በነበሩ ስድስት ሰዎች ቢሆንም ቀስ በቀስ ብዙ የኢጋዴን ጎሳዎችን ከነኑ አሰልፏል።

በወቅቱ የደርግ መንግሥት በሰሜኑ ጦርነት ተጠምዶ ስለነዘር፣ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር ማሊያውን ቀደር አብነግ ሆኖ ሲመጣ በእንቅላሉ ለመቅጣት አድል አልነዘረውም። የደርግ መንግሥት ተገርሥሦ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ አብነግም የሽግግሩ መንግሥት አባል ሆነ።

ኢህአዴግ የደነገጠው፣ በሽግግሩ መንግሥት ወቅት በተደረገው ምርጫ አብነግ የሶማሌን ክልል ሰሚኒያ በመቶ ድምፅ ሲለበስብ ነዘር። በክልሉ መንግስት የፓርላማ መንዘሮች ውስጥም የአብነግ ሰዎች ያልተቀመጡባቸው እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ ሆነው ታዩ።

ኢህአዴግም "እሾህን በእሾህ" በሚለው ፈሊጡ፣ በሶማሌ ክልል ሌላ ኢጋር ሁርሶ ላይ አስመሠረተ - "የኢትዮጵያ ሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ሊግ"። ቀጥሎ በተደረገ አጠቃላይ ምርጫም አብነግ በጎደል ተገፍቼ ከምርጫው እንድወጣ ተደርጓልሀሁ በሚል ጩኸቱን ማሰማት ቀጠለ። አባላቶቼ ተገድለውብኛል ቢልም ክሱን አሰማ።

ጩኸቱን አሰምቶ አልቀረም፣ ጠበንጁውን አንስቶ ወደ ኢጋዴን በረሃዎች መርዶ የጥይቱን ጩኸት አሰማ። ራሱ ጎላፊነት የወሰደባቸውን ጥቃቶችም መሠዝሩን ቀጠለ። ኢጋዴን ውስጥ በነዳጅ ፍለጋ ላይ የተሠማሩና ለመሰማራትም እቅድ የነበራቸው ካምፒዎችም ሥጋታቸውን መግለፅ ጀመሩ። ከተዝታዣው ጦርነት በኋላም ኢጋዴን እንደገና የጦርነት አውድማ ሆነች።

እኔ እዚህ ዋሽ ውስጥ ታስሬ እስከተጣልኩበት ሰዓት ድረስ የኢጋዴን ሰማይ ባሩድ እንጂ ደመና አያዞርበትም። የኢጋዴን ምድርም የተቀበረ ፈንጂ እንጂ ድንች አይቆፈርበትም። "አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ" የተባለው ብሂልም፣ በኢጋዴን ንፁሃን ላይ አውን መሆኑ እንደቀጠለ ነው። አብነግን ለማፅዳት የገባው የኢትዮጵያ ጦር በአንድ በኩል "ኢጋልጥ" በሚል ሰበብ፣ ብዙዎችን በአሥርና በቶርቼር ወጣቶቻውን ይልጣል። በሌላ በኩል የአሸነፈው ቡድን የጦር አዘጋዞች "ባንኖ" በሚል ፈሊጥ የኦጋዴንን ህዝብ ፍዳ ያወርዱበታል። ከዚህም በላይ ዓለም ያላወቃቸው በየጊዜው የሚነሱ አማፂ ቡድኖችን ቁጥር መዘለት አይቻልም።

እኔንና አያንን ወደዚህ እንጦርጦስ ያወረደን ቡድን የትኛው ወይም በማን የታዘዘ እንደሆነ እስኩሁን አላወቅሁም። አያንም እስኩሁን ምን እንደደረሰበት አላውቅም። እየተደፈረች ይሁን ወይም እየተቀላች ጨለማው ዋሻ አልነገረኝም። ክፉ ሀሳቦች አእምሮዬን ወረውታል። ግንም ሊደርስልን አይችልም። ማንም።

Scanned by CamScanner

ተቢታትና ነበር። ይሁን እንጂ በ1984 ዓ.ም "የኢጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር" በአግሩ ተተካ።

ምንም እንኳ የሶማሌ ብሔር፣ የአብሳም፣ የጌራ እና የመርሐን ነገዶችን ያቀፈ ቢሆንም፣ አብነግ ግን በዋናነት ከፍተኛ ነገድ የሚመዘዘው የኢጋዴን ጎሳ ስብስብ ነበር። ሲመሠረት የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር አመራር በነበሩ ስድስት ሰዎች ቢሆንም ቀስ በቀስ ብዙ የኢጋዴን ጎሳዎችን ከጎኑ አሰልፏል።

በወቅቱ የደርግ መንግሥት በሰሜኑ ጦርነት ተጠምዶ ስለነበር፣ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር ማሊያውን ቀይሮ አብነግ ሆኖ ሲመጣ በእንቁላሉ ለመቅጣት እድል አልነበረውም። የደርግ መንግሥት ተገርሥሦ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ አብነግም የሽግግሩ መንግሥት አባል ሆነ።

ኢህአዴግ የደነገጠው፣ በሽግግሩ መንግሥት ወቅት በተደረገው ምርጫ አብነግ የሶማሌን ክልል ሰማኒያ በመቶ ድምፅ ሲሰበስብ ነበር። በክልሉ መንግስት የፓርላማ መንበሮች ውስጥም የአብነግ ሰዎች ያልተቀመጡባቸው አጀግ ጥቂቶቹ ብቻ ሆነው ታዩ።

ኢህአዴግም "እሾህን በእሾህ" በሚለው ፈሊጡ፣ በሶማሌ ክልል ሌላ አጋር ሁርሶ ላይ አስመሠረተ - "የኢትዮጵያ ሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ሊግ"። ቀጥሎ በተደረገ አጠቃላይ ምርጫም አብነግ በጎይል ተገፍቼ ከምርጫው እንድወጣ ተደርጌአለሁ በሚል ጨኽቱን ማሰማት ቀጠለ። አባላቶቼ ተገድለውብኛል ሲልም ክሱን አሰማ።

ጨኽቱን አሰምቶ አልቀረም፣ መደገፉን አንስቶ ወደ ኢጋዴን በረሃዎች መርዶ የጥይቱን ጨኽት አሰማ። ራሱ ኃላፊነት የወሰደባቸውን ጥቃቶችም መሠንዘሩን ቀጠለ። ኢጋዴን ውስጥ በነዳጅ ፍለጋ ላይ የተሠማሩና ለመሰማራትም እቅድ የነደፉቸው ነዎርኮችም ሥጋታቸውን መግለፅ ጀመሩ። ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላም ኢጋዴን እንደገና የጦርነት አውድማ ሆነች።

እኔ እዚህ ዋሻ ውስጥ ታስሬ እስከተጣልኩበት ዕኅት ድረስ የኢጋዴን ሰማይ ባሩድ እንጂ ደመና አይዞርበትም። የኢጋዴን ምድርም የተቀበረ ፈንጂ እንጂ ድንች አይቆፈርበትም። "አይጥ በፀላ ጻዋ ተመታ" የተባለው ብሂልም፣ በኢጋዴን ንውነን ላይ እውን መሆኑ እንደቀጠለ ነው። አብነግን ለማዕጹት የገባው የኢትዮጵያ ጦር በአንድ በኩል "ኢጋልኘ" በሚል ሰበብ፣ ብዙዎችን በእሥርና በቶርቼር መገላቸውን ይልጣል። በሌላ በኩል የአሚሲው ቡድን የጦር አበጋዞች "ባንኛ" በሚል ፈሊጥ የኢጋዴንን ህዝብ ፍጻ ያወርዱበታል። ከዚህም በላይ ዓለም ያላወቃቸው በየጊዜው የሚነሱ አማፂ ቡድኖችን ቁጥር መዘለት አይቻልም።

እኔንና አያንን ወደዚህ አንጦርጦስ ያወረደን ቡድን የትኛው ወይም በማን የታዘዘ እንደሆነ አስዓሁን አላወቅሁም። አያንም አስዓሁን ምን እንደደረሰባት አላውቅም። አየተደፈረች ይሁን ወይም አየተቀሳች ጨለማው ዋሻ አልነገረኝም። ክፉ ሀሳቦች አእምሮዬን ወረውታል። ግንም ሊደርስልን አይችልም። ግንም።

Scanned by CamScanner

፲፮

ሳላውቀው ከወሰደኝ ጥልቅ እንቅልፍ የቀሰቀሰኝ የዋሻው በር መከርገድ ነበር። በጠኔ ከመያዜ የተነሳ ይሁን አልያ በሁነብ በመናወዜ ምክንያት እንቅልፍ ሲያሸልበኝ አላስታውስም። ለምን ያህል ሰዓታት እንደተኛሁም አላውቅም። እንቅልፍን ያህል እረፍት ከወዴት ይገኛል? ...ከረሃቤና ከሀሳቤ እንቅልፍ ባይገላግለኝ ኖሮ አስነሁን በህይወት መቆየቴን አጠራጠራለሁ።

የዋሻው በር እንደተከፈተ ሁለት ሰዎች አያንን ወደ ውስጥ ወርውረዋት ሲያበቁ ዋሻውን እንደገና ዘግተውት ሄዱ።

"አያን!?" አውር ድንበራን ወድቃ ወደምታስተበት አትጣጫ ተንከባለልኩ። "ጎዱሽ?"

"እ...አይነ!ርም!" መናገር አትቷት ጫን ጫን መተንፈስ ያዘች። "እህ!እህ!"

በእጇ ጻብሼ የተጎጻችውን ማዎት አልችልም። ሁለቱም እጆቿ የፊጢኝ ተጠፍንገው ታስረዋል።

"እ...እርቃኔን አቁመው እጆቻቸው እስኪዝሉ ገረፉኝ!..." አለችና ስትስት ብላ ማልቀስ ጀመረች።

"...ም...ምን ፈልገው ነው?...እነማን ናቸው?"
"...ኪ ...ከሞያቂዎቻቸው እንደ ተረዳሁት... በሰላይነት ጠርጥረውናል።..."

"ምን ለመሰለል የመጣን መስለናቸው ነው?_"
"እጋያን ውስጥ ከነጻጅ ምስጢር በቀር ሌላ የሚደበቅ ምን ምስጢር ይኖራል?"

"ነጻጅ..."
"ከእንግዴህ ዋጋ የለኝም" ብላ እንደገና መንሰትሰት ጀመረች።
"አያን ምነው? እንዲህማ በቶሎ ተስፋ ትቆርጫለሽ ብዬ ማሰብ ይከብደኛል።"

"ተፈራረቱብኝ!" ሰቅሶዋን መቆጣጠር አቃታት።

"ምን ማለትሽ ነው?" አፌ ደረቀብኝ። "ይህን ማመን አልችልም። ሊሆን አይችልም!"

"ሆኗል! ...ስንት እንደሆኑ እንኳ ማስታወስ አልችልም!... ተፈራረቱብኝ! ...እንደ አውሬ አያንሩ ደፈሩኝ ...ለእንግዴህ ተስፋ የለኝም።...በቱሜ ተበረውኛል..."

መናገር አቃተኝ። እርሷን ማፅናናት ቀርቶ ራሴ መፅናት ተሳነኝ። አፈኝ ደም ደም አለኝ። ጭንቅላቴ ዞረብኝ።

Scanned by CamScanner

፲፯

የእኔ ተራ መድረሱን ያወቅኩት የዋሻው በር ሲከፈት ነበር። ፈርሳማ እጆች ክንድና ክንዴን እንጠልጠለው እየጎተቱ ከዋሻው አወጡኝ። ከዋሻው እስክርቅ ድረስ የአያን ድምፅ ከውስጥ እየተሰማኝ ነበር።

"ተውት! ተውት! ...ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። የምትሉት ሁሉ ቅዠት ነው። ንፁህ ሰው ነው። ተውት..."

የሰማት የለም። ወደ ሆነ ክፍል አስገቡኝና ከቆመ ሞሰሶ ጋር አሰሩኝ። ይህኛውም ዋሻ ነገር ሳይሆን አይቀርም፣ እያንዳንዱ ኮቴ ያስተጋባል። ምንም አይነት ጥያቄ ሳያቀርቡልኝ የመጀመሪያው ቆሞጥ ከጀርባዬ አረፈብኝ። ሾ ካሁኑ አጥንቴ የተሰበረ መሰለኝ። ከዚህ በፊት አውጥቼው የማላውቀውን የማቃሰት ድምፅ አወጣሁ። ያለ አንዳች ርህራሄ እየተንጠራራ ይመሸልቀኝ ጀመር። የመጀመሪያው ሲደክመው ሁለተኛው ተተካ።

"አፈቲ ማረብታ?!" ይለኛል በሱማልኛ እየተንጠራራ ዱላ ባሳረፈብኝ ቁጥር። ምን እያለ እንደሆነ

አላውቅም። ሌላም ብዙ ቃላት ተናገረል። የእንዴንም ትርጉም አላውቅም። "ማረብታ!"

የጀርባ አጥንቱ እስኪሰባበር ተረባርቦው እርቃኔን አቁመው ከገረፉኝ በኋላ ከቆመው ግንድ ላይ ፈቱኝ። እንደ ልጥ ተጣጥፌ ወለሉ ላይ ጥቅልል አልኩ።

ቀስ እንዲለበልበኝ መሰለኝ ሁለቱም በወደቅኩበት ሸኑብኝ። ለመሮህ እንኳ አትም አልነበረኝም። ወድቄ ተረፁ። በምዕት እየተሳሳቁ ሸንተውብኝ ካበቁ በኋላ አንድ ሌላ ሰው ከውጭ ሲገባ ሰማሁ። እሱን ተከትሎ ደግሞ ሌላ ሰው ገባ።

"እቲነ መቃ?!" ሲል ተናገረ መጀመሪያ የገባው።

"ሲም ማና?" አለ ሁለተኛው። አስተርጓሚ መሆኑ ነው። "እንቲ ና...ኮ! ማቲመልስ ካሆና ያኑፋ ናጋር ይነታላል።"

"ዶክተር ዲዲሞስ ደራ አባላለሁ" አልኩ እንደምንም አትሜን አስባስቤ። እስከሁን ያለምንም ጥያቄ የገረፉኝ ሞራሌ እንዲላሽቅና በፍርሃት ተሸፋ በመቀረጥ ምስጢር እንድዘረግፍ መሆኑ ንቡቶኛል። ይሁን እንጂ ምንም ምስጢር የለኝም። ወደዚህ በረሃ የመጣሁበት ጉዳይ ምስጢር አይደለም።

"አፈቲ ማረብታ?!" አለ ጠያቂዬ ሙክ ባለ ድምፁት።

"እዚህ ላምን ማታህ?!" ሲል አስተርጓሚው ቀጠለ።

"እዚህ የመጣሁት ስምርምር ሥራ ነው።"

"ሚንዲ ና ሚትማራምራው?"

Scanned by CamScanner

ጮክብሬሰብ ለዋኔ ነኝ።ሳቫል አንትሮፖሉጂስት ነኝ።"

"እታችባርቢራ! ወናቱን ማናጋር ቢቾ ኖ ሚያዋተው!"

"ዋምናገረው እውነቱን ብቾ ነው።"

"ይህ ,ጋና ማጃማራ ኖ! ...ክታቱን ናጋር ሊቲማክት ያገድህን ቲናጋራላህ!"

"ምንም የተደበቀ ነገር የለኝም። እውነቱ ይህ ብቾ ነው። ይህ ደግሞ የሚጠቅመው የአካባቢውን ነዋሪ ነው።"

"ለኛ ቲክም እንቱን ማን ፋሊጋ? ኢኛ ሲላራሳችን አናውክም ብሉ ያሳክህ ማናን?!"

"ስለራላችሁ እታውቱም ማለት አይደለም። ክእናንተ የበለጠ ስለ እናንተ ማንም ሊያውቅ አይችልም። ግን... ይህን ለዘመናት የተረሳን ምድር በሳይንሳዊ ዘዴ አጥንቶ ለዓለም ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። የአጋጁንን ችግር መፍታት የሚችለው የአካባቢውን ሳንካዎች ጠለቅ ብሉ ዘግቦት ነው።"

"ሚንዲ ኖ ሳንካዎችን?"
በውስጤሳንካዎቼማ እናንተ ናችሁ! አልኩ።
"ችግሮች ማለቱ ነው።" አልኩ ጥቂት አስብ አድርጌ። "ዋችግር የመፍቾ ቁልፍ የሚገኘው ራሱ ችግር ውስጥ ነው።"

"እታችባርብር! ...ሳላይ ናህ!.... እውነቱን በኋላ ቲናጋራላህ!"

ሁለቱ ሰምቾ ጥለውኝ ሲመጡ፣ ገራፊዎቼ እየንተቱ፣ ቀድሞ ወደ ነበርኩበት ዋሻ መለደው መረመሩኝ። አያን አሁንም ድረስ አያቃሰተች ነበር።

Scanned by CamScanner

፲፰

የሚያንዘገዝው የጀርባ ቁስላችንን ማከታመም አልቻልንም። እጆቻችን የፊጥኝ እንደተጠፈነጉ ናቸው። ሰምን እስከሁን እጆቻችንን እንደማይፈቱልን አልገባኝም። ከውጭ አሳት የሚተፋ ነፍጥ ያነገበ ወንበዴ አለ። የትም ማምለጥ አንችልም። "የፊሪ ዱላ አስራ ሁለት ነው" የሚባለው እንዲህ አይነቱ ነገር ነው። ደም የጎረሰውን የጀርባ ቁስል መፈወስ ባይቻል እንኳ እንዲያው መጸዳዳ ቢቻል ምን ነበረበት?!

ከስዓታት ቆይታ በኋላ የዋሻው በር ተከፈተና የሚገባ ሰው ኮቴ ሰማን። ወደ ወደቅንበት ቀረብ አለና፣

"ቴናሱ!" አለ።

መነሳት የሚያስችል አቅም አልነበረንም። ለመነሳት ይቅርና አንገት ቀና የሚያስደርግ ጡንቻ የለንም። አጥንታችን እንደ ቄራሮ ተሰባብሯል። ጡንቻዎቻችን እንደ ዘር ተበጣጥሰዋል።

"አቲናሱም?!" አለ እንደገና። "ማብላት አቲፋልጉም?" የሚለላ ነገር ይዟል ማለት ነው።

"አያን!..." አልኩ የሞትሞቴን ካንገቴ ቀና ብዬ። "...ቀና በይ ነፍሳችንን እንያዛት።"

"እጆቻችን ሳይፈቱ በምን እንመገባለንን?" አልኩት ካንገቴ ቀና አንዳልኩ። እጆቻችን ፈታልን። የደም ሥሬ አብጦ ነበር። ጣቶቼ ዝለዋል። በእርግጠኛነት የአያንም የደም ሥሮች ከእኔ በከፋ ሁኔታ ተጎድተዋል።

ጣሳ መሰል ነገር አስጨበጠኝ። ተስገብግቢ ወደ አፌ አስጠጋሁት። የስጋ ሾርባ ነው። የምን ሥጋ እንሆን ግን አላውቅም። የዛው መከረኛ ግመል ሥጋ ሊሆን ይችላል። አጋዴን ውስጥ ግመል የማይሆነው የለም። ይጫናል፣ ይታረስበታል፣ ይታሰባል፣ ይታረዳል። ለእንድ አጋዴናዊ ግመል ከሰው ሳይቀር ሳይበልጥበት አይቀርም። ሁሉ ነገሩ ነው።

በዚህ ሰዓት ምግብ መምረጥ ቅብጠት ነው። በሞት ሽረት መሃል ያለ ሰው እንኳ ሥጋ አግኝቶ ይቅርና ድንጋይ ቢነክስ አይፈረድበትም። ለም አፈር ባገኘ ያለ እንዳች ማመንታት ተጎንብሼ እሽመሸመው ነበር። በናዚ ማጎሪያ ጣቢያዎች ውስጥ የነበሩ አስራኤላውያን የሰው ሥጋ መብላታቸውን አንብቤአለሁ። የበሉት ሰውዬ በቁመቱ ልክ በተሰራ ብረት ድስት ውስጥ ሆኖ ከአሸዋትዝ ማሰቃያ ጣቢያ መሃል እየተንፈቀፈቀ ነበር። ሰውዬው እንዲቀቀል የተደረገው ሥጋው ከእንጥኑቱ ሲላቀቅ ለመዋቅረ አጥንት (አናቶሚ) ጥናት ለማዋል ነበር። የናዚ ዶክተሮች ከሚንፈቀፈቀው ብረት ድስት ርቀው አስክሬኑ መክክ ብሎ በስሎ ከአጥንቱ እስኪላቀቅ እየተጠባበቁ ነበር። በረሃብ የተጎዱት አስራኤላውያኑ ትልቁን ብረት ድስት በመመልከት የእለቱ ምግብ ሾርባ መሆኑን በማመን ፈጣሪያቸውን አመስግነው እየተጠባበቁ ነበር። ሾርባው

Scanned by CamScanner

ዘንዙ። ወደ እነርሱ ሊመጣ አልቻለም። እነሱ ወደ ሾርባው መሄድ ነበረባቸው። ወደሚንፈቀፈቀው ብረት ድስት ቀንጉ። ቡድስ ቡድስ ያለ ሥጋ በአራት ማዕዘን ጉነጣ መሰል ብረት ድስት የሚንፈቀፈቅ ውሃ ላይ እየተንሳፈፈ ተመለከቱ። አንዱ በአንዱ ትከሻ ላይ እጁን አያሳለፈ የገሃነብ ያህል የፈላውን ውሃ ከምንም ሳይቆጥር ሥጋውን ተሻማ። የራሱ እጅ እስኪበስል ብረት ድስቱ ውስጥ ገባ። ሥጋ የፈለገም አልተጣም። ከረጂሙ የብረት ድስት ሥር ዘንጦ የነበረው ግን የሰው አፅም ነበር። ሥጋውም የወገናቸው ሥጋ ነበር። ከረዛብ በላይ የከፋ ነገር የለም። ተረት ይሁን ታሪክ ባይታወቅም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰተ ረዛብ እናት ልጇን በልታለች ይባላል።

ቢደውን ጣለ መለስኩለት። አያንም ሾርባውን ጨርሳው ነበር። ሰውዬው ጣሏቸውን ይዞ ዋሻውን ዘግቶብን ሄደ። እጆችን መልሶ አሳሰረንም ነበር። ተመስገን ነው። የጀርባዬን ቁስል ጻበስኩት። ይዘገንናል።

የአያንንም ቁስሎች ጻበስኳቸው። ሰቀጠጠኝ። እርሷም ሳግ እየተናነቃት የእኔን ቁስሎች ጻበሰቻቸው።

"እዘናለሁ" አለች አንገቱ ሥር ተወሽቃ። ትክሻ እንባዋ ሞቀኝ።

"ለምን ይመስልሻል ሾርባ የሰጡን?"

"እንዳንሞት ነዋ። ግና ይመረምሩናል። ብዙ ምስጢር እንደያዝን ነው የሚያስቡት። አላመኑንም። የፊለጉትን ምስጢር ሳያገኙ ብንሞት፣ ኪሳራ እንደሆነ አምነዋል ማለት ነው። ቀጣዩ ምርመራ ከዚህ እንደሚከፋ መገመት ቀላል ነው።"

"ምን አይነት ምስጢር?..."

ጥያቄዬን ሳትመልስልኝ የዋሸው በር ተበረገደ። ሾርባ ያመጣልን ሰውዬ ስህተቱን ስገነዘብልኝ መመለሱ ነበር። እጆቻችን እንደገና የፊጥኝ አስሮን ሄደ። በተፈታንበት ቅፅበት የታሰሩ ዓይናቸችን መፈታታትና ከመሞታችን በፊት መተያዬት እንችል ነበር። አስረኛ ራሱም ራሱን እንደሚያስር የገባኝ ያኔ ነው። ሁሉታችንም ቀጨን። ከዚህ በኋላ ንግግራችንን ቀጠልን።

"ሾርባውን መርዘውት ይሆን?"

ወደየኋላችን ተዘረርን።

Scanned by CamScanner

፲፱

የቀመስናት ሾርባ ነፍሳችንን ይዛልን ቀፎች። በየርሣሬያችን መሠረት ሾርባው አስካሁን አልገደለንም። ደም የንረሰው ቁስላችን ግን እረፍት የሚነሳ ጥዝጣዜ ሰቶበን ውሏል ወይም አድሯል። ዓይናቻችን ታስረው ዋሻ ውስጥ ስለተወረወርን ቀንና ሌሊቱን ለይተን ማወቅ አንችልም። የወፍ ድምፅ እንኳ የማይሰማበት እልም ያለ በረሃ ውስጥ እንደሆንን ገምተናል። ይሁን እንጂ ወደዚህ ሲያመጣው የተሻገርነው ወንዝ እንደምልክት በመቁጠር ዋቢ ሸበሌ አካባቢ እንዳለን ገምተናል።

አያን እንቀሳፍታለች እኔ ግን ጭልጥ ካለ ሀሳብ ውስጥ ንብቻለሁ። አያን ከመተኛቷ በፊት ለዚህ ሁሉ ፍዳ የዳረገን ነገር ምን እንደሆነ ብጠይቃት፣

"ይህ በረሃ ከነዳጅ በቀር ሌላ ምንም ምስጢር የለውም።" ስትል ነገር የጀመረችልኝ።

"ነዳጅ ቢኖር ኖሮ አስካሁን ሰምነ አልወጣም? ወይስ ነዳጅም እንደፍልፈል ውስጥ ለውስጥ እየቆፈረ ከአሳጂ ያመልጣል?" ነዳጅ አጋዴን ውስጥ የለም የሚሉትን ሰዎች መላ ምት እየደረደርኩ ተከራከርኳት።

አያን ስለኢትዮጵያ ታሪካች የነዳጅ ፍሰጋ ታሪክ ጥልቅ እውቀት እንዳላት የተረዳሁት ከዚህ በኋላ ነበር። "ለምን ያለምንም ስለነዳጅ ይህ ሁሉ እውቀት ሊኖራት ቻለ? ስል፣ እኔ ራሴ አስከጠራጠራት ድረስ ነገር አንድ በአንድ የተረከችልኝ።

ታሪኩ የሚጀምረው የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ መሠረት ከከተሩት ከአጤ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ነው። እንደ ዝርዝሳውያን አቆጣጠር ከ1860 ዓ.ም አካባቢ ጀምሮ፣ በአጋዴን ሸለቆ ውስጥ "ነዳጅ ገነፈለ" የሚል ወሬ መሰማት ጀምሮ ነበር።

በጅጋ አቅራቢያ በፋፋን እና በገርገር ወንዞች ሸለቆ አካባቢም ነዳጅ ከከርሰ ምድር ሰርጎ የመውጣቱ ዜና ይሰማ ጀመር። ከዚህም አልፎ በጋራሙለታ ተራሮች ግርጌም እንደተበጣ ደም ሥር ነዳጅ ተንፎለፎለ ይባል ጀመር። አንዳንድ የውሃ ጉድጓዶች ሳይቀር የነዳጅ ስፈፍ ታየባቸው ተባለ። ከዚህ በኋላ ነበር ኢትዮጵያ የሃይድሮ ካርቦን እምት ኃይል እንዳላት የታወቀው።

ይህንን ታሪክ፣ "ቧራ ወለደ" አይነት እንደሆነብኝ ለአያን ስነግራት፣

"እሳት በሌለበት ጭስ የለም።" በማለት ነገር ትረካዋን የቀጠለችልኝ። "...ግመል ባለበት ነዳጅ አለ' የሚባለውንስ አለሰማህም?"

የአጋዴን በረሃ አስር ሺህ ያህል ውፍረት ያለው ሴዲሜንታሪ ሮክ (ዝቅጤ አለት) የተነጠፈበት ነው። ጂኦሎጂስቶች እንዳጠኑት ይህ የአለት ንጣፍ፣ አስከ አራት

Scanned by CamScanner

ሙቶ ስኩዊር ኪሉ ሜትር ይሸፍናል። ይሀም ቪረግ ድፍድፍ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ እንዳረዝ ምልክት ነው።

ከዮንት ዘመን ጀምሮ የእንስሳትና ክአፅዋት ቅሪተ አካል በመዝቀጥ ጠንክሮ ወደ ቋጥኝነት የተቀየረበት ይህ አካባቢ በየይድር ካርቦን ብልፅግናው ከመከከለኛው ምሥራቅ ምድር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ስነ ምድር እንደሆነ ጂኦሎጂስቶች ደርሰውበታል።

አጥኒዎቹ፣ ኢትዮጵያ አምስት የዝቅጤ ድንጋይ (ሴዲመንታሪ ርክ) ሽለቆዎች እንዳሏት ደርሰውበታል። በቀንጭት አጋዴን ባዚን፣ አባይ ሸለቆ፣ የአሞ ሸለቆ፣ ጋምቤላ እና መተማ እንደሆኑም ተለይተዋል። በእነዚህ በሚፅድን የበለፀጉ የኢትዮጵያ ሽለቆዎች፣ የነዳጅ ፍለጋው የተጀመረው ከ1920ዎቹ ጀምሮ ነው።

በዘጊዜው ቡሚነሱ ግጭቶችና ጦርነቶች የነዳጅ ቁፋርው እየቆመ ኩባንያዎቹም እያቋረጡ ባይወጡ ኖር፣ እስክሁን ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብቷ መበልፀግ የምትችልበት ተስፋ ነበረ።

ሲንክሌር የተባለ የነዳጅ አሳሽ ኩባንያ፣ በጅፕሰም፣ በመዳብና በቤንዚን የከበረ ነው የተባለውን የአጋዴን ሽለቀ ከነገሥታቱ ዘመን ጀምሮ ያስሰው ነበር። ነገር ግን ላይታሰብ በ1950ዎቹ ውስጥ እቃውን ሸክፎ ወጣ። የሲንክሌር ኩባንያ አጋዴንን ለቆ በወጣበት ወቅት ብጣቂ መረቀት እንኳ (የነዳጅ ካርታ) አልተወም ነበር። ፍለጋ ያካሄደበትን ወይም ያሳካሄደበትን ሥፍራ የሚጠቁም ካርታም አልተገኘም።

ሆኖም በኋላ አንዲ ጎርጎርሳውያን አቆጣጠር በ1970ዎቹ፣ ፋንኩ የተባለ የአሜሪካ ኩባንያ አጋዴን ንዳፅ ሳደረገው ዘሰስ ሁለት ጉድጓዶች ውስጥ ነዳጅ አንዳገ ገልያ ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጂ ከመፈገላቱ በፊት ኮሚኒስቶች አብዮት አፈነዱ። መሠረቱ ከካፒታሊስት ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኟ አሜሪካ የሆነው ፋንኩ ከብጉያም ነዳጅ ሳያወጣ አግራ አውሮፕላ ብሱ ከአጋዴን ወጣ።

በቱንኩ አግር ከሚኒስት ርዕዮተ ዓለም አራማጂ ሶቭዬት ህብረት የተነሳው ነዳጅ አዳኝ ኩባንያ በአጋዴን ረዮጫ በረሃ ላይ አግርቹን ተከለ። የአሜሪኩ ኩባንያ የጀመራቸውን ገደሱችም ይቆፍር ጀመር። በኢሳህና ወሰብ የነዳጅ ጉድጓዶች ተሰፋ ሰጪ ፍንጮች እንዳገኘ ቢገልፅም፣ የደርግን መውደቅ ተከትሱ ከአጋዴን ምድረ ገፅ ላይ ተሰፋውን ሰርዞ ወጣ።

ከ1980ዎቹ በኋላ የኢህአዴግን መግባት ተከትሱ፣ እንደገና ሁለት የአሜሪካ ኩባንያዎች ወደ አጋዴን በረሃ ብቅ አሱ። እነዚህ ሃንት እና ማክሲስ ኢነርጂ የተባሱ የአሜሪካ ኩባንያዎች የአጋዴንን ምድር ሲቆፍሩ ከቆዩ በኋላ ማክሲስ ሁለት አመታት ብቻ ሞክሮ ሲወጣ ሃንት ግን ለሦስት አመታት አደኑን ቀጥሱ እጁን አዝሱ ወጣ።

ከዚህ በኋላ ነበር ገዢው ፓርቲ አቀራረቡን የቀየረው። ለነዳጅ አሳሽ ኩባንያዎች ብሱኮፎን ከማከራዱት ይልቅ ከሚገኘው ነዳጅ የጥቅም ተጋሪ እንዲሆኑ ወሰነ። ይህንን ተከትሱ በርካታ ኩባንያዎቹ የፊርማ ክፍያ ሳይቀር ራሳቸው እየከፈሱ የሴድመንታሪ ርክ (ቅዝጤ አለት) ባዩባቸው የኢትዮጵያ ሽለቆዎች ሁሱ ለቁፋር አዮበሱ። የፊርማው ክፍያ አላማ ነዳጅ በሚቆፈርባቸው አካቢዎች ለሚገኙ ህዝቦች የጤና፣ የትምህርትና የንፁህ ውሃ

Scanned by CamScanner

እንልግሎት እንዲውል ቢሆንም፣ በዚህ ተጠቀምኩ ያሉ አካባቢ ግን አልተገኘም። ለንዳጅ አዳኖች አካባቢውን ምን አለመሆናቸውም፣ ተጠቃሚ አይደለንም መደፈትም ተጠቃሚ እንሆንም ብለው ከማሰባቸው የተነሳ ነው።

ይሁን እንጂ ጀር ሰፊ ልዩስ ያሉት ኩባንያዎች ገፀተው ማሰሰቸው አልቀረም። የዩናይትድ ኪንግደም ጎይት ናይል፣ የዩናይትድ ስቴቱ ኢንተር ግሉባል፣ የስዊድኑ ሱንዲን፣ የማሌዢያ ሁለት ኩባንያዎች ፔትሮናስ እና ፒቻኮ፣ የሆንግ ኮንጉ ሳውዝ ዌስት፣ የአሜሪካው አሩር አክሰፕሎረር፣ የቻይና ሁለቱ ኩባንያዎች ዦንግያን እና ፖሲግሌፕ ኮርፖሬሽን እንዲሁም ሌሱች ኩባንያዎች፣ በኢትዮጵያ የዝቅጤ አለት ሽለቆዎች ተሰማሩ። ለአያንዳንዳቸውም አካባቢዎች ተለይተው ተሰጡዋቸው።

የአሩር አካባቢ ለአሩር ኤክሰፕሎረር፣ አዲጋላ እና ሪዩት ሼል ለአሩብ አይል ኮርፖሬሽን፣ መተማ- ለኩሲቫሊ ፔትሮል፣ ደቡብ አሞ -ለቴሱው አይል፣ የአባይ ሸለቆ - ለፋልኮን ፔትሮሊዬም፣ ጋምቤላ እና ጅማ ለሳውዝዌስት ኢነርጂ፣ እንዲሁም ፍፁም ተሰፋ የተጣለበት አጋዴን ለተለያዩ በርካታ ድርጅቶች መታደሱን መረጃዎች ያሳያሉ።

አጋዴን ውስጥ በጎላጅ ቁፋሮ ላይ የተሰማሩት ፒሸክ፣ ኒው ኢይ፣ ሳውዝዌስት ኢነርጂ፣ ፖሲግሩፕ ኮርፖሬሽን እና ዦንግያን የተባሉት ኩባንያዎች ቢሆኑም፣ ዦንግያን የተባለው የቻይና ኩባንያ ግን በተረፀመበት አስቃቂ ጥቃት ጥሎ ወጥቶ እንደነበር ይታወቃል። አጋዴን ውስጥ የሚንቀሳቀሰው አብዛኛ የተባለው አማፂ ቡድን ጥቃቱን አንዳደረሰ በተጠቀሰው በዚህ ሞኖፍሞፋ፣ አደሌ በተባለው ቦታ ከድሳ አምስት ኢትዮጵያውያንና ሰባት ቻይናውያን እንደተገደሉ በወቅቱ ተገልፆ ነበር።

አያን ይህንን ሁሉ ነገራችን ስታዩ ነበር ጥቃቱ ላይ ስትደርስ ያቆመችብኝ። ምናልባት በየትኛው ጥቃት እሩኛዋ እንደተገደለ ባላውቅም ነገሩን ላለማባከክ ዜጩ ከመጠየቅ ተቆጠብኩ። በዚህ ሰዓት ሁሉታችንም ቦቂ ጥቃት ደርሶብናል። ምናልባት የቀረን መቀላት ብቻ ይሆናል። ወኤለማ ውስጥ የወረወረን አካል ማንነቱ ባይታወቅም በቀላሉ ሊለቀን እንደማይችል ግልፅ ነው።

በዚህ ሰዓት ሁሉታችንም የምናስበው አሚሚታችን እንዴት እንደሆነ ነው። በዓይን ህሊናችን የሚላለው፣ ወዳራም ግንድ ላይ አንተርሰው አንገታችን ሲቀሱት ነው። ከአንገታችን በላይ ያለውና የተቀላው ሞንቅላታችን፣ ህይወቱ አስኪያከትም ድረስ፣ ከወላያ ወዲህ እየተራወጠ ሲቃዥ ነው።

Scanned by CamScanner

፰

ጥቂት የሰቶታ ሰዓታትን በእንትልፍ ገፍቼ ነቃሁ። አያ ቀድማ ነትታ ነበር።

ገና ከመንቃቴ ነበር ከማንቀላፋታችን በፊት ጀምሬልኝ የነበረውን ታሪክ እንድትቀጥልልኝ የወተወትኳት።

"ለመሆኑ ነዳጅ ተገኝቷል? ወይስ ገዙም ብለው ነው አላራችን የሚያበሉን?" ስል ጠየኳት። "ይህ ሁሉ ግርግር ከምን የመጣ ነው?"

"በኢላላና በካሉብ ባሉ ብሎኮች ውስጥ ነዳጅ መገኘቱ ተረጋግጧል።" ስትል ቀጠለች። "ች..ችግሩ ከዚህ በኋላ ነው የሚከተለው።"

"ምንድን ነው ችግሩ?"

"...በደርግ ዘመነ መንግሥትም፣ በአክባቢው መረጋጋት ስላልነበር በምስጢር ተይዞ እንጂ፣ ነዳጅ ተገኝቶ እንደነበር የሚናገሩ የኅይን አማኖች አሉ። ነገር ግን አጋጄን የጦርነት ቀጣና ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ኢትዮጵያ ለነዳጅ ማጣሪያነት ሊያገለግሉ የሚችሉት የቀይ ባህር ወደቦቿም፣ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት አስተማማኝ አልነበሩም። የደርግ መንግሥት ከአጋጄን አሰብ ወደብ ድረስ የነዳጅ መስመር ለመዘርጋት እትድ ነበረው። ነገር

ግን በምሥራቅና በሰሜን በጦርነት በመወጠሩ ምክንያት አልቻለም። ነዳጅ መገኘቱ ብቻውን ዋጋ የለውም። ነዳጁን ማጣሪያ መስመር ወደ ወደብ መዘርጋት ያስፈልጋል። የነዳጅ ቱቦው የሚያልፍበት ቀጠናም ከአደጋ ጣዮች የፀዳ መሆን ያስፈልገዋል።"

"ስለዚህ ነዳጁ መገኘቱ ምን ዋጋ አለው? ለዚህ ሁኔታ በአጋጄን ምድር ላይ የነዳጅ ቧንቧ መዘርጋት እንዴት ይቻላል? መደየትስ ነው ቱቦው የሚዘረጋው? ኢትዮጵያ ወደብ የላትም።"

"ችግሩ ይኸው ነው። ይኸም ሆኖ ፖሊሩፕ የተባለው የቻይና ኩባንያ ከኢትዮጵያ ጀቡቱ የሚዘረጋውን የነዳጅ ቱቦ መስመር ለመዘርጋት ከገዢው ፓርቲ ጋር ተስማምቷል። በዚህም መሠረት ክሉብ እና ከኢላላ የነዳጅ ጉድጓዶች የተገኘው የተፈጥሮ ጋዝ ጀቡቲ ወደብ ላይ ተጣርቶ ወደ ኢትዮጵያ ይመለሳል ማለት ነው። ከአጋጄን ልብ የሚነሳው ይህ የነዳጅ መስመር፣ ከጀቡቲ ወደብ ለመድረስ አንድ ሺህ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ማቋረጥ አለበት። ኢላላና ካሉብ የነዳጅ ጉድጓዶች እምስት ትራሊዱን ጫማ የተፈጥሮ ጋዝ እንደሚያመርቱ ቢገመትም ይህን ምርት አንተባ ለማጣራት የሚዘረጋው መስመር ግን አራት ቢሊዮን ዶላር ይፈጃል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ ሶስት ቢሊዱን ያህሉ ገንዘብ የሚፈሰው ጀቡቲ ውስጥ ነው። ከዚህም ሌላ ለዚህ ትብብር፣ ጀቡቲ ሁለት ኤርፖርቶች እንደሚገነቡላት ቃል ተገብቶላታል።"

"ከተጣራ በኋላስ..." አልኩ አያን እንደ ፀሱት ባጠናችው መረጃ እየተገረምኩ።

"ወላጁ የቻይና ድርጅት ሲሆን መላው የአሜሪካ ድርጅት ነው። ብላክ ሮኪኖ የተባለው የአሜሪካ ኩባንያ

Scanned by CamScanner

ሃያ ኢንች ዲያሜትር ያለው የቢንጂ መስመር ከጀቡቲ ወደብ እስከ አዋሽ ማዘሪያ ድረስ ሰመዘርጋት ተሰማምቷል። አምስት ሙቶ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ይህ መስመር ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር የሚሸጋገገዘብ ይፈጃል። ባንጂው በቀን እስከ ሁለት ሙቶ ሃምሳ ሺህ በርሜል የሚጠጋ ነዳጅ ያንቀሳል ተብሎ ይገመታል።"

"ከእፍ የወደቀች ጥሬ የምታክለው ሀገር ጅቡቲ ኢትዮጵያ ወደብ ቢኖራት ናሮ በምን ትተዳደር ነበር?" በማለት ተዝሚ ሳበቃ፣ "ጅቡቲ ምን ያህል ብትታመን ነው ኢትዮጵያ እጣ ፋንታዋን ሁሉ ይህን ያህል ያጣበቀችባት?" ስል ጠየቅኳት።

"ከነዳጁ መስመር ትገረማለህ እንዴ? ጅቡቲ ወደብ ላይ በአመት ከሚራገፈው አምስት ሙቶ ቶን ያህል ካርጎ ውስጥ ከሰማኒያ በመቶ በላይ የሚሆነውን የምታነሳው ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ በአመት ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ጅቡቲ ለምትሰጣት የወደብ አገልግሎት ትከፍላለች ማለት ነው። ባጠቃላይ ዘጠና በመቶ የሆነው የኢትዮጵያ ኢምፖርትና ኤክስፖርት የጅቡቲ ጥገኛ ነው። አሁንም ቢሆን በቀን እስከ ሃምሳ ሺህ በርሜል የሚሆን ነዳጅ ተጠቃሚ የሆነችው ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ በኩል ነው የሚራገፍላት። ከዘጠኝ መቶ ኪሎ ሜትር በላይ ተንተፉ አዲስ አበባ ሲገባ ዋጋው ምን ያህል እንደሚሄ መገመት ቀላል ነው።"

"ማኩረፊያ የሚሆን እንኳ ሌላ ጣቢ የሚከል ወደብ ቢገኝ ምን ነበረበት?"

"እርሱ ሀልም ነው። ገገርው ፓርቲ ለዚህ ጥያ የሚሰጥህ ምላሽ፣ የሶማሌ ላንድ ንብረት የሆነውን

ወርቡራን፣ ፖርት ሱዳንን፣ ወይም የኬንያውን ሞምባሳን በአማራጭነት መጠቀም እንችላለን የሚል ነው።"

ሰረቂም ደቂቃዎች ዝም አለችና፣ ቀጠለች።

"ከሁሉም በላይ፣ በድርቅ፣ በረኃብና በሞርጥ የሚታመሰው የኦጋዴን ምድር ቀን ሳያወጣለት መሞቴ ያሳዝነኛል። አንድ ቀን፣ የምታዋለው ፀሐይ በትወጣ የምትናፈቅበት ጊዜ ይመጣል የሚል ህልም ነበረኝ። ነገር ግን ይህ የደም ምድር አሁንም ድረስ ሀዘኑ በደም ይለወሰበታል። ነዳጅ ሳይሆን ደም ይንፎለፎልታል። በሽላበ፣ በደናን፣ በጎዴና በፊት ሸለቆዎች ወታደር ደርመሰመሰበታል። በዶሎ፣ በቡርሑር፣ በገላጲ ኮረብታዎች መንበሩ ያደፍጥበታል።

"የኦጋዴን ሽለቆዎች ተቃጥሰው የቀሙ ታዝኝ እንጂ በተሰፋ የቀሙ ሰዎች አይታዩባቸውም። በወገኖቻችን ደም ከጨቀየው ምድር እንዲት ጠብታ ነዳጅ እናስየም የሚሉ ኃይሎች አሁንም ድረስ አሸዋ ከለበሰው ጎን ነፍጣቸውን ደግነው አሸዋ ለብሰው አድፍጠዋል።" ደም፡ እየጨመረ መጣ።

"ምንድን ነው መፍትሄው?" አልኩ ቢጨንቀኝ።

"የለውም።"

"መፍትሄ የሌለው ነገር የለም።"

"...የቼገረ ነገር የጠፋ ሰመሳ፣

አስታራቂው በዛ እኛ ሳንጣላ።"... የሚለው ያዝማሪ ግጥም ነው መልሱ" አለችና በብሽቀት አከላላች።

Scanned by CamScanner

፳፩

አያንዳንዱ ሰአንድ የዝለለለምን ያህል ረዝሞብናል። ከአስፈናቂው ትንፋሻችን በቀር የሚሰማን ነገር የለም። ጭንቅላታችን ቀሚል። ባዶ... እንደ ባዶ ጭንቅላት የሚከብድ ነገር የለም።

ጥልቅ በሆነው ደንዝዜ ውስጥ እንላለን፤

"ለምን ስለማምለጥ አናስብም?" አያን ድንገት መሆቀኝ።

"እንዴት ሲሆን ይችላል?"

"ተቀምጠን ሞታችንን ለምን እንጠብቃለን?! እደ ሰጥቶ ከመሞት አየርው መሞት ይሻላል።"

"አቢሸል?!..." አልኢት ባመጣችው ሃሳብ እየተገረምኩ። "መታሰራችንን ረሳሽው እንዴ?"

"ጭንቅላታችን አልታሰረም።"

እያደረቹ እንደሆነ ንመትኩ። ደምሥራችን አስኪያብጥ ታስረናል። ዓይኖቻችን ድብን ባለ ጥቁር ዓይን ራግፅ ታደስዋል። እንዴት ማምለጥ ይቻለናል?...ጭንቅላታችን ቁም አስላችን ተለይቶ አደርጥ ነገር! ምን ማለቷ ነው?

"ምንም የሞክርነው ነገር የለም። ቢያንስ እንኳ ስለማምለጥ አላስብንም።" አለች አያን እንደገና።

"...ለመሞክር አለማሰብን ያህል ድክመት የለም።" የተናገረችውን ማሰብ ጀመርኩ። "...እየሞክርነው ነገር ይልቅ! ያልሞክርነው ነው ሚቆጨኝ" ያለውን ፀሐፊ አስታወስኩት። አያን ትክክል ናት።

አለመሞክርን ያህል ደዌ የለም። እርግጥ ነው ማጥ ውስጥ ንፀተናል። ችግር ውስጥ ነን። የባሰው ችግር ችግሩን ተቀብለን መቀመጣችን ነው። እስከንሞት መጠበቅ ሳይሆን እስከንሞት መሞክር ነበረብን። ችግሩን ሰማለፍ አንዳች ጥረት የማያደርግ ሰው ከአስከፊን አይሻልም። አንዳንድ ችግሮች ፅናትን ለማጎናፀፍ ይፈጠራሉ። ችግርን ያህል ታሳት ዩኒቨርስቲ የለም። ታሳላት ሰምች የተመረቁት ችግር ከሚባል ታላቅ ትምህርት ቤት ነው። የሆን የመነቃቃት መንፈስ ወረረኝ።

"እንዴት ማምለጥ እንደምንችል ያሰብሽው ነገር አለ?" ጠየቅኳት።

"ሕርስ በሕርስ እንፈታታ።"

"እንፈታታ ስትይ..."?

"ዘጥርሴ ያንተን አስር ለመፍታት ልሞክር ካቃተኝ አንተ የእኔን ትፈታልኛለህ።"

"ከደንብ አስበሽዉታል?"

"አስቤዉታለሁ።"

"ስንሞክር ብንገኝስ? ...የባሰ ችግር ውስጥ መግባታችን እንደሆነ አስበሽዋል?"

"አው... ስንሞክር ቢያገኙን የባሰ መከራ ያደርሱብንና ኑሞሞለው ያስሩናል።" ፀጥ ረጭ አለች።

Scanned by CamScanner

"እስርቻችን ፈታተን ከዚህ ዋሻ ወጥተን ሌመርጥ ብንሞክር እንኳ ከደርባችን በጥይት ይጥሉናል።"

"...እርሱ እንኳ ይሻላል። እንስትን ከመቀላት በጥይት መሞት ይሻላል።"

"ገደለሽም...ተረጋግተን እናስብበት..."

"ለለ ምን ማድረግ እንችላለን? ለላ ምን የማምለጫ መላ ይኖረናል?"

"እስማት..." አልኩ ሳላሰልሁ።
"እገ" አለች በድንጋጤ። ገም ሰላት ጊዜ ምኔት የሚመስል ሳቋን ትሰቀው ይመር።

ሃያ

"ለለ አስማት እውቀት ያለሽ አልመሰለኝም አልኒት ለለ አስማት ረዚም ጊዜ ካወራን በኋላ። "ወደም ላስማውቅ አለምርበን ዘንተሸዋል።"

"አታስቀኝ" አለች እያን ደረት ሳት ሲቃዋኝ ሲታዪዶ። "በአስማት ከዚህ ዋሻ መውጣት እንችላለን እው ምትለኝ?"

"አምኖ"

"እሺ የእኔ ክርስቶስ! ምክረህ አሰምን ሁሉ ...ሊባል እንደሰማሁት ሊየሱስ ክርስቶስ እው ፀተዜን ወር መንፃትና መውጣት የሚችለው።"

"እያን! ...አድምጪኒ! ...ባለፈው በአስማት ምክንያት ሀይሎቱ መትና እንቁሳ አጣውደሽ ነበር። አላመንሽኝም ነበር ማለት ነው?"

ምርጥ የልብ ወለድ ድርሰት የምታወራኝ ነበር የመሰለኝ። ወደ ውስጥ በአስማት ተለወጥህ። ወደ

Scanned by CamScanner

ሰውነት እንደገና መመለሻውን አስማት አላጠናህም ነበር። በዚህ የተነሳ ለአንድ አመት ያህል ከደቡብ ኢትዮጵያ እስከ አዲስ አበባ ተንገዘገዝ። ቤትህ ስትደርስ ሚስትህ ሌላ ባል አግብታ ጠበቀችህ።"

"አጥብቄ የምጠላውን ባላንጣዬን!..."

"አየህ? በደንብ ሰምቼሃለሁ ማለት ነው። ነበዘ ደራሲ የፃፈው ድርሰት የመሰለውን ታሪክህን ግን ለማመን ይቸግረኛል።"

"የንጉርኩሽ ስለ እኔ ማወቅ ስለፈለግሽ እንጂ እንድታምኚኝ፣ ወይም እንደ ህፃን ልጅ ተረት ተረት እያሚወትኩ ላስተኛሽ አልነበረም። ካልሽስ እኔ ራሴ ወደ አስማቱ ዓለም መመለስ አልፈልግም።"

"ለምን?"

"ህይወቴን ያዘበራረቀው አስማት ነው። ከልጅነቴ ጀምሬ ሳጠናው የኖርኩት የአስማት ጥበብ ከነለም ነጥሶኛል። ወደዚህ በረሃ ሰጥናት ስጋበገ ያለ አንዳች ማቅማማት የመጣሁት ከገባሁበት የአስማት ዓለም ለመውጣት ካለኝ ጉጉት የተነሳ ነበር።"

"አጋዴን የአስማት ዓለም ሆና ጠበቀችህ።"

"ያው ነው። እንዲያውም ሳይብስ ይቀራል?...."

"እስኪ በደንብ አሰረዳኝ ...ከልብህ ነው አስማት የምትለው? ታምንበታለህ?"

"በደንብ! ...ሳይንቲስቶች መከራ የሚያደርጉት በልዩ ልዩ እንስሳት ላይ ነው። እኔ ግን አስማትን ያህል አስፈሪ ነገር የምከርኩት በራሴ ላይ ነው። ከራሴ በላይ ማረጋገጫ የለኝም።"

"ለምን ታዲያ አሁን ወደ ሆነ ነገር አትለወጥምና ከዚህ ዋሻ አታመልጥም። መለወጥን ያህል ጥበብ እያለህ ለምን ሞትን ትጠባበቃለህ?"

"እንደገና ወደ ውሻነት አልለወጥም። ውሻ ሆኜ የደረሰብኝን የማውቀው እኔ ነኝ።"

"ወደ ድመት ተሰወጣ ታዲያ?"

"እንደገና ወደ ሰውነት መመለሻውን አላውቅም እንጂ ወደ ድመት መለወጫ አስማት አለኝ።"

"እባክህ አታስቀኝ። ወደ ድመት ብትቀየር አንቱ ነበር የምንድልህ። ድመትን ያህል ጠላት የለኝም። ህፃን ወንድሜን የበላው ድመት ነው። ድመት ባዙ ቁጥር በጦርነት ያጣኋቸው ቤተሰቦቼ ናቸው የሚታወሱኝ። እስከ አሁን ለቁጥር የሚያዳግት ድመት ፈጅቻለሁ። ብዙ ድመት አሰቃይቼ ገድያለሁ። ሰዎች 'ተይ ድመት የገደለ ሰው ሽባ ይሆናል' ሲሉኝ አልሰማቸውም። እስካሁንም ሽባ አልሆንኩም። ...ወደ ድመት አለመግለሁ ብለህ እንዳትሞክር። ሰምሮህል ከተቀየርክ ንጻይህ እኔ ነኝ።"

"ካልሽስ ወደ ድመት መለወጫው አስማት ተሳል ነው።" አልኳት በለሆሳስ። "ለአንቺም አስማቱ የሚቀልሽ ወደ ድመት መለወጫው ነው።"

"አኡዝቢሊላህ! አንተ ዝም በል!" ጮኸችብኝ። "ዊራሽ እኔ ወደ ድመትነት!"

"መቼም በአንቱ አንነትን ተቀልቶ ከሙሞት የማይሻል ነገር የለም። ብዙ ህልም፣ ብዙ ተስፋ ያለው

Scanned by CamScanner

ሰው ሞትን ዝም ብሎ መቀበል የለበትም። ክፉ ቀን እሸህ ያስፈራባል። ጎደሉ ቀን ከሰውነት ክብር ዝቅ ያደርጋል። ምንም ይሁን ምን፣ በየትኛውም መንገድ ጎደሉ ቀናችን ማለፍ ነው ቁም ነገሩ። ለእኔ ጀግና ሰው ማለት እንበላን ታግሎ የሚጥል አይደለም፣ ክፉ ቀንን በጥበብ የሚያልፍ ነው። ሁሉም ሰው "ግብ እስክቾለ ድረስ፣ ክፉ ቀናቹን የሚያልፍበት መንገድ አጼ ላይ አያጣም። ዘጠና ዘጠኝ በሮች ሲዘጉ ሙቶ በሮች ይከፈታሉ። ለእኛ ለጊዜው የተከፈተው በር፣ በእጃችን ያለው የአስማት ጥበብ ነው። አስማትን አጥብቂ አጠላለሁ። ነገር ግን በዚህ ሰዓት ሌላ ምርጫ ስለሌለኝ አጠቀመዋለሁ። ማንም ሰው መጀመሪያ መጠቀም ያለበት በእጁ ላይ ያለን መፍትሄ ነው።"

"አስረዳኝ!" አለች አያን ድምፅዋን ተዝቀዝ አድርጋ። "አስረዳኝ... አሁንም ድረስ በአስማት ለማመን አዕምሮዬ አልተዘጋጀም።"

"እንቺን ስለ አስማት ለማስረዳት ሰዓታትን ሊፈጅብኝ ይችላል። በዚህ መሀል አሳሪዎቻችን መጥተው እንገቶቻችን ሊቀሏቸው ይችላሉ።"

"አስረዳኝ! ካላመንክበት አይሠራ ይሆናል።"

፳፫

ለአያን ስለ አስማት ለማስረዳት ሰዓታትን ፈጀሁ። ስጦንት ዘመን ጀምሮ ስላለው የአስማት ጥበብ አመሰካከት ቅዱሳን መጣህፍትንና ርዕሳን መጮቱሱችን ጭምር አምጣዕኩ ተረኩላት። በመሃል በመሃል ሰምትጠይቀኝ ጥያቄዎችም ከበቂ በላይ መልስ ነበረኝ። ከልጅነቴ ይዝቼ ያጠናሁት የአስማት ዓለም ጥበብ፣ በሰዓታት ብቻ ተተርኮ የሚያበቃ አልነበረም። አያሌ መጣህፍት የሚወጣውን ታሪክ ጨምቂ የንባርኒት ጨለማ ውስጥ የወረውሩን ወንዘዲዎች አንገታችንን ሳይቀሱን ለማምለጥ ካለን ጭንቀት የተነሳ ነው።

ብዙ ሰዎች አስማት፣ መተት፣ ድግምት፣ ምትሐት ሰይተው አያውቁም፣ የሳይኪክ ጥበብና የቴሌፓቲ (ስድስታኛው ስሜት) ተሰጥኦ ይምታቱባቸዋል። ለአያን እነዚህን ሁሉ ፀየፈርጃ አስረዳኒት።

አስማት፣ በጥቅሉ ልዕለ ተፈጥሮ (ሱፐር ናቹራል) የሆነውን ኃይል የመጠቀም ጥበብ ነው። ይህ ጥበብ ቅደም ተከተሎችን (ሪቾዋልስ)፣ ጠልሰሞችን (ሲምቦልስ) እና ታላትን (ስፔል) የመጠቀም ጥበብ ነው። በጥንታዊ ጥቅሶች ላይ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጠልሰሞች

Scanned by CamScanner

(ሲምባልስ) ተመልክቻለሁ። የወከሉትን ነገር ለመረዳትም አያሌ ጥናቶችን አድርጌለሰሁ። ይሁን እንጂ በውል ያተኮርኩት በቃሳት በሚገልፀው የአስማት ጥበብ (ማጂክ ሰፔል) ላይ ነው። በዚህም የቃሳትን ኃይል ተምሬአለሁ።

አስማት (ማጂክ) የሚለው ቃል ከክርስቶስ ልደት በፊት ከነበተኖው ከፍለ ዘመን ቀደም ብሎ በፔርሺያ ምድር "ማጉ" በመባል ይታወቅ ነበር። ቃሉ ወደ ግሪክ ሲገባ አስፈሪ ትርጉሜ ያዘ። ከክርስቶስ ልደት በኋላ በአንደኛው ከፍለ ዘመን አካባቢ በክርስቲያን ቲዎሎጂ ውስጥ፣ በሳቲን ትርጉሜው ከሃይማኖት ተሻራሪ የሆነ ትርጉሜ ከተሰጠው በኋላ፣ ከሰይጣን ጋር በማያያዝ፣ አያሌ የአስማት መፃህፍት ይቃጠሉ ጀመር።

ከእሳት የተረፉት የአስማት መፃህፍትም በጥቂት ሰዎች እጆች ስለገቡ፣ በተለይ በምዕራቡ ዓለም ሰዎችን ማስፈራሪያና መበገዣ ሆነ። አዋቂዎቹ ተሳደው ስለተገደሉ አባይ ጠንቋዮቹ የአስማት ጥቅሱቹን መጫወቻ አደረጓቸው።

ከቀኝ ግዛት በፊት በአፍሪካ አያሌ አዋቂዎች እንደነበሩ ጥናቶች ያሳያሉ። ዘመናዊ ህክምና ከመስፋፋቱ በፊት፣ አፍሪካውያን ይታከሙ የነበሩት በእነዚህ አዋቂዎች የቅጠላቅጠልና የሥራሥር ጥበብ ነበር። ኩተፈጥሮ ጋር ጥበቅ ቁርኝት የነበራቸው አዋቂዎች ትጠላ ቅጠልን ብቻ ሳይሆን ልዕለ ተፈጥሮ (ሱፐር ናቹራል) ኃይልንም ይጠቀሙ ነበር። ነገር ግን ለህፀት ቅርምት በሃይ[illegible] ስጠኩት የነው መራሪዎች፣ አዋቂዎችን በህዝብ ፊ[illegible] ጥቅሱቻቸው በእሳት አቃጠሏቸው። በየዋሻው ተ[illegible] የተገኙት ጥቂት ጥቅሱች ብቻ ናቸው ሰጥናቸ[illegible] የተረፉት።

በሀገራችን ኢትዮጵያም ኦሮንት ዘመን ይምር አንቱ የተባሉ አዋቂዎች እንደነበሩ ይታወቃል። ሕዝቡን በቅመሳ ቅጠልና በሥራሥር ከመፈወስ አልፈው፣ የውስጥ ደዌን በመከታጠት ቁልጭ አድርገው የሚያዩ፣ በልዕለ ተፈጥሯዊውን ኃይል በመጠቀም በውሃ ላይ የሚራመዱና በደመና የሚጫኑ የአስማት ሊቃናት እንደነበሩ ይነገራል። ሆኖም ከሃይማኖት ምሁራን ጋር ባለመስማማታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ተወግዘው ከህዝቡ በመለየታቸው ቀስ በቀስ እንዲጠፉ ተደርገዋል።

በሃይማኖት መፃህፍት ውስጥም እነዚህ የአስማት ሊቃውንት መናራቸው ተመዘግቧል። በዮንታዊቷ ግብፅ ፈርኦናች ፊት ልዩ ልዩ ጥበቦችን ያሳዩ እንደነበርም በመፅሐፍ ቅዱስ ሳይቀር ተጠቅሷል።

ከምድያም ምድር ጥበብን ተከኖ፣ ፈርኦን ህዝቡን እንዲለቅ ተአምር ያሳይ የነበረውን ሙሴን፣ በአስማት ጥበባቸው ተገዳድረውታል። የፈርኦን ጥበቦችም በትራቸውን ወደ እባብ በመለወጥ ጥበብ አላይተዋል።

በዘፀአት መፅሐፍ እንደተጠቀሰው። ሙሴና አሮን፣ ፈርኦንን በተአምራት ለማስፈራራት ወደ ንጉሡ ይገባሉ። አሮንም በትሩን በፈርኦንና በባሮቹ ፊት ይጥላል። እባብ ትሆናለች። ፈርኦንም የግብፅን መቢጣ ፈጥኖ ይጠራል። በአስማታቸው በትሮቻቸውን ወደ እባብነት ይለውጣሉ። በዚህ ጊዜ ግን ወደ እባብ የተለወጠችው የአሮን በትር የግብፆቹን በትር ትውጣለች።

Scanned by CamScanner

በትንቢተ ዳንኤል ላይ፣ ስለ ባቢሎን ጠቢባን እያሉ ጊዜ ተጠቅሷል። የባቢሎኑ ንጉሥ ምስጢር አዋቂዎች፣ ህልም ፈቺዎችና ታላቁኖች እንደነበሩት በስፋት ተጠቅሷል።

በዘፍጥረት መፅሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው፣ ልዩ ልዩ ጥበቦችን ያደርጉ የነበሩት ኔፍሊም የተባሉ የሰውና የመላእክት ዲቃላዎች ናቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ፍጡራን፣ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ እስኪፀፀት ድረስ አሳዝነውታል።

በዘፀዓት ላይም፣ "መተተኛይቱ በህይወት እንድትኖር አትፍቀድላት" ሲል ያወግዛል።

የዘሌዋውያን መፅሐፍ "አስማት አታድርጉ፣ ሞራ ገላጭም አትሹ።" ሲል ይመክራል።

ዘኁልቁ፣ "በዕያቆብ ላይ አስማት የለም፣ በእስራኤል ላይም ሟርት የለም።" ሲል ያውጃል።

ዘዳግም ላይ፣ "ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፣ ሟርተኛ፣ ሞራ ገላጭም፣ አስማተኛም፣ መተተኛም፣ በድግምት የሚጠቀልም፣ መናፍስትንም የሚጠራ ጠንቋይም፣ ሳቢም ባንተ ዘንድ አይገኝ ይልና፣ አስማት በላ ጌላ ቀር ህዝብ ውስጥ ምን ያህል ተስፋፍቶ እንደነበር ያሳያል። መናፍስትን መጥራት የሚችሉ፣ ምንም ሳይታጠሉ በእሳት ላይ የሚረግመዱና የሞቱ ሰዎችን እንኳ ስለው በመጥራት የሚያናግሩ ጥበበኞች እንደነበሩ ያስረዳል።

በመፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ላይ ዝርዝት የሚፈጥር የሙታን መጥራት ጥበብ ይታያል። በዚህ ትረካ ላይ፣

ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ሊወጉ ይመጣሉ። በወቅቱ ሳሙኤል ሞቶ ነበር። በዚህ ጦርነት የሚፈጠረውን ነገርና ምን ማድረግ እንዳለበት (የጦርነት ትንበያ) ሳሙኤል ሞቶ ስለነበር የሚነገር ይጠፋል። ቀደም ብሎ ሳኦል መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ከምድር አጥፍቶ ነበር። ያለው ብቸኛ አማራጭ ሳሙኤልን በአስማት ከሙታን መሪዎች ዘንድ አስጠርቶ ማነጋገር ነበር። በዚህ ጊዜ ባለያዥነቱ አይንዶር በተባለ ምድር አንዲት መናፍስትን የምትጠራ ሴት እንዳለች ሰምኦል ይነግሩታል። ሊገድሳት የፈለ መስሏት እንዳትሸሽ ሳኦል እንደተራ ሰው ተሸፋፍኖና መልኩን ሰውጦ ወደ አይንዶሯ አስማተኛ ይሄዳል። ይለምናታል። እርሷ ግን በሳኦል ታስገድለኛለህ ብላ ሰኦልን እንደማይናገር በእግዚአብሔር ይምልላትና አስማተኛዋ በድግምቷ ሳሙኤልን ከተኙ አደረገችለት። "የምተፈልገውን ጠይቀው!"

በትንቢተ ኢሳይያስ መፅሐፍ ላይ ደግሞ፣ እግዚአብሔር በአስማተኞች በመማረር ቢጎይል ሲዝት ያሳያል።

"የሐሰተኛዎችን ምልክት አንቱ አደርጋለሁ፣ ሟርተኞችንም አሳብዳለሁ፣ ጥበበኞችንም ወደ ኋላ እመልሳለሁ። አውቀታቸውንም ሰንፍና አደርጋለሁ።" ይላል። ፈጣሪን የሚንዳደሩ አስማተኞች እንደነበሩ ዛቻው በደንብ ያስረዳል።

ጳዉሎስም አስማተኞች እንዳያጠፉት አምላኩን ሲማፀን እንደነበር የሚያስረዳ መዝሙር አለው። በሰውይ ብቻ ሳይሆን በሐዲስም ላይ ስለአስማተኞች ብዙ ቦታ ላይ ተጠቅሷል። በሐዋርያት ሥራ ላይ ስሰ ጉደኛው አስማተኛ ሲሞን ተተርኳል። የሰማርያ ከተማ በእርሱ ከሰሙት ትደነቅ ነበር። በሲሞን ተአምራዊ የአስማት ችሎታ ውስጥ የፈጣሪ ኃይል እንዳለበት የሚያምኑም ነበሩ። ሐዋርያው

Scanned by CamScanner

ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ገብቶ ህዝቡን ሰብኩ አጣመቀ በኋላ ግን ራሱ አስማተኛው ሲሞንም ሊጠመቅ ይመጣል። ከተጠመቀ በኋላ ግን መንፈስ ቅዱስን በገንዘብ ይሸጡት እንደሆን ጠየቀ። በዚሁ መፅሐፍ ላይ ብዙ አስማተኞች መዒሕፍቶቻቸውን ሰብስበው እንዲቃጠሉና ዋጋውም ሐምሳ ሺህ ዲናር እንደሆነ ተዘግቦአል።አንዳንድ ተመራማሪዎች፣ "መፅሐፈ ጠቢባን" የተባለና ከብዙ ታዋቂ አስማተኞች ጥበብ ተጨምቆ የተፃፈ ድንቅ በዚህ ወቅት እንደተቃጠለ ይናገራሉ። ጳውሎስ ለንሳትያ ሰዎች በፃፈው መልእክትም አስማትን አውግዞአል። ይሁን እንጂ በዮሐንስ ራዕይ መፅሐፍ ላይ አስማተኞቹ ጨርሰው እንዳልጠፉ ይናገራል። ይህ ማለት ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ባለው የመፅሐፍ ቅዱስ ትረካ ላይ እንደተገለፀው አስማት በቀደምት ህዝቦች ዘንድ የታወቀ ጥበብ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ይሁን እንጂ ስለ አስማት ሥረ መሠረትና የት መጨነት በደንብ ትንትን ብሎ የተገለፀው በመፅሐፈ ሔኖክ ላይ ነው። በአያሌ የአስተርዮጂ ጥበቦችና በሀዋ ምስጢሮች የተሞላው መፅሐፈ ሔኖክ፣ አስነሁን ድረስ ሳይንስ ያልደረሰበትን ጥበብ እንደያዘ ይገመታል። በርካታ ሳይንቲስቶችም ጥናት እያካሄዱበት ይገኛሉ። የአውሮጳ አሳሾች መፅሐፈ ሔኖክን ለማግኘት ከየጉት በመን ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ እየገቡ ያላደረጉት ጥረት አልነበረም። በሃይማኖት ስብክት መልክ የገቡ የካቶሊክ ቄሶች ሳይቀር ዋና ግባቸው መፅሐፈ ሔኖክን ማግኘት እንደነበር ይታመናል።

በመፅሐፉ በመን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈሰጉት በንጻጽ የበለፀጉት ጉድጓዶች ሳይሆኑ ሁለት ቅርሶች ነበሩ፣ መፅሐፈ ሔኖክና ፅላተ ሙሴ። በተሰይ ራሳቸውን

የኤሊያን ዜሮች ነን ብለው የሚቆጥሩ ህዝቦች ታሪካቸው በውል የተከተበበትን መፅሐፍ ሰመራስን ኢትዮጵያ ውስጥ እየገቡ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ነገር ግን መፅሐፈ ሔኖክን በማግኘት የተሳካለት አንድ ሰው ብቻ ነው- ጀምስ ብሩስ። ይሁን እንጂ፣ ተገኝተም ምስጢሩ ያልተገኘው መፅሐፍ፣ ስለ ስነ ፈለክና ስለ የኀሸርስ ምስጢራት ብቻ ሳይሆን ስለ አስማት ጥበብም ትንትን አድርጎ ያስረዳል።

መፅሐፈ ሔኖክ ስለ ስነ አፅዋት ከዘረዘረ በኋላ፣ ስለ ስነ ሰብዕ ይተርካል። በገጻዩ ቃኤልና የሚቹ አቤል ምትክ በሆነው የሴት ልጆች መሳከል ስለተደረገ ጋብቻ በመተሰክ የሰው ልጅን ታሪክ ይጀምራል። የሴት ልጆች በቃኤል ልጆች መልክ መልካምነትና ደመ ግቡነት ይማረካሉ። እርስ በእርስ ይጠራራና ከመኖሪያቸው ከደብር ቅዱስ ተነስተው የአርሞንኤም ተራራ ራስ መደሆነው ወደ አርዲስ ወርተው የቃኤልን ሴት ልጆች ለማግባት ይሄዳሉ። ወደ አርሞንኤም ተራራ የወጡትን የሴት ልጆች የዝበ አሰቶች መፅሐፈ ሔኖክ በዝርዝር ያስቀምጣል።

አሥራ ስምንት ናቸው። ስማዝያ፣ ዑራኪባራምኤል፣ አኪቢኤል፣ ሚምኤል፣ ራሙኤል፣ ዳንኤል፣ አዚቃኤል፣ ሱሩቃኤል፣ አስኤል፣ አርሞርስ፣ በየርኤል፣ አናንኤል፣ ዝቂኢ፣ ሳምሳፒኤል፣ ስርትኤል፣ ጠሩኤልያም፣ ያኤልና አራዝያል ይባላሉ። እነዚሀና ሌሎች የተከተሏቸው የሴት ልጆች ቃኤልን ዙር የተወሰዱትን ቀንጸት ሴቶች ከአርሞንኤም ተራራ ቀንሙ ድረስ ወጥተው ጠለፈው ተጻሯቸው አጋቿው። ከተጠለፉት የቃኤል ዜርችም፣ ሥር መግስንና ቅጠል መቤከስን ተማሩ። አስማትና ድግምትን አጠኑ።

Scanned by CamScanner

የወንሱት ሴቶችም ከዚህ ቀደም ታይተው የማይታወቁ ረጃጅም ልጆችን ወለዱ። ቁመታቸው ሦስት ሺህ ክንድ ያህላል። እናትና አባቶቻቸው እነሱን መቀለብ እስኪሳናቸው ድረስ የሰበሰቡትን ሁሉ አሟጠው በሉት። ሞራሽ እናትና አባቶቻቸውን አንቀው ይበሏቸው ጀመር። አእዋፍንና አራዊትን አላደው ይዘው እስከነፍሳቸው ይዘለግፏቸው ገቡ። መጦንብ ተሳናቸውና እርስ በእርሳቸውም መበላላት ቀጠሉ። እንዱ እንዱን ይዞ ደሙን መጥጦ ይጥለዋል። ቫምፓዩር የሚባሉት የዘመናችን የፊጠራ ገፀ ባህርያት መነሻ ይህ ታሪክ ሳይሆን አይቀርም።

ከነዚህ መሀል የሳቀ ጥበብ የነበራቸው ሰዎችም ነበሩ። ፈረስና በቅሎን ከሰው ጋር አዳቅለዋል። አዛዝኤል የተባለው በዚህ የተካነ ነበር። ለወንዶች ሰይፍ መስራት፣ ጋሻ መሰንደንና ሽለላን፣ ለሴቶች እንሶሳላ መሞቅን፣ መኳኳልንና መቀንደብን አስተምሯል።

ጋኔን መሳብን፣ አስማትንና ምትሃት ማሳየትን አሚዛራክ፣ ኮከብ ቆጠራን- በረቅአልም፣ ምልክት ማሳየትን- ኮከብኤልም፣ የፀሏረቃ ምህዋርን- አሰራድኤልም እንደስተማሩ መፅሐፈ ሔኖክ ያትታል።

አያን በበኩሏ እንዳስረዳችኝ በቁርዓንም ስለ አስማት ብዙ ሐተታዎች አሉ። ዘመናዊዎቹ ምሁራን አስማትን ለሃይማኖትና ለሳይንስ ማንዐሪያነት ያቀርቡታል። ሶሻሉጂስቶቹ አስማት የሃይማኖት ተቃራኒ እንደሆነ ሲገልፁ፣ አንትሮፖሉጂስቶቹ የሰውን ልጅ እድገት ቅደም ተከተል በማጥናት አስማት፣ ሃይማኖትና ሳይንስ የአእምሮ እድገት ማሳያ ቅደም ተከተሎች እንደሆኑ በማስቀመጥ አስማትን የኋላ ቀሩ የሰው ልጅ ማሳያ አድርገው ያቀርቡታል።

ሲግመን ፍሩድ አስማትን ከስነ ልቡና ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው አስረድቷል። አስማትን የሰው ልጅ ፅኑዕ ተምኔት ውጤት አድርጎ ያቀርበዋል። አስማት የሰው ልጅ የምኞት ውጤት እንደሆነ በማስረዳት ፈቃዱን ለመፈፀም ሲል መሠረት የሌላቸውን ነገሮች በሀሳቡ የሚስማበትና የሚያይበት መሣሪያ ነው ሲል ይከራከራል።

ይሁን እንጂ፣ በጥንቱ እና በመካከለኛው ዘመን የታሪክ ፀሐፍት፣ አንዳንዴ ከሰይጣን አሠራር ጋር አንዳንዴም ከሰው ልጅ የአእምሮ አድጉት ጋር እየተያያዘ ሲገሰፅ የኖረው የአስማት ጥበብ፣ በጥቅሱ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎችን ይዟል። ጥቁር አስማት፣ ነጭ አስማትና ተፈጥሯዊ አስማት በሚል ተከፍሎ ይታያል።

ጥቁር አስማት ተብሎ የሚታወቀው፣ ልዕለ ተፈጥሯዊውን ኃይል ለጎጂ ተግባራት አገልግሎት እንዲውል የሚያደርገው ክህሎት ነው። ፓራሳይኮሎጂስቶች ይህንን የአስማት ጥበብ ከግለሰብ አእምሮ ሀገር ድረስ በህይወትና በንብረት ላይ ከሚደረግ ጉዳት ጋር ያይዙታል። በምዕራቡ ዓለም ሙሴ እንደፃፈው ባይረጋገጥም፣ ጥሙሴ መፅሐፍ የሚባል የድግምት መጥቀል አለ። ሙሴ የአስማት ጥበብ ችሎታ እንደነበረው በመግለፅ መፅሐፉ ገብቶት የተጠቀመ ሰው ሱሲፈርን አስሮ የፈለገውን ሊያሠራው እንደሚችል ለማሳመን ይሞክራሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥም ከዚህ ሊመደቡ የሚችሉ፣ እንደርቢ፣ አፍዝ አደንግዝ፣ ጥላ ወረ፣ ምስሐበ ንፍይ የተባሉ ጥቁር አስማቶች እንዳሉ ይታመናል። እንደርቢ ወርዶባቸው በማያውቅ መንፈስ ቤታቸው ላይ ድንጋይ ወርዶ ጣራቸው የደቀቀባቸውና የቤት እቃቸው ሁሉ

Scanned by CamScanner

ዱቄት የሆንባቸው፣ ሰዎች አስማተኞች እንደርኩን እንዲያቆሙላቸው ደንጋይ ተሸክመው እንደሰመጉ አምነ ሆነው የቀረቡ ማስረጃዎች አሉ። በረድ የሚያዘንቡ፣ ተባይ የሚያዘንቡ አስማተኞች እንዳሉ ይነገራል። አውደ ነገሥትና ሐተታ መናፍስት የተባሉ የታተሙ መፃህፍት ቢኖሩም፣ አደገኛው የአስማት ጥበብ የተከተበባቸው መፃህፍት ግን በብራና ተፅፈው በጥቂት ሰዎች እጆች ላይ ብቻ እንደሚገኙ ይታመናል።

ሁለተኛው የአስማት ክፍል "ጉዊ አስማት" የሚባለውና ልዕለ ተፈጥሯዊን ኃይል ለበጎ ተግባር የማዋል ጥበብ ነው። የጥቁር አስማት ተቃራኒ ነው። በኢትዮጵያ ሰዚህ የቪ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አስማቶች እንዳሉ ይታወቃል። መፍትሔ ሥራይ፣ አቃቤ ርዕስ፣ ሴባ ንትር፣ ዘኢያንድፍ (መስተፋቅር?) መዘተረፈ በዚህ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው።

ሶስተኛው የአስማት ክፍል በዘመናዊ አጥንቼዎች ዘንድ "ተፈጥሯዊ አስማት" በመባል ይታወቃል። ከአስማተኞች ልዩ ተፈጥሯዊ ችሎታ ጋር ይያያዛል። ከተመሰጠ ጋር ጥበቃ ቁርኝት ሲኖረው የሳይኪክ ጥበብን ይጠይቃል።

በሳይኪክ ጥበብ፣ በቁስ አካሎች ላይ በመመስጥ ብረቶችን ማሻሻም፣ እቃዎችን አየር ላይ ማንሳፈፍ፣ የሚበር ንጥርን ቀጥ ማድረግ መቀየርና የመሳሰሉ ጥበቦች ይገኛሉ። በዘራፍን ከዚህ ክፍል የሚመደቡ የመሳሰሉ ጥበቦች እንዳሉ ይታወቃል። ንዑሱን አካል ክፍይን እይታ መሰወር ወይም ቦታ ቀይሮ እንዲሸ የሚያደርግ ኃይል የመጠቀም ጥበብ ነው። ግድግዳ ሲያስፈልገው የሚያልፍ፣ በውሃ ላይ የሚራመድ፣ ፍጡሮችንና በአየን ውስጥ እንዳንፈተፍቁ ሊድራት

ሚችሉና አብደናን በሕሳት ውስጥ የሚመላለስ የሳይኪክ ጠቢብ በአናም ሀገር እንደነበርና አሁንም እንዳለ የሚገልፁ አሉ።

የተፈጥሮ አስማት (ናቹራል ማጂክ) እየተባለ በምሁራን ዘንድ የሚታወቀው ይህ የሳይኪክ ጥበብ፣ ለፈውስም ያገለግላል። በምሁራኑ ዘንድ ይህ ጥበብ ለህክምና ሲውል "ፓዚኪስኅቲክ" እየተባለ ይጠራል። የፈውስ ሥርዓቱ በእይታ ብቻ ወይም የተመረጡ ቁሶችን በመሸተናው ላይ በማስተመጥ ይከናወናል።...

"ቬረ ለመሆኑ የሳይኪክ ጥበብ ምንድን ነው? ይህኛው ጥቂት የተሻለ ይመስለኛል" አለች አያን ስለ አስማት ለሰዓታት ያዘነብክባትን ገለፃ ባለመሰልቸት አጣጭጣ ስታበቃ።

"ሳይኪክ ማለት የሰው ልጅ ካሉት አምስት የስሜት ህዋሳት ሌላ በረቂቅ ሁኔታ ካልታወቀ ኃይል፣ ከህሉት የሚቀበል ሰው ማለት ነው።" ሰል ትንታኔዉን ቀጠልኩላት። "ሳይኪክ ኃይል ያለው ሰው በሌላ ሰው አእምሮ ውስጥ የሚመላለውን ሀሳብ ልክ እንደተገለጠ መፅሐፍ ማንበብ ይችላል። በሌለበት ቦታ የሚከናወኑ ድርጊቶችን አድማስ በማይገድበው ዓይኑ መመልከት ይችላል። መደፈት ስላለው ጊዜም መተንበይ ይችላል። ባጠቃላይ ሳይኪክ ማለት የስውር እውቀት ባለቤት የሆነ ሰው ማለት ነው። ለምሳሌ በሃገራችን እንደ ሼህ ሁሴን ጅብራል አይነት ሰዎችና ሌሎችም አሁን አስነሰንበት ያለውን ዘመን ጥንቅቅ አድርገው ተንብየዋል። የወደፊቱንም ተንብየዋል። ይህ አንዱ ማረጋገጫ ነው።"

አያን ሌላም አያሌ ጥያቄዎችን አንስታ ነበር።

Scanned by CamScanner

"ጊዜ የለንም!" አልኒት እንገታችን የሚቀላበት ጊዜ ጸናው እየቀረበ የመጣብኝ ያህል እየተጨነቅሁ።

"መለወጥ ባንችልስ? ማለቴ ድመት መሆን ባንችልስ? ድመት ከሆንን በኋላ እንደገና ሰው መሆን ባንችልስ?"

አሁንም ሌላ የጥያቄ መዓት አዥጎደጎደችብኝ።

ሸዕ

አያን በነገርኒት አስፈሪ ታሪክ ስትርበተበት ቆየች።
"ጥቅት ጥያቄ መልሱም ጥበቅ ነው" አልኒት መደንገጧ እያስገረመኝ።

"እሱነሁን ያስረዳቹኝ ስለ አስማት ነው" አለች በሚሰባበር ድምፅ። "ከአስማት ወደሌላ ፍጡርነት ስለመለወጥ ግን አልነገርከኝም።"

"ልብ አላልሽኝም እንጂ ነግሬሻለሁ። የእርግ በትር ወደ አባብኑት መለወጧን መፅሐፍ ቅዱስን አጣቅሼ ነግሬሽ ነበር። ክስምች ተለይተህ ትሰደዳለህ፤ መኖሪያህም ከምድር አራዊት ጋር ይሆናል፤ እንደ በሬም ሣር ትበላ ዘንድ ትገደዳለህ የተባለው ናቡከነፆር፤ ጠጉሩ እንደ ንስር ጥፍሩ እንደ ወፍ እስኪረዝም የምድረ በዳ አውሬ ሆኗል። እንደ በሬም ሣር ግጧል። በግሪክ ሚቶሎጂ ውስጥም እያሌ ወደ ሌላ ፍጡርነት የመለጥ ትረካዎች አሉ። አንዱን ስምሳሌ ልጥቀስልሽ።" አልኒትና ሶግዳመጥ ዘገጃ መሆኗን ለመገንዘብ ሰጥቂት ሰከንዶች ዝም አልኒት።

"ይገርማል!... እሺ ቀጥል።"
"በግሪክ ሚቶሎጂ ውስጥ ...የመንገደኞች ጠባቂ የሚባለው የሐሜስ ዘመን ትንሣርት ነው። አባቱ

Scanned by CamScanner

የአማልክት አባት ዜውስ ይባላል። እናቱ ኤራ ትባላለች። ነገር ግን ዜውስ፣ ኢዮ የምትባል ሴት በሚስቱ ላይ ይወሸምቧታል። ኤራ በንዴት አብዳ ወደ ኢዮ ትሄድና በረቂቅ ጥበቧ ወደ ላም ትለውጣታለች። በዚህ አላበቃችም፣ ለአርጎ መቶ ዓይናች ትሰጠውና እንዲጠብቃት ታዛዋለች።

"አርጎ ሲተኛ እንኳ አምሳውቹ አይናቹ ሲከደኑ ሃምሳዎቹ ቁልጭ ቁልጭ ይሉ ነበር። ዜውስ ይህን ይሰማና ሐሜስ አርጎን ገድሎ ወደ ላም የተለወጠችው ኢዮን ነፃ እንዲያወጣት ያዝዘዋል። ሐሜስ ወደ አርጎ ሄዶ ለመግደል ሲጠባበቅ አርጎ ባለመቶ ዓይን በመሆኑ በሃምሳው ሲያንቀላፋ በሃምሳው እየነቃ ያስቸገረዋል። አንድ መላ መጣለት። ጥውም የሆነ የሙዚቃ ቃና እያጫወተው ሁሉም ዓይናቹ እንዲከደኑ ያደርገውና በድንጋይ ቀጥቅጦ ይገድለዋል።"

"ኢዮን አስፈታት?" አለች አያን። "ከላምነት ወደ ሰውነት እንደገና መለሳት?"

"በአፈ ታሪኩ መሠረት ሐሜስ ኢዮን አስፈትቷታል። ነገር ግን ከላምነት እንደ ገና ወደ ሰውነት እንደለወጣት የሚገልፅ ነገር አላነበብኩም።"

"ይህን ነው መፍራት!...." አለች አያን እየተርበተበተች። "ድመት አድርገህ ልታስቀረኝ ሃሳብ አለህ ማለት ነው። አልሞክረውም።"

"ወደ ድመትነት መለወጥ እንደምትችይ ግን አምነሻል ማለት ነው።"

"ሰው ሆኖ ሰው መሆን ባልተቻለበት ዘመን፣ እንዴት አውሬ ሆኖ ሰው መሆን እንደሚቻል ልታስረዳኝ ትሞክራለህ?! እ?!... ደፋር! "

"ሰው መሆን እንጂ አውሬ መሆን ቀላል ነው። ትክክል ነሽ። ወደፊት ተስፋ ያለው ሰው ግን ክፉ ቀኑን ከሰውነት ክብር በታች ሊያስቀምጠው ይችላል። እያልኩሽ ያለሁት ይህንን ነው። እኔ በአንድ ወቅት ውሻ ነበርኩ። ሰው ለመሆን የበላሁትን አላር አውቀዋለሁ። ተስፋ ቆርጦ ኖሮ ውሻ ሆኜ እሞት ነበር። አሁን ሰው ነኝ። ነገር ግን በየትኛው ሰከንድ እንደሚቀላ አላውቅም። ወደ በድንነት ከመለወጤ በፊት ወደ አውሬነት ተለውጬ ህይወቴን ባቆያት እመርጣለሁ። እንዳች ጥረት ሳናደርግ እንዴት ህይወታችን ታክትማለች?"

"እሺ..." አለች አያን ሳቋ እያፈናት። ይሄ ነው የሚገርመኝ ጠባይዋ። በዚህ ሞንቅ ጊዜ ሳቋ ከየት ነው የሚፈልቅ?

"ምን ያስትሻል?"

"ሳብድ ነው መሰለኝ። ሞንትላቱ ዞረብኝ። ድመት ሆኜ... ጅራቴን ስቆላ፣ ስናዝር፣ አይጥ ሳሯሩጥ... በእእምሮዬ ስስለው አጥወለወለኝ። ...ኤክ! ...ውይ ውይ...! ድመት ከመሆን ውሻ መሆን ይሻላል። ድመት መሆን አልፈልግም።"

"እኔ ደግሞ ውሻ መሆን አልፈልግም።"

Scanned by CamScanner

"ለምን?!.. እባክህ ውሻ ብንሆን ይሻላል! ...ውሻ ብንሆን ከዚህ ቀደም ሆነህ ስለምታውቅ እንደገና ወደ ሰውነት ለመለወጥ አንቸገርም። በዛ ላይ... 'ድመት አልወድም' ብዙ ሺህ ጊዜ ነግረሃለሁ።"

"ሁልጊዜም የወደድሽውን መሆን አትችይም።"

"ድመት ሆነን ብንቀርስ እሺ?"

"ይልቁንስ አስማቱን ማጥናት ጀምሪ"

"ፈራሁ።... የልቤ ምት አይሰማህም? ዋሻውን ሊንደው ደርሷል እኮ። ተንፏቃ ተጠጋችኝና ደረቴ ላይ ተሰጠፈችብኝ።

እንደወደደችኝ አውቄባታለሁ። እንደወደድኩዋት አውቃብኝ ይሆን? ... ከዓመታት በኋላ ልቤ የናፍቅር ደም ሲረጭ ታወቀኝ። ወደ አውሬነት ከመለወጣችን በፊት ትኩስ የነበሙ ከንፈሯን ግመጠው ግመጠው አለኝ። ቀደመችኝ።

፳፭

አስማቱን አለማምዳት ጀመር። አያን እየተከሳተፈች የአስማቱን ቃላት ትጠራና መልሳ አሻፈረኝ ትላለች። በመሃል ደግሞ ያችን ሳቋን ታመጣለች።

"ውሻ ብንሆን ይሻላል" ትላለች።

"ስሚኝ!... ያለነው አጋዴን ውስጥ ነው። ዘጠና ዘጠኝ በመቶ የአካባቢው ህዝብ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነው።"

"ቢሆንስ..."

"ውሻ ነጻላ መሆኑን አታውቂም ማለት ነው?"

"ነው! አም በእስልምና ሃይማኖት መሠረት ውሻ ነጻላ ነው።"

"ውሸት ሆነን አጋዴንን ሰናቋርጥ ከስንት ትዝምዝም ማምለጥ እንዳለብን ገባሽ? አንዴ በደሴ ድንጋይ ወገር ቢንደለንስ?"

"ድ... ድመት ብንሆንስ ምንም ችግር እንደ ማያጋጥመን በምን እርግጠኛ ሆነህ?..."

Scanned by CamScanner

"ሰው ሆነንም እኮ ችግር አጋጥሞናል። ድመት ብንሆን ችግር አይገጥመንም ማለቴ አይደለም። ሰውሬ መሆን በራሱ ችግር ነው። ውሻ ከመሆን ግን ድመት መሆን ችግሩን ይቀንሰዋል። በተሳሱ ለመሸሹከሱነው የድመት መጠን አንስተኛ በመሆኑ ከጠላት ለመደበቅ ያመቻል።"

ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ እንደገና የአስማት ዋናቱን ትቀጥላለች። ትነሳተፋልች። ትስቃለች። ትቀጥላለች።

"...አክስ፣ ኮሞስ፣ አጠሮስ
ፓፓር፣ አንበር፣ ፓፓር
ሙራኤል፣ ሙራኤል፣ ሙራኤል
አሞሶስ፣ አሞሶስ፣ አሞሶስ፣
ዶርጋሞን፣ ዶርጋሞን፣ ዶርጋሞን
ሄሌሜት፣ ካሮን፣
ሄሌሜት፣ ፒጋሱን፣
ሄሌሜት፣ አራዮን
ጀምጀርታን፣ ጀምጀርታን፣ጀምጀርታን፣
አናሳሪምን፣ አናሳሪምን፣ አናሳሪምን፣
አውቃስ፣ አውቃስ፣ አውቃስ፣
መሲፈልጠን፣ መሲፈልጠን፣ መሲፈልጠን፣
አፀሊን፣ አፀሊን፣ አፀሊን፣
ሻላክርስ፣ ሻላክርስ፣ ሻላክርስ፣
አናስዮስ፣ አናስዮስ፣ አናስዮስ፣
ፓፓርስ፣ ፓፓርስ፣ ፓፓርስ፣
ሄናኤል፣ ሄናኤል፣ ሄናኤል
ሸድቃኤል፣ ሸድቃኤል፣ ሸድቃኤል፣
ጀማይኤል፣ ጀማይኤል፣ ጀማይኤል፣
ኢክስ፣ ኮማስ፣ አዘሮስ፣
ኢላማየጢንኪን፣ኢላማየጢንኪን፣

አሆን፣ አስማቱን በደጋገመችው ቁጥር መገዘፍዘፍ ጀመረች።

"ፈራሁ... ፈራሁ... ፈራሁ... ልቤን ኾነው" አለች ድምፅዋ እየተቆራረጠ።

"እጀ መታሰሩን ረሳሽ?... ሰው ሆነን ታስረናል። አውራ ሆነን ነፃ እንወጣለን። ...አናስዮስ አናስዮስ አናስዮስ አጥፍሙ ባረኩባት። "ፓፓርስ፣ ፓፓርስ፣ ፓፓርስ፣ አክስ፣ ዝያስ፣ አዘሮስ ድምጢሙ... አላሪምስ፣ አላሪምስ፣ አላሪምስ፣ ጠበቅ አድርገሽ በይው፣ ... ሰው ሆነን ታስረናል፣ አውራ ሆነን ነፃ እንወጣለን። ...ፓራሜስ፣ ታራሜስ፣ ሓራሜስ" ሳላስበው አየሙሉ ነበር።

እሷን ሳልለውጣት ራሴ ልለወየ ነው እንዴ?!... አይደረግም፣ አይሆንም፣

Scanned by CamScanner

፳፯

ከውጪ የብዙ ሰው ኮቴ ይሰማል። ሊቀሱን እየመጣ መሆን አለበት። አከተመልናል። ለአያን አስማቱን ስማስጠናት ካለኝ ንጉት የተነሳ ከጫፍ ጫፍ ደገምኩት። አያንም በሂደትና በድግግሞሽ ረቂቆቹን ታሳት ታዝለብላቸው ጀመራለች። መርበትብታ ግን እያየለ መጥቷል።

ለአያን መለወጥ ያለኝ ንጉት እየጨመረ ከመምጣቱ የተነሳ አስማቱን በከፍተኛ ተመስጦ መሉውን መድገሜ ትዝክል አልነበረም። ትቻት ላለመለወጥ ታገልኩ።

'አይደረግም'

አስማቱን ከመጨረሴ ዋሻው ይንቀጠቀጥ ጀመር። ንውፅውፅታ ...አሳተ ንምራ ይንጠው ይመስል ታስረን የተጣልንበት ዋሻ ድብልቅልቁ ወጣ። ከውጭ የብዙምቹ ሰምች ርምጃ ይበልጥ እየቀረበ ሲመጣ ይሰማኛል። የተፈጠረውን ትንግርት ሰማዬት ይሁን ወይም ሊቀሱን መስንውበን እንደሆን ባላውቅም መንበያዎቹ እየመጡ እንደሆነ ግን እርግጠኛ ነኝ።

"ፍጠኚ! ድንሚው!... አያን!.." ደንፋሁባት። "...ሻላርስ፣ ሻላርስ፣ ሻላርስ... አናስዮስ፣ አናስዮስ፣ አናስዮስ፣ ጀማጅኤል፣ ጀማጅኤል፣ ጀማጅኤል፣ አክስ፣ ካማስ፣ አክሮስ!...."

ከዚህ በኋላ የተፈጠረውን ሳላውቅ ከአለሴና ከመንፈሴ ተለያዩሁ። በማላውቀው ቅዠብርብር ባለ ዓለም ውስጥ ራሴን አገኘሁት። ብዙ አይነት ህብረ ቀለማት ያሳቸው የብርሃን ጨረሮች ብቻ ናቸው የሚታዩኝ። ቀጥሎ... ከዚህ ቀደም የማላውቃቸው ፍጡራን ይታዩኝ ጀመር። በልጅነቱ በዜተ መቅደስ ላይ ተስሎ ያየሁት ሰብድአት አይነት እንሰሳ ያለበት ዓለም ውስጥ ያለሁ መሰለኝ።

ሰብድአት ከወገቡ በላይ የሰው አካላዊ ቅርፅ ሲኖረው ከወገቡ በታች የእንስሳ ቅርፅ ያለው ቅጥ ያጣ ፍጡር ነው። ጅራቱ ምላሶቻቸው እንደ ሙስታ የረዘሙ አባቦች ናቸው። ይህ አይነት ፍጡር ያለበት ዓለም ውስጥ የገባሁ ይመስለኛል። መነሻ የሌለው አሳት ይጥመለመላል። ረጃጅሞቹን ተራሮች ሲዞር ቆይና ወደ እኔ እየተጥመለመለ መጣ። ቁመቶቻቸው ከተራሮች ሚፍ ለመድረስ የቀረው ሰዎች፣ እሳቱን ለማምለጥ ወደ እኔ አቅጣጫ ሲሮጡ ተመለከትኩ። የእኔ አካላዊ ቅርፅ ባይታየኝም ይህን የሚመሰክዘኝ የእሳት ሳንቃ ማምለጥ እንደማልችል በመገመት ተሰፋ ቆርጬ መወቅኩት። እሳቱ ተውጀምድም መጥቶ ከዋጠኝ በኋላ የማቲቃውሰው አንዳች ነገር አጣሁ።

Scanned by CamScanner

ሽኒ

ምን ያህል ጊዜ እንዳለፈ አላውቅም። ከድብልቅልቁ ዓለም ሰነቃ ራሴን ያገኘሁት በክባድ አውሎ ነፋስ ውስጥ ነው። አካባቢው ሁሉ የምዕዓት ቀን የደረሰበት መስሏል። የጥያት ድምፅ ሁሉ ይሰማኛል። ምንም ነገር ለማዬት አልቻልኩም። የተፈጠረውን ነገር ሙሉ በሙሉ ለመገንዘብ በርካታ ደቂቃዎች የፈጀውን አውሎ ነፋስ መጠበት ነበረብኝ።

እስከ ሰማዬ ሰማያት የሚጥመለመለው አውሎ ነፋስ አካባቢውን አተራምሶት ካለፈ በኋላ፣ ራሴን በአነስ ድመት አገኘሁት። የት ነው ያለሁት? ራሴን ጠየኩ።

ከአያን ጋር በታሰርኩበት ኮረብታ መንብ ላይ እንደሆንኩ ተገነዘብኩት። የወታደሮች ካምፕ የመሰለው ኮረብታ ከክባዱ አውሎ ነፋስ ተጠልለው ያመለጡት ወታደሮች ከወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ። አሁንም ወታሮቹ የሆነ የእግዚ ቡድን አባላት ይሁኑ ወይም የኢትዮጵያ ጦር አባላት መለዬት አዳገተኝ። ዘበጦቹ ውስጥ የተሰቀለ ሰንደቅ አላማ የለም።

'ከዋሻው እንዴት ወጣሁ?' ራሴን ጠየኩ። አካባቢውን እየቃኘሁ ራሴን መጠየቄን ቀጠልኩ። ወደ ኋላ

ሦራ ስመለከት ታስረንበት የነበረው ይሁን ወይም ሌላ ዋሻ በሩ ክፍት ሆኖ ተመለከትኩ።

'አያን የት ገባች? ሰቀሏት? በአውሎ ነፋሱ ውስጥ የሰማሁት የተኩስ ድምፅ አያንን የገደሉበት ጥይት ድምፅ ይሆን?' እንደ ሶብሩት ሠራሽ ሚሳዬል ተወንጭፌ ዋሻው ውስጥ ገባሁ።

አያን በዋሻው ውስጥ የለችም።

'እርሷም እንደኔ ወደ ድመት ተለውጣ ይሆን?' የዋሻው ግድግዳ አያንን ይተፋ ይመስል በሾሉት የድመት ጥፍሮቼ እየሚጨርኩ እንራ ጀመር። ድምፂ ራሴን ሳይቀር አስደንገጠኝ።

እንደገና ከዋሻው ተፈትልኬ ወጣሁና አካባቢውን እራውየበት ጀመር። ከሩቅ ካለ የቆንጥር ጥላ ሥር ከምችት ያሉ ወታደሮች ታዩኝ። እንደ አቦሸማኔ ተወንጭፌ ሄድኩ።

በእግራቸው ሥር ተሹሉክሉኬ ገባሁ።

'ያንት ያለህ!'

እመሣላቸው ወፍራም ግንድ ተጋድሟል። በግንዱ ላይ ደግሞ የአያን እንጉት አርፏል። የሚያብለጨልጭ ፋስ የያዘ ፈርጣማ ወንበዴ መፍለጫውን እንጉቷ ላይ ለማሳረፍ ከፊት ለፊቷ ተንቆርጥጦ የሚያናዝዛት አለቃውን ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ነው።

Scanned by CamScanner

፳፫

እያን ከሞት ጋር ተፋጣ ተመለከትኳት።

"አስማቱን ሞክረው! አስማቱን ሞክረው፡ የድመት ቋንቋዬን ታውቅልኝ ይመስል ጥቁር ጅራቱን እያወናጨፍኩ ተንጨረጨርኩ። ዓይኖቿን ፍለጋ፣ የወንበዴ ጫማ እንዳይረግጠኝ እየተጠነቀኩ ከወጪያ ወዲህ ዛበርኩ።

"ዋቲ ኖ ያሄዶው?" ከፊት ለፊቷ የተንቆረጠጠው ሰውዬ በጥያቄ ያጣድፋታል። እኔ እምጥ ልግባ ስምጥ ልግባ ባለመታወቂ ትተፋኝ ይመስል ወጥሮ ይሄታል። ፋሱ ካንገቷ በላይ ይብለጨለጫል።

"አላውቅም!" አሰች እያን አልሀ እየተናነቃት። ከመት ጋር ተፋጣ እንኳን ፍርሃት የሚባል ነገር አይታይባትም። "ዋት እንደሄደ አላውቅም! ዓይናቹ ታስረው ነበር። እንዴት አድርጌ የሄደበትን ላውቅ እችላለሁ? የቁሻውን በር የከፈታችሁት እናንተ ናችሁ።"

"ማሬት ገባ ታጻ?!"
"አላውቅም!"
"ሊባሱ ታጋኝቷል! አሳውሮ

እያን መልስ መስጠቷን አቆመች። ወደ ሌላ ፍጡር መለወጤን ሳትረዳ አልቀረችም።

"ሞክረው! አስማቱን ሞክረው፡ በድመት ድምጼ ቃተትኩ። ድንገት ከእያን ዓይናች ጋር የድመት ዓይናቼ ተገናኙ። አፈጠጠችብኝ...

በዚሁ ቅፅበት እያን አስማቱን ታገዘሰብለው ጀመር። ወደ ድመት መለወጤ ገብቷታል ማለት ነው።

"...ኢኮስ! ካሞስ! አዝሮስ!
ፓፓር! አንበር፣ ፓፓር!
ሙራኤል! ሙራኤል! ሙራኤል!
ጴርጋሞን! ጴርጋሞን! ጴርጋሞን!..." እያን ጮኸች። አስማቱን አልተሳሰተችም። ፈነጠዝኩ...

"ሚንዲና ሚታዎራው?" አለ ጠያቂዋ አስተርጓሚው ላይ ላይቀር አፈጠጠ። "ሚን ኪንኪ ና?"

ሁሉም በድንጋጤ እርስ በእርስ ከመተያየት በቀር መልስ የሰጠ የለም።

"...ሄሊሜት! ካፍን!
ሄሊሜት! ፒጋሱን!
ሄሊሜት! ኡራኖን!..." እያን ቀጠለች። እስከ አሁን አንዳችም የሳተችው የአስማት ቃል የለም። ጅራቱ እስኪሸሽ ድረስ እያወናጨፍኩት ተቁነጠነጥኩ።

"...ጅምጀርታን! ጀምጀርታን! ጀምጀርታን!
...አናሳራምን! አናሳራምን! አናሳራምን!..."

በድንገተኛ አውሎ ነፋስ አካባቢው ተናወጠ። ማንም ማንንም ለማዬት አልቻለም። የሚጀመሰመሰው አውሎ

Scanned by CamScanner

ነፋስ የአቧራ ምሰሶውን እስክ ሰማይ ተክሎ ይጥመሰመሰ ጀመር። የቆንጦር ዛፎች ሸሃቸውን እስኪጥሱ እስኪንቅቀሉ ድረስ ምድሩ ቀውጢ ሆነ።

ከአያሌ ደቂቃዎች በኋላ፣ ክላዱ አውሎ ነፋስ ሽቱ ኮረብታውን ዙሮ ሄደ። ቀስ በቀስ አነባቢው ሲጠፋ የወጻደቀው ወንበዴ ሁሉ አቧራውን እያራገፈና እያሰለ ከወጻደቀበት ተነሳ።

እኔ ከአንድ ቋጥኝ ጥግ ተወሽቂ ሳበቃ፣ መሬቱን በጥፍሬ ሰፍቼ በመያዝ በክላዱ አውሎ ነፋስ ከመወሰድ አምልጫለሁ።

ከተወሸቅኩበት ቋጥኝ ጥግ ወጥቼ አካባቢውን ቃኘሁ። አንዲት ነጭ ፀአዳ ድመት አቧራዋን እያራገፈች ቁቅ አለች። ከፍተኛ ጩኸት ካሰማች በኋላ እያጉረመረመች ወደ እኔ መጣች። አያን ወደ ድመትነት ተሰውጣ መሆን አለበት።

ወንበዴው ሁሉ ግራ በመጋባት ይንጫጫ ጀመር። አንደኔ ሊቀላ የንበረችው አያን ከግንዱ ላይ የለችም። በግንዱ ጥግ ወድቆ የሚታየው ሰው እያለች ሰብሳው የነበረው ልብኋ ነው።

ነጯ ውርዬ ወደ እኔ እንደደረሰች በድመትኛ ተንጫጭታን ከኮረብታው ወገብ ቁልቁል ተፈተለክን።

ሽዕ

ቁልቁል ኮረብታውን ተንደርድረን ወርደን ስናበቃ ከወንዙ ጫር ስንደርስ ድንገት ቀጥ አልን።

በውሃው መሰታውትነት ራሴን ተመለከትኩት። የጉን ልጥልጥ የመሰልኩ ጥቁር ድመት ሆኛለሁ። አስፈሪ ጥልማሞት ድመት። ረጃጅሞቹ አንቴና የመሰሉት የአፈ ጫር ጢሞች ሳይቀሩ ጥቂቁር ናቸው ጨለማ። የአጋጌን ሰቀቃ ያጠለሸኝ ይመስል፣ ወደ ጥልማሞትነት ተሰውሠ አርፌዋለሁ።

ከጎኔ የቆመችው ነጯ ድመት አያን ምሰልም በውሃው ውስጥ ብሯር ብሯር እያለ ይታየኛል። ሀሚ በረዶ የመሰለች ድመት ሆና ተሰውጣለች· ውተት የመሰለች ድመት።

ከሰውነት ክፀር አውርዶ፣ ወደ አውሬነት የቀየረን ችግር፣ ወርዶ በማያልቀው ወንዝ ውስጥ ገፀቶ ይፈስ ይመስል ያሳለፍነው መከራ ሁሉ አንድ በአንድ ተሳለፀኝ። ሁሉንም ችግር አስቧኩት። የአኔን የግሌን ችግር፣ የአጋጌንን ችግር፣ የሀገሬን ችግር... ከአውነት በታች የጣለንን ሰቀቃ ሁሉ ሳስበው፣ "Rivers of Babylon" የሚለውን የሺን መዝሙር መሰል እንጉርጉሮ አዚም አዚም አለኝ።

"By the rivers of Babylon, there
We sat down, yea we wept,
When we remembered Zion..."

Scanned by CamScanner

በግዕዝ ቋንቋ ላይቀር፣ በዳዊት መዝሙር ውስጥ ግጥሙን አውቀዋለሁ።

"ውስተ አፍላገ ባቢሎን ህየ ነበርን ወበከይነ
ለቦ ተዘክርናሃ ለጽዮን እምነ...
...በባቢሎን ወንዞች ማዶ ተቀምጠን
ጽዮንን ብናስብ እምርረን አለቀስን።"

ይህ ዜማ የሀገሬ ፍኖ ማሳያ ለሆነው ለአጋጄን የተዜመ ይመስለኛል።

"ውስተ አፍላገ ዋቢ ህዩ ነበርን ወበከይነ
ለቦ ተዘክርናሃ ለኢትዮጵያ እምነ
ወለ አጋጄን ስታይን...

... በዋቢ ወንዝ ማዶ፣ ተቀምጠን ሳለን
ኢትዮጵያን ብናስብ፣ እምርረን አለቀስን
አጋጄን ቁስላችን፣ እጅግ ጠዘጠዘን"

የሰው ሥጋ ለምደው ህጻናትን ወደበሉት ድመትነት የለወጠንን ፈተና የሚገልፀውን ግጥም ማዜም ብንችል እንዴት ጥሩ ነበር? በኩራን ወደሚበላው ድመት የለወጠን የሀገራችን ችግር እንደ ባቢሎን ግንብ የሚናድበት ቀን መቼ ነው?

እኔና አያን ከእንግዴህ በእኅለ ድመት ውስጥ የታፈንን ፍጡራን ነን። በኩራን ወደ ሚበላ ድመትነት ያስለወጠን ችግራችን መቼ አብቶ ወደ ሰውነት እንደምንለወጥ ማሰብ የጀመርነው ገና ከአሁኑ ነው። አውሬ መሆን ቀላል ነው- ሰው መሆን ግን አሳር ነው። በምን እንደተግባባን ሳይገባን እርስ በእርስ ተያየን።

፴

ሰው የሆንኩት ሰው ምን እንደሆነ ላላውቅ ነው። የሰው ልጅ አሁንም ድረስ ራሱን ፍለጋ ላይ ነው። ድመት መሆን ግን ራስን መሆንን አያጠያይቅም። ድመት ሲፈጠር ያው ድመት ሆኖ ነው የተፈጠረው። ሰው ግን ሙሉ ሰው ሆኖ አያፈጠርም። ሙሉ ሰው ለመሆን ወደ መጣበት አስኪመለስ ድረስ ይታትራል። ይህም ሆኖ ሙሉ ሰው ሆኖ የተቀበረ የለም። ድመት ወደ ዚህ ምድር ሲመጣ ግን ሙሉ ድመት ሆኖ ነው የሚመጣው። ሲሄድም ድመትነቱን ጠብቆ ነው። የሰው ልጅ እንደሰው መኖቱ እንደ እንስሳ ናር ወደመጣበት ሊመለስ ይችላል። እንዲያውም የብዙ ሰዎች እጣ ፈንታ ሰው ሆኖ መኖቱ እንደ እንስሳ ታይቶ ማለፍ ሆኗል።

ድመት ስለሆንኩ ብዙም ስለድመት ማውቅ አያጠበቅብኝም ነበር። ስለ ድመት ለማውቅ ጉጉት ያደረብኝ የሰውነት አመሌ ገፋፍቶኝ ነው። ሆኖም ድመትን የማውቃት ውሻ እያለሁ ነው። የሴቶች ጠባይ ወኪል ነበረች- ድመት። እያለሁ ሰው እያለሁ አምርሬ ሴቶችን በመኮላቴ ምክንያት ወደ ውሻነት የተለወጥኩ ሰሞን በድመት መሰየጬው ድመት መስለው ይታዩኝ ነበር። ድመት ወተት ካላያት ከማንም ሞን ላይ ፊጥ

Scanned by CamScanner

እንደምትል ሴትም ካሰው ጋር መንከውከው ጠባይዋ ነው- አልነበር፣ ውሻ እያለሁ። ሁሉንም ሴት ፈጣሪቀ በድመት መመሰል ግን ትክክል አልነበረም። ሁሉንም ወንድ ፈጣሪልቀ በውሻ መመሰልም አይቻልም። እንደ ድመት ባዩበት ጅራቱን የሚቆላ ወንድም ሞልቷል። ዓለማችን በሰው ኑባሬ ውስጥ ያለን ሰው ጠባዩን ያውሬ እንዲያደርግ ትገፋፋለች። ከዚህ አዙሪት ራሳቸውን ጠብቀው ለመኖር የታደሉት እጅግ ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

ወደ ድመትነት የሚለውጠውን አስማት ባጠናሁበት ወቅት እንደገና ወደ ሰውነት የሚመልሰውን ድግምት ያላጠናሁት አንድ ቀን ድመት እሆናለሁ ብዬ አስቤ ስለማላውቅ ነው። ሰው ሆኖ ተፈጥሮ ሳለ ድንገት ወደ አውሬነት የሚቀይር ሁናቴ የገጠመው ሰው ሞልቷል። ይሆን እንጂ ከአውሬነቱ አምልጦ ወደ ሰውነቱ ለመመለስ አይሞክርም፣ በአራዊት መንጋ ውስጥ ሰው ሆኖ ለመገኘት መሞከር ትርፉ መበላት እንደሆነ ስለሚገባው፣ የገጠደ አራዊት ኑባሬውን ይቀጥላል። የሚያፈነግጡትና ከኑባሬ አራዊት የሚያመልጡት እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው።

ስለ ድመት የማውቀው እጅግ ጥቂት ነው። ይህንኑም ጥቂት እውቀት የቀሰምኩት ሰው ሳለሁ ወደ ድመትነት የሚቀይረውን አስማት ባጠናሁበት ወቅት ነው። በዛ ወቅት ወደ ድመትነት አለመለወጤ እድለኛነቴን ያሳያል። ቢሆንም እንደ ገና ወደ ሰው የሚለውጠው ጥቅል እጀ ላይ ነበር። አሁን ሰማንያኛት ያልሞከርኩት ሰው ሆኜ ለመቀጠል እድልና ጊዜ እንዳለኝ በመገመቴ

ነበር። ትክክል አልነበርኩም። ዛሬ እንጂ ነገ በእጀ አለመሆኑን ተረድቻለሁ።

አሁን ከድመትነቴ ወደ ሰውነቴ የሚመልሰኝ አስማት የሚገኘው በመቶ የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን ርቆ ነው- አዲስ አበባ። ከኢጋዴን አዲስ አበባ ድረስ በድመትነቴ የመቀጠል ግዴታ አለብኝ። በድመት ህሳቤ፣ በድመት ኑባሬ፣ በድመት ቀናና እና ደግማ ውድማ ሰውድማ መሻከር ግዴታዬ ነው። ምግቤ እንደራ በወፐ ሳይሆን የገደል አይጥ ነው። ጉዳይ ለማስፈፀም ቢሮ ሰቢር መሻራ ቀርቶ፣ የዕለት እንደራዬ በሹል ጥፍሬ ላይ ሆኗል። ጥፍራ እስካለች ድረስ ደጅ መፅናት አይጠበቅብኝም። ቢሮዬ የኢጋዴን ቢረሃ ሆኗል። አለቃ የለኝም። ድመት ነኝ። አይጥም አይጥ ነው። አይጥ በመሆኑ ሊኮራ ይችላል። አይጥ ለመያዝ ምንም አይነት የብቃት ማረጋገጫ ማውጣት አያስፈልገም። የብቃት ማረጋገጫዎቼ በመዳፌ ላይ የተቀለመሙት የጣ ጥፍሮቼ ናቸው። አድናቂዬ የማለም መብቴን ስማገም አልጠይቅም። የማምለጥ መብቴ ደግሞ የአደው ነው - አትም ካለው። ኪላ ላይ እንዲያዝ ስልክ አይደወልም።

ከዚህ በኋላ ባልንደራዬ ሴቷ አፍራታ ሳትሆን ድመቷ አያን ናት። ውርዬ የበረሃ ጓዴ፣ ነጭ ጀራቷን እንደ መኪና ዋይፐር እያወናወነች ካጠጪ ቆማ ሽቅብ ወደ ተራራው እየተመለከተች ነው። የጉሀ መስመራችን እየነደፈች መሆን አለበት። ሰው እያለች የምታውቀው የኢጋዴን ምድር ድመት ሆና ሊጠፋባት አይችልም። ኧረ ለመሆኑ ዮት ነን? ወደ አርሷ ዶሬ ተቀለጨለጭኩ። እየቸኮና ሽቅብ ወደ ጣቱ ተረተለከች።

"ሚያው" እያልኩ ተከተልኳት።

Scanned by CamScanner

ሽፅ

የተራራውን ጫፍ ወጥተን እናቱ ላይ ቆምንና ቁልቁል ተመለከትን የኢላላ ኮረብታዎች የምድር ቡጉር መስለው ከታች ይታያሉ። የንጻጅ ፍሊጋ የሚጣጣፍባቸው አካቢዎች እነዚህ መሆናቸውን እያን ነገረችኝ። ውርዬ እያን የምታወራኝ በሰው ልጅ ቋንቋ አይደለም። እኔም ውሮ ዶክተር ጂጂሞስ ዶራ የምረጻት በእፈ ሰብ ቋንቋ አይደለም። የምንጋባባው "በቱሊፓቲ" ነው። በውስጧ የሚመላለሰውን ሀሳብ ለማምቅ የቻልኩት ወደ ድመት ከተለወጠችና ከተለወየኩ በኋላ ነው። የሰው ልጅ በቋንቋው እንኳ አይግባም፣ ሰው እያለሁ ይህን አውቃለሁ። የሰው ልጅ ተነጋግሮ፣ ተነታርኮ፣ ተከራክሮና ተነጣጥሎ ሳይግባባ ይለያያል። አንዱ የአንዱን ሀሳብ አይረዳውም።

ምድር ላይ ያለው ቋንቋ መብዛት የሚያሳዩው ይህንኑ ነው። ሊታውኑት ቅዱስ መጽሐፍን አጣትሰው ቋንቋ እንዴት እንደተቀያየረ ያስረዳሉ። በዘፍጥረት መጽሐፍ መሠረት ሲያብራሩት፣ ምድር ሁሉ ባንድ ቋንቋ ነበረች። ነዝ ግን በሰናዖር ምድር የአማ ልጆች ከተማ ይገነባሉ። ፈጣሪም እንደ ተፈታተኑት ሲያውቅ ይወርድና ቋንቋቸውን ይደባልቀዋል። በዚህም ምክንያት የሰናዖር ምድር ባቢሎን ተብሏል። ባቢሎን የመለያየት መገለጫ ሆኑ የመቢታቸን ፍቺ ሆነ። ባቢሎን፣ የመለያየቱ መንፈስ ሀገሬ ላይ ዛሬም ድረስ እየፈነጨባት ነው። ዘመናዊ ምሁራን ደግሞ የሰውን

ልጅ ቋንቋ መለያየት ከጂኦግራፊ መራራቅ ጋር ያያይዙታል።

ይሁን እንጂ የሰው ልጅ አሁንም ባቢሎን ውስጥ ነው- አንድ ቋንቋ እየተናገረም አይግባም። ባልና ሚስት አንድ ላይ ተቃቅፈው ቋንቋቸው ለየቅል ነው- አሊጋቸው ባቢሎን ነው። እኔና አያን ግን ለመግባባት ቋንቋ አያስፈልገንም። በቱሊፓቲ ሀሳቤን ልትም አድርጋ ታውቀዋለች። እኔም እንደዛው።

"ቱሊፓቲ" ስድስተኛው የስሜት ህዋስ ነው። ይህ ፀጋ ለሰው ልጅ በሙሉ አልተሰጠም። እንኳን ስድስተኛውን ስሜት አምስቱን ህዋሳቱን እንኳ በትክክል የማይጠቀም ሰው ሞልቷል። የሰው ልጅ አካባቢውን ሁሉ በአምስቱ አካላዊ ህዋሳቱ ዳብሶ፣ ዳሶና ተጨላምሶ ስመረጻት ይሞክራል።

ስድስተኛው ስሜት ወይም ቱሊፓቲ ግን ከአምስቱ ህዋሳት ተግባር በላይ የሆነና ልዩ በሆነ ስውር ኃይል ሊላው አእምሮ ምን እያሰበ እንደሆነ የመረጻት ከሱት ነው። ርቀት ሳይገድበው ያሰምንም መሣሪያ የማየት ጥበብ ደግሞ "ክሊርቪውናንስ" ይባላል።

"የክሊርቪውናንስ" ችሎታ ያለው ፍጡር ከአርሱ በብዙ ሺህ ማይል ርቆ ያለን ድርጊት በዓይናቹ ያዬ በጆሮው የሰማ ያህል ይረጻዋል። ይህ ችሎታ ያላቸው ሰዎች በምድር ላይ ተከስተው እንደነበር ፓራሳይኮሎጂስቶች በጥናት ደርሰውበታል። በትንሹም ቢሆን ይህ ተሰጥኦ በእጅጉ በሚዋደዱና በሚፋቀሩ ሰዎች መካከል መኖሩ ተደርሶበታል። ጉዞ ፍቅር ያላቸው ሰዎች ሳይነጋገሩ ይግባባሉ። በተለያዩ ቦታ ሆነው እንኳ ማን ምን እያደረገ

Scanned by CamScanner

እንደሆነች ችግር ደርሶበት እንደሆነ ሀሊና ተብሉ በሚገለፀው አካላቸው ላይ በግዘፍ የማይገኝ አካላቸው ይረዱታል። በእናትና በልጅ መካከልም ይህ ስሜት እንዳለ ተደርሶበታል።

ይህ የሚያሳየው ግርግርና ኳኳታ ባንኮታኮተው ዓለም ውስጥ የጠፋው የሰው ልጅ ብዙ ያልተጠቀመባቸው ችሎታዎች እንደነበሩት ነው። አሁን ግን እንኳን ስድስተኛ ሀዋሱን ይቅርና አምስቱን ሀዋሳቱን እንኳ መጠቀም የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱ በግልፅ የሚታይ ነው። በተመስጦ ውስጥ ያሉ በየገዳሙ ያሉ አባቶች፣ "ይህ ታይቶኛል፣ እንዲህ ሊሆን ነው" እያሉ የሚናገሩት በትዝት ተተርጎምባቸዋል። ወይም እፀ ሰጠጢራ ነፍተው ነው ሊባሉም ይችላሉ ሀሸሾሞች።

እኔና ውርዬ ግን ሀሸሸም ሆነ ስጠጢራ ሰንነፋ ይኸው እየተግባባን ነው። ሳንነጋገር እንግባባለን። አንድም ቃል ሳንለዋወጥ ሀሳቧን መረዳት ችያለሁ። እርሷም እንደዛው። ማን ያውቃል? ከሰው ልጅ በልጠንም ሊሆን ይችላል። ጠማና ዝንጀሮን እንዳልሰለጠኑ የሚቆጥረው ስልጡን ነኝ ባይ ፍጡር ጠማና ዝንጀሮ እየሳቀበት መሆኑን ቢረዳ ናሮ በራሱ ያፍር ነበር።

ሽለቆዎችን እያቋረጥን፣ ኮረብቶችን እየወጣንና እየወረድን የንጻጅ ቁፋሮ ወደ ሚሟሟፍበት የኢሳላ ምድር ስንገሠ አንድ ሀሳብ በድመት አእምሮዬ ውስጥ ተሰነቀረ። በድንጋጤ ከው ብዬ ቆምኩ። ውርዬ አያንም ቀጥ አለች። የመጣብኝ ሀሳብ አርሷም ጋር ከመቅፅበት ነበር የደረሰው። አንዱ ድመት መንገድ ላይ እግሩቶ ቢያስረግፁትስ?

ያንት ያለሀ በርሬ ዛጀ አጠገቧ ቆምኩ።

ሽፂ

ሰው እያለሁ ስለድመት ብዙ አለማዎቁ ይበልጥ ስጋቴን ጨመረው። ሰው እያለሁ ይህ ወቅት የድመቶች የሥሪያ ወቅት ይሁን አይሁን አላውቅም። ጭራሽ ድመቶች የሥሪያ ወቅት ይኑራቸው አይኑራቸው አላውቅም።

ሰው እያለሁ ስለ ድመቶች ከማውቀው ውስጥ ከሰባ በላይ የድመት ዝርያ አይነት መኖሩ ይገኝበታል። የሰው አመሌ ገፋፍቶኝ ስለድመት ዘርና፣ እኔና አያንም ከየትኛው የድመት ዘር እንደምንመደብ አስብ ጀመር።

እንደሰው ልጅ አንዱ የድመት ዘር ከሌላው የድመት ዘር እበልጣለሁ የሚል አብረት ይኑረው፣ ወይም አንሳለሁ የሚል የበታችንት ዝቅጠት ይኑርበት አላውቅም። ይሁን እንጂ ሁለቱም በሽታ ነው። አብረት የንበረው የበላይንት ስሜትንና፣ ዝቅጠት የቀደረው የበታችንት ስሜትን ያህል ደዌ የለም። በሁለቱ መሃል ያለው መመሻሸት የሰውን ልጅ ቁልቁል ሲንፋ የኖረ ሀቅ ነው። የበታቹም የበላይ የሆነ ጊዜ በቀሱ አይቻልም። በድመትስ እንዲህ አይነት የዘር ዛር ይኖር ይሆን?

Scanned by CamScanner

.... ከድመት መንጋ ውስጥ ካልተቀላቀልኩ በቀር ይህን ጉዳይ ላውቅ አልችልም። መሆን የማምቅ ማህሰት ነው። ሰው እያለሁ፣ ፈሊስ ካተስ ተብለው የተሰየት የቤት ድመቶች፣ ከሌሎች ፈሊንስ ተብለው ከሚጠሩት ነገዶቻቸው የሚለዩት ከሰው ልጅ በቀላሉ መላመዳቸው ብቻ ይመስለኝ ነበር። የሰው ልጅ ፀረ አይጥ መሣሪያመቼ አድርጎ በወጥመድና በመርዝ ፋንታ ይጠቀማቸዋል።

ድመቶች የተሻለ የማሽተት አቅምና ዝቅተኛ የሆነ ቀለምን የመለየት ችሎታ አላቸው (ይቅርታ አለን)። ድመት ከሆንኩ በኋላ እንደሰው ማሰቤን ማቆም አለብኝ። ከሆኑ ወዲያ ሆኑ ነው። "ሚያው" የሚለው ቋንቋችን በተለያዩ ድምፀት እልፍ ትርጉም አለው። ከፍተኛ የሆነ የፐፐር ችሎታ አለን። ተቀናቃኝን አሳዶ ቅታውን የማጥፋት ኃይል። ይህን የድመቶችን ችሎታ ሳስብ ድንጋጤ ወረረኝ።

ዘራቸውን የበረዘውን የሰው ነፍስ፣ ከጣነበት የድመት አህል ለማባረር ከፍተኛ የሆነ ሞፐርጅ አዋጅ ሊያወጁብን ይችላሉ። ምናልባት እኛ በአህለ ድመት ውስጥ የገባን ርኩሳን-መናፍስት ልንመሰላቸው ይችላል። ...መጠንቀቅ ነው። ከድመት መንጋ መቀላቀል የለብንም።

ድመቶች ከፍተኛ የማሽተት አቅማቸውን ተጠቅመው፣ የሰው ርኩስ መንፈስ ድመትነታቸውን ለማቀሸሽ እንደገባ ከተረዱ፣ ሞፐርጂንግ አዋጅ ለመላው የድመት ዘር ያውጁሉ- ልክ አንድ ፓዝ ፓርቲ በተቃዋሚው ላይ የ "አላደህ በለው" አዋጅ እንደ ሚያውጀው። የድመት ፐፐር ደግሞ በጨበጣ ውጊያ ነው- እጅ በእጅ። እኛ እንደሆንን ልምዱ የለንም።

የፐፐርጂ አዋጅ ሳይነገር አዲስ አበባ ንፁቱን ወደ ሰውነታችን መመለስ አለብን። የምናውቀው የሰው ልጅ "ፐፐር" ይሻል ይሆናል።

የሰው ልጅ ፐፐር ሲታወጀ በስለላ ሞያ የተካኑ የሥርዓቱ ሰዎች መንደር ለመንደር አሰላ ያካሂዳሉ፣ በሾፈው ያደፍጣሉ፣ አብረው ከተቃዋሚ ጋር ፀርሞቶ ፈጠሰው ካቲካላ ይጎነጫሉ፣ ወሬ ያውጣሳሉ። የሥርዓቱ ተቃዋሚ መሆኑን ካረጋገጡ ጀርባውን አዋንተው "ፐፐር" ያውጁበታል ፣የአሳደህ በለው ፐፐር። ኢትዮጵያ ውስጥ አስርቤቶችን ያጣበቡት አስረኞች ማንቆርቆሪያ የለረቀ ሌቦች ብቻ ያልሆኑት ለዚህ ነው። የፐፐር ሰለባ የሆኑት የፓለቲካ ሰዎች፣ ተቃዋሚዎች፣ ጋዜጠኞችና ደራሲዎን ናቸው።

የድመት ፐፐር (ፀርን የማዋፋት ዘመቻ) ከዚህ የሚለየው ፐፐር የሚታወጀበት ድመት ያለበት ቦታ በቴሌፖቲ መታወቁ ነው። የዘመናችን ፐፐሮች ግን ተቃራኒያቸውን የሚያደርሱበት በቴሌኮምኒኬሽ በኩል ነው። ልዩነቱ ፍጥነቱ ብቻ ነው። ድመት ቴሌፖቲን ተጠቅሞ የጨዋታ ውሂ ሲሰነዝርብህ፣ መንግሥት ቴሌኮሚኒኬሽንን ተጠቅሞ ካለህበት ከች ይልና ከቸከቸ ከርፍሌ ያልከሃል።

እኔና ውርዬ አያን፣ ለረጅም ሰዓት ቆመን በዚህ ሀሳብ ከናወዘን በኋላ በሞንቶት ተወየሬን ማተረምም ጀመርን።

"ጀሪ ዝም በይ ይደርሱብናል" አልኩ አያን በከፍተኛ ድምፅ ስታተረመርም ጊዜ። "ነዘርሽ አንዱም ንግግራችን በቴሌፖቲ ተሰሰ።

Scanned by CamScanner

ወደናዝሬቶች ድመትነት ተሰውጣ ይሆንን፡ ስል በውስጤ ከማሰቤ ወዲያው ሀሳቤን ቀሰብ አድርጋ፣

"እንቫልኝ!" አለች- አሁንም እየተቁነጠነጠች። "ስሥሪያ ወደ ደረሰች ድመትነት መሰለኝ የተቀየርኩት- ለካ መሰለኝ ድምጼ የጎረነነው!...."

እየናዝሬት ከሆነ አንዱ የቴሌፓቲ መልእክቱ የደረሰው የጹር ድመት መጥቶ ሊሰራት ይችላል።

'ያንት ያለህ!

በሁለቱ የፐርፎና የሥሪያ ስጋቶች ተወጥረን ሩጫችን እናስነካው ጀመር።

ሽቦ

በሁለቱ ሥጋቶች ተወጥረን ኢላላ ደረስን። ኢላላ የጎደደ ቁፋሮ የሚሟሟናበት የእጋዴን በረሃ ክፍል ነው። ቻይናዎች ከወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ። ኢትዮጵያውያኑ የደረቁ ቅጠሉች መሰለው ይንጠራወዛሉ። የቻይናዎቹን ጨዝት ከመጤፍ አይቆጥሩትም። እነዛዉን የኢትዮጵያ ጦር ነፍጡን ሰንሞ ይቆጣጠራል። ጹር ገደሉ መሣሪያ ባቀባበለ ወታደር ታጥሯል። ስወታደሩ እኔና አያን ተራ ድመቶች እንጂ ስምች አይደለንም።

ተሹሉክሉክን ወደ ብሉትቹ ተጠጋን። ነጻዊ ወጥታል ወይስ ዝም ብሉ ወሬ ብቻ ነው?... ከብሉክ ብሉክ ቡጥንቃቂ ተራወጥን። ሰምች በዚህ አካባቢ የሚራመዱት በከፍተኛ ጥንቃቂ ነው። የተሳጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ ስቦ ሊያፈርጣቸው ይችላል። እኛም ወት ደርሶን ይሁን ወይም ሰው እንደነበርን ትዝ ብሉን የማናውቀው ሁኔታ ስንራመድ ቡጥንቃቂ ነው።

እዚህ ግንም ሰማይ ሰማይ አያይም። ለነገሩ የእጋዴንን ሰማይ ማዬት አያስፈልግም፣ ዘወትር ያው ነው- ጥርት ያለ ቢድመት ምላስ የተሳለ ሳሃን የመሰለ ሰማይ። እጋዴን

Scanned by CamScanner

ምድሩም ተመሳሳይ ነው- አሸዋና እሾህ። የቆንጥር፣ የአጣንና የሰው አጥንት እሾህ።

አጋዴን ምድሩና ሰማዩ ሳይሆን ከርሰ ምድሩ ነው ለምለም። እዚህ "አባባዬሁሽ" ሊዘፈን አይችልም- "ቆፍሬ አየሁሽ" የሚል ዜፈን ሊዘጋጅለት ይገባል። አጋዴን እንደ በሰሰ ላዩ እሾህ ውስጡ ወተት ነው። አጋዴን ላዩ ግለት ውስጡ ዘይት ነው። ሊሳለ ደግሞ ብዙ "ቆፍሬ አየሁሽ" የተዜፈነላቸው ብሱኮች የተሠሩባት የንጻጅ ገደሉች ማህፀን ናት። እንዳንዶቹ በብዙ ጥረት ተቆፍረው ሲያበቁ፣ ከው ያሉ ተስፋ ቢስ ገደሉች ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ግን የተፈጥሮ ጋዝ አረፋ የሚደፍቁ ጉድጓዶች ናቸው።

የንጻጅ ጠበል የፈለቀላቸው ብሱኮች ሠራተኞችና "ቆፍሬ አየሁሽ" ዘፍነው አጨብጭበው የቀሩ ተስፈኞች፣ አረግመሳቸው እንኳ ሰየቅል ነው። እኔና አያን ይህን አየታዘብን ከአንዱ ብሱክ ወደ ሌላው በመራመጥ፣ የሚበላ ነር ፍለጋ ኳተንን። ሰው ብንሆን ናሮ ልናገኘው የማንችለውን ምከጢርም አስኪበቃን በመቃረም ላይ ነን። ብሱክ ስሞነት ጥግ አንድ ወደል አይጥ ሰጥቷት አመለጠን። ገና ልምድ አስማጸበራችን ብቻ ሳይሆን የሰው አምሮአችን እንደ አርኩስ ስለቆጠረው ይሆናል አይጡ እንዲያመልጥ ያደረገው።

ቁጥሩን ወሳለወቅሁት ብሱክ ሄድንና ወደ መጠለያው ሥፍራ ገባን። ከምሳ በኋላ ነበር የደረስነው። ሠራተኞቹ በልተው ጨርሰው ያወራሉ። መራቱን ቆፍረው ፍሪጅ ሠርተዋል። ከውስጡ በፐላስቲክ የታሸገ ውሃ እያወጡ ሲዘው ገረመን። መቀቱ በሻፖኒ ብቻ እንዲቀመጡ አስገድዷቸዋል። አርቃናቸውን አስመቀመጣቸውም የሰውነት ክብራቸው አስገድዷቸው ነው።

እኔና አያን የበሱባቸው ሰሀኖችን ማሰስ ጀመርን። እንደ ድመት የላሷቸው ይመስል፣ ሰሃኖቻቸው እንደ አጋዴን ሰማይ ክው ያሉ ናቸው። ተስፋ ቆርጠን ልንመለስ ስንል የአንደኛው ወሣደር ወሬ ጀሮዎቻችን ቆንጥጦ አስቀረን። ስለ ነጻጅ ነው ወሬው።

እዚህ ወሬዉ ሁሉ ጋዝ ጋዝ ይሸታል። ከዚህ ቀደም ሰው ባንሆን ናሮ ለድመቶቹ ለእኔና ለአያን፣ ከነጻጅ ድፍድፍ መገኘት ይልቅ ሰበር ዜና የሚሆንብን የሰባራ ገል ወተት ነበር።

"ይህ ነጻጅ የወጣ ቀን..." ሲል ነበር ወሬውን የጀመረው ወሣደሩ- በፐላስቲክ የታሸገ ውሃውን አንቀርቀር ሲያበቃ። "ፍጅት ነው መቼም... ፍጅት!"

"እታሚርት ባክህ" አለው ሌላኛው እጁን አወናጭፎ ሲያበቃ። "...እንተ ሁልጊዜም የምታስዉ ሁሉ አወንታዊ አይደለም። ምሀረቱ ሳይሆን መጎቱ ነው ሚታይህ!"

"ምናለ በለኝ የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በእርሱ ባይባላ!"

"ዘም በል ባክህ!"

"ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና አንድነት በሌለበት ሀገር፣ እንዲህ አይነቱ የከርሰ ምድር ሃብት በገፍ ከወጣ የማጭት መንስኤ መሆኑ የግይቀር ነው። በሌላ በኩል የአጋዴን ነገ አውጪ ግንባሮች ከዚህ ምድር ሀብት ሲዛቅ እጃቸውን አጣጥፈው አይመለከቱም።"

"ዘም በል!... ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም. ሲባል አልሰማህም?!"

Scanned by CamScanner

"ከዚህ ቀደምም ነጻ አውጭዎቹ ሲያስጠነቅቁ ቆይተዋል።" ቀጠለ የመጀመሪያው። "ደማችን ላያፈስ ነጻቹን አይፈሰም፣ ሲሉ ዝተዋል። ነፃ አውጪዎቹ ነጻቹን በነጻ አይሰጡም!..."

"ደም ሲፈስበት የኖረ ምድር ነው" አለ ሁለተኛው ቁጣ ብሎ።

"አሁንም ይቀጥላል።"

"ያምሃል እንዴ አንተ ሰው?!"

"ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በሌለበት ሀገር የግጭት መንስኤው የሚሆነው ያው ሃብት ነው።"

"ነጻቹም ይወጣል! ደሙም ይፈሳል!..." አለ ሶስተኛው ሰው በዝምታ ሲያደምጥ ቆይቶ። "ኢትዮጵያ የምድሯ ሀብት ተጠቃሚ መሆን አለባት። በልመና እስከመቼ ትቀጥላለች?!... ነጻቹ ይውጣ፣ ይዋጣልን። ይህ ምድር ከየጎኑ ጀምሮ አባቶቻችን ደማቸውን ሲያፈሰበት የኖረ ነው። ደም መበጣቱ ይብቃዋል። ይትፋው!... በነጻ መልኩ የአባቶቻችንን ደም ይትፋው። ካሳችን ይሄ ብቻ ነው።"

"ከርከራችን የገባህ አልመሰለኝም..." አለ የመጀመሪያው።

"ገብቶኛል!" ሰከተኛው ውሃ ተጎንጭቶ መለሰ። "ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በሌለበት ሀገር፣ ሀብት በራሱ የግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል፣ የሚለውን ሀሳብህን ሰምቻለሁ። የትኛው መቅደም እንዳለበት ግልፅ አይደልም። ፍትሐ ነው ሀብቱ መቅደም ያለበት? ፍትፍት ነው ፍትህ የሚቀድመው? ይህች ሀገር ፍትህ የተጠማች እንደሆነች የአደባባይ ምስጢር ነው። ሆኖም... ፍትህን በሀብት ለማምጣት መሞከር አደጋ አለው። ሀብቱ ጥንትም በዘርሰ

ምድራችን ውስጥ እንዳለ ይታወቃል። ከፍትሐም ከሀብቱም ለመቅደስ ግን መስዋዕትነት የማይቅር ነገር ነው። ለሁለቱም በቁርጠኝነት መፋለም ግድ ይላል። ሀገራችን ጥቅም ላይ ያልዋለ የከርሰ ምድር ሀብት ብቻ አይደለም ያላት። ሀብቷ ጥቅም ላይ ያልዋሰው መቶ ሚሊዮን ህዝብ ጭምር ነው። የሰው ሀብታችንን በአደት ከመቁጠር በማስተዋል ሀብታችን አውጥተን መጠቀም አለብን።"

"ብጥብጡን ለማን ተውከው?" አለ አሁንም የመጀመሪያው።

"ብጥብጡ ከኢፍትሃዊ የሃብት ክፍፍሉ የሚመጣ ነው። አይደለም እንዴ? ለፍትሁም መፋለም ይጠይቃል። ኮንፍሊክት እኮ..."

"በአማርኛ አውራ!... እንጂት ጫቡም ያዝኩ ብለህ አትበጥብጠን!"

"...ግጭትን በአግባቡ ማኔጀ የሚያደርግ መሪ ካለ ግጭት በራሱ ለማህበረሰብ እድገት ጠቃሚ ነው። ግጭት ከራስ ይጀምራል። ከራስህ ጋር በቀን ሽህ ጊዜ ትጋጫለህ። ግጥትህን በአወንታዊ መልኩ ካልተረጎምከው ራስህን ልትሰቅል ትችላለህ። በሰዎች መካከል የሚከሰተው ግጭት መቅኖና ቀዝቃዛ ተብሎ ሊከፈል ይችላል። መቅ ግጭት በጠንካራ ስሜትና በሚታይ ውጥረት ሲገለፅ፣ ቀዝቃዛው ግን በታመቀ ዝምታና በማይታይ ቁጭት ይገለፃል። ይህኛው ነው አደገኛው። እምቁ ዝምታ የፈንዳለት ግጭቱን ማብረድ ከባድ ነው። ይህን ለመቆጣጠር በአመራር ጥበብ የተካነ መሪ ያስፈልጋል።"

"እሱ ከየት ይመጣል?"

Scanned by CamScanner

"... `when the student is ready the master will arrive` ...ሲባል አልሰማህም?"

"እትዬጥዬጠን ጣማርኛ አውራ።"

"ብጥብጥና ግጭት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ግጭት ውስጥ ጥቅም አለ። ብጥብጥ የሚመጣው ግጭቱን በአግባቡ ማስተናገድ ካልቻልክ ነው። የጎረጥ እየተጫነ ዘለለም በድህነት ከምንኖር የክርስ ምድር ሃብታችን በፍትሐዊ መልኩ ለመጠቀም እንጋጭ... ሁ ኪርስ"

"ኧረ አባክህ!"
"ያበጠው ይፈንዳ ያመጣል ክፉ እኛ"

"ሄይ ወሪያ ሰዓት ደርሷል ወደ ሥራ_" አለ አንድ ሰው ወደ መጠለያቸው እየገቡ። ሌሎቹም ተከራካሪዎች ጭጭ ምጭጭ ብለው መስስ አሉ።

ሸዕ

ብሱክ ስድስት አጠንብ በሚገኝ የቆሻሻ ክምር ሥር አንድ የወደቀ አጥንት አግኝተን አፈጠጥንበት። በሁለታችንም ውስጥ አጉሱ የሰውነት አመል እየተመላለሰ እንድንጠየፍ ሊያደርገን ሞከረ። በሞሸለቱን የረሃብ ስሜትና ባቅለሸለሸን ጠባይ መነከል ሆነን ክብ ዓይናቻችን አንቀዋለልንበት።

አጥንቱ ረዥም ነው። የግመል ጉልጥምት ሊሆን ይችላል። ጥቂት ፍትፋቂ አለው እንጂ ለማነዶነት ከሚውል ፍልጥ አይለይም፣ ተፈቅፍቋል። የቆዩ ግን አይደለም። ጥቂት ገጽቦች ሰፍረውቢታል። ቢቀርብን ይሻላል። ትተነው እንደገና ወደ ብሱክ ስድስት መጠለያ እመራን።

ብሱክ ስድስት እስክ አርባ የሚደርሱ መሃደሮች ይኖሩቢታል። ነጻጁ መሃንቱ ከተረጋገጠ ወዲህ ሸርጉዱ ይወጣ እንጂ የጥጋብ ምልክት አይታይም። ጥጋብ ቢኖር ኖሮ ትርፍራፊ ይወጣ ነበር። ሃሰሳ ሥጋችን ተጠሉ።

የብሱክ ስድስትን ጥጋጥግ ስናስስ ቆይተን በቆራጥነት ወደ ግብስያ ቤቱ ዘው ብለን ገባን። ከመግቢታችን ነበር በአንድ መዘናዘፊያ ውስጥ የተቆሰለ ሥጋ የተመለከትነው። አያን ሚያው፣ እንጻትል ፀለያኑ። ድምፅ ሳናሰማ አንዱን ሙጻ ሥጋ ይዘን ከዚህ ካምፕ መሸሽ አለብን።

አያን ሚያው ሰማስት ጊዜ አልነበራትም። ከአንዱ ሙጻ ሥጋ ላይ ተወርውራ አረፈችበት። የሽንጥ ሥጋ መሆን

Scanned by CamScanner

አለበት። እንደስዞርና፣ እየጎተተችው ሥትወጣ አንዱ ሻኛ ተመለከታት።

"ወስደችው! ወስደችው!" ሁለት ቢላዋ አከታትሉ መረመረባት። አያን ዞራ አላዩችም ቁልቁለቱ አካባቢ ወደ ሚገኘው ጥሻ ተፈተለከች። እኔ ባዶ አፌን ተከተልኳት።

ሼፉ ተስፋ ቆርጦ እየተራገመ ሲመለስ መንገድ ላይ ተገጣጠምን።

"አሁን ማን በላው ሊባል ነው? የተረገመች ልታሳግኝ ነው። ድሮም ደሜ መራራ ነው።..." በእርሷ ቁጭት እኔን በደበል ድንጋይ ደጋግሞ ሳተኝ "...ሰይጣናች!"

አያን ቁልቁለቱ ላይ የሚገኝ ቆንጥር ዛፍ ጥግ ይላ እያግተመተመች ጠበቀችኝ።

"ለምን ሌላ አላመጣህም?" አለች በተለመደው የቴሌፓቲ መንገድ።

"ይበቃናል ብዬ ነው።"

"ሥጋ አይቶ ያለፈ የመጀመሪያው ድመት መሆን አለብህ!" አለች ውርዱ አፏን እያቀላጠፈች። "በል ያዝ ረጂም ጉዞ አለብን።"

በወዲህኛው ሜዳ መጉመድ ጀመርኩ። ጣፋጭ የሽንኮ ሥጋ... ሰረጀሙና አድካሚው ጉዟችን ጥሩ ስንቅ ነው። ሞናውን አስፋልት ይዘን ለመጓዝ ተስማምተናል። ይህ ሽንኮ ብዙ ሽኮ አቋርጠን ሞናውን አውራ ጉዳና አስክንይዝ ሊበቃን ይችላል።

ሽረ

ከአላላ ኮረብታዎች ተነስተን ለሰዓታት ከተጓዝን በኋላ አደዋ ገባን። አደዋ፣ ከንዴ ከተማ ሰላሳ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ በሞናው አስፋልት ላይ የምትገኝ ከተማ ቀመስ መንደር ናት።

አደዋ ስንደርስ ከየአቅጣጫው የመጣ የግመል መንጋ ተመለከትን። አደዋ የግመል ከተማ ናት። ብዙ የውሃ ጉድጓዶች ቢኖሩባትም ውሃው ጨዋማ በመሆኑ ለእኛ ለድመቶቹ አልተመቸንም። በሚጋፋው የግመል መንጋ እግር ሥር ተሹለክለክን ገብተን፣ ከውሃው ሞዋለና ሞዋለና አድርገን ምላሶቻችን ከአራስን በኋላ ወጣን። እዚህ እንደ ውሃ ውድ ነገር አለመኖሩን ተመለከትን።

የግመሎቹ እረኞች ግመሎቻውን ሰግጠጣት እኔ እቀድም እኔ እቀድም ይንጫጫሉ። ትንትንት። ውሃ እንጂ ነዳጅ ለእነርሱ ዋጋ የለውም። ከበርሜል ሙሉ ነዳጅ ይልቅ ለእነዚህ አረኞች ጥርኝ ውሃ ይበልጥባቸዋል። እንዳንዶቹ ጉድጓዶች ለራሳቸው ውሃ ጠሚቸዋል። በአካባቢው ድርቅ በመግባቱ ምክንያት የውሃ ጉድጓዶች ንቃታት ህዝ ልጅ ይውጣል።

እኔና አያን ብዙ ከተመከርን በኋላ አደዋ ለማደር ወሰንን። ወደሚቀጥለው ከተማ ደናን ጉዟችንን ለመቀጠል ብናስብም፣ መድረስ ለመቻላችን እርግጠኞች አይደለንም።

Scanned by CamScanner

መንገድ ላይ ደግሞ የሚያጋዮመን እናውቅም። የምደ
በዳ አውራ ሲላይ ልንሆን እንችላለን።

አንድ ጤነኛ ድመት በቀን መንዝ የሚችለው እስከ አሥር
ማይል ብቻ ነው። በታሪክ ረጂሙን ጉዞ ተጉዞ የተጓዘ
ድመት የተገዘው ርቀት ለስት መቶ ሃያ ሁለት ኪሎ
ሜትር ብቻ ነው። ይህ ግን በጤነኛ እረማመደ እንጂ
እንደኛ ሰው ለመሆን በቻኮለ ድመት ላይ በተደረገ ጥናት
መሠረት አይደለም። እኛ የዚህን ጥናት ብዙ እጥፍ በቀነ
ካልተገዘን በቀር አዲስ አበባ መግቢታችን ያጠራጥራል
ይሁን እንጂ ለዛሬው፣ ከዚህ በላይ ጉዟችንን ከተመለከ
ደናን ሳንደርስ መንገድ ላይ ሊመሽብን ይችላል። ትልቁ
ሥጋታችን ጤንነታችን ነው። ሰው እያለን እንደምናውቀው
ድመቶች አምስት ገጻይ በሽታዎች አሉባቸው። እኛም
እንደ ሰው ልጅ ኤፍ. አይ. ቪ. የተባለ ቫይረስ ያጠቃናል
ፌላይን ኢሚኖዲፊሸንሲ ቫይረስ ይባላል። በድመቶን
መካከል በሚነሳ ቡሞሪያና ንክሻ ከመተላለፉ በተጨማሪ
በሥሪያም ይተላለፋል።

በንብረ ድመት ኮሚተላለፈው ኤፍ አይ ቪ በተጨማሪ
በንክሻና በቡሞሪያ የሚተላለፉ ፈላይን ሉኬሚያ
የመሳሰሉ በሽታዎች ያጠቁናል። የተበላሽ አይጥ በመመገብ
የሚመጣ ነው። የኩላሊት በሽታ ሳይቀር ይይዘናል።

የበሽታ መከላከል አትማችን ከተዳከመ፣ ቶክሶፕላዝሞሲስ
የተባለው በሽታችን ይነሳብናል። ቶክሶፕላዝሞሲስ
ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ በተባለ ፓራሳይት የሚመጣ በሽታ
ነው። በተፈጥሮ በእኛ በድመቶች ሰገራ ውስጥ መኖር
ይመቸዋል። ሰገራችን የምንቀብረው ለሰው ልጅ ሽንት ቤት
መጠቀምን ሰማስተማር አይደለም። ፈጣሪ ሲፈጥረን
ይህንን ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ የተባለ ተህዋስ ቅበሩ ብሎን

ነው። የበሽታ መከላከል አትማችን ከወረደ ይህ ተህዋስ
እኛን በማታዊ የማድረግ በሃይ አለው። ያቅበዘበዝናል።
በሽታው ሲጠናብን ሰገራችንን መትበራችን ትተን ምድር
ላይ እንወዳለን። በዚህ ጊዜ ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ
ይሬራዊና ከብቶች ሳር ሲግጡ ይገባል። ከዛም ሰዎች ጥሬ
ሥጋ ሲመገቡ ይበሉታል።

ሰዎች የበሽታ መከላከል አትማቸው ሲዳከም ስማታዊ
የሚሆኑት፣ ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ በእኛ ሰገራችን
ለመትበር በመዘናጋታችን ምክንያት ወደ እንርሱ ስለሚገባ
ነው። ብዙ ኤች. አይ. ቪ የያዛቸው ሰዎች ኑሮናሚና
ስማታዊ የሚሆኑትና፣ ራሳቸውንም እስከ ማጥፋት
የሚደርሱት ቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ የተባለው ተህዋስ
በሽታቸውን የመከላከል አትማቸው መውረዳን ተከትሎ
ስለሚሰራጭባቸው ነው።

የጨና ባለሙያ ብሆን ናሮ ጥሬ ሥጋንና ስማታዊነትን
በደንብ አጠናው ነበር። ርእሱንም "ጥሬ ሥጋና
ስማታዊነት" አለው ነበር። እንደ ማንኛውም ድመት
በአናቱ ሐበሻ እንደነበረ ሰው፣ ጥሬ ሥጋን ማውገዝ
አልነበረብኝም። ነገር ግን እውነት በቀራጭ ሥጋ
አይለወጥም። ጥሬ ሥጋና ድራፍት የሚሸጡትና
አሽከርካሪዎች በድኅረት ሲጋፉ የሚውሉት፣
በቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ አነሳሽነት፣ ስማታዊ ስለሚሆኑ
ጭምር መሆኑን ከመገለጽ፣ ድመት መሆኔ ሊከለክለኝ
አይገባም። በድመት ፍጥር የተለከፉት አሜሪካውያን
በሽማታዊነት የታወቁ ናቸው። ሙከው ካልተናገሩ በቀር
የሚደመጡ አይመስላቸውም። ስልሳ ሚሊዮን ያህሉ
አሜሪካውያን ከቶክሶፕላዝማ ጎንዳይ ጋር እንደሚኖሩ
ሱተረዳ ግን ስማታዊነታቸው ከምን እንደመነጨ ስመረዳት
አያዳግተውም። በከተሞች መስፋፋት ምክንያት እኛ

Scanned by CamScanner

ድመቶች ሰገራችንን መቅበሪያ ኮማጣታችን የተነሳ፣ ዓለም በስሜታዊነት ብትታመስ ተጠያቂዎች አይደለንም. ሰብዮብው ሃላፊነት መውሰድ ያለበት፣ ሰራሱ መቀበሪያ እንኳ ያጣው የሰው ልጅ ነው።

እኛ ድመቶች ሰገራችንን የምንቀብረው ቸክሰፕሳዝግ ሳንጻይን ለመቅበር ብቻ አይደለም. እንደ ውሾች ጉረኛ፣ ባለመሆናችን ጭምር ነው። ውሾች "እሰኛ" ሰግለትና ግዛታቸውን ለማስከበር ውጪ ሲፀዳዱ እኛ ድመቶች ግን ከወላቶቻችን ጥቃት ራሳችንን ለመከላከል ስንል ጭምር ሰገራችንን እንቀብራለን።

ለዚህም ነው አያን ከእኔ ርቃ የሄደችው። ነገሩ ስለገባ አልተከተልኳትም። ወደ ኮረብታው ጥግ ሄደችና ከአንደ የአጣን ዛፍ ሥር ሜር ሜር አድርጋ ተቀመጠች። መሬቷን ስትቆፍር ያዬ ሰው፣ ነጻጅ የምታውጣ መስሎት ወንብ ዛላዋን ሰውሱ እንዳያባርራት አልሰጋሁም። ያሳየሁ በመምሰል ፊቴን ወደ ግመሉ መንጋ አዞርኩ። ከደቂቃዎች በኋላ ስትመለስ ምንም እንዳልተፈጠረ ዝም ብላ አጠገቤ ቀመች።

እየመሸ በመሆኑ፣ ከሩቅ ወደሚታይ ጎጆ አመራን። እሳ ተጠግተን እድረን በነጋታው ጉዞ ለመጀመር ወሰንናል። በዚህ ሰዓት ወደ ደናን ጉዞ መጀመር አደጋ አለው። በሌሊት የሚያጋጥመንን አናውቅም። ሰንገሩ እዚህም ቢሆን ሁሉ ነገር አስተማማኝ አይደለም። ድንገት በድመት መንጋ ልንከበብ እንችላለን። ያልገመትነው ዱብዳም ሊገጥመን ይችላል።

ሽኜ

ወደ ደላሳው ጎጆ ስንጠጋ፣ የሥጋ ጥብስ አወደን። አንድ አሳውንት የተቀቀለ የግመል ሥጋ በርከት ላሉት ልጆቹ ሲያድል ነበር የደረስነው።

እኔና አያን እድፍጠን ሁኔታውን ተከታተልን። ቀስ በዙ ጀራቴን እየቆላሁ በአሳቱ ዙሪያ ወደ ተኮለኮሉት ልጆች ተጠጋሁ። ጥቁር ከመሆኔ የተነሳ ይፈሩኝና በፍልጥ ወጪን ሰብረው ያባርሩኛል ብዙ ሰግቼ ነበር። ከቀብ አልጣፋኝም። ውሻ ከመሆን ይልቅ ድመት መሆን የፈለኩት ለዚህ ነበር። ነጻላ ተብዬ ከመደብደብ ብሎም ከመገደል የተረፍኩት ድመት በመሆኔ ነው።

ድምፄን አጥፍቼ ከልጆቹ ደርባ በመቀመጥ እቀለጨሉጭ ጀመር። አያንም ፊራ ተባ እያለች መጥታ አጠገቤ ቁጢጥ አለች።

በሚንበገበገው እሳት ዙሪያ የተኮለኮሉት ልጆች አባታቸው የሚሰጣቸውን የግመል ጥብስ ይሾማሉ። ተመሳሳይ ከመሆናቸው የተነሳ ባንድ ሴሊት የተወለዱ የመሰሉት ልጆች፣ ትኩሱን አጥንት ይግጣሉ። ሶስት ከሳዋ ሴቶች ከደሳሳዋ ጎጆ ውጣ ገባ ይላሉ። ሴቶቹ ከመከሳታቸው የተነሳ ቆዳቸው ከአጥንታቸው ላይ የደረቀ ይመሰላል። ደማቸው የተንጠፈጠፈ ይመስል፣ ከልብሶቻቸው ሾልኮ የሚታየው ቅልጦማቸው የደረቀ እንጨት መስሏል።

Scanned by CamScanner

አባቢው በድርቅ በሽና በመመታቱ ረሃብና ቸነፈር አጥብቆ የነረፈው ቤተሰብ መሆኑን የተረዳሁት ወዲያው ነበር።

አባወራው በጥልቅ ሀዘን ውስጥ ሰጥሟል። ሥጋውን በአሳቱ ዙሪያ ለተኮለኮሱት ልጆች ብቼኛ ግመሉ መሞቱን በሥራት ይናገራል። የሚጭነውና የሚያርሰው ግመሉ የደከመ ጉልበቱ ድርቁን መቋቋም አቅቶት ሞቶበት ኖሯል።

አባወራው፣ ቅቅሉን ሲበላ ካቀረቀረ በኋላ ሳግ ተናንቀው። እንደ ነጻ ገደል ከንደኃደው ቅንድቡ ሥር ብቅ ያሉት ዓይናቹ፣ ቅቅሉ ላይ ሲንቀዋለሉ ከቆዩ በኋላ፣ የዕንባ ውርጭ ወደቀባቸው።

በአሳቱ ዙሪያ የተሰተሩ ልጆቹን አንድ በአንድ ቃኝቶ ሲያበቃ ቅቅሉን ሳይቀምስ ተነሳና ወደ አጥሩ ጥግ ሄደ። አላስችል ብሎን እኔና አያን ተከተልነው። አባወራው አጥሩ ሥር ካለች የደረቀች ቆንጥር ሥር ተቀመጠና ስቅስቅ ብሎ ያለቅስ ጀመር። ድመት ባንሆን ኖሮ እኛም ስቅስቅ ብለን እናለቅስ ነበር። ልባችን ተነክቷል። ወደ ድመትነት የመለወጣችን እንዴ ጥቅም ይኸው ነው። የበረሃውን አሰቃቂ ኑሮ በየሥርቻው አየገባን ለመመርመር ያመቻል።

የድመት መንጋ አጋጥሞን የፐርጅና የሥሪያ ሥጋት ባይኖርብን ኖሮ መላ አጋዴንን ለማጥናት ወደ ድመትነት መለወጣችን ያመች ነበር። ሰው ሆኖ በዛ ላይ ወዘልውጥ ሆኖ በዚህ በረሃ ውስጥ መከሰትና የህዝቡን ኑሓሬ ለማጥናት መሞከር መዘዙ ብዙ እንደሆን ከቀናት በፊት ያጋጠመን ስቃይ በቂ ምስክር ነው። አያን ሰው እያለን እንደነገረችኝ፣ ወደ አጋዴን መጥተው ቀልጠው የቀሩ

ተመራማሪዎችና ጋዜጠኞች ብዙ ናቸው። እኛም ወደ ድመትነት ባንለወጥ ኖሮ እስካሁን አንገታችን ላለመቀላቱ ማንም አርግጠኛ መሆን አይችልም።

አባወራው፣ ሞቶ ለቅቅል የበቃ ግመሉን፣ በአንዛ ጠል ከተሰናበተው በኋላ ወደ ቤተሰቡቹ ተመለሰ። እኛም እንር እግሩን ተከትለን ተመለስን። መሳትና ግልቀስ ለእንሰት የተሰጠ ፀጋ ቢሆን ኖሮ እኛም አልቅሰን ቢወጣልን ጥሩ ነበር። ይህ ሁሉ ቤተሰብ ከአንገዱህ ከግመሉ ቅቅል በቀር ሌላ ምንም ጥሪት እንደሌለው ስናስብ፣ ሀዘን እንደሞር ተቀብቶብን። እንኳን እጥንቱን ሙላ ሥጋውን እንኳ ቢሰሙን ለመብላት አትም የለንም።

Scanned by CamScanner

ሸኚ

አጋዴናውያን!

"አጻም ወደ ምድር ቢመለስ በትክል የሚያስታውሰው ሥፍራ ኦጋዴንን ነው" የሚሉት ፍፁም ሀሰት የለበትም። ቀንና ሌሊቱ ከመፈራረቁ በቀር በዚህ በረሃ ውስጥ የተለወጠ ነገር የለም።

የኦጋዴን የሀይምት ኑደት ሁልጊዜም ተመሳሳይ ነው መምሸትና መንጋት ብቻ። ተመሳሳይ ምድር፣ ተመሳሳይ ሰማይ። ድመት የሳሰው ሰሃን የመሰለ ሰማይና አሸዋ የተደፋበት አርቃን ምድር። ባደርጋበት የስቃይ ጎጆ ረሃቁ ምክንያት ህዘን እንደጦር ሰፍቶ እንደያዘን ወጣ አለ። የኦጋዴን ምሥራቃዊ አድማስ ፍም መሰለ። ፀሐይዋ የእግተ ገሞራ ቅልጥ አሰት መስላ ብቅ ብላለች። መዓቷን ሳታወርደው ጉህ መጀመር አለብን።

ከአደዋ ጻናን ያለው ርቀት በድመት አረማመድ ምን ያህል ሰዓት እንደሚፈጅ አላወቅንም። ብቻ ግን በረሃብ የተጠበሰውን ጎጆ ሰቀን ወጣንና ዋናውን አውራ ጎዳና ይዘን ሰከሰከ ማለት ጀመርን። በመንገዱ ግራና ቀኝ ችንፈር የረገጠው ምድር ተሰዋቷል። የአሸዋ ስፐ የተሰጣበት ምንጣፍ ነው-ያገጠጠ ምድር።

መንገዱን እየገፋን ስንመጣ ጉዱም ይበልጥ እየፈጠጠ መጣ። አካባቢው በመሉ በዜት እንስሳት ጥንብ ተበሳል። አፉን ከፍቶ ጥርሱን አሞጥጦ የወደቀ የግመል በድን፣ ቁምጫ እንደተደገፈ የሞተ ፍየል፣ በሞት ላይ የሚሰቱ ይመስል ጥርሱን አሞጥጦ የወደቀ የአህያ አስከሬን፣ ሆዱ ከዘር እስኪያክል የተጎፋ የክብት ሬሳ....

ከፊት ለፊታችን ከነጋበት ጅብ ጋር ተገጣጠምን። አልደነገጥንም። ይህ ሁሉ በድን ምድር ላይ ፈስሶ እኛን ይፈልገናል ብለን አልገመትንም። አህያ የሚያክለው ጅብ እንጋጦ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ያፈገፋል። ይህን ሁሉ መንገድ ስናቋርጥ አንድም አውሬ የጀመረው በድን አላማኡታችን ግን ገርሞናል። የሁሉም እንስሳ በድን በጅብ አልተገመጠም። የኦጋዴን ጅብ የሞተ እያበላ ይሆን? ጅቡ እኛን መከተል አለመከተሉን እየተነጋገርን እያሉን መፈርጠጣችን ተያያዝነው።

የሞት ሪጃጅም ጥላዎች የወደቁበትን ምድር አድርጠን ወደ ደናን መገሥገሣችንን ቀጥለናል። ርምጃችን ወደ ሶሶማ ብሱም ወደ ሩጫ ከተቀየረ ቆይቷል። ፀሐይዋም የእሳት ሳንቃዋን ከፍታ እሳት መትፋቷን ከጀመረች ቆይታለች። ደናን ንብተን ማደር ስላለብን በክልሳሏ ውስጥ መንገዝ ግዴታችን ነበር። አስፋልቱ እንደ ብረት ምጣድ ግሏል። አሸዋው እንደ ፍም ይፋሻል። የድመት ሚማ የለም። ...መቆም አይታሰብም። ቆሞ ከመቃጠል መሮጥ ይመረጣል።

Scanned by CamScanner

ሰኟ

የማታ ማታ ደናን መግቢታችን አልቀረም። ሁሌታችንም እንደ አንገት ፎጣ ተዝለፍልፈናል። እንደ ልጥ ልንቁለፋለፍ እንዳልን ወደ አንድ ሥጋ ቤት አመራን። የግመል ሥጋ እንደትድ የሚበላበት ቤት ነው። ቅቅል ሲራወጥ ደረስን።

ከአንዱ ተመጋቢ ላይ አፈጠጥኩበት። አያንም ከወዲያ በዙል ካለ ማዕደኛ ላይ እየተቁለጨለጨች ነው። በክልቶ ሲጠልፋት ተመለከትኩ። ከፉኛ ከግድግዳው ጋር ስትላተም አዛው ላይ እንደ መጫጫ ተጣብቃ የምትቀር መስሎኝ ነበር። የድመት ነፍስ መች እንዲህ በቀላሉ የሚወጣ ነውና! እንደ አባብ አፈር ልሳ ተነሳች። በንዴት ጦፌ ወደለውዱው ሄድኩና አግተመተምኩበት። በዚህ ጥቁረቱ ውስጥ ነጫጭ ረጃጅም ሰንቀጣጤዎችን ሳሳዩው ጊዜና! ዓይኖቹ ፈጠው በፍርሃትና በድፍረት መሀከል ሆኖ ይመለከተኝ ጀመር።

"እንዲ ነችና!?" አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ። "እነዚህ ድመቶች ናቸው ወይስ ነብሮች?..."

"አቦ ሸማኔ እንዳይሆኑ ፀልይ!" አለው ከፊት ለፊት ሌላ ቅቅል የሚበላ ሰውዬ በማፈዝ መልክ ስቆ። ነብርንና አቦ ሸማኔን ሊጠሩ ይበልጥ ወኔ ተሰማኝ። እኛ ድመቶች በመጠን እንኳ እንዲ ነብር፣ አንበሳና አቦ ሸማኔ የቅርብ ዘመዶቻችን ናቸው። ከድመቶች ሁሉ የአለምን

ረዘርድ በኩበት የያዘው ባለ ሃያ አንድ ኪሱ ግራመድት፣ ከአንድ ኮስማና ነብር አይተናነስም።

መጠናችን ይነስ እንጂ የጀርባ አጥንታችን እንደ አቦ ሸማኔ እንደ ፈለግነው የሚታዘዝ ነው። እንዲያውም መንጋጋችን ከፊት ለፊቱ ከሚያላምጠው ሰውዬ አስር እጅ ይሻላል። ምንድን ነው ይህ ሁሉ ጉራ?! እነተው እነተው አለኝ። ሰውዬውን ጉርንቦውን ልመዝለት አችላለሁ። እንዲያውም በአረማመድ ዘይቤአችን ከሚያላምጠው ግመልና ከተሮኔ ጋር እንመሳሰላለን። መቶትን በመቋቋም ከሰውዬው በብዙ እጥፍ እንበልጣለን። የእኛን የመቶት መቋቋም ፀጋ ፈጣሪ ቢያድለው ኖሮ ሰውዬው አጋዴንን ንት ያደርገው ነበር። እንደ እርሱ ላባችን በብብታችን አይንጠፈጠፍም። መቶት የምናስወግደው በአፋችን ነው። ተገደን ሥጋ በል ሆነን ተፈጥረን እንጂ፣ እንደ እርሱ እርሶ ያበላውን ግመል እንመኝም ነበር። ምግቦቻችን ውስጥ ገዴታ ሃያ በመቶ ፕሮቲን መኖር አለበት። ኩሩዎች መሆናችንን ለዚህ ሰው ማን በነገረው?!

ሰውዬው ላይ እንላፈጠጥኩ ነኝ። የምሽቱን ጨለማ ለመግፋት የበሩት መብራቶች ነጫጭ ዓይኖቼ ላይ ሲንቦገቦጉ አስፈራኑቱን ይጨምሩት ይሆናል። ሰው ከሚያደብት ብርሃን እንድ ስድስተኛውን ካገኘን እኛ ድመቶች ልቅም አድርገን ማዬት እንችላለን። ያ ማለት ከሰውዬው ይልቅ የግመሉን ቅቅል በማዬት እኔ ስድስት እጥፍ እበልጣለሁ ማለት ነው። በማሽተትስ ቢሆን!? ...ከሰውዬው ይልቅ የግመሉን የቅቅል መረት አስር እጅ ጠልቄ ማሽተት አችላለሁ።

Scanned by CamScanner

ሰውዩው የሚበልጠኝ በምላሱ ብቻ ነው። በግጥም አትሙ። ሐበሻን በምላስ ማንም አይችለውም። ሃኒ በሙሉ በምላስ ጅም የተሞላ ይመስል ከንጋር በቀር ተንኮር የለም። የሚራብበትና የሚታረዝበት፣ የጫነውንና እርሱ ያስላውን ግመል አርዶ የሚበላበት ምድር፣ በንጻጽ የተሞላ ነው። የምድሩን በረከት አውጥቶ ከመጠቀም ይልቅ በምላስ አንም ጠቀም ጦርነት እንስቶ ሀብቱን ሰባዕዳን አሳልር ሰዋቷል።

ሰውዩው ጋር እንደተፋጠጥን ነን። ፈርቶኛል። ነገር ግን ፍርሃቱ እንዳይታይበት ሌላ ፍርሃት ፈርቷል። የብዙ ጠረን ለራሱ አይድረሰው እንጂ ለእኔ መፍራቱን በብዙ እየነገረኝ ነው። ቦቅቧቃ! ...አንበሳ ብሆን ኖሮ አሰባብረው ነበር። ለነገሩ ሰዎች ፍርሃቱን እንዳያውቁበት አንበሳ ብሆን አደጠላም። የሰው ልጅ የሚበልጠውን የመፍራት አዜ አለበት። በሃብትም በጉልበትም የሚበልጠውን ይፈራል። የሚበልጠውን ያመልካል።

ግውቱን አጠራጠራለሁ እንጂ፣ እኛ ድመቶች በጥንታዊቷ ግብፅ እንመለክ ነበር። ባስቴት የተባለችው የግብፅ አምላክ ድመት ነበረች። በታችኛው ግብፅ ባስቴት የጦርነት አምላክ ነበረች። የላይኛውና የታችኛው ግብፅ ከመዋሃዳቸው በፊት፣ በ3100 ዓመተ ዓለም ባስቴት ትመለክ ነበር። ሐውልት ተሰርቶላታል።

ባስቴት፣ ከዚህም በተጨማሪ፣ የሴቶች ምስጢር፣ የመባዛትና የመላመድ አምላክ ነበረች። ሴቶችንና ህፃናትን ከክፉ ነገር፣ ከበሽታና ከሰይጣን ትጠብቃለች ተብሎ ይታሰብ ነበር።

የዐሐይ አምላክ የሆነው ያራ ልጅ እንደመሆኗ መጠን፣ ሁሉንም የሚያዩው ዓይን "The All Seeing Eye" የእርሷ ነው የባስቴት የድመቷ። የጥሩ ሽታ ምልክትም እንደሆነች ስለሚታመን በግብፅ ፒራሚዶች ላይ ተቀርጻ የምትታዩው ሞንቱላቷ የድመት፣ ሴላ አምላ የሰው የሆነችው ባስቴት ናት። በእጇ የቶን ምስል ታንጠለጥላለች።

ውሻ እያለሁ ሴትን በድመት መመሰል ለዚህ ነበር ...ባስቴት ናት። ሞንቱላቷ የድመት አምላ የሰው። የብዙ ሰዎች ችግር ይኸው ነው። በሰውነታቸው ውስጥ የተሸሸገ አውሬነት በብዙ ሰዎች ውስጥ አለ። ይህ የሚገለጠው ከፉ ቀን ሲያጋጥም ነው።

በህይወቴ ውስጥ ብዙ ባስቴቶች አጋጥመውኛል፡ የጥቂ ጥቅም ባስቴቶች። ሚስቴ አንዷ ነበረች። ባስቴት፣ ...በልጅነቴ በቤተ መቅደስ ገድግዳ ላይ ተስሎ ያየሁት የሰባድዓት ስዕል ድትን የሚልብኝ የድሮ ሚስቴን ሳስባት ነው።

ባስቴትን ሳስብ የማይክል ጀክሰንን ሙዚቃ አስታወሰኩ- "Remember The Time" የሚለው። ጠላቴን እንቢታ ሰፈታችኝ ሚስቴ ማን ቢጋዘልኝ? በፈርአን ፈት ቆሞ የሚያቀነቅንበትና በድመት ምዥት የሚደምረው ተንቀሳቃሽ ምስል ድትን አሰብኝ። ፈርአን ንግሥቲቷን ሰማዘናጋት ወይኑን እየተጎነ ጥበቦችን ይጠራል። አላት ባቱ የሚጎርፅ ቢመጣ፣ ሰርከስ የሚያሳይ ቢመጣ ንግሥቲቷን ሰማዘናጋት አልተቻለም። ወደ አንበሳ እንዲጣሉ ይደረጋል። ሚይክል የአስማት ጠበሩን በትና ይዝና ሲያቀንቅን፣ ንግሥቲቷ በድመታዊ ድምፁ ትመሰጣለች።

Scanned by CamScanner

"Do you remember when we fell in love?
We were young and innocent then
Do you rememeber how it all began?
It just seemed like heaven?
So why did it end?
Do you remember, back in the fall?
We'd be together all day long
Do you remember us
holding hands?
In each other's eyes
We'd stare tell me
Do you remember the time?
When we fell in love
Do you remember the time?
When we first met, girl?
Do you remember the time?
When we fell in love
Do you remember the time?
Do you remember how we used to talk?
You know we'd stay on the phone
at night till dawn
Do you remember all the things we said?
Like "I love you so, I'll never let you go"

...እያለ ይቀጥላል። ባስቱትን ላስብ ለውፍው ላይ ማናጨሴን ትቼው ናሯል። ቅቅሉን ፈርሶ ሄዷል። ላላሽው ዘናጌት ይሆን? የግሙሉን አጥንት እንደ ጥምቀት ሐርሞኒካ ዘፍኖት እንደሄደ የተንዘፈፉት የደቀቀውን አጥንት አስተናጋጅ መጮቶ ሲጠርገው ተመልከቺ ነው። ውርዱ እያን በወዲያ በኩል ካለው

ጠረጴዛ ላይ ወጥታ ትርፍራፊ ስትሰጥም ተመለከትኩ። እት ወንድ ጎኗ ብዙ ስፋወየ እርሷ የመግቧትን አልዘነጋችም።

ወደ እያን ጠረጴዛ ብዛድ ጥሩ ሲላይ እንደነመግት ተመለከትኩ። እንዲ ጥሩ አፒታይት የሌለው ሰው አስተርፎት የሄደው ጥሩ ቅቅል ፓየሚታል። የደመት አመጓ አልከለከለኝም። ተጋራጊት።

ሪሃሳችንን በትርፍራፊ አስታግሰን ማደሪያ እንፈልን ጀመር። የድመት መንጋ ፓየሞን ሶርት እንዲይታወይብን እየተጠነቀቅን፣ ከደናን ወደ ቀዬ ደሃር የሚወስደውን አውራ ንዳና ይዘን ከተጣዘን በኋላ ከከተማው መውጫ አካባቢ ከሚገኝ ቤት ማራ ላይ ወጣን። ጣራው ላይ ሆንን፣ ደናንን ቀልቀል እየተመለከትን ለማየት እንደተሰናዳ ወታደር እደፈጥን።

Scanned by CamScanner

ሻዕ

የድሙት መንጋ እንዳያጋዮመን ከፍተኛ ጥንቃቄ እያደረግን ካደርን በኋላ፣ የደናን ሰማይ ከመናነቱ በፊት ኮባራው ላይ ተነሳን። የከተማው መብራት የፀደይ አበባ መስሏል አደይ። በመብራት የደመቀው ደናን ወገግ ሲል ጉዱ መገለጡ አይቀርም።

ሰው እያሰሁ ስለደናን ብዙ አውቃለሁ። ከጎዱ እስከ ጆጅጋ በተዘረጋው አውራ ጎዳና ላይ ካሉ ከተሞች አንዷ የሆንችው ደናን፣ ወደ አሥራ አንድ ሺህ የሚጠጋ ህዝብ ይኖርባታል። በድርቅ፣ በረሃብና በወንበዴዎች እንቅስቃሴ ምክንያት የተፈናቀሉ ሰዎች ደናን ውስጥ በተሠራ ካምፕ ተሰማችተው ይኖራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ደናን የምትታወቀው በከፍተኛ መቀቷ ነው። ለዚህም ነው በባልያን ወረራ ወቅት ለአሥር ቤትነት የተመረጠችው።

ደናን፣ በከፍተኛ ገዛኦግሃዊ መቀቷ ምክንያት ነበር ጣሊያን በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያን ሲወር ለማሳያ እስር ቤትነት የመረጣት። በግራዚያኒ ላይ በተቃጣው የመገደል ሙከራ ምክንያት የጣሊያን ባንዳ ኢትዮጵያን አየንዳ ደናን አውርዶ ያጉር ነበር። በዚህ ወቅት ወደ አራት መቶ የሚጠጉ አስረኞች መቀቱን መቋቋም አቅቷቸው አልቀዋል። የወባ በሽታ የፈጀውም ብዙ ነው። በዛ ወቅት ደናን የሞት ደን ሆና ነበር- የአልቂት ሜዳ። ከወባውና ከከፍተኛው መቀቱ በተጨማሪ እስረኞቹ ያለቁት፣ ተገደው ነፍሳቸውን እስኪስቱ በሚሠሩት የጉልበት ሥራ ነበር።

ደናን፣ አሁንም ድረስ ወታደራዊ ካምፕ ይገኝባታል። በዚህ የሚያልፍ መንገደኛና መኪና ሳይፈተሽ ንቅንቅ አይልም። ለነገሩ ይህ በመሳው ኢጋዴን የሚደረግ የየዕለት ተግባር ነው። ኢጋዴን ውስጥ በየአሥር ኪሎ ሜትሩ የፍተሻ ኬላ ማጋጠሙ የማይቀር ጉዳይ ነው።

"ድሙቶች" ስለሆንን ኬላውን ሳንፈተሽ አለፍን። ደናንን ከነአሰቃቂ ታሪኳ ወደኋላችን ትተናት ሄድን። ከደናን ቀብሪ ደሃር ስመግባት አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ያህል የሚረዝመውን መንገድ መንገዝ አሰብን። ለዚህም ነው፣ ሳይነጋ ጉዞ የጀመርነው። ጉዞ እንደገና ሰው ወደ መሆን...

ከደናን ወጣ ብሎ፣ ሳጥን መሰል ደሳሳ ጎጆዎች የፈሰሱበትን መንደር አለፍነው። እንዲህ አይነት መንደር ድሙት በብዛት ስለሚኖርበት የፐርጅ ሥጋታችን አይሉ ነበር። ከመንደሩ ወጣ ብሎ ከርከር ባሉው መሬት ሲጋጥ ተመለከትን። አለፍ ስንል ደግሞ፣ ሻግራዎች በሰልፍ አውራ ጎዳናውን አቋረጡት።

ሰው እያሰሁ ሲነጋ መመልከት ያስደስተኝ ነበር። በስተምሥራቅ የሚፈነውን ሰማይ በተስፋ መመልከት ያስፈነድቀኝ ነበር። አሁን ግን ንጋቱን ላይ፣ የማሁበት ድሙት ማልቀስ ቢችል ኖሮ ተንሰቅስቀ እንዘሙን ባንዘቀዝኩት። የኢጋዴን ምሥራቃዊ ሰማይ በሐምራዊ ቀሰም ቢፈክም፣ ንጋቱ ንጋት አይደለም። አዲሱ ቀን አዲስ ተስፋ ይዞ አይመጣም። ትናንት ዛሬ የሚደገመው እዚህ ነው- ኢጋዴን ውስጥ- ኢትዮጵያ ውስጥ። በየሸንተረሩ የሚታየው ሁሉ የመርገጥ አሻራ ነው። በየሸለቆው

Scanned by CamScanner

የቆመው የብልፅግና ምልክት ሳይሆን የተቃጠለ መድፍና ታንክ ነው።

ወደ ቀበሪ ደሃር ማራቶናችንን ቀጥለናል። የመንገዱ ርዝማኔ፣ አበበ ቢቂላን መሆንን ያስመኛል። ውሃ አልባ ወንዞን ተሻገርን። የአሸዋ ጀሪቶችን አለፍን፣ የፅንባ ውቧታ ታህል ውሃ የሌለባቸውን ወንዞች።

ወደ ቀበሪ ደሃር ስንቃረብ አሳት የለበለበው ከመሰለው በረሃ ውስጥ ምላሱን የጎለጎለ የተኩላ መንጋ ሲወጣ ተመለከትን። ተኩላ ድመት ይበላል?... ነፍሴ አውሮኝ እንከንፍ ጀመር። በድንገት እንደ አቦ ሸማኔ ተወነጨፍን።

፱

ከምድረ በዳ አውራ አገሬ አውሮኝ እያመለጥን ቀበሪ ደሃር ጉበቱን አደረገን። አልፈናቸው ከመጣን መንደር ሊባሉ ከሚችሉት አንስተኛ ከተሞች ቀበሪ ደሃር ይመቀ ያለች ከተማ ናት። ወደ ስልሳ ሺህ የሚጠጋ ህዝብ ይኖርባታል። ከወልወል ጉጭት በኋላ ጣልያን ወታደሮቹን ያስማችባት የንበረች ከተማ ናት።

ከቀበሪ ደሃር ወልወል ለመዝለት፣ በቶራቼ፣ በዝረንቼ፣ በዋርደር አድርጎ ወልወል የሚያስገባውን መንገድ መያዝን ይጠይቃል። ወደ ምሥራቅ አንድ ሙቶ ስልሳ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት አለው።

ወልወል ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር ነዝር የፈጸሰት ሥፍራ ነው። ከጉጭቱ በፊት እንግሊዝና ጣሊያን ኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ጥቅም ለማስከበር የጋራ ስምምነት ነበራቸው። የእንግሊዝ ሶማሌ ላንድና የጣሊያ ሶማሌ ላንድ ግዛቶቻቸው ከኢትዮጵያ ጋር በመዋሰኑ ምክንያት አንዱ ሸምጋይ አንዱ ተሸምጋይ በመሆን ኢትዮጵያን ሲፈታተኑ ቆይተዋል። የወልወል ጉጭት በይፋ የተከፈተው በ1927 ዓ.ም፣ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ የወሰን ኮሚሽን ወልወል በደረሰ ጊዜ ነበር።

ጉጭቱ በይፋ የተጀመረው፣ የጣሊያ ባንዳዎች የወሰን አካላይ ኮሚቴውን በማስቀሚያቸው ነው። የወሰን አካላይ ኮሚሽኑን አይቦ የሄደው የኢትዮጵያ መታደር በወሉ፣

Scanned by CamScanner

የጎንደሮችን እብሪት አይቶ ቁጣው ባንረሊ። ወልወል በወቅቱ ወደ አራት መቶ የሚጠጉና እያንዳንዳቸው ሃምሳ ሜትር ያህል ጥልቀት ያላቸው የውሃ ጉድጓዶች የነበሩባት ምድር ስመሆንም በተጨማሪ፣ ለግጦሽ መሬት ቅርብ በመሆንዋ ለበረሃው ነዋሪ ተመራጭ ነበረች። አካባቢውን ለመቆጣጠርም በወቅቱ ውሃና ግጦሽ ዋናው መሣሪያ ነበሩ። ከዚህም ሌላ በጊላ የሊንክላር ኩባንያ ነዳጅ ያስስባት የነበረች በማዕድን የበለፀገች ምድር ናት።

በእንደኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ፣ ሙሶሉኒ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ካሉበት ወልወል በተጨማሪ፣ የዋቢ ሸበሌ ተፋሰስን፣ ቆራሄን፣ ቀብሪ ደሃርን፣ ገረንቢንና ፋፋን በሙሉ እንዲያዝ ለሶር አዚጋቸው ትዕዛዝ አስተላለፈ። የጣልያን ባንዳዎች ጉጭቱን አውሮፕላን ላይ በተጠመዱ መትረዬሶች ከመጀመራቸው ነበር የወልወል ምድር በታንክ ትርዝንብ የደመረችው። የኢትዮጵያ ጀግኖችም በቁመህ ጠበቁና አርኔ ጠብመንጃቸው ወልወል ላይ ተዋደቁ። ቀጥሩ ወደ ሰባት መቶ የሚጠጋ ባንዳ ደመ ወልወል ላይ ሲቀጻ፣ በኢትዮጵያ በኩል ግን ዘጠና ያህል ሰው ብቻ ነበር መስዋዕት የሆነው። ከዚህ ውስጥ የወልወሉ አውሱ ንፋስ አሊ ኑር ብቻ ከመቶ በላይ ባንዳ ፈጅቷል።

የቆራሄው አጥር ግራዝማች አፈወርቅ ቆራሄ ላይ መሽጎ ሰማሊያን አውሮፕላናች አልበር ያሰውም ከዚህ በጊላ ነበር። ግራዝማች አፈወርቅ የጣሊያንን አውሮፕላን በአርሊንክን ሲጥል ሲሞክር ቢቆስልም ቁስሉ አልተሰማውም. የተሰማው ሀገሩ የመደፈሯ ቁስል ነበር። የቆሰለ እግሩን እየንተተ በአርሊንክን የሀገሩን ሰማይ ይጠብቅ ይመር። ከዛያ በላይ አውሮፕላናች ተመላልሰው በአንድ ቀን ብቻ በንብ ሲያዘንቡ፣ አርሊንኩ ዝም ያለው

አፈወርቅ ደመ ተንበናፕፎር አልቆ፣ በአናት ሀገሩ ምድር አፈር ላይ ሲደፋ ነበር።

ቀብሪ ደሃር ውስጥ ለሁለት ቀናት ያህል ረፍት ካደረገን በጊላ ወደ ደንሃቡር ንሚችንን ቀጠልን። የእንዴን ጦርነት ምልክቶች አሁንም ድረስ አካባቢው ላይ ይታያሉ። በለስተኛው ኮማንዶ ጦር ነፃ ከመውጣቷ በፊት አስርኛው ብርጌድ የተዋደቀባት ቀብሪ ደሃር የአያሉ ኢትዮጵያውያን ቀብር ናት። ወደ ጊላችን ቀረች። ከቀብሪ ደሃር - ደንሃቡር ድረስ ያለው አውራ ንዳና ሁለት መቶ ሃያ ያህል ኪሎ ሜትር ቢሆን ነው።

በመኪና ሶስት ሰዓት ያህል የሚፈጀው መንገድ ለእኛ ግን ቀናትን ፈጀብን በዚህ ሁኔታ አዲስ አበባ እንዲትና መቼ መግባት እንደምንችል አላወቢ አየሁንበን መጭ በአየር በመከራ ደንሃቡር በንጣ፣ ንለዲ፣ ጂይጅ፣ ጭቆድ፣ ሽኮችና ቢርኩት ከሚባሉ ታናናሽ መንደሮች አድረን ነበር።

Scanned by CamScanner

ሻፅ

ድመት መሆናችን ባንድ በኩል ጠቅሞናል። ይህን የምለው ምናልባት ራሴን መቀበል ግዴታዬ ስለሆነብኝ ይሆናል። አሁን ሰው አይደለሁም። ድመት ነኝ። አውሬ ነኝ። ሰው መሆን ቢያቅተኝ ቢያንስ ጥሩ አውሬ መሆን አለብኝ መልካም ድመት። የዘመኔ ሶፀድዓቶች (ግማሽ ሰዎች ግማሽ አውሬዎች) ከሁለቱ አንዱን ቢመርጡ እንዴት ጥሩ ነበር! የኔዎቹ ባስቴቶች (ድመት ጭንቅላት ሴቶች) አንዱን ቢመርጡ እንዴት መልካም ነበር! ትውልዴ አንዱን ሊመርጥ አልቻለም። አውሬነቱን በሰውነቱ ውስጥ ሸፍኖ አልቻለም። እንደ ቁምጣ ያጠረ ግንጥል ማንነቱ የአውሬነት ቀንዱን ሊሸፍንለት አልቻለም።

እኔ ድመትነትን ያስመረጠኝ የገጠመኝ ችግር ነው። አያንዳ ድመት የሆንችው በተመሳሳይ ችግር ምክንያት ነው። ከችግሩ ለማምለጥ አውሬነትን መምረጣችን ትክክል ላይሆን ይችላል። ግን በክንቱ መሞት የሰበንም ስል አስባለሁ። ህልም ያለው ሰው የችግሩን ወራት እንደ አውሬ ተቀጥሮ ቢያልፍ ነውር የለውም። የትውልዴ እጣ ፈንታ ይህ ሆኗል። ለዘመናት ተተክሎ ሥር የሰደደ ችግሩ አውሬ አድርጎታል። አላሳቢ የሆነው ሰው ለመሆን አለመጣሩ ነው። ሰውነቱን ያልፈለገው አውሬ መሆኑ ክርሱን ለዘለውም ቢሆን ስለሞላለት ነው። ሳቢድዓት እና ባስቴት ሆኖ ግማሽ ሰውነትን ግማሽ አውሬነትን የወረሰው ትውልድ ምሉዕ ሰው የሚያደርገውን መድኃኒት የሚቀምምለት አጥቷል። መድኃኒቱ እንዲገኝ የፈለገም አይመስልም። ከሠሙ ብዛት የተነሳ ፈውስ የሚገኝለት ስላልመሰለው ተስፋ ቆርጦ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን

ምንጊዜም ቢሆን መድኃኒት ትንሹ ይጠቃል። ግዙፉ ዝሆን ከሠመሙ የሚድነው ባንዲት ትንሽ እንክብል ነው። ሠመማችን ብዙ ቢሆንም መድኃኒቱ ትንሽ ነው።

እኔና አያን ድመት ከመሆናችን የጠቀመን እንድ ሶስተኛ የሆነውን የህገራችንን ክፍል፣ ሠመሙን፣ ገበናውን፣ ስቃዩን በየጎራንጉሩ ገብተን ለማዬት ስላስቻለን ነው። ማህበረሰቡን ሰው ሆኖ ጠልቆ መመርመር ክፍተ ሆኗል። ለዘመናት በጦርንት አሳሩን ሲበላ ፍላውን ሲንንት በመኖሩ፣ ወዘልውጥን እንደ ዓይኑ ብሌን ይሕታተላል። ይጠራጠራል። በሌላ በኩል የዚህን አህጪ ልውቅልህ የሚሉት አባይ ጠንቋይ መሰል የዘመኑ ፖለቲከኖች የችግሩ አጋፋሪዎች ናቸው። አጋዴንን አለም ረስቶታል። አጋዴንም አለምን ረስቷል። አጋዴንን ድመት ሆንን ስናቋርጥ እየተመለከትን ያለነው ይሆንኑ ነው።

በጀረር ወንዝ ላይ የተሰራውን ድልድይ አቋርጠን ደገሃቡርን ወደ ኋላችን ትተናት ስንሄድ ጀረር ወንዝ ውሃ አልነበረውም። ከአሸዋ ዝምር በቀር ጠብታ ውሃ የለበትም።

ደገሃቡር በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ወደ ጠርሐራ መደብ ለሚደረገው ንግድ የሲራራ ንጋዲዎች መሸጋገሪያ ነበረች። የንግድ መስመርነቷ፣ ኃላን መሰረት እያደረገ በሚነሳው ግጭትና ብጥብጥ ሳይተንፍስ ናር፣ እንዲህ ኮስምና አትቀርም ነበር።

ከደገሃቡር ወደ ተባሬ በሆሀ ጉዟችንን ቀጥለናል። እርቃናቸውን የቀሙት ኦሮቡቶች አሙሉ ነፋስ ይጥመለመሉባቸዋል።

Scanned by CamScanner

አውሎ ነፋሶቹ እንዳያወስዱን እየተጠነቀቅን፣ ወደ ቀበሪ በያህ ስንጓዝ ሰው እያለሁ አሰማው የነበረው የንዋይ ደዘበን ሙዚቃ የበረሃው አውሎ ነፋስ አስታወሰኝ። ስንኞቹን ሙሉ በሙሉ ባለስታውሳቸውም በድመት ዊንቅላቱ ውስዋ እያዜምኩት ወደ ቀበሪ በያህ መንቶስቶሴን ተያያዝኩት።

በበረሃው አውሎ ነፋስ
በበረሃው አውሎ ነፋስ
በፈጣኑ ባህር ፈረስ
ገና ቡሄው መስቀል ሳይደርስ
ከደጅሽ ላይ ድንገት ልድረስ።

...

ጥይት ያልበገረው በሞር ያልተፈታው
ውበትሽ ማረከው ሽንጥሽ ልቤን ረታው።

...

ፈጣኑ አውሎ ነፋስ የበረሃው ፈረስ
አምጥቶ ከጣለኝ እዛው ደጅሽ ድረስ
ይቀመስ ጉሽ ጠላሽ
ይበላ እንጂ ዳቦሽ

...

ከማጀት አምባሽ ቀይ አምባ
ልብ ያለው ደፍሮ ከገባ
ፍሪዳ ስንጋው ተጥሎ
እንዲያው ሲያስንመጅ ተንጋሎ
ታናሽ ታሳቅሽ የት ጋ ነው
ሰቁርጥ ይመቻል ሥጋ ነው
ፍሪምባ ሻኛሽ ባዋዜ
አቤት ሲጣፍጥ ያን ጊዜ
ክትፎ ከጥሬው ሲመደብ
እንዲያው ጣድ አርጎ ሰብስብ

ሰብሰብ ሰብሰብ
ከራብው ሆዴ ሲል ጎርበብ
ሰብሮድ አንቺን ነው መደረብ

...

በሰማይ በምድሩ እከንፍልሻለሁ
ላውጻሙት ጠብቂኝ እመጣልሻለሁ
እንግዲያው ባዋጅ በገሃድ
ነፍሴ ከነፍስሽ ሲዋሃድ
ባውሎ ነፋሱ ምገድ
ተያይዞ ነው ማበድ
ጥርሶችሽ ደስታ ሲረጩ
ፍቅር እየቀዱ ከምንጩ
ላውጻሙት ሞያሽ ሲገለጥ
ክትፎው ከዶሮው ሲመረጥ
ከጎሮ ቢሆን ከንፍም
ለወዳጅ ቢሰጥ አይጎም
አይጎም አይጎም
ብትሰስችም ለሆጭም
መቼም አትሸሽም ባጭም።

...በበረሃው አውሎ ነፋስ....

እንኪን በድመት በሰው ፈት እንኳ ሲዘፈን ምሬት የሚያስውጥ የሚመስሰውን ዘፈን በውስጤ እያንጎራጎርኩ መንገዴን ቀጠልኩ። በዘፈኑ ንኖም ውስጥ ያሉት የሥጋ ብልቶች የሥጋ አምሮቴን ተስቅሰው የበረሃ ምሬቴን አስጨረሱኝ። ፍራፍሬ፣ ፍሪምባው፣ ሽኛው፣ ክትፎው፣ ጥሬው... የሚሉትን ቃላት ስሰማ፣ ይህ አውሎ ነፋስ ተሸክሞ መሰደ ሥጋት ደጅ ላይ ቢጥለኝ ተመኘሁ። በዘፈኑ ውስጥ የሚዘፈንላትና ሽንጥና ጸሊም የሚያማልለው ውበታም ሴት በሥጋ ዜሮች ውስጥ ተሰመረችብኝ። ምን ላርግ፣ ድመት ነኝ። ስጊዜው ሥጋ

Scanned by CamScanner

እንጂ ግብረ ሥጋ ሊያማልሰኝ አይችልም። ግብረ ሥጋ ስል የድመት መንጋው ሥጋታችን ትዝ አለኝ።

የድመት መንጋ ፕሮሞን አያን እንዳትሠረር አስቀድመን የሊጋነው ሲጋት እንደ ኤሌክትሪክ ነዘረኝ። አያንም ያስብኩት በቴሌፓቲ ደርሷት ድንገት ተጥ አለች።

"ምን ይሻላል?" አልኳት በውስጤ በዓይነ ህሊናዬ አንድ ድመት መጥቶ ሲሰራት እየታዬኝ። መሰረሯ ብቻ አያደለም እችሩ ...ታረግዛለች። ከዛም የድመት ግልገል ትወልዳለች።

"ያንት ያለህ"

"እስክሁን የጠበቀን ፊጣሪ ያውቃልኮ" አለች ሞንቶቴ በቴሌፓቲ ደርሷት። "ይልቁንስ በጊዜ ቀብሪ በሃህ መግባት አለብን እንፍጠን። ይልቁንስ መፍራት ያለብን ሞራሽ የዱር ድመት እንዳያጋጥመን ነው። ታግለን እንኳ ማምለጥ አንችልም። አስገድዶ ከሰረረኝ ማርዝ አይቀርም። ከዛ ምን እንደሚፈጠር ታውቃለህ። ሰው መሆኔን አትርሳ። ድመት ወልጀ..."

"ተይ ተይ አትጨርሺው!" ፊቴን በድመት ጣቴ ሸፈንኩ። "ከሁሯን የምትበላ የድመት አራስ...."

"...ይሰውረኝ!"

"ያ ከሆንማ የሀገሬ የኢትዮጵያ ተምሳሌት ሆነሽ ማረፍሽ ነው። በኩሯን የምትገድለው ጀግናዋን የምትቀብረው! የሀገሬ ተምሳሌት ...ድመት"

"አያድርስ ነው። ምናለ ያ የታጠቂ መጥረቢያ እንትቴን በቀነጠሰው!"

ሩጫችን ተያያዝነው። ወደ ቀብሪ በሃህ... ሰው ወደ መሆን።

ሰባ ዩ

እንዳሰብነው አልሆነም። እንዳለምነው አልተቻለም። በደንሃቡርና በቀብሪ በሃህ መሀል አራርሲ ከተሜኛ አንስተኛ መንደር አድረናል። ከሁለት ቀናት ንዞ በኋላ መሆኑ ነው ቀብሪ በሃህ የገባነው። እየተጓዝን ነው። በእነዚህ ቀጫጭን እግሮቻችን ተቀንጭሮ የማያልቀው መንገድ እንኳን አዲስ አበባ ጀጀጋ እንኳ በተሳሳ ሊያስገን አልቻለም። እንዲህ በተሳሳ ሰው መሆን አልተቻለም። አውራ ሰመሆን በፍጥንት የሚሠራው አምባት ሰው ሰመሆን ግን ይለንግዛል። በአርንየ ወደ ሰው የሚለውጠውን አስማት አልሞክርውም። እንምር ብኔ እንኳ ከአስማቱ የማውቀው ጥቂት ቃላት ብቻ ነው።

"የማያላልት ፀሎት ነን ያስደል' እንዳለ ላያላልቀኝ አስማቱን ግርዝስ ይሆናል ወይ በመሲንቱ ልሞክረው አልፈለኩም።

ቀብሪ በሃህ ከሃያ ሺህ የማያንስ ህዝብ የሚኖርባት ከተማ ናት። የከተማዋ ነዋሪዎች አንድ አስኩን ካሰፍናቸው የአጋጄን ከተሞች ለየት ያለ በዛይ አላቸው። አዲስ ነገር ለማምጣት ካላቸው ጉጉት የተነሳ ይሁን ወይም ለላ፣ ግልብጥ ብለው ይወጡና መንገድ ጫር ይቆማሉ።

አንዱ የዚህ ከተማ ነዋሪ ስለንድ ምንብ ቤት በር ላይ ቀሞ ሚስቱን ወደ ቤቷ እንድትሄድ ሊለምናት አይቼ ተገረምኩ። ውርዙ አያን፣ ሶማልኛውን በቴሌፓቲ ጠልፋ ተረዳሁችልኝ።

Scanned by CamScanner

"ይህን ከተማ ጥለን መሄድ አለብን!" ይላታል በምሬት። "ቦሌቶችም የወንዶቹም ጠባይ ተመሳሳይ የሆነብትን ይህን ከተማ ጥለን ካልሄድን መቼም እንለወጥም። ሴቶቹ ብዙ ነገር ያምራቸዋል። ወንዶቹ ግዘድ ነው የቀራችው።"

"እትም ያለው ለስት ሚስት አግብቶ ሁሉንም አኩል ያስተዳድራል። ምነው አንተ ባንዲት በእኔ ተማረርክ?!"

"ሴትን ከማስተዳደር አገር ማስተዳደር ይቀላል። ለስት ትያለሽ እንዴ ደግሞ! አንቺን እንዲታገሱ አልቻልኩም። አየሽው ይህን ድመት?!" አለ እኔን ቁልቁል እየተመለከተ። "ሴት ማለት ድመት ያያት ሥጋ ማለት ናት።"

"ያያት እንዳይትታት ማድረግ ደግሞ የጀግኖች ሥራ ነው። ቀናህ እንዴ እዚህ ስቶም ጊዜ?"

"እም!...የሃምሳ ሳንቲም ሥራ ላይሠራ የብር ከሃምሳ ምሳ ሼር ደረሰ' አሉ!" ሰውዬው አግምትሞ እሾን ይታጠብ ጀመር። "እዚሁ ልብላ እንጂ እንግዴህ! ነይ በይ ታጠቢ እንብላ..."

"...እሺ እዘህ ጠብቀኝ መጣሁ..." አለችው እጇን ልትታጠብ እያግዘሰች። መታጠቢያው ከውጪ ውሃ ተሞልቶ ደረጃው ላይ የተቀመጠ ቢጫ ጀሪካን ነው። ጎኑ በአሰራ ሁለት ቁፕር ሚስማር ተበስቶ ራሱ ሚስማሩ ተወትፍቧል። ለመታጠብ ሚስማሩን መንቀል! ለመዘጋት ደግሞ የሚስማሩ አናት ቀዳዳውን አስኪደፍነው ወደ ጀሪካኑ ሆድ መግፋት ነው። ሴትዮዋ ታጥባ ከጣች በኋላ በማስታጠቢያው ጀሪካንና በሁኔታው እየተገረምን ንሏችንን ቀጠልን። ሰው ብሆን ኖሮ ስቂ ባላበቃሁ።

ከተባራ በሆህ መውጫ ኪላ ላይ ሰዎች ተሰልፈው አየን። ሰለጥ ሰለጥ ሰው በወታደር እየተገደደ መድኃኒት ሥራ ይፈጫል።

ይህን ካለፍን በኋላ ከመንገድ ወጣ ብሎ የሚታይ ነገር ተመለከትንና ወዳየነው ነገር አመራን። ያየነው ነገር አስገራሚ ቤት ነው።

ቤቱ የተሠራው ከታንክ ነው። በአጋዴን ጦርነት ወቶት በወንብ ከጋዜ ታንክ ውስጥ ሰው ይኖርበታል። እኔና እሾ በቀዳዳው እሙልቀን ነዋሪዎችን ባናይ ኖሮ፣ የሰው ልጅ ተቃዮሎ በዛን ታንክ ውስጥ ይኖራል ብንል በፍጹም አናምንም ነበር።

"ያንት ያለህ!" አልኩ እሙልቀ ቤተሰቡን ከፍቱ በኋላ። "ከዚህ በላይ የአጋዴንን ሰቶታ የሚሰላይ ምን ነገር ይኖልን?!"

"ተመልከት! ...አየህ?! ...ይህ እየሠነ ያለው ከክልሉ ዋና ከተማ ጥቂት ዚሉ ሜትሮች ወጣ ብሎ ነው። የሰው ልጅ እዚህ ውስጥ ይኖራል። አፈር በልቶት አለመ ታንክ ውስጥ። አይ ኢትዮጵያ..."

"...እኔ አፈር ልብላ..." ሰው ብሆን ኖር አልትሸ ይመጣልኝ ነበር። ነገር ግን እንሰላ ነኝ። የሠነ ፈተና አውራ ያደረገኝ ዕንባ አልባ ሰው። እንባ አልባ ድመት። በትኑዚ ተውጠን መንገዳችን ልንተጥል ዘወር ስንል በድመት መንጋ ተዘን ፊቶችን እንኝው። ከታንኩ አፈሙዝ የወጣ እንር ተልላ የመሰለ ድምት እንደ መድፍ ተተኩሶ አረፈብኝ።

Scanned by CamScanner

ሻቦ

የፊታችን ፕርጅ ከታወጀብን ወዲያ ሁለት ምርጫዎች ብቻ ነበር የነበሩን። ጠንከር መዋጋት ወይም እግሬ አውጭኝ ማምለጥ። ሁለቱም ቀላል አማራጮች አልነበሩም። መዋጋትም ማምለጥም ጥበብ ይጠይቃል።

አያን ውርዬ፣ አንድ አንዛ የመሰለ ድመት ጋር ስትፋለም አየኋት። ሙርሚን አፈር ውስጥ ተብራ የጨለማ ውሃ ላይ ናት። ድመቱ ከጊላ ዞሮ ሊወጣበት አያንሬ ይዶራታል። እርሷም እንደ ጣይቱ በር እየተሽከረከረች ከኑሮ አፏ ውስጥ ያሉ ጥርሶቿን አሞጥጣ በደመ ነፍስ ትፋለማለች። ከሠመረለት የሚፈጠረውን ነገር መገመት ተሳል ነው። ማሰብ አልፈልግም።

እኔን ዘሎ ያነቀኝ ድመት አንገቱ ሥር ክፉኛ መገቶኛል። የውሃ ልምድ ባይኖረኝም በደመነፍስ ነፍሴን ለማትረፍ ተፋለምኩ። የድመት መንጋ ከቦ ያዋከበኝ ጀምሯል። አሊራው ሲጨስ ሰተመስከተ የድመት ሳይሆን የአንበሳ ጮርንት የተከፈተ ይመስላል። እንዴ እንደፋድፎኝ ሲሄድ ሰለኛው ይተኳበኛል።

ሲመናብኝ እግሬ አውጭኝ ተፈተለኩ። አየር ላይ የተንሳፈፍኩ መሰለኝ። በትዕበት ዞር ብዬ ሳይ አንዛ የመሰለው ድመት አያን ላይ ወጥቶባታል። "ያንት ያለሀ

የምት ሞቷን ተወንሞፈ ወደ አያን ተመለስኩ። ከጊላዋ ወጥቶ ሙርሚን ፍሲጋ ያዶረዱራል። ጀራቱን ስቀም አደረኩና በጥፍሮቼ ወግቼ ከጀርባዋ ላይ ጉትቼ አወረድኩት። እርሱ ወደፊት ሲሰብ አያን ጀራቷን ቀልፋ ተፈተለከች። ለትቂው በደመ ነፍስ ተከተልኳት። ደርሳት ይሆን? ማለቴ...

እግሬ አውጭኝ ወደ አስፋልቱ ከሮጥን በኋላ ወደ ጀጀጋ የሚወስደውን አውራ ጎዳና ይዘን ስናበቃ፣ ወደ ጌጓችን ተመለከትን። የድመቱ መንጋ እየተንጋጋ እንደ ተኩላ ሲከተለን ተመለከትን። ፍጥነት ጨመርን።

ጎሳዬ ተቦዳድሷል። ወኑሬ ተንሟሟቷል። ደምቻለሁ። እንዲያውም ከእኔ አያን ትሻላለች። አሷን ለመከረር እኔን ነበር ክፉኛ ያጠቁኝ። ቁስሉ ብቻ አልነበረም ችግሩ። ሲጋቱ አንድ በሽታ ይዞን ሰው ሳንሆን አንዳንምት ነበር። በዛ ላይ የድመት እድሜ አጭር ነው። በአማካይ የድመት እድሜ ከአስር እስከ አስራ አምስት አመት አደበልጥም። ይታሰብ የተመዘገበው በእድሜ ዘልሳለው ድመት በሰባነ ስምንት አመቱ ነው የሞተው። እንደ እርሱ አርጅቶ ለመሞት በጉሮው የተቀማጠለና ሐኪም የሚቀጥር ባለቤት ያስፈልጋል። እኛ ግን በዘረፃ አየዘንን ነው። በዛፉው ጮርንት በተላለፉ በሽታ አለመለከትን ያጠራጥራል። ይህን የምናውቀው ስንሞት ብቻ ነው። ወዛ ላይ ከሌው ወደ ድመት ስንለወጥ የማንሰው ድመቶች እድሜ አይታወቅም። በዚህ ሁኔታ አዲስ አወ መግለጥን ያጠራጥራል።

Scanned by CamScanner

ሻዕ

ጀጀጋ እንደገባን ከአንድ የግመል ምግብ ቤት ደጃፍ ላይ እንደጨርቅ ተሰጣን። በተለይ እኔ ላይ በታወደው ፕርደ ምክንያት አካሌ በመድቀቁ የምግብ ፍላጎቱ ድራሹ ጠፍቷል። እንኪን የተጋጠ አጥንት ቀርቶ፣ ድመት በልጇ ልትሰውረው የምትችለው ውተት በጉሮሮዬ ቢንቀረቀር እንኳ መገርገጭ የምችል አይመስለኝም።

ሆኖም "ድመት መንኩሳ አመሏን አትርሳ" የተባለችበትና መንኩሳም ያም የሚያስገድፋት ውተት ሲያምረኝ ይቀራል። አሱን ለማግኘት የዘላን ድመት መሆንን ይጠይቃል። እኔ ግን ውተት እንደ ውሃ ከሚደፋበት ዘላን ቤት የተፈጠርኩ ድመት ሳልሆን ችግር ከሰውነት ወደ አውሬነት የሰወጠኝ የአስማት ፍጥረት ነኝ። ወደ አውሬነት የሰወጠኝ ድግምት እንደ ገና ወደ ሰውነት ይሰወጠኝ ይሆን? አንጃ!

ወደ አውሬነት መሰወጥ ድጥ ቢሆንም ወደ ሰውነት መሰወጥ ማጥ ሲሆን ይችላል። አሱም ቢሆን አስማቱ ክሰራ ነው። ታናሽ መሆን ቁልቁለት ሲሆን ታላቅ መሆን ግን ጸጋት ነው።

አያን ወደ ምግብ ቤቱ ገቢታ ስትልተመቱም ቆይታ ተመሰሰች።

"ብስ! ብስ! አንጀትሽ ይበስብስ!" የሚሉ ድምፆች ከውስጥ የሰማሁት ለዚህ ኖሯል። የአንዱን ተመጋቢ ሰውዬ የግመል አጥንት ይዛልኝ ከች አለች። ከእኔ ጉዳት የእርሷ ጉዳት ቀላል ነው። የተናቸፋነብት የእግር ጥፍሬና አገጩ የወላለቀ ይመስል አጥንቱን የመጋጥ አትም የለኝም።

አጥንቱን ካፉ ጥማ አስተምጣ፣ ብይ የመሳሰሉ "ብሉንድ" ሳይኖቿን አቁለጨለጨች። አትም እንዳጠረኝ ገበቷት ሀዘን ሳይኖቿ ውስጥ እንደ ጉም ሲረጭ ተመለከትኩ።

"አረ ጉድ ተመልከቱ!" አለ በመጥረጊያ ወንበ ላለዋን ብሉ ያባረራት አስተናጋጅ እኛን እየተመለከተ። "ድመትም ይታዘዘናል እንዴ?!"

"ና! በል ወደ ሥራህ ተመለስ! ወሬኛ" አለው ኑሮ ጋዋን የለበሰው ሰውዬ። ኃላፊው መሆን አለበት።

"ውቼው ጉድ! ... ሰው ሙተዝን ባቶመበት ዜመን ድመት ሲተዝን ማየት ያስደንቃል።" እያለ መጥረጊያውን አያወዛወዘ ገባ።

እንደ ምንም ብዬ አጥንቱ ላይ ያለውን ሥጋ መላስ ጀመርኩ። የድመት ደካም፣ እንደ ውሻ ቀስል ተሉ እንደሚድን ተገነዘብኩ። ከደቂቃዎች ማጥዛት በኋላም ከሥጋው መንጨት ጀመርኩ። በአያን ዓይናች ላይ የደስታ መስመሮች ሲሰመሩ ተመለከትኩ።

ከውስጥ ተመጋቢዎች በስግልኛ ቋንቋ ሲጫጫሁ ይሰማኛል። ሚጫታቸውን ለሰማ፣ በድብደብ ሳስተኛውን

Scanned by CamScanner

የአለም ሶርጎት የሚቀሰቅሱት ይመስለው ይሆናል። እኩል እያተንጋገሩ እኩል መደማመጣቸው ሰመጡ ሰው አጀኒ ያሰኛል።

ከዛ ሁሉ መሟሟሄ በኋላ ግን ሲመጡ እየተሳሳቁ ነው።

"አብሸር!"

"መርሃባ!"

ተቃቅፎ ተሳስሞ መለያዬት።

ከሸሞ መጥፎ ድመት ስለሆኑት ለእኔ የተነበርኩ ሰው ስንበርኩት፣ ይህ ሁኔታ ቢያስቀናኝ አይገርምም። የመሳል ሀገር ሰው ጫላ ቀረሽ ንግግር ከተንጋገሩ በኋላ ቀጥን መገመት ቀላል ነው። አስከራን ባይቆጠር እንኳ ጥርስ ሊሰቀም ይችላል።

ለነፍላችን መያዣ እንደምንም ከተልቀመቀምን ከሰነታት በኋላ፣ ስለቀጣዩ ጉዟችን መነጋገር ጀመርን።

"ከዚህ በኋላ በናፁም በእግር መንገዝ የሰብንም" አለች አያን በቱሊፓቲ። "እንዱ ድመት ሊሰረኝ ይችላል።"

"አልተሰረርሽም ማለት ነው?! ደማሪ ሆይ ተመስገን! እንደ ዝንጂ ከተነጠፍክበት መሬት በደስታ ንይል በድግ አልክ።

"... ይ አንዛ የመስለ ድመት ..ወጥቶብኝ ነበር። ግን መርጠ የብልቴን ሚፍ ነክቶ ከመመለሱ በቀር ወደ ውስጥ አልገባም።"

"የዘር ፍሬው ነክቶሽ እንዳይሆን?..."

"አይመስለኝም።"

"አንድ ሀሳብ መጥቶልኛል።" አልኳት ጥቂት ካሰብኩ በኋላ።

"ምን አይነት ሀሳብ?"

"ሰው እያሰሁ አንዲት ሴት ውሻ ነበረችኝ። ወንዱው አየወለደች ቡችሎቿን ማሳል ሲታከተኝና ከፈጣሪ እንዲያጣላኝ ሰል ምን እደረኩ መሰለሽ! ...የውሾቼ የከረታ ወቅት ደርሶ ውሾቼ ገቢዬ አባባ ሲሰማቸ አንድ ምሳ መጣልኝ። ወደ ነጻ ማደያ ሄድኩና ዝቃጭ ይዤ መጥቼ ጓሳዎን ተበጀት።"

"ጥሩ ሀሳብ ነው" አለች አያን። "... ስለዚህ ወደ ማደያ እንሂድና ጓሳዬን መለቅለት እንችላለን።"

"በትክክል!... በነገራችን ላይ ድመቶቹ ብልሆች ነን። ቀደምት የሰው ልጅ ጠዚዛን ሰነ እዕምትን ሳይቀር ያጠኑት የድመትን ብልሃት ተጠቅመው ነው። ለምሳሌ ድመት አባብ ከነደፋት፣ ወደ ዱር ትሂደና ትወሊን የምተወት እዕ አለች። ይህን የተመለከተ አንድ ጠቢብ በድፀ ተከታትሎ ድመቷ አባብ ከነደፋት በኋላ ከምትምሳት እዕ ለሰው ልጅ መድኃኒት ቀምሟል።"

በቱሊፓቲ አያወራን የጎጆ ማደያ ፍለጋ ይጀጋን አለስናት። ከአሸዋና ከውኃ ላስተኮቹ በቀር ምንም ጠፊተ ውኃ በሌለበት በቶኃ ወንዝ ላይ የተሰራውን ድልድይ አቋረጥን።

ይጀጋ ወጥንቱ ጊዜ አሬረር አለ ጹደላ በሚሰልተው የንግድ መስመር፣ የሲራራ ንጉሥዎች ማረፊያ ነበረች። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ሐረርና ሀርጌን የሚያዛኘው አውራ ጎዳና እምብርት ናት። በተን ውጫሌ በኮል ሚገባው

Scanned by CamScanner

ኦንትሮግንድና ሽቀጥ ማራገፊያ በመሆኗ ከከልሉ ከተሞች ሁሉ ደምቃ ትታያለች። ይሁን እንጂ ፍተሻቁ አይጣል ነው።

እያን በቱሊፓቲ ተማባት እንዳስረዳችኝ፣ ፍተሻው የጠነከረው የመንግስት ባለስልጣናት ጅጅጋን ግዕዝል አድርገው በቶጎ ውጫሌ በኩል ወደ ውጪ ሀገራት ስለሚጠፉ ነው። አንዳንዶቹ ሀገርን ዘርፈው ሲሆን ሌሎቹ ግን ሥርዓቱን ተቃውመው ነው። ይሁን እንጂ ሌሎች ከስሜን የሚመጡ ቤጎችም በዚህ በኩል ከሀገር ይወጣሉ።

ፍተሻው የጠነከረው በእርግዮ በዚህ ምክንያት ብቻ አይደለም። እጋያን በንዳጅ ምክንያት የፍጅት ቀጠና እንዳይሆን ነው። ከዚህ የተነሳ መኪና እየቆመ በጥበት ይፈተሻል። ወዘ ልወየ ብቻ ሳይሆን የከተማው ነዋሪም በግ በወጣ ቁጥር ደጁ ላይ ሳይቀር የመፈተሽ ግዴታ አለበት። እንዲት የቤት ሰራተኛ ሱቅ ደርሳ እስክትመለስ ሶስትና አራት ጊዜ ልትፈተሽ ትችላለች።

ጅጅጋ የተመሠረተችው በፈታውራሪ ተክለ ሐዋሪያት ተክለ ግርያም ነው -በ1916 ዓ.ም። ይሁን እንጂ፣ በከተማዋ እምብርት ላይ የቆመው፣ የሰይድ መሐመድ ሐውልት ነው። ሐውልቱ አስፈሪ ጎራዴውን ወደ ሰሜን ቀስሮ ሲጋር ፈረሱ ላይ ተቀምጧል።

እንግሊዞች አብዱ መላህ እያሉ የሚጠሩት ሰይድ መሐመድ አብደላ ሐሰን፣ በአንዳንድ ሶማሌዎች ዘንድ "ሶማሌ ቤሐር አባት" እየተባለ ይጠራል። የተወለደው በቀድሞዋ የእንግሊዝ ሶማሌ ላንድ ሲሆን፣ በ1899 ዓ.ም ከእንግሊዞች ጋር ተጣላ። ይኸውም "የኢደን ሥጋ ቤት" እያሉ ከሚጠሯት በርበራ ውስጥ የስተመጡትን የጦር

መሣሪያ ስርተሃል በሚል ነው። ሐሰን ይህን መሣሪያ ፈርሚያ የተባለ ሶማሌዎችን ሁሉ አንድ ያደርጋል ላለው የእምነት ቀመስ አንትስቃሴው ለመለመላቸው ተከታዮቹ አስታዋቂው ነበር።

ይሁንና ጥቂት መሣሪያ ይዞ፣ ከኢትዮጵያ ግዕስየ መንግሥት ጋር ሊገጥም ጅጅጋን ወረረ። ሰይድ መሐመድ ከመቅፅ የኢትዮጵያ መሪ ከምኒልክ ጋር ብቻ አልነበረም የተጣላው ከጣልያንና እንትስቃሴውን ካልደገፉት ሶማሌዎችም ጭምር ነው። ከሁሉም ተጣልቶ እጋዴን ውስጥ ሲኳትን የኖረው ሰይድ መሐመድ፣ ለሸምገልና የተላኩ 32 ሰዎችን ሳይተር በአንድ ጎራዴ፣ ጉርዶ ጎርዶ ካስቀረ በኋላ እንደ አብድ በመቆጠሩ ዓላማው አልተሳካለትም። የራሱ ታጣቂዎች ሳይቀር በተደጋጋሚ ጊዜ ተበትነውበታል።

ተከታዮቹን እንደገና ይሰበስባቸው የነበረው በአስገራሚ ሁኔታ ቀስቃሽ በነበሩት ግጥሞቹ ነበር። እንግሊዞች "አብዱ መላህ" ያሉት ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። ከሁሉም በአንድ ጊዜ በመጣላቱ። በመጨረሻም አብዱ መላህ "እንግሊዞች አቆጣጠር" በ1920 ዓ.ም በኢንፉሉዌንዛ በሽታ ኦጋዴን ውስጥ በ64 አመቱ ሞቷል። ይሁን እንጂ አስከሬኑ አልተገኘም። የክልሉ መንግሥት በቅርቡ አስከሬኑን አግኝቼ ቀብሬአለሁ ቢልም፣ የሰይድ መሐመድ አስከሬን ግን የት እንደደረሰ አልታወቀም።

ሐውልቱን ስመለከት ያለኦታው እንደቆመ ከማለቤም በተጨማሪ፣ ለአርበኝነቱ ሳይሆን ለንግግሩ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ከጎራዴ ይልቅ ሳብ ባለመጨበጡ አላማውን እንደሳተ ይመስለኛል።

Scanned by CamScanner

ይልቁንስ ሐውልቱን ላይ ያስታወሰኝ ሌሎች ኢጋዴን ላይ የተዋደቁ ጀግናችን ነው። የወልወሉን አውሎ ነፋስ አዲ ነብርን፣ የቆራሌውን መብረቅ አፈወርቅንና የኤል- ዙሩን አየር ኡመር ሰመተርን...ነው ያስታወሰኝ።

ኡመር ሰመተር፣ ጣልያን አድዋ ላይ ድል ከተደረገ ከአርባ አመት በኋላ ሰመጀመሪያ ጊዜ እንደገና ድል ያደረገ የሶማሌ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ነው። ከወልወል ግጭት በኋላ የጣልያን ወራሪ ኃይልና የኢትዮጵያ መንግሥት እርቅ ሰማውረድ ባደረጉት ድርድር፣

የጣልያኑ ተደራዳሪ፣ "ኡመር ሰመተር እጁ ተያዞ ይሰጠና ሲል ጥያቄ በማቅረቡ ድርድሩ ሳይሳካ ይቀራል።

ኡመር ሰመተር ይህን ሲሰማ የተናገረው እስከ ዛሬ ሲጠቀር ይኖራል። "ከእንሬ አፈር የሚደባልቅ ቢልጅማና ሳራዱ ይኙ እንጂ ሜት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ" የሚለ መልዕክት ነበር ለጣልያን የላከበት።

ከአፈወርቅ ሞት በኋላ በጎርሰ ጉቤ፣ በቶራሌ፣ በሸዋ፣ በኤል-ዙር እና በጀጅጋ አየተዘዋወረ ጣልያንን መውጫ መግቢያ አሳጥቷል- ኡመር ሰመተር። ከአርሞ፣ ከሶማሌና ከአማራ የተውጣጣ የራሱ ቅንጅታዊ ጦር ነበረው። ይህን የጀግና ስብስብ መርቶ ኤል-ዙር ላይ በ1930 ዓ.ም የጣልያንን ስድስት ባታሊዎን ጦር፣ በሌሊት አመደ በማድረጉ ከአርባ አመት በኋላ ጣሊያን እንደገና አስከሬኑን መቁጠር ላይችል ቀርቷል። ለወሬ ነጋሪ የተረፉለት ብዙ አግራ አውጪኝ አምልጠዋል።

ጣልያን ድል ሆኖ ነጭት ከተመለሰ በኋላ፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ንግግሩን አትሞት ነበር- የኡመር ሠመተርን።

"የሀገሬን ህዝብ የፈጀው ጠላት በጀግናች ክንድ ተሸንፎ ሲሠጣ በዓይኔ ተመልክቻለሁ። የመማት፣ የመቁሰልና የመረገጥ አድል ምን እንደሆነ ተመልክቻለሁ። እንደ ንብ ከሆምሸት አየገቡ የሚነድፉ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች መሆኔ ኮርቻለሁ። በታሪክ የሰማሁትን የአደዋ ደማቅ ድል ሰማስመስከር ልጀቻቹ ኢጋዴን የጣሊያንን እንቅ ሲቆርጡ አይቻለሁ። የዚህ ህዝብ ልጅ በመሆኔ አኩራለሁ። የማዝነው ግን መላው ሶማሌዎች ተባብረው የአንዲት ኢትዮጵያ ልጅ ሆነው ባገደ ሰንደቅ አላማ ስር ሲጠቃለሉ ሳላይ መሞቴ ነው። ኡመታወርም ውስጥ ምኞቴ ይህ ነው።" ይህ ነበር የደገናው የመጨረሻ ቃል የኡመር ሰመተር ቃል።

የሰይድ መሐመድን ሐውልት ስለረ ስሄድ የኡመር ሰመተር ጀምዕ ኮኋላየ ይመስል፣ የድመት ጀርዙን እንደ ጦር ቀስሬ ወደ ኋላ እየሳጅ ነበር። ትውልዱ ዋናውን ፈለጉን የማይፈልግበት ወይም እንዳይፈልግ የሚዘምተው ሥርጉት ሴራ ማሰያ የሆነውን ሐውልት ስልፈን ስሄድን በኋላ፣ ነፍሩ ማደያ ፍለጋችን ተጠልን። በድመት አእምርሮ ውስጥ የተመላለው ሠጎብ በሙሉ ሰውርዙ በቴሌፓቲ ደርሷት ናፊል።

"ትውልዱ ጎደለኝ ወይም ፈለግ እንዳይናነው ስምን እንደማይፈለግ ይገነዛል። የማያንቀላፉት ጠላቶቻችን ሴራ እንደ ኢጋዴን ነፍጽ ተገፅ እያልትም ለሰች ከፈት ለራቱ ሰከበት ማለደን አቀማ። "ኡመደል ህገር ሰው ሶማሌዎች ኢትዮጵያን የሚወዱ አይመስለውም። እውነቱ ግን ተቃራኔው ነው። እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለአናት ሀገሩ የተዋደቀ ሶማሌ ስናር ቁጥር የለውም። እንዲውም የሶርጉቱ ዕሱ ቀጥሚ ገፈት ቀማሽ ነው።

Scanned by CamScanner

"ዘአርግዮ ኢትዮጵያዊነቱ እንዲሸረሸር ግፁ ተስርቶበታል። ይህም ሆኖ በረሃብ፣ በድርቅና በቸነፈር አሳሩን እየበላም ሀገሩን ይወዳል። በአርግዮ መገለል አልደረሰበትም ማለት አይቻልም። የተረሳ ህዝብ ነው። በቅኝ ገዥዎች ርዝራዥ አስተሳሰብ፣ ኢትዮጵያን እንደትና ንዚ ሀገር እንዲያይና በጎሳ ጦርነት እንዲታመስ ተደርጓል። ቀደም ሲል በነበረውን የማዕከላዊ መንግሥት ልል ትስስር ሰበብ አድርገው ሙሴዎቹ ራሱን ገንጥሎ እንዲያይ ሰብከውበታል። የአሁኖቹ የፖለቲካ ኃይሉች በመንግሥት ስልጣን ውስጥ ከላይ እስከታች አንድ ነገ ደልድለውበታል። ሌሎችን ባይተዋር አድርገዋቸዋል። ኮታ እንጂ ችሎታ ዋጋ ያጣበት ሀገር ነው። ይህ ነው ችግሩ። አደሉ በሌለው መሰረተ ልማት፣ ራሱን ባሳተፈ ችግር ፈችንትና በትምህርት ኢትዮጵያዊነቱን መከትከት ያሻል።"

"ልክ ብለሻል የኔ ውድ..." ማደያ ስናይ ቀጥ አልኝ እርስ በእርስ ተያይተን ወደ ነጻጅ መቅሻው ገሰገስን።

አያን ደሀና ዝቃጭ ያለበትን ቦታ ፈለገችና በሞፍሯ ትጭረው ጀመር።

"ደግሞ ነጻጅ ልታወጣ ነው ተብሎ ወታደር እንዳያዘዝሽ አልኩ በውስጤ። ዝቃጩ ላይ ቀጭ አለችበትና ቲሚን ሰቅልታው ተነሳች። በነጭ ነጣም ላይ የታተመው ጥቁር ቀለም ዝንጀሮ አስመስሏት ነበር ስትመለስ። ከዚህ በኋላ የስሪያ ሲጋት እንደማይኖርብን ተሰፋ አደረግን። ነገር ግን አውንም እርግጠኛ መሆን አንችልም።

ዘወር አስችና ተቁለጨለጨችብኝ።

"ሞክር አስቲ... ወንድ አደለህ እንዴ? ሰማለት ይሆንም የቱሊፓቲው መልዕክት አልደረሰኝም።

የሰው ጭንቅላቱ ከድመት ጭንትቱ አውተት ተድቶ በቶሱ ቢያፈጣጥልኝ ስል ተመኘሁ። መፍራቴን አይታ፣

"ይህ ዘዴም ላይሰላከለኝ ይችላል። ከዚህ በኋላ በእግር ጉዞ መቀጠል የለብንም። ንብተን ሰው እንሆናለን ብለህ አታስብ።"

"ታዲያ ምን ተሻለን?"

"አውቶቡስ መሳፈር አለብን።"

"ሰው ብሆን ኖሮ እስት ነበር። ...እንዴት ነው መሳፈር የምንችለው?"

"ሌሊት ተነስቶ፣ ከጅጅጋ - አዲስ አበባ የሚጭን አውቶቡስ አለ። ሰውን ሁሉ ጭኖ፣ የተሳፋሪ እቃ ቀርቅብ ካበቃ በኋላ፣ እኛ ከላይ ፖርቶ መጋላው ላይ እንውሰን።"

"ጥሩ ሀሳብ ነበር። ግን አውቶቡሱ ሲጀር ንፋስ መስሶን ብንነጣጠልስ?"

"እሱ ሌላ ጉዳይ ነው። የትኖውም መፍትሔ እንበን የለሽ አይደለም። ችግሩን አውቶቡሱ ላይ ከመጣ በኋላ እናያለን። ምናልባትም አውቶቡሱ እቃ የሚያስፀኔው ሌንላ ይኖራል። እዛ ውስጥ ሰርስረን እንገባለን።"

"ሴት መሰኛ ናት የሚባለው ሀሰት የለበትም። ደሙት ስትሆን ደግሞ ይብስባታል ልበል?"

ወደ አውቶቡስ ተራ ሄደን መሸንንና አውቶቡሱ ሌሊት አስኪነሳ መጠባበቅ ጀመርን። ቀፀ ሰው ወደ መሆን።

Scanned by CamScanner

ሻሸጉ

ከጅጅጋ ወደ አዲስ አበባ የሚሄደው አውቶቡስ እያቃሰተ የካራማራ ተራራን ጫንቃ በመውጣት ላይ ነው። እኔና አያን ከላይ ፖርቶ መጋላው ላይ ነን። አቃው ከተጫነ በኋላ ነበር ወደ ላይ የወጣነው። ከዛም ሌንሳው ውስጥ ተወሸቅንና ከጅጅጋ በአውቶቡስ ወጣን።

ካራማራ ጫንቃ ላይ ሆነን፣ ጅጅጋን ወደ ጌላ ቦረን ተመለከትናት። ሲሲቱ እየንጋት ቢሆንም ሙቢራቹ ገና አልጠፋም። ተሰውንቂን መሰላ ትንሀዝጋሰች። ትናንት ዱማሲ ነበርኩ። ወደ ምሥራቅ ዓይናቸችን አዞርን።

ከካራማራ ተራራ አናት ላይ ጉም ይንጉማለል። ጥቅየት ደመና ሰመጀመሪያ ጊዜ ስንመለከት፣ የአጋዴን የሰቆታ ጉሟችን እዚህ ላይ ያከተመ መሰለን።

ካራማራ በአጋዴን ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያን መክቶ ከጠላት ያዳነ ባለውለታ ተራራ ነው። በአናቱ ላይ ጉም ሳይሆን ታሪክ ይንጉማለልበታል። የሶማሊያ ወራሪ ጦር እዚህ ድረስ ተስቦ ከመጣ በኋላ ነበር በኢትዮጵያ የቀርቦ ቀን ልጆች ካራማራ ስር አፈር ድሜ በልቶ የተመለሰው። የመጀደያ ቀበና ውስጥ መግባቱን አላወቀም ነበር። ኢትዮጵያውንን ተራራ ላይ ማሸነፍ እንደማይቻል ሰማሊያኑት የተላከ ይመስል፣ በአጋዴን ሰጥ ያለ በረሃ

ውስጥ ሲጋልብ የነበረው የሶማሊያ ጦር ካራማራ ላይ ቀጥ አለ። የኢትዮጵያ ጦር ከጎኑ ሰቶ ከመጣ በኋላ ይተለያዩ የሸሹት ተሞኒ ጦሮች እየተመታ ካራማራን በማለፍ ቆሬ ላይ ነበር የማጥቃት ውጊያውን የጀመረው።

የካራማራን ጫንቃ አውቶቡሱ እየወጣ ላለ ነበር የተላውን ትዝታዬን ተስቃሽ በዶን ያስታወሰኩት።

"...ወደ ፊት በሉሰት
ይለይለት!
ወደ ፊት በሉሰት
ይለይለት!
የጀግና ሰው ከብሩ
ሻር ድንበሩ!
...
የጠላትን አንሮ
በስደፍ ሰግውሰት
ቢያስፈልግ በጎንጸ
ልቡን ሰመስንመት
ወደ ፊት በሉሰት
ይለይለት!
ወደ ፊት በሉሰት
ይለይለት!
...
የምን ጠላ ወላ
የምን ወደ ጠጂ
ጠላትን መጨረስ
ውናርን ነው እንጂ!
ወደ ፊት በሉሰት
ይለይለት!_"

Scanned by CamScanner

ይህን ቀስቃሽ ዘፈን፣ ሠራዊቱ በራዲዮ በቀጥታ እንዲሰማ ተደረገ። ከዚያም "ወደፊት"...ተባለ። የማጥቃት ትእዛዝ በዘፈን የተላለፈለት የመጀመሪያው ሠራዊት የኢትዮጵያ ሠራዊት ሳይሆን አይቀርም።

ከዚህ በኋላ፣ ከቆራ እስከ ካራማራ ያለው ሽለቆና ሸንተረር እንደ ቆሎ ተዘራበት። አስከሬን ተደራረበበት። ከባድ መሣሪያዎች አጋሰበት። ታንኮች አኘከሱበት። መድፎች እሳት ተፋባት፣ ሞርታሮች አጓሩበት። የስትሬላ ሚሳዬሎችና የዙ 23 መትረዪሶች የካራማራን ሰማይ አረሱት። የመትረዪስ ጥይት የሚያዘንቡ ሄሊኮፕተሮች ተንደቀደቁበት።

በዚህ የእናት ሀገር ሰማይ ላይ፣ እነ ብርጋዴር ጀኔራል ሰዝሠ ተፈራ፣ ኮ/ል በላይህ ጴጥሮስ፣ ኮ/ል አምሃ ደስታ፣ ኮ/ል ንጉሤ ዘርጋው፣ ብርሃኑ ውቤነህ፣ ንጉሤ ዘርጋው፣ ተጫነ መስፍን፣ ተሰፋ ደስታ፣ መስፍን ኃይሌ፣ አሸናፊ ንብረጻድቅ፣ ኃ/ሚካኤል ብሩ፣... እንደ ንብ ተናደፋበት። ሚግ 21 እና ኤፍ.5 የጦር ጀቶቻቸውን እንደ ንሥር አሞራ አስንፋበት። የሶማሊያን መራሪ ጦር ካራማራ ላይ አይቀጡ ቅጣት ቀጡት። በዚህ ተራራ ስር በአንድ ቀን ብቻ ከሳት መቶ በላይ አስከሬኑን አስቆጠሩት። በአየር ላየር ትንቅንቅ የጦር ሚንቹን ወደ ነበልባልነት ቀየሩበት። ብ/ጀነራል ሰዝሠ ተፈራ ብቻውን አምስት የሶማሊያን ጀቶች ወደ ነበልባልነት ቀይሯል። በምድር ደግሞ የእናት ሀገር ልጆች ከጠላት ጋር በጎንጎ ተማትረዋል። የኩባ ዘማቾች ሳይቀር በካራማራ ተራራ ስር ሰቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ተዋድቀዋል።

ከዚህ በኋላ ነበር የአጋዴን ቀንጥሮች ልብሱን ወደኋላ እየገፈፉት እግሬ አውጭኝን አስከ ሞቃዲሾ የቀጠሉው።

ከራማራ የዚህ ሁሉ ቃራር መስሉ በዝሞታ ወደኋላችን ቀርቷል።

በአጋዴን ምድር ላይ የፈሰሰውን ደምና የተከሰከሰውን አጥንት ከካራማራ በላይ ምስክር የለሰ ይመስል ጉም ጧሪውን ተሸፋፍኖ ይተክላል። አሁንም ድረስ፣

"...ተጉዞ ተጉዞ እንደ ጀፌ አሞራ
መመለሻው ጠፋው ያንሩ ጎፍኖ የሚለውን ዜማ
የሚያጉተመትም ይመስላል።

አውቶቡሱ ወደፊት ሲገሰግስ የእኔና የአያን አእምሮ ግን ከካራማራ በር ላይ ቀረ። የአጋዴን ምድር ሰቀቃ አንቆ አስቀረን። ቻው ቻው አጋዴንያ!

አውቶቡሱ ባቢሌን አልፎ መጋላውን ቀመሰ። አደጋ - ሐረር ድረስ ካለው ሰማኒያ ኪሎ ሜትር ውስጥ የምሳ ያህሉን ተጉዘናል ማለት ነው። ሐረር ለመግባት ገና ሰላሳ ያህል ኪሎ ሜትር ይቀረናል።

ከባቢሌ አለፍ ብሎ የቁልቃ ሽለቆ ይጀምራል። ጎለምራቂዉ ሽለቆ እየተባለ ይጠራል። የድንጋዮች ተአምር የሚታይበት ምድር ነው። በአስገራሚዎቹ የአሳተ ፕሮሬ ቋጥኞች ትርኢት እየተገረምን ስናልፍ፣ እነና አያን ሰው ቀንሰን ኖሮ እንተፋፈር ነበር።

ከተዛዙሰት ቋጥኞች ውስጥ የወንድን ብልት መስሎ የተገተረው ይገኝበታል። የምድር ብልት ይመስላል - እንደ ጠዋት እንቡን ተከትር ሽቅብ ሰግደን የሚያይ ቋጥኝ። የብልቱ አናት ከጠጉ ላይ በምን ተአምር እንደቆመ የትኛውም ሳይንቲስት ሙተንተን የሚችል አይመስለኝም። በወንድ እና በሴትነቱ መሃል ጣት የምታክል ነገር ነች

Scanned by CamScanner

ታሳቀን ቋጥኝ ለዘመናት ሚዛኑን የጠበቀችው። አሰከ ላሬ ከርከርና ፈቲጥ ያልሸኘውን እንትን አለናነው።

ድንጋይ የፈሰሰበትን ምድር አልፈን ስናቢቶ፣ አስገራሚዎቹን የተራራ ቅርጾች እያየን ወደ ሐረር ገሰገስን። አውቶብሱ ሰቀርስ ሐረር ሲቆም እኔና አያንም ወጥ ይድረስን ብለን ወረድንና ሐረር ከተማ ውስጥ መልቀምቀም ጀመርን።

ቤታቦቂቷ የሐረር ከተማ ውስጥ የሐረር ሰንጋ ኮሚዕላቸው እውቅ ሥጋ ቤቶች ካንዱ ደጅ መጥናት ቀጠልን። አንዱ ቁርጥ የሚበላ ሰውዬ እየመተረ ሲጥልልን ሰው እያለሁ ተከብሬ የሸኘሁት ሐረር ድመት ሆኜም ፍቅሯን ባለመክልከሏ በድመት ልቤ መረቅኳት።

ሰው እያለሁ የጀኃል ግንብንና የእውቀ ባለቅኔ አርቱር ራምቦ መኖሪያ የነበረውን ቤት መጎብኜቴን አስታውሳለሁ። ከሐረር ፍቅር ተነድፈ ወደ አዲስ አበባ መመለስ ስላቃተኝ ራስ ሆቴል ውስጥ ለበርካታ ቀናት ተቀምጫለሁ። በሆቴሉ ጎደጎዳ ላይ በሚገኙት የአሰ ፈሰን ሰላም ስዕሎች ፍቅር ተይዤ እንደነበርም አስታውሳለሁ።

አውቶብሱ ከመንቀሳቀሱ በፊት ፖርቶ መንላው ላይ እኔና አያን ወጥተን አደፈጥን።

"ሰው ከሆንኩ እመሰሰብሻለሁ" አልኩ በውስጤ አውቶቡሱ ሐረርን ለቅቶ ሲወጣ ወደኋላ ዞሬ።

አውቶቡሱ መነሻን ቀጥሏል ወደ አዲስ አበባ። ከሐረር ቀጥሎ አስማያን አለ። ደንገጎ ጫጉት ከር ወደ ቀኝ ደራሽዎን ትቷት ወደ ቀልቢ ገሠገሠ። ከዛም ካራሚሌንን

ሰራኛን፣ ሄርኖንና ፈለንቆን አልፎ አሰበ ተራሪ ቆመ። እኔና አያን እዚህ አልወረድንም። ካንዱ ሥጋ ቤት ዙር ላይ በንቀሰፈሰሎ ጥሱን ይዟዟል ብለን በመሲንታችን ተሳፋሪዎች የሚተማምሱትን ተማምሰውና ውሃ ይዤው አሰኪመሰሱ የፖርቶ መጋሳውን ኬንላ ሙጥኝ ብለን ጠበቅን።

አውቶብሱ ተንቀሳቀሰ። ሜኢለን፣ አዮሽን፣ መተፃራን፣ መለንጪቲን... ሲያልፍ ውሱ ናዝሬት አሰኪጃ አኔና አያን ፖርቶ መጋሳው ውስጥ እንደተሸንኮን አንቀላፍተን ነበር።

ድመት ሲተኛ መላ አካሉ እንደውሃ ፍሰስ አለምጊል ነገር አለመኑን ረሰቶ ነው። ምሥራቃውያን የድጋን ጥበብ ከድመት ሳይቀስሙት አይቀርም። እንር አዶራው አውቶቡስ ናዝሬት ላይ ጥቂት ስቶመ በኋላ፣ ቢረጭ መንገድ በከሉ ወደ አዲስ አበባ ይሰንፍ ጀመር።

የሚታ ማታ አዲስ አበባ ገባንና መስቶል አደባባይ ላይ ተራገፍን። አብሮት አደባባይ በንደርስ የሌጋዲን ትውስታዬ ይብልጥ በረታ። ስኔ 18 ቀን 1969 ዓም በዚህ አደባባይ የነበረውን ሰልፍ ልደ ሆኜ ተመልክቻለሁ። ህዝባዊ ሠራዊቱ አያዜመ የገበረው ቀሰቃሽ ዘማሪ አውንም ይደርሳ የተንቀረቀረ መሰለኝ።

"... ይህ ነው ምቂቱ
እኔ ቤሕይወቱ
ከራሱ ይሬት ለሊተዮጵያ እናቱ..."

በብዙ ሺዎች የሚቆጠረውና፣ ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል ቀርቶ እናቷን መውደር የሚችል ሠራዊት ገንባታስች ተበላ የታማኝበት ህዝባዊ ሰራዊት ሰልፍ በድመት ዓይኔ

Scanned by CamScanner

ላይ ድቅን ብሉ አሙት አደባባይ ላይ ጥቂት ከቆምኩ በኋላ እያጋን አስከትዬ ወደ ቤቴ ከንፍኩ። ልቤ መምታት ይመረ። አስማቱ ባይሰራስ? እንደገና ሰው መሆን ባንችልስ?

ሚጌ

አዲስ አበባ እያንዳንዷች ነው። መሸቷል። ከቀበና ወንዝ ማዶ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤቴ ደረስን። የሁለታችንም ልብ እየመታ ነው። ዶኖ ዝናብ እየወረደ ነው። ሰማዩ በመብረቅ ልባችን በሥጋት ይታረሳል።

የሚውን አጥር ተንጠላጥለን ገብንና ከመኖው ቤት ጥግ ተወሸቅን። ዝናቡ ቀስ በቀስ ጋብ አለ እንጂ አላቆመም። ግቢው ውኖ ረግፎ ብሏል። ልጆቼ እንዴት ሆነው ይሆን? ጥያቄው ስጠፋ በናፍቆት ሳይናቸው ጎድጉዶ ይሆን? ውሻ እያለሁ እንደተፈጠረው ሞቷል ብለው በዘበን ተቆራምደው ይሆን? ... ከመኖው ቤት ውስጥ ድምጽ የሰማሁ መስሎኝ ጆሮዬን እንደ ጦር ቀሰርኩ።

"ወይ ድፍረትሮ ይላል በተደጋጋሚ ሙሮ አሙ ዘወኖዬ። እስከ ዛሬ ከኔ አልተለየም። ደሀነቱ ከፀናን አላስጣለውም።

"የድፍረትም ድፍረት እንጀሮ ቀሰብ ናት ሰራተኛዬ። የዛሬ አራት አመት አካባቢ ከሙዳት ወደ ሰውነት ከተለወጥኩ በኋላ ልጆዬንና አነሱን ይዤ ከዘር ወደዚህኖው ቤቴ የመጣሁት። ያኔ ሚስቴ ገደኖዬን አግብታ ነበር የመሰቀኝ። ደግሞ ዛሬ ምን ተፈጥሮ ይሆን? የጌ ጉሮ አያልቅም ሙዩም።

"እንዲሁ ይቅር ይለኛል ብላ ማሰብም በራሱ ተአምር አይደለምኮ ይላል ሙር ዘግርምት።

"ደፋር ናት ውሙ ደፋር ናትኮ ተላለች ቀሰብ።

"ያን ሁሉ ወደል እንዴት ይረሳልኖል ብላ አሰበች በፈጣሪን! ... ሰው ሁሉ ሳይኑን በጨው ማጠብ ይችልበታል! በላይ

Scanned by CamScanner

ሆና ሳለ የተበደለ መስሎ እንደሚቀርብ ሰው ልዩ ችሎታ ያለው ያለ አይመስለኝም።"

"ዝባኪ ላይ ያውም ዓይኖውን፣ ያውም በሞድር ላይ እንደኖ ባለንጣ የሆነውን ሰው መወሸሚ ላይቀር፣ በኋላ ደሞ ላይሞት ሞቷል ብላ በላዩ ላይ ማማቷ ሳያንስ፣ ... አሁን ደግሞ ሁሉን ንብረቷን ሻሸጣ አፍንጫሽን ላሽ ካላት በኋላ መምጣቷ... ከኤፍራታ በላይ ሞድር ደፋር እንደለለ ያሳያል።"

"ሁልጊዜ ይቅርታ ይደረግልኖል ብሎ እንደሚያስብ ሰው ደደብ የለም። ደደብ ናት፣ ሙት መሮ... ኤፍራታ ማለት ወፍ ራስ ነገር ናት። ያን ሁሉ ንብረቱን ሙልጭ አድርጋ በዋና ወላቱ ካስወሰደችበት በኋላ፣ በራሱ አሏ ላይ ከማነጠችበት በኋላ፣ ይቅርታ ሳይጣት በቀልን ለፈጣሪ ሰጥቶ ሁሉንም ትቶላት፣ ልጆቹን ይዞ ከወጣት በኋላ፣ አሁን ያ መናጢ ሜንጦ ጉድ አድርጓት ሲሄድ ዓይኗን በልጨው አጥባ ይቅር በላኝ ብላ መምጣቷ እንዴት ያለ ድፍረት ነው?"

"ጋሼ እንደገና ይቅር ካሏት ይገርመኛል፤ በጣም ይገርመኖል።"

ነፃኛ። ኤፍራታ ወደቢሀኖው ህይወቱ መጥታለች። ያ ከፉ ወላቱ ሜንጦ ያላትን ሁሉ ሻሽጦ ካገር ጥሏት ጠፍቷል። ከአመር ዘሰማሁት መረጃ መሰረት፣ እስያ ደግ አደረገ ስል በውስጤ ምቤ ረገጥኩ። ሰው አስዘሠን ቻኮልኩ። የደሙት ሠራ አስኪቀም አሳት ሰዘልኩ፣ አሳት ጎረስኩ። አያንን አስከትዬ ወደ ጥናት ክፍሌ በረርኩ። ተቀልፏል። በሆት ንብዩ ያንን ከአውራነት ወደ ሰውነት የሚለውጠውን አስማት ሳገኝሁት?

ሰባኒ

አልነጋ አለኝ። የጥናት ቤቱ በር አስኪለት፣ ብይ የመሳሰሉ ዓይናቹ ሲንከራተቱ አደሩ። እንዴ ሰማን እንዴ ምድሩን ሲላ ጊዜ ደግሞ በር በሩን ስመለከት አደርኩና አይንጋ የለም ነጋልኝ።

አዲስ አበባ እንደለመደባት መንሚሚት ይመረኝ። ከሮት ካለ ቤተክርስቲያን መዝሙር ይሰማኖል።

"... አሰፍሱት በንቱን
ማዕበሉን..."

ከመስጅድ ደግሞ አማን።
"አላሁ ወአክበር"

ውሾች ማለዘን ይመሩ፣ የታክሲ ወያላዎች ተሳፋሪ መጮራት ይመሩ፣ ሥጋ ቤቶች ቢላ ማሩጨት ይመሩ፣ ህይወት እንደኖ...

ከጥናው ቤት አንዲት ሴት ስትወጣ ተመለከትኩ። ኤፍራታ ናት። አስንት ጊዜ በኋላ አየኋት? ሐምራዊ የሴቷት ልብስ ለብሳለች። ባጥንቷ መቆሚን ያየሁት የጥናት ቤቱን ለመሠራት ባጠጪ ስታልፍ ነበር። የሆነ ነገር ታንቧረቆብኝ ምን እንደሆነ አይሰማኝም።

Scanned by CamScanner

የኖናት ቤቱን ከከፈተች በኋላ፣ የሆነ እቃ አንጠልጥላ፣ አሁንም እንቅርቅሮውን እንደቀጠለች ተመለከች። በጋራ ወርሃን ፊቷን ተመለከትኩት። መንፈሷ ተሰብሯል። ያ እንኩይ ይመስል የነበረ ትንሣኤ ከክቷ የተነሳ እንደ ዛቢለ ቂየኝ ንሣል። ለእኔ የወረወረችው የከሀደት ጦር ተመልሶ እንደወጋት በግልፅ ይታወቅባታል። ወደ ሞናው ቪላ ስትገባ ኋላዋን ተመለከትኳት። ያ ሞንሳላ የነበረ ጸሊዋ ሚሸ እንደ ጣራያ አጥንቷ ላይ ተሰጥፏል።

ባንድ በኩል ሀዘን በሌላ በኩል በቀል ሰንጎ ያዘኝ።

ምን ልትሠራ መጣች? ለምን አትተወኝም? ለምን?! ለምን የራሴን ህይወት እንድናር አትተወኝም? አንዳንድ ሰዎች የማንግርባቸው ስህተቶቻችን ናቸው። እስክሰተ ሞታቸው እንደ ይራት የሚከተሉን ጭራዎች። የድመት ፀጉራ ቆመ። ወደተከፈተው በር እንደ ጥይት ተተኮስኩ። አያገም ተከተሰችኝ። በተዋታ የነሰንስኩት የአስማት ጥቅሉችን ወደማስቀምጥበት ሳጥን ነበር። ተከፍቷል። በድንጋጤ ደርቂ ቆምኩ። የአስማት ጥቅሎቼን አውጥታ ጥላቸው ይሆን? ዘልዬ ሳጥኑ ውስጥ ገባሁ።

ሰባኛ

የአስማት ጥቅሎች የሚገኙበትን ሳጥን በደመ ነፍስ ስተረማምሰው ቆየሁ። ሳጥኑን ለምን አፈተችው? ምናልባት የተፈረመበት ቼክ ፍሊጋ ይሆናል። አርሷ ለእኔ ገንዘብ እንጂ ሌላ ምን ፈልጋ ታውቃለች? ያ የድሮ አመሏ በድግምትም በጠበልም ይለቃት አይመስለኝም። ያ ሚንጠ ጥሪት ገንዘቧን በልቷት፣አርቃኗን ጥሞሟ አስቀርቷታል። ክፋ እንኳ አለመግሯ ይገርማል። የከሀዲትን ጀዋ ተገንዝቧ እንኳ ከክቱ ተጣሪ አልታቀበችም። ከሀዲትን የመጋት እንጂ የማጣጣም አትም ሳይኖራትም፣ ያ ከሃዲ ስለነዳት ደስ ብሎኖል። ከሃዲዎች በሰፈሩት ቁና ሲሰፈሩ ኮማየት የበለጠ ስተከዳ ሰው ካሳ ያለ አይመስለኝም።

በአርግጥ ኤፍራታ ከሳጥኑ መክሲት እንጂ አውቀት አለመፈለጓ ጠቅሞኛል። ጥቅሉችን አተረማምሳ ቢታበታ፣ የፈለገችውን ቢታጣ ሳትቆልፈው ሄዳለች። ለአርሷ እነዚህ ጥቅሎች ተራ መጥቀሱች ናቸው።

ጥቅሎቹን ተራ በተራ ዘርመት ጥናሬ እየተረተርኩ መመልከቴን ቀጠልኩ። አያን በነሮ ቅንድቧ ጉድንድ ሥር የተቀበሩ ዓይናጅን በልጥጣ ትመለከተኖለች። ሰው የመሆን ፕንቷ ከእኔ ላያይል አይቀርም። ወደ ድመት ከሚቀይረው አስማት ቢታች ምልዋጡኝ ተመለከትኩት። እንደና ወደ ሰው የሚለውጠውን አስማት። ከደስታዬ

Scanned by CamScanner

ብላት በስሜት አስማቱን ላስኩት። አያንም በድመትኛ ፈነጨች።

"... አዛሄል አዛሄል አዛሄል...." ሲል ይደጋገማል አስማቱ።

"...ኩርናስኤል ኩርናስኤል ኩርናስኤል
አብሆስ አብሆስ አብሆስ
ማራስ ታራስ ጋማስ
ኤላስ ኤላስ ኤላስ
ላልመን አልመን ላሊመን
ሙኪን ላኪን አኪን
ሚጥ ሚጥ ሚጥ
እም አንስላ ሃብ ሰብዕ
ሚጠን እምአንስላ ሃብ ሰብዕ
ቤታ ሌታ ሴታ
ሚጠን እምተዋርዶ ሃብ ኩሰር
ዮርኤል ሱራኤል አዘኤል
ሚጠን እም አርዋ ሃብ ሰብዕ
በርዶልኒስ በርዶልኒስ በርዶልኒስ
በርዶለሊስ በርዶለሊስ በርዶለሊስ
መግራጻ አግራጻ አግራጻ
ሚጠን እምአርዋ ሃብ ሰብዕ..."

የአስማት ጥቅሱን ከሳጥኑ ይዤ ከመጣሁ በኋላ መሰሉ ላይ በርግቼ አነበንበው ጀመር። አያን እንደ ባለፈው አልከበላትም። ከውስጧ የፈንቱላት ሰው የመሆን ስሜት እያንሳንሱን ቃል በየጥና እንድታይ አደረጋት። ሰው የመሆን ጥማት... በአፈ እንስላ ታነበንብ ጀመር።

ሻቢ

ከውጪ እንደገና ጾፍ ዝናብ ይወርዳል። የመሸረቁ ብልጭታ በመስኮት በኩል ሲገባ ነበልባል የሚስተዘን ይመስላል። አስማቱን በደጋገመው ቁጥር ነንድጓዱ እያየለ መጣ። ምድሩ በነንድጓዱ ሲርገበገብ ሰማዩ በመሸረት ሲናጥ እኔና አያን ሰው የመሆን ምጣችን ቀጠለ። ምጣችን ጠና። ሰው የመሆን ምጥ።

አያን አስማቱን እያጠናች ላለ፣ ትውልዱ በሙሉ ይህን አስማት ቢያውቀው ስል ተመኘሁ። ሰው የሚያደርገውን አስማት። በውስጡ የሸሸገውን አውሬነት የሚያስወግደትን አስማት። የሰው መልክ የነሳውን የተሸፈነ አውሬነት የሚነቅልለትን አስማት። ሰውነቱን ያረከሰውን አውሬነት ታቅፈውን መንፈስ አርቃን የሚያወጣለትን አስማት።

ሳስቴት... ድመት ራስ ሴት... ወይ ድመትነቷን ወይ ሴትነቷን የሚያረጋግጥላትን አስማት... ሳቢያንት... ወይ ሰውነቱን ወይ እባብነቱን እንዲነጥል የሚያደርገውን አስማት... ትውልዱ ቢያውቀው ምን አለበት?

ሰባሲው ... እንዲህ ብሎ ቢሰጠስ?

"ሳስቴት ሆይ ... ሞንትላትሽን የሞላውን አውሬነትሽን ተይ... ሳቢያንት ሆይ ... ጥማሽ አውሬነትህን ላል... ሰው ሁን! አውሬው ሆይ ትውልዱን ገፀበህ ውጣ ... የታደረውን የተከደረውን ኢትዮጵያዊ ሰው መደ አውሬነት የቀየርህ መንፈስ ውጣ ... በሥላሴ ስም ውጣ በጌታ ስም ውጣ ሰለ አማህ ፀለህ ውጣ..."

Scanned by CamScanner

... ጉርምርምታው ምድርን ሲያንቀጠቅጥ መቢረሳ ሰማዩን ሲንጥ እኔና አያን አስማቱን መድገማችንን ቀጥለን ነበር።

"..... ዜናዊ አርዊ አክሌ
ጸራቅሊስ፣ ቱርናስ፣ ኢክናስ
ሚጥ እምአርዊ ሃበ ሰብዕ
ሚጥ እምግባረ እንስሳ ሃበ ምግባረ ሰብዕ..."

በዚህ ቅፅበት የጥናት ክፍሉን የሚያርበደብድ ንውፅውፅታ ተፈጠረ። መብረቅ የወደቀ ይመስል አካባቢው ድብልቅልቅ ወጣ። ወደቡ ጣሪያውን ሊነቅለው ደረሰ። የአስማት ጥቅሉ ወደላይ ተንሳፈፈ። ሁለታችንንም የማናውቀው ኃይል አየር ላይ እንሳር ከመጽሀፍ መደርደሪያው ጋር አጋጨን። የማስታውሰው በአያሌ መጻህፍት የተሞላው መደርደሪያ ወድቆ፣ ወለሉ በመጻህፍት ሲሞላ ነው። ከዚህ በኋላ የሆነውን ሁሉ አላስታውስም።

፱

ከሰንታት በኋላ ካለሁበት ልዩ ዓለም ውስጥ ነቃሁ። የተጫነኝን የመፃህፍት ክምር ፈንቃትዬ ተነሳሁ። መለመላዬን ነበርኩ- ዕርቃኔን። አላመንኩም። ወደ ሰውነት ተሰውሬለሁ። በስስት ንላዬን ጻፍኩት። እንደገና ወደራሴ ተመልሻለሁ- ወደ ጂጂሞስ ዶራ (ይቅርታ ወደ ደዝተር ጂጂሞስ ዶራ)።

እርቃኔን ነኝ፣ ልክ በገነት ውስጥ ከብሩን እንደተገፈፈው አዳም መለመላዬን ቆሜአለሁ ሀፍረተ ሥጋዬን በሁለት እጀቼ ከድኜ አያንን መፈለግ ጀመርኩ። እርሷም እንደኛ ወደ ሰውነት ተሰውላ ይሆን? ልቤ ይመታ ጀመር።

ከሰንት ጊዜ በኋላ የልቤን ምት አዳመጥኩት በሞቴ?... በወጣትነቴ ፍቅር ሲይዘኝ ነበር እንጂህ ልቤ መምታቱን የማስታውሰው። ያሁኑን አያርገውና ያኔ የልብ ምት ነበረኝ። ዛሬ ካልደከመኝ በቀር ፍፁም የልብ ምት የሰኝም። ለካስ የልብ ምትም ይናፍቃል። ትክክለኛ ስሜት፣ ትክክለኛ የራስ ጠረን፣ የሚወዱት ሰው ጠረን ለካስ እንጂህ ይናፍቃል። ስንቱ የልብ ምቱ ተዘቅዝ ይሆን? ስንቱ የራሱን ጠረን በትኖ ይሆን?

ወለሉ ላይ የተበረገፈውን የመጽሐፍ ናዳ እየደለለኩ አያንን ማሰስ ጀመርኩ። የለችም።

ተጣራሁ።

"አያን! ..." የራሴ የድምጽ ማሚቶ በሆነው የጥናት ቤት ውስጥ አስተጋባ።

Scanned by CamScanner

"... አያ! ..." የሰማዙ ጉርምርምታ እና ንውፅውፅታ ተከተለ። የአያን ድምፅ ግን የውሃ ሽታ ሆነ።

"አያ! ... አያ.... አያ!..." ደጋግሜ ብጮይል ተጣራሁ።

ከደቃቂዎች በኋላ የሚያቃስት ድምፅ ሰማሁ፣ ከወላያቸው የግድግዳ ጥግ ነው። በፍጥነት ሄድኩ። አያን አርቃኗን ቀማለች።

"ሰው ሆንክ!.... ተሰወርኩ!... ላንክ!... ይሀን ማመን አልችልም!...." ድምፅዋ ይንቀጠቀጣል፣ ሰውነቷ ይንዘፈዘፋል። አቀፍኋት። ትኩስ እንባዋ በደረቴ ላይ ሲንፎለፎል ታወቀኝ።

"አሁንም ድረስ አንገቱ ላይ ሊያርፍ የንበረው ፋሰ እየታየኝ ነው። በህይወት አለሁ አርግጠኛ ነህ?..."

"እም አለሽ... በህይወት አለሽ አያን ውዴ ...."

"አርግጠኛ ነህ?.... "

"እም አርግጠኛ ነኝ፣ ከፈለግሽ ራስሽን በመስታውት ታይዋለሽ።"

" መ... መስታውት የታለ?...."

"ቆይ ልብስ ላምጣልሽ..."

ወጥቼ ወደ ዘወኛው ቤት ሮጥኩ። በዝናቡ ውስጥ አርቃኔን ሲያየኝ ሰይጣን የመጣ መስሎት መደንገጡ የማይቀር ነው። የዘወኛውን ቤት በሀገ ተጠልዬ ተጣራሁ።

"መሮ! ... መሮ!..... መሮ!...."

"አቤት!" አለ መሮ ርክር ኩተንሳ በኋላ። "ማነው?"

"እኔ ነኝ መሮ... ዲዲሞስ ነኝ።"

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!..." መሮ ፀሩን ከመከፈቱ በፊት ሰይጣን የጠራው መስሎት ጸሎት አደረገ።

"እውነት ከሆነ ደግመህ ተናገር!"

"እውነት ነው መሮ... እኔ ዶክተር ዲዲሞስ ዶራ ነኝ።"

ጥቂት አሰመጠና፣

"በስመ አብ በል!" አለ።

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!" ያዘዘኝን ፈፀምኩ።

መሮ በዝግታ በሩን ከፈተና አያ ተቀምጣበት የነበረውን ግራና ቀኝ ተመለከተ።

"መሮ ... እንዴት ነህ?"

ባትራውን ተግ፣ አድርጎ አበራብኝ።

"ጋሼ ... አረ ምን ጉድ ነው?"

"አትደንግጥ! ..."

"ምነው አርቃንምን?! ... ጋሼዬ አረ ምኑን ነው ምመለከተው? ሰለሊ ለነ ቅድስት... ማን ዘረፈው ...?" ራቱን ወደጋላ አዙር የለበሰውን ብርድ ልብስ አተለለኝ።

"ወደቤት ግባና ልብስ አምጣልኝ።" አልኩት በለዘኝ ብርድ ልብስ አርቃኔን ተግኜ ሳበቃ። እየሮጠ ወደ ቅልቀ ቤት ገባና ከደቂቃዎች በኋላ ልብስ ይዞልኝ ተመለሰ። ለላ ልብስ እንዲያመጣልኝ ወደ ቅልቀ ቤት ላኩት። አሁንም ከደቂቃዎች ቆይታ በኋላ ለላ ሙሉ ልብስ ይዞልኝ መጣ። ይህኛው ለአያን ነበር። ወደ ጥናት ክፍሉ መለስኩት።

Scanned by CamScanner

የወንድ ልብስ ቢሆንም ሙሉው ሱፍ በእያን ቁመና ላይ ሂዶ ልክክ አለ። እንዲያውም አማረባት።

ፈገግ አለችና፣

"እንደምና ሰው ሆንኩ ማለት ነው?" አለች ያችን የአጋጁን ነጭ ጥርሷን እያሳየችኝ። "በፍጹም ላምን አልችልም፣ እንዴት ላምን እችላለሁ?፣ ... ራሴን የሆንኩ ስላልመሰለኝ መላ አካሌን ስነክካ ነበር፣ ቃላት ይህን ያህል ኃይል ያላቸው አይመስለኝም ነበር። አውራም ሰውም የሚያደርጉት ቃላት መሆናቸውን ሰማመን በእኔ ህይወት ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል።"

"ይገባኛል ይህ እውነት በእኔ ህይወት ውስጥ ተደግሟል" አልኳት። "ቃላት አውራም ሰውም ያደርጉሱ።"

"እኔምልህ..." አለች እየተቁለጨለጨለች። "ዝያኔ ሲያነሷት የነበረችው ሴት... ሚስትህ ናት? ማ... ማለቴ ይቅርታ ልትጠይቅህ መጥታ ነው?...ማ... ማለቴ ይቅርታ ልታደርግላት ነው?..."

"በፍጹም ይቅርታ ላደርግላት አልችልም።"

"ሰምን?..." ጠልቀው በሚመረምሩ ዓይኖቿ ጠልቃ ተመለከተችኝ።

"ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ይቅርታ አድርጌላታለሁ። ታሪካችንን በዝርዝር አጫውቼሻለሁ። ያንን መድገም አይጠበቅብኝም።" ይህንን ስንነጋገር ምድሩን ያጨላለመው ዝናብ እያባራ ነበር። ጀንደት አበቃ።

ወጥቼ አዲሱን ቀን ሰማዩ ላይ ፈሰንሁት። ወገግ ብሏል፣ ፈገግ ብሏል፣ ከጎላዬ እጅ ሲነካኝ ተሰማኝ ሾርኩ። በእንባ ከተሞሉ ዓይኖች ጋር ተጮላለምኩ።

"ይቅር ባለኝ፣ ይህን ሰል እያፈርኩ ነው። ይህን ሰል በፀፀት ውስጤ እየታመሰ ነው። ላንተ የማይገባውን ሁሉ

አድርጌብሃለሁ፣ ጠላትህን እገብርብሃለሁ..." አፍራታ ናት። ተንበረከከች።

እያን ኮኮናት ከፍሱ ስትወጣ ተመለከትኳት። ነጭ ሱፍ ሰውነ ሳቢሳ መስላለች። ሱፍ ሴት ላይ እንዲህ ያምራል እንዴ? የሰበሰችው ነጭ ልብስ ንፅህናዋን ለማሳየት ቃሬር የቆመ ይመስል መልአክ አስመስሏታል።

የአፍራታ ቀንድ ግንባሯ ላይ ሲቆም ተመለከትኩ።

"ይህቺ ደንሞ ማን ናት?!" ከተንበረከከችበት ፈጥና ተነሳች።

"ማንስ ብትሆን? ..." በለሆሳስ መለስኩላት። "ይህ አንቺን አይመለከትም!"

"አይደረግም!"

"ተደርጓል፣ ላንተ ነው። ሠርጋችን በቅርቡ ይደገሳል። ከፈሰገሽ መገኘት ትችያለሽ፣ ተመርተሻል።"

እያን ፈገግ አለች፣ አፍራታ እሳት ለበሰች።

"እንታለሁ፣ የባሌን ልብስ አውልቂ አንቺ ስድ! ከፈታሽኝ አራት አመታት ተቆጥረዋል፣ አይደለም እንዴ?"

"እንግዲያውስ በትዳር ላይ ትዳር በመመስረትሽ ወንጀለኛ ነሽ።"

"አይደለሁም... ሞተህ ነበር።"

"ሙቼ ታዘርሽኝና ነው?"

"ባልተወርሀም ሞተህ ነበር።"

"አልምትስም፣ ሞተሽ የነበርሽው አንቺ ነሽ። በምድር ላይ የሚመላኘንና፣ በህፃቴ ብቻ ምራቁን ሲውጥ የኖረውን ባደኛዬን አንበተሽ ነበር የጠፀቅሽኝ፣ ይህ ሀገር የሚያውቀው ሀቅ ነው። የእኔ ስህተት በስህተት እንቺን

Scanned by CamScanner

አስመገደሉ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ከመገደል የበለጠ በቀል ነው! ይገባሻል አይደል?...ስለዚህ የሞትሽው እንቺ እንጂ እኔ አይደለሁም።... እኔ አንቺን ብሆን ኖር እኔን ፍሊጋ አልመጣም ነበር። ሌላው ይቅርና ልጆችሽን እንኳ በዚር ብሎ ያሳሰበ ልብሽ ዛሬ ምን ተፈጠረና ነው እኔን ፍሊጋ የመጣሽው? ... የቀረችኝን ልብ ልንረባት! ተይኝ! ከሀያውቱ ውጭልኝ!" በዚህ ሰዓት ድምጼን የሰሙት ልጆቼ እየተንደረደሩ ደረጃውን ሲወርዱ ተመለከትኩ።

"አባዬ!... አባዬ!..." ነፍሳቸው በደስታ ሲቃ ልትመነጠት ምንም አልቀራት።

"አባዬ አለ! አልሞተም!..."

መላእክትን ይመስላሉ። ተንበርክኬ እጀን ከፍቼ ጠበኳቸው። ተስገብግበው አቀፉኝ። እንታቸው ስር የማውቃትን፣ ማንም ኪሚስት ሊተምጣት የማይችል ጠረናቸውን ማጣጌት።

"እማዬ አኮ ሞቷል ብላን ነበር።"

"እርሷ ሁሌም እንደዚህ ነው የምትሰው። እናንተን ትቼ ላለመሞት ብዬ ብዙ ችግር አልፌ ነው የመጣሁላችሁ። ህልም ያሰው ሰው በክንቱ አይሞትም። ህልሞቼ እናንተ ናችሁ።"

"አባዬ ... ከዚህ በኋላ ትተሽን አትሄድም አደል?" አለች ሴቷ ልጀ ጥብቅ አድርጋ አቅፋኝ።

"በፍፁም ትቻችሁ አልሄድም። ሰሥራ እንደሄድኩ ታውቃላችሁ። አይደለም እንዴ?... ብርድ ነው ግቡ። በኋላ የማጫውታች ብዙ ነገር አለኝ። ግቡ።" ልጆቼ የእኔና የእርሷን ጭትጭት እንዲሰሙ አልፈለክም።

ሃያ

አፍራታ ግቢውን ጥንድ አግሩ ታቆመው ጀመር።

"ሰሚ አንቺ ወፍ በራሽ አሁኑኑ ግቢዬን ለቀሽ ውጪልኝ!" አፍራታ ተንጨረጨረች።

"ያንቺ ግቢ አይደለም" ደሜ ፈላ። "ሂጂና ከዛ አውራ ብፀት ሥር ተወሸቂ። እኔ በእንቺ ዘንድ ሞቻለሁ። በምድር ላይ የለሁም።"

"እሱም የለም።" አለች አምነረቀች።

"ፕሱሽ ሄደ? ጠገበሽ?... የእድሽን ነው ያገኘሽው!... ሁሉንም ሰምቻለሁ። ሜንሎ ውፀትሽንና ህፀትሽን አሟሎ ፕሱሽ ሄሷል።መራራውንና የዘገየውን ፅዋሽን አስንጭቶሽ ከዶሽ ላይመለስ ሄሷል።"

"እባክሀን እንደዚህ አትፀል..." ተንሰቀሰች ጀመር።

"እባክህ ይቅር በለኝ።"

"ያኔ.... አንቺ ብትሆኚ ኖሮ ለማንም የማታደርጊውን ይቅርታ አድርጌልሻለሁ። ያ ይቅርታ ለልጆቼም ሰማኔመም አይገባችሁም ነበር። በልጆቼ አናት ላይ እጀን አላነሳም ብዬ እንጂ አንደ ሥራሽ ቢሆን ኖሮ በምድር ላይ መኖር አልነበረብሽም ነበር። ያን ሁሉ በደል በልጆቼ ፊት ነው የፈፀምሽብኝ።"

"አሁን የድርሞ አፍራታ አይደለሁም! ሁሉንም ነገር የማስተካክልበት እድል ልትሰጠኝ ይገባል። እሱን አፀርን ሰንኖር የምታየው ይሆናል።"

"ከናውም አፀርን አንኖርም!"

"እባክህ ይቅር በለኝ?!" አፍራታ እግሬ ስር እንደና ተንበረከከች።

Scanned by CamScanner

"ይቅርታ አድርግላት የልጆችህ እናት ናት" አለች አያን ወደ ግቢው በር እየተራመደች። "ችግርህ ልሆን እዚህ ድረስ አልመጣሁም። ወደ ሰውነቱ መመለሱ በቂ ነው።" የእገዛ ሳጎ እየተናነቃት መሆኑን ከድምፅዋ አወጣዋ ተረዳሁ።

ኤፍራታን በተንበረከክችበት ትቻት ወደ አያን ሮጥኩ። የግቢውን በር ከመክፈቷ በፊት ደረስኩባትና እጇን ለቀም አድርጌ ወደ እኔ አዞርኳት። ጉንጯ በእንባ ጭቅጭቋል።

"ውስጤ ነግሮኝ ነበር። ውስጤን ማዳመጥ አትቶኝ ነው" አለች እንባዋን እየሞገዞች። "ሚስትህ እንተን የመሰለ ሰው መጣሏ ቆጭቷት እንድ ቀን ወዳንተ እንደምትመለስ አስቤ ነበር። ይህን እያሰብኩ እንኳ አፍቅሬሀ ነበር። ቁስሌን ሁሉ የምትጠግንልኝ መድኃኒቴ አንተ እንደ ሆንክ አስቤ ነበር። ሳላስበው ነው። በደንብ አላሰብኩበትም። ፍቅር እንደ ውኃ ሙላት እያሳሳቀ ነው የወሰደኝ። ተሳስቻለሁ።"

"አልተሳሳትሽም። እኔም አፍቅሬሻለሁ። ሰውም አውራም ሆንሽ ከእኔ ጋር ብዙ መከራ አሳልፈሻል። አዲስ አበባ ንፁተን ሰው ከሆንን በኋላ እንደማያሸ ድመት ሆኜ እንኳ እያሰብኩ ነበር።"

"በፍፁም አይሆንም። ...ለልጆችህ ስትል ይቅርታ አድርግላትና ከእርሷ ጋር ኑር።"

"አላደርገውም! ልጆቼን እንደም እናት እንደ ምትሆኖችው አምናለሁ። ልጆቼም ቢሆኑ አድገዋል። አራት እመት ሙሉ እናትም አባትም ሆኜ አሳድጌአቸዋለሁ። ያኔ ዞር ብላ አላየቻቸውም። ለምን አሁን እንደመጣች ታውቂያለሽ?" አልኳት እንደገና በጉንጯ ላይ የሚፈስ እንባዋን እየጠረኩ። "አሁን ወደ እኔ

የመጣችው፣ እኔን ትታ ያገባችው ዓደኛዬ የነበረው፣ ንያዬ ውስጥ ተወሽቆ ምርጥ ጠላቴ የነበረው ሚገሙ፣ ሀብቷን ሁሉ ሽጦ ውበቷን ሁሉ አሟጦ ጥሏት ስለሄደ ብቻ ነው። አልደብቅሽም። እርሱ እያለ እኔን መርጣ እንደገና ብትመጣ ናሮ በደሌን ለፈጣሪ ሰጥቼ እተዘላት ነበር። አሁን ግን እንደዛ አይደለም።"

"ትክክል ነህ" የሚል ድምፅ ከኋላዬ ሰማሁና ዞርኩ። ራሷ ኤፍራታ ነበረች። የሆነ ብልቃጥ ነገር በቀኝ እጇ ይዛለች። "ያኔ ያደረክልኝ ይቅርታ ራሱ የማይገባኝ ነበር። አሁን የምፈልገው..." ድምፅዋ ተንቀጠቀጠ። "አሁን የምፈልገው ፍፁም ይቅርታ እንድታደርግልኝ ብቻ ነው። የበደልኩህ በደል የአንተን ቀርቶ የእኔንም አጥንት ዘልቆ እየተሰማኝ ነው። ሜገሙ ንብረቱን በሙሉ ወስዶታል። እርቃኔን ቀርቻለሁ። ሃብቱን ብቻ አይደለም የወሰደብኝ። የአንተንም ፍቅር ነጥቆኛል። የሚወደህን ሰው ከማጣት በላይ ማጣት የለም። ማጣትህ ዘልቆ የሚሰማህ የሚወድህንና የምትወደውን ሰው ያጣህለት ነው። ልክ ነህ። ከዚህ በላይ ሳቆስልህ አይገባም። አውነቱን ልንገርህም አለችና እጀን ሰባ ሆኗ ላይ አደረገችው።

"ምንድን ነው?"

"ኮሜንስ አርግዣለሁ። ከአባብ ባረግዝ ይሻለኝ ነበር። እንዲህ ሆኜ ነው ግሱኝ የሄደው። የእርሱን ዲቃላ መቼም አልወልድም።" የያዘቸውን ብልቃጥ ከመ ትዕዛት ወደ አፉ አስጠጋችውና ዥው አድርጋ ጠጣችው።

"ምንድን ነው?" ሳላስበው ሙሀኩ። ልጆቼም እንደኛና እየተድፈረ መጡ።

"ይቅር በለኝ! እማዬ ይቅር በለኝ!" ስትል ቀየችና እደን እንደያዘችኝ እጥፍጥፍ ብላ ወደቀች።

Scanned by CamScanner

"እማዬ! ልጆቹ ተጫጫዙ። ቀሰብና መር እየሮጡ መጥተው ሰማንሳት አዙኝ።

"ኤፍራታ! ሁሉ ነገር ዞረብኝ። "ፈኅኝ ነሽ! ለልጆችሽ እንኳ መኖር ከበረብሽ... ፈኅኝ ነሽ! ... ፈኅ .... እሺ ይቅር ብዬሻለሁ። ይ...ቅ...ር...ታ..." ከመሮ ጋር ተጋግዘን መኪናዬ ውስጥ አስገብተናት ወደ ሐኪም ቤት በረርኩ።

ድካማችን ከንቱ ነበር። ሐኪሙ ህይወቷ ማለፉን የነገረን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነበር። አምርሬ አሰቀስኩ። በቀብሯ ሰዓት ላይቀር ለያዥ ለናዥ አስቸገርኩ። የኤፍራታ የሕይወት መቅኖ ከንቱ መሆኑ ብቻ አልነበረም ያስለቀሰኝ። ምንም ቢሆን የልጆቼ እናት ናት። የልጆቼን እንባም መቋቋም አልቻልኩም። በደሏ ሁሉ እንደ እርሷው በድን ሆኗል። ሞቷል።

በኤፍራታ ቀብር ላይ፣ አያን ሳትቀር አምርሬ ስታለቅስ አይቻለሁ። ታሪካችንን የሚያውቅ ሰው ሁሉ ቀብሯ ላይ ያላለቀሰ አልነበረም።

አያን፣ የኤፍራታን ሰሜኒያ እስከወጣ ድረስ እያፅናናችኝ አብራኝ ከረመች። ልጆቼ አልጠሏትም። እንዲያውም ቀስ በቀስ ወደዋታል። ትምህርት ቤት የማመላለሱ ሥራም የእርሷ ነበር።

ከኤፍራታ ሰሜኒያ አንድ ሳምንት በኋላ፣ በአንዲት ብሩህ ጠዋት ፀሐይ እየሞቁ ሰቶዝም፣

"ወደ አጋጄን መሄዴ ነው።" የሚል ድምፅ ከጆሮባዬ ሰማሁ። ዞርኩ። አያን ሻንጣዋን ሸክፋ ለመሄድ ተንሰታ ነበር። አፌ ደረቀ።

"ም... ም ---- ምን?"

"ተሸናፊ መሆን አልፈልግም። አንተ የተፅናናህ ያመስለኛል። እዛ ግን ብዙ ዕናት የሚጠይቅ ሥራ አለብኝ። የአቅሜን ያህል ያንን አካባቢ ሰመሰወጥ እታገላለሁ።"

"አይሆንም" ተከተልኳት።

"ቀበሬ አጋጄን ውስጥ ይሆናል። የዚያ ህዝብ ሕያውት መሰወጥ አለበት። በዛ በረሃ ውስጥ አንዲት ጠቢታ እንኳ መሆን አለብኝ።"

"አያን!" እጇን ያዝኳት። "እኔም ካንቺ አልለይም። ቀጣዩ ሕይወቴ ስለ አጋጄን ማጥናትና ማስተማር ነው። የዛን አካባቢ ሰቆቃ ሰዓለም ማሳወቅ ነው። አብረን ሄደንም ትምህርት ቤት እናቋቁማለን። ታላቁ የሰውኖ መሣሪያ ትምህርት ነው። የቻልነውን ያህል ለሰውነ እንታገላለን። ከዛ በፊት ግን...." ወደ ቤት ሮጡ ገባሁና አስቀድሜ አዘጋጅቼላት የነበረውን ስጦታ ይዤ ተመለስኩ። ልጆቼንም አንድ ምስጢር ነግሬ ይዣቸው መጥቻለሁ። በነገርኳቸው መሠረት በግራና በቀኝዋ ቆሙ። ከአልማዝ የተሠራውንና ፊርጡ የሚንፀባረቀውን ቀለበት በጣቷ ላይ ሳስገባ ዕንባዋን መቋቋም አቅቷት ነበር።


"እነዚህን ከአጋጄን ድመቶች የተረፉ ልጆቼንም ተረክቢኝ! ሰኖይሻለሁ" ሁለቱም ተጠመጠመባት። ዕንባዋን አበሰላት። በደስታ ሲቃ ተውጣ አቀፈቻቸው። ከልጆቼ ጋር አቀፍናት።

Scanned by CamScanner

አስተያየተምን ከዚህ በሚከተለው አድራሻ ቢልኩ ለደራሲው ይደርስልምታል::

E-mil:- ramatohara@gmail.com

Scanned by CamScanner



"ከአገሬ አፈር የሚያባልት ቢወድኅና ጎራዴ ይዤ አንጀ
ሚት ተሸከሙኝ የምመጣ አንላያመስልህ!"
አጼ ቴዎድሮስ

• ...በአገራቸው ሥር ተሸሉከሉኪ ዝሁ። አመላላቸው ወፍራም ግንድ ተያይሚል።
በግንዱ ላይ ደግሞ የአያን አነንት አበቃል። የሚያብለጨልጩ ፉስ የያዘ ፈርጣማ
ወገቡና መቱለማውን እንዲሁ ላይ ሰማይረፍ የአሊቃውን ትዕዛዝ በመጠበቅ ላይ ነው።

• ...ህዝን ወመታደሮች እኛ ወደቅት። በአሰቆሩ ሁኔታ ተደፍራ በመጨረሻም ተገድላ፣
በንደ ጎላና ላይ ለሳይን የሚሀሪነን በድኗ ለመቀባጫነት ተጣለ። ያቺ የዋቢ
መንዝ ዳር አበባ የመሰለች ውቧ ህሪን ፈራረለች። እስከትፈራርስ ድረስ በድኗን
ለመቅበር የደፈረ አንኳ አልነበረም። ይህም የሆነበት ምክንያት ለኢትዮጵያ መንግሥት
እንደምትሰልል በመጠርጠሯ ነው።

•...ነዋሪዎች የመርነት ቀጠና የሆንችውን ከተማ ለቀው ሲወጡ ድመቶች የወዳደቀውን
እስከሬን ቀመሱ። ሲደቀኖች ሲመለሱ ከተማዋ በድመት መንጋ ተወራ ጠበቀቻቸው።
ድመቶች የሰው ሥጋ ለመደው ዝር። የቤታቸው ድመት ወደ አውሬነት ተቀይሮ
ጠበቃቸው። ልጆቻቸውን፣ ውሻት አጠጥተው ያሳደጓቸው ድመቶቻቸው ነጠቋቸው።
የእንም እናት ህሆን ልጇ ጠፍተባት ስትፈልግ ሰንብታ ይህን ወሬ ትሰማና የቤቷን
ታላ ሲታስበ ትንገሽ የሆን አጥንቶች ታገኛለች። ልጇን ድመቶች ተቀራምተውት
ነበር። ልጇን ድመት እንደበላባት ሲገባት በቁጣ ተዝለፍልፋ ወደቀች። አልተነሳችም።

•...አጋጅን ውስጥ በንጣጅ ቁፋሮ ላይ የተሰማሩት ፔሽኮ፣ ኔው ኤጅ፣ ሳውዝ ዌስት
ኢነርጂ፣ ፓሲፊሩፕ ኮርፖሬሽን እና ጉጉግያን የተባሉት ኩባንያዎች ቢሆኑም፣ ጉጉግያን
የተባለው ደቻይና ኩባንያ ግን በተፈፀመበት አሰቃቂ ጥቃት ጥሎ ወጥቶ እንደነበር
ይታወቃል።

•..."ነጻጀም ይመጣል! ደመም ያጠፋል!..."
ሶስተኛው ሰው

Scanned by CamScanner